# ኦሪት ዘኍልቍ

ዜና ዘኍልቍ ሲል ነው የውሉድን የቍጥራቸውን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ። ኦሪት ዘፀአት የአበውን ቍጥር ይናገራል፤ ኦሪት ዘኍልቍም የውሉድን ነገር ይናገራል ። ይህን አርእስት ሠለስቱ ምእት ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲሰጡ ሰጥተዉታል፣ እሱ ግን "ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ„ በገዳመ ዘሲና በውስተ ደብተራ መርጡል ብሎ ይጀምራል ።

| ምዕራፍ ፩ ። | | ምዕራፍ ፩ ። |
|---|---|---|
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ በገዳም ዘሲና በውስተ ደብተራ ዘመርጡል አመ ርእሰ ሠርቀ ካልእ ወርኅ በካልእት ዓመት እምዘወፅኡ እምድረ ግብጽ ። | ፩ | እስራኤል ከግብጽ አገር በወጡ በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር መባቻ በሲና ምድረ በዳ ልዩ በሆነች ድንኳን እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው ። |
| ወይቤሎ ፣ አኀዙ እምጥንቱ ወኍልቍሞሙ ለኵሉ ተዓይነ ደቂቀ እስራኤል በበነገዶሙ ወበበቤተ አበዊሆሙ ወበበአስማቲሆሙ ለለአሐዱ አሐዱ ። | ፪ | የእስራኤልን ልጆች ሠራዊት ሁሉ በየነገዳቸውና በየ አባቶቻቸው ወገን በየስማቸው እያንዳንዱን (ከሮቤል) ከበኵሩ ጀምራችሁ እስከ ታናሹ ድረስ ቍጠሩዋቸው ። |
| ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ፣ ኵሉ ዘይወፅእ ፀብአ እምኀይለ እስራኤል ወአስተፋቅድዎሙ በበኃይሎሙ አንተ ወአሮን ። | ፫ | ከሃያ ዓመት ጀምሮ ያለው ወንድ ሁሉ ከዚያም በላይ ያለውን ወንድ ወንዱን ሁሉ ከእስራኤል ሠራዊት ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣውን ሁሉ አንተና አሮን በየሠራዊቶቻቸው ቍጠሩዋቸው (አስቆጥሩዋቸው) ። ዘኍ፣ ፫ ፴፯ ። |
| ወየሀልዉ ምስሌክሙ አሐዱ አሐዱ እመላእክተ ነገዶሙ እለ እምአብያተ አበዊሆሙ ። | ፬ | ከአባቶቻቸው ወገኖች ከሚሆኑ ነገዶች አለቆች አንዱም አንዱም ተውጣጥተው ከናንተ፤ጋር ይኑሩ አለው ። |
| ወዝንቱ ውእቱ አስማተ አበዊሆሙ ወአስማቲሆሙ ለውእቶሙ እደው እለ መጽኡ ምስሌሆሙ ዘእምሮቤል ኤሌሱር ወልደ ሴድዩር ። | ፭ | ከነርሱም ጋር የመጡት የነዚያ ሰዎች ስምና ያባቶቻቸው ስም ይህ ነው ፣ ከነገደ ሮቤል የተመረጠው የሴድዩር ልጅ ኤሌሱር ነው ። |
| ወዘእምስምዖን ፣ ሰላምያል ወልደ ሴሩሳዴ ። | ፮ | ከነገደ ስምዖን የተመረጠው የሴሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ነው ። |
| ወዘእምይሁዳ ፣ ነአሶን ወልደ አሚናዳብ ። | ፯ | ከነገደ ይሁዳ የተመረጠው የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው ። |
| ወዘእምይሳኮር ናትናኤል ወልደ ሰገር ። | ፰ | ከነገደ ይሳኮር የተመረጠው የሰገር ልጅ ናትናኤል ነው። |
| ወዘእምዛብሎን ፣ ኤልያብ ወልደ ኬሎን ። | ፱ | ከነገደ ዛብሎን የተመረጠው የኬሎን ልጅ ኤልያብ ነው ። |
| ወዘእምትውልደ ዮሴፍ ዘእምኤፍሬም ፣ ኤልስማ ወልደ ሰምዩድ፡ ወዘእምናሴ ገማልያል ወልደ ፈዳሱር ። | ፲ | ከዮሴፍ ከተወለዱ ከኤፍሬም ነገድ የተመረጠው የሰምዩድ ልጅ ኤልስማ ከነገደ ምናሴም የፈዳሱር ልጅ ገማልያል ናቸው ። |
| ወዘእምብንያም ፣ አቢዳን ወልደ ጋድዮን ። | ፲፩ | ከነገደ ብንያም የተመረጠው የጋድዮን ልጅ አቢዳን ነው ። |
| ወዘእምዳን ፣ አክያዜር ወልደ ሳሚሳዲ ። | ፲፪ | ከነገደ ዳን የተመረጠው የሳሚሳዲ ልጅ አክያዜር ነው። |
| ወዘእምአሴር ፣ ፋጋኤል ወልደ አክራን ። | ፲፫ | ከነገደ አሴር የተመረጠው የአክራን ልጅ ፋጋኤል ነው። |
| ወዘእምጋድ ፣ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል ። | ፲፬ | ከነገደ ጋድ የተመረጠው የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ነው። |
| ወዘእምንፍታሌም ፣ አኪሬ ወልደ ኤናን ። | ፲፭ | ከነገደ ንፍታሌም የተመረጠው የኤናን ልጅ አኪሬ ነው ። |

፲፮ እሉ እሙንቱ ኅሩያነ ተዓይኒሆሙ ወመላእክተ ነገዶሙ ዘበበአዝማዲሆሙ ወመሳፍንቲሆሙ ለእስራኤል እሙንቱ ።

በየወገኖቻቸው የሚጠሩ ከነገዶቻቸው የተመረጡ የነገዶቻቸው አለቆች እሊህ ናቸው ፤ የእስራኤልም ገዢዎች እነዚህ ናቸው ። ዘኍ፡ ፳፮ ፲፡ ፯ ፪ ።

፲፯ ወነሥእዎሙ ሙሴ ወአሮን ለእሉ እደው እለ ተሰምዩ በበአስማቲሆሙ ።

አሮንና ሙሴም በየስሞቻቸው የተጠሩ እነዚህን ተቀበሉዋቸው ። ፩ ዜና መዋ፡ ፲፪ ፴፩፡ ዕዝ፡ ፰ ፳ ።

፲፰ ወአስተጋብኡ ኵሎ ተዓይነ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ክልእ ፡ በካልእ ዓመት ፤ ወኈለቍዎሙ በበነገዶሙ ወበበአዝማዲሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘእምሥራ ዓም ወላዕሉ ለኵሉ ተባዕቶሙ በበርእሶሙ ።

በሁለተኛው ዓመት ፤ በሁለተኛው ወር መባቻ ሠራዊቱን ሁሉ ሰብስበው በየነገዶቻቸው በየስሞቻቸውና በየዘመዶቻቸው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱን ሁሉ ቈጠሩዋቸው ። ዕዝ፡ ፪ ፶ ።

፲፱ ወበከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ፤ ኈለቍዎሙ እሙንቱ በደብረ ሲና ።

እነሱም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው በሲና ተራራ ቈጠሩዋቸው ።

፳ ወኮኑ ደቂቀ ሮቤል በኵሩ ለእስራኤል በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ፤ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፤ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፤ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ፤ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የያዕቆብ የበኵር ልጁ የሮቤል ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸውና በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስማቸው ቍጥርና በየራሳቸው ከሠራዊቶቻቸው ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ሁሉ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለውን ወንድ ወንዱን ሁሉ ቈጥሮ ።

፳፩ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ሮቤል ፤ አርባዕቱ እልፍ ወስሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት ።

ከሮቤል ነገድ የተቈጠሩት ቍጥራቸው አራት እልፍ ስድስት ሺሕ አምስት መቶ ሆነ ።

፳፪ ወደቂቁ ለስምዖን በበትውልዶሙ ። ወበበሕዘቢሆሙ ፤ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፤ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፤ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የስምዖንም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ሁሉ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ ተቈጥረው ።

፳፫ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ስምዖን ሐምስቱ እልፍ ወተስዓ ምእት ወሠለስቱ ምእት ።

ከነገደ ስምዖን የተቈጠሩት ቍጥራቸው አምስት እልፍ ፤ ዘጠኝ ሺሕ ፡ ሦስት መቶ ናቸው ።

፳፬ ወደቂቁ ለይሁዳ በበትውልዶሙ ፤ ወበበሕዘቢሆሙ ፤ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፤ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፤ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የይሁዳም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸውና በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጠሩ ።

፳፭ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ይሁዳ ሰብዓቱ እልፍ ወአርባዓ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ።

ከይሁዳም ነገድ የተቈጠሩት ቍጥራቸው ሰባት እልፍ ፡ አራት ሺሕ ፤ ከሰባት መቶ ነው ። ዘኍ፡ ፳፮ ፲፰ ።

፳፮ ወደቂቁ ለይሳኮር በበትውልዶሙ ፤ ወበበሕዘቢሆሙ ፤ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፤ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፤ ወበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የይሳኮርም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸውና በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱን ሁሉ በየራሳቸው ተቈጠሩ ።

፳፯ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ይሳኮር ሐምስቱ ምእት እልፍ ወአርባዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

ከነገደ ይሳኮር የተቈጠሩት ቍጥራቸው አምስት እልፍ አራት ሺሕ አራት መቶ ነው ። ዘኍ፡ ፳፮ ፳፪ ።

፳፰ ወደቂቁ ለዛብሎን በበትውልዶሙ ፤ ወበበሕዘቢሆሙ ፤ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፤ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፤ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የዛብሎንም ልጆች በየአባቶቻቸው በየትውልዳቸውና በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጠሩ ። ፩ ሳሙ፡ ፳፬ ፱ ።

፳፱ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ዛብሎን ሐምስቱ እልፍ ወሰብዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

ከዛብሎን ነገድ የተቈጠሩትም ቍጥራቸው አምስት እልፍ ፤ ሰባት ሺሕ ፤ አራት መቶ ነው ።

፴ ወደቂቁ ለዮሴፍ ደቂቀ ኤፍሬም በበትውልዶሙ ፤ ወበበሕዘቢሆሙ ፤ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፤ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

ከዮሴፍ የተወለደው የኤፍሬም ልጆች በየትውልዳቸውና በየአባቶቻቸው ቤቶች በየስማቸው በየራሳቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ ተቈጠሩ ።

፴፩ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ኤፍሬም ፤ አርባዕቱ እልፍ ወሐምስቱ ምእት ።

ከኤፍሬም ነገድ የተቈጠሩት ቍጥራቸው አራት እልፍ ፤ አምስት መቶ ነው ።

፴፪ ወደቂቁኒ ለምናሴ በበትውልዶሙ ፣ ወበበሕዘቢሆሙ ፣ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፣ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፣ ዘበበርእሰሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወጽእ ምስለ ኀይል ።

የምናሴም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጠሩ ።

፴፫ ኍላቄሆሙ ዘእምነገደ ምናሴ ፣ ሠለስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወክልኤቱ ምእት ።

ከምናሴም ነገድ የተቈጠሩት ቍጥራቸው ሦስት እልፍ ሁለት ሺሕ ፣ ሁለት መቶ ነው ።

፴፬ ወደቂቁኒ ለብንያም በበትውልዶሙ ፣ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፣ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፣ ዘበበርእሰሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የብንያም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳ ቸው ተቈጠሩ ።

፴፭ ኍላቄሆሙ ዘእምነገደ ብንያም ፣ ሠለስቱ እልፍ ወሐ ምሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

ከነገደ ብንያም የተቈጠሩት ቍጥራቸው ሦስት እልፍ አምስት ሺሕ ፣ አራት መቶ ነው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፳፯ ።

፴፮ ወደቂቁኒ ለጋድ በበትውልዶሙ ፣ ወበበሕዘቢሆሙ ፣ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፣ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፣ ዘበበርእሰሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የጋድም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስሞቻቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጠሩ ።

፴፯ ኍላቄሆሙ ዘእምነገደ ጋድ አርባዕቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ወሐምሳ ።

ከጋድም ነገድ የተቈጠሩት ቍጥራቸው አራት እልፍ አምስት ሺሕ፣ ሰባት መቶ አምሳ ነው ።

፴፰ ወደቂቁኒ ለዳን በበትውልዶሙ ፣ ወበበሕዘቢሆሙ ፣ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፣ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፣ ዘበበርእሰሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የዳን ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባ ቶቻቸው ቤቶች በየስሞቻቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ወንድ ወንዱ ሁሉ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው በየራሳቸው ተቈጠሩ ።

፴፱ ወኍላቄሆሙ ዘእምነገደ ዳን ፣ ስድስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ።

ከነገደ ዳን የተቈጠሩት ቍጥራቸው ስድስት እልፍ ፣ ሁለት ሺሕ ፣ ሰባት መቶ ነው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፴፯ ።

፵ ወደቂቁኒ ለአሴር በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ፣ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፣ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ፣ ዘበበርእሰሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የአሴርም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸውና በየአባቶቻቸው ቤቶች በየስሞቻቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳ ቸው ተቈጠሩ ።

፵፩ ኍላቄሆሙ ዘእምነገደ አሴር ፣ አርባዕቱ እልፍ ወዓሠ ርቱ ምእት ወሐምስቱ ምእት ።

ከነገደ አሴር የተቈጠሩት ቍጥራቸው አራት እልፍ ፣ አንድ ሺሕ ፣ አምስት መቶ ነው ።

፵፪ ወደቂቁኒ ለንፍታሌም በበትውልዶሙ ፣ ወበበሕዘቢ ሆሙ ፣ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ፣ ወበበኍልቈ አስማቲ ሆሙ ፣ ዘበበርእሰሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላ ዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኀይል ።

የንፍታሌም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ቤቶች በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጠሩ ።

፵፫ ኍላቄሆሙ ዘእምነገደ ንፍታሌም ፣ ሐምስቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

ከነገደ ንፍታሌም የተቈጠሩት ቍጥራቸው አምስት እልፍ ፣ ሦስት ሺሕ ፣ አራት መቶ ነው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፴፬ ።

፵፬ ዘቲ ይእቲ ፍቅድ እንተ አስተፋቀድዎሙ ሙሴ ወአ ሮን ወመላእክቲሆሙ ለእስራኤል ዓሠርቱ ወክልኤቱ እደ ው አሐዱ አሐዱ ብእሲ እምአሐዱ አሐዱ ነገድ እምነገደ አብያተ አበዊሆሙ ውእቶሙ ።

ሙሴና አሮን አሥራ ሁለቱም የእስራኤል አለቆች የቈጠሩዋቸው (ያስቈጠሩዋቸው) ቍጥር ይህች ናት ፣ እሊ ህም ከየአንድ አንዱ ነገድ የተመረጠው ከአንዱም ከአን ዱም የተመረጡ የቤት አለቆች ነበሩ ።

፵፭ ወኮነ ኵሉ ኍላቄሆሙ ለደቂቀ እስራኤል በበኀይ ሎሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ዘይወፅእ ፀብአ እምእስ ራኤል ፣ ስሳ እልፍ ወሠላሳ ምእት ፣ ወኀምስቱ ምእት ፣ ወኀምሳ ።

ከእስራኤል ልጆች ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዓ መት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነው በየሠራዊቶቻቸው ሁሉ የተቈጠሩት ቍጥራቸው ስሳ እልፍ ሦስት ሺሕ አም ስት መቶ አምሳ ነበር ። ዘኍ፣ ፳፮ ፶፩ ።

፵፮ ወሌዋውያንሰ ምስለ ነገደ ልደቶሙ እሙንቱ ወኢ ኀለቍዎሙ ምስለ ደቂቀ እስራኤል ።

ከነርሱም የተወለዱ ወገኖቻቸውንና የሌዊን ልጆች ግን ከእስራኤል ልጆች ጋር አልቈጠሩዋቸውም ።

፵፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ዑቅ ኢትኍ ልቆሙ ለነገደ ሌዊ ወኢትትመጠው ኍላቄሆሙ እምደ ቂቀ እስራኤል ።

የሌዊን ነገድ እንዳትቈጥራቸው ዕወቅ ቍጥራቸው ንም ከእስራኤል ልጆች ጋር እንዳትቀበል ዕወቅ ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፷፪ ።

፵፰ ወሚሞሙ ለሌዋውያን ዲበ ደብተራ ዘመርጡል ወዲበ ኵሉ ንዋያ ፡ ወዲበ ኵሉ ዘሀሎ ውስቴታ ፡ ከመ እሙንቱ ያንሥእዋ ለደብተራ ወከመ እሙንቱ ይግበሩ ውስቴታ ወዐውደ ደብተራ ይትዐየኑ ።

፵፱ ወእመኒ ግዕዘት ደብተራ ይትክልዋ ሌዋውያን ወአመሰ ኀደርት ይእቲ እሙንቱ ያነሥእዋ ።

፶ ወዘእምባዕድ ዘመድ ዘቀርበ ምስሌሆሙ ሐዊረ ለይሙት ።

፶፩ ወይትዐየኑ ደቂቀ እስራኤል ብእሲ ብእሲ በበተዕይንቱ ፡ ወብእሲ ብእሲ በበምስፍናሁ ወበበኀይሎሙ ።

፶፪ ወሌዋውያንሰ ይትዐየኑ ፍጽመ ውስተ ዐውደ ደብተራ ዘመርጡል ወኢይኩን ጌጋይ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ፡ ወይዕቀቡ ሌዋውያን ሕጋ ለደብተራ መርጡል ።

፶፫ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘአዘዞሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ከማሁ ገብሩ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ብእሲ ብእሲ በበሥርዐቱ ወበበትእምርቱ ወበበቤተ አበዊሆሙ ይትዐየኑ ደቂቀ እስራኤል አንጻረ ዐውደ ደብተራ ዘመርጡል ።

፪ ወእለ ይቅውሙ ተዓይኖ መንገለ ጽባሕ ይኀድር ተዓይኑ ይሁዳ ምስለ ኀይሉ ፡ ወመልአክሙ ለደቂቀ ይሁዳ ነአሶን ወልደ አሚናዳብ ።

፫ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሰብዓቱ እልፍ ወአርብዓ ምእት ወስድስቱ ምእት ።

፬ ወእምድኅሬሆሙ ይትዐየኑ ነገደ ይሳኮር ፡ ወመልአክሙ ለደቂቀ ይሳኮር ናትናኤል ወልደ ሰገር ።

፭ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሐምስቱ እልፍ ወአርብዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

፮ ወእምድኅሬሆሙ ይትዓየኑ ነገደ ዛብሎን ወመልአክሙ ለደቂቀ ዛብሎን ኤልያብ ወልደ ኬሎን ።

፯ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሐምስቱ እልፍ ወሰብዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

፰ ወኵሉ እለ ተኈለቁ እምትዕይንተ ይሁዳ ዐሠርቱ ወሰመንቱ እልፍ ወስሳ ምእት ፡ ወአርባዕቱ ምእት ፡ ምስለ ኀይሎሙ እሙንቱ ይቀድሙ አንሥአ ።

፱ ወየኀድሩ ትዕይንተ ሮቤል መንገለ አዜብ ምስለ ኀይሎሙ ወመልአክሙ ለደቂቀ ሮቤል ኤልሱር ወልደ ሴድዩር ።

፲ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ፡ ወስሳ ምእት ፡ ወሐምስቱ ምእት ።

፲፩ ወይትዐየኑ በገቦሆሙ ነገደ ስምዖን ወመልአክሙ ለደቂቀ ስምዖን ሰላምያል ወልደ ሴሩሳዴ ።

፵፰ እነርሱም ድንኳኒቱን ያነሷት ዘንድ ዕቃዋንም ሁሉ ያነሱ ዘንድ በውስጧም ሥራቸውን ይሠሩ ዘንድ የሌዊን ልጆች በውስጧ ባለው ዕቃ ሁሉም በደብተራ ኦሪት ላይ ሹማቸው በድንኳኑም ዙርያ ይስፈሩ ። ምዕ፡ ፫ ፳፫ ፴፱።

፵፱ ደብተራ ኦሪት ለጉዞ ስትነሣ ሌዋውያን ይንቀሏት በምትሰፍርበትም ጊዜ እነሱ ይትከሏት ።

፶ ከሌላ ወገን የተወለደ ከነርሱ ጋር በመንገድ አንድ የሆነ ሰው ቢገኝ ይሙት ። ዘኍ፡ ፳፮ ፱ ።

፶፩ የእስራኤል ልጆች እያንዳንዱ ሰው ከባልንጀራው ጋር በየሰፈሩ በየዓላማው ፡ አንዱም አንዱም ሰው በየሠራዊቶቻቸው ይስፈሩ ። ዘኍ፡ ፳፯ ፳፬ ።

፶፪ ነገር ግን በእስራኤል ልጆች ላይ ዕዳ እንዳይሆንባቸው ሌዋውያን በደብተራ ኦሪት ዙርያ ፊት ለፊት ይስፈሩ ፡ ሌዋውያን የደብተራ ኦሪት ሕጓን ሥርዓቷን ይጠብቁ አለው ፡ ፩ ሕፀ፡ ፳፫ ፴፪ ።

፶፫ የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው እንዲሁ አደረጉ ።

ምዕራፍ ፪ ።

፩ እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ፤ የእስራኤል ልጆች አንዳንዱ ሰው በየሥርዓቱ በየምልክቱ በየአባቶቻቸው ቤቶች ልዩ በሆነች ድንኳን ዙርያ አንጻር ይስፈሩ ። ዘኍ፡ ፩ ፶፪ ።

፪ በምሥራቅ በኩል አስቀድመው የሚሰፍሩት እንደየሠራዊቶቻቸው የይሁዳ ሰፈርተኞች ከሠራዊቱ ጋር በምሥራቅ በኩል ይስፈሩ ፡ የይሁዳም ልጆች አለቃቸው የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው ።

፫ ከነገዱም የተቈጠሩት ሰባት እልፍ ፡ አራት ሺሕ ፡ ስድስት መቶ ናቸው ። ምሳ፡ ፲፱ ፮፡ ኤር፡ ፲፮ ፲፯ ።

፬ ከነሱም ቀጥሎ የይሳኮር ነገድ ይስፈሩ ፡ የይሳኮርም ነገድ አለቃቸው የሰገር ልጅ ናትናኤል ነው ።

፭ ከነገዱም የተቈጠሩት አምስት እልፍ ፡ አራት ሺሕ ፡ አራት መቶ ናቸው ። ዘፍ፡ ፵፱ ፲፫ ።

፮ ከነርሱም ቀጥሎ ነገደ ዛብሎን ይስፈሩ ፡ የዛብሎንም ልጆች አለቃቸው የኬሎን ልጅ ኤልያብ ነው ።

፯ ከሠራዊቱም ጋር የተቈጠሩት አምሳ ሰባት ሺሕ አራት መቶ ናቸው ።

፰ ከይሁዳም ሠራዊት ወገን የተቈጠሩት ሁሉ አሥራ ስምንት እልፍ ፡ ስድስት ሺሕ ፡ አራት መቶ ናቸው ፡ እነሱም አስቀድመው ከሠራዊቶቻቸው ጋር ጓዛቸውን ያንሡ (ይጓዙ) ።

፱ የሮቤልም ነገድ ከሠራዊቶቻቸው ጋር በአዜብ በኩል ይስፈሩ ፡ የሮቤልም ልጆች አለቃቸው የሴድዩር ልጅ ኤልሱር ነው ።

፲ ከሠራዊቱም የተቈጠሩት አርባ ስድስት ሺሕ አምስት መቶ ናቸው ።

፲፩ ነገደ ስምዖንም በጐናቸው ይስፈሩ ፡ የስምዖንም ልጆች አለቃቸው የሴሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ነው ።

፲፪ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሐምስቱ እልፍ ፣ ወተስዓ ምእት ፣ ወሠለስቱ ምእት ።
፲፫ ወየኀድሩ በገቦሆሙ ነገደ ጋድ ፣ ወመልአክሙ ለነገደ ጋድ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል ።
፲፬ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ፣ ወስድስቱ ምእት ወሐምሳ ።
፲፭ ወኵሉ እለ ተኈለቁ እምትዕይንተ ሮቤል ዐሠርቱ ወሐምስቱ እልፍ ፣ ዐሠርቱ ወአርባዕቱ ምእት ወሐምሳ ፣ ምስለ ኀይሎሙ ፣ ወበገዳም ያነሥኡ እሙንቱ ።
፲፮ ወይትነሣእ ደብተራ መርጡል ወትዕይንቶሙ ለሌዋውያን ማእከለ ተዓይን በከመ ይትዐየኑ ከማሁ ያነሥኡ አሐዱ አሐዱ ዘዘይቃለው በበምስፍናሁ ።

፲፯ ወየኃድሩ ትዕይንተ ኤፍሬም መንገለ ገጸ ባሕር ምስለ ኀይሎሙ ወመልአክሙ ለደቂቀ ኤፍሬም ኤልሳማ ወልደ ኤሚድ ።
፲፰ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ፣ ወሐምስቱ ምእት ።
፲፱ ወየኀድሩ በገቦሆሙ ነገደ ምናሴ ወመልአክሙ ለደቂቀ ምናሴ ገማልያል ወልደ ፈዳሱር ።
፳ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሠለስቱ ምእት ፣ ወክልኤቱ ምእት ።
፳፩ ወየኀድሩ በገቦሆሙ ነገደ ብንያም ፣ ወመልአክሙ ለነገደ ብንያም አቢዳን ወልደ ጋድዮን ።
፳፪ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሠለስቱ እልፍ ፣ ወሐምሳ ምእት ፣ ወአርባዕቱ ምእት ።
፳፫ ወኵሎሙ እለ ተኈለቁ እምትዕይንተ ኤፍሬም ዐሠርቱ እልፍ ፣ ወሰማንያ ምእት ፣ ምስለ ኀይሎሙ ፣ ወበሣልስ ያነሥኡ እሙንቱ ።
፳፬ ወየኀድሩ በገቦሆሙ ነገደ ዳን ምስለ ኀይሎሙ ገጸ መስዕ ወመልአክሙ ለደቂቀ ዳን አክያዜር ወልደ አሚሳዴ ፣

፳፭ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ስድስቱ እልፍ ፣ ወዕሥራ ምእት ፣ ወሰብዓቱ ምእት ።
፳፮ ወየኀድሩ በገቦሆሙ ነገደ አሴር ወመልአክሙ ለደቂቀ አሴር ፋግሔል ወልደ አክራን ።
፳፯ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ወዐሠርቱ ምእት ወሐምስቱ ምእት ።
፳፰ ወየኀድሩ በገቦሆሙ ነገደ ንፍታሌም ፣ ወመልአክሙ ለደቂቀ ንፍታሌም አኪሬ ወልደ ኤናን ።
፳፱ ምስለ ኀይሉ እለ ተኈለቁ ሐምስቱ እልፍ ፣ ወሠላሳ ምእት ፣ ወአርባዕቱ ምእት ።
፴ ኵሎሙ እለ ተኈለቁ እምትዕይንተ ዳን ዐሠርቱ ወሐምስቱ እልፍ ፣ ወሰብዓ ምእት ፣ ወስድስቱ ምእት ።
፴፩ ወእሙንቱ ደኃርያን ያነሥኡ በከመ ሥርዐቶሙ ።

፴፪ ዝንቱ ውእቱ ኍላቌሆሙ ለደቂቀ እሥራኤል በበአብያተ አበዊሆሙ ኵሉ ኍልቈ ተዓይኒሆሙ ምስለ ኀይሎሙ ስሳ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት ወሐምሳ ።

ከሠራዊቱም ጋር የተቈጠሩት አምስት እልፍ ፣ ዘጠኝ ሺሕ ፣ ከሦስት መቶ ናቸው ።

በነርሱም አጠገብ የሚሰፍሩ ነገደ ጋድ ናቸው ፣ የጋድ ልጆች አለቃም የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ነው ።

ከሠራዊቱም የተቈጠሩት አርባ አምስት ሺሕ ፣ ስድስት መቶ አምሳ ፣ ናቸው ። ፩ ሕፀ ፫ ፩ ።

ከሮቤል ሠራዊት የተቈጠሩት በየሠራዊቶቻቸው ሁሉ አሥራ አምስት እልፍ አሥራ አራት ሺሕ አምሳ ናቸው ፣ እነርሱም ቀጥለው ጓዛቸውን ያነሣሉ ። ዘፍ ፵፫ ፫ ።

(ከዚህ በኋላ) ደብተራ ኦሪት ትነሣ ፣ የሌዊም ልጆች ሰፈርተኞች በሠራዊቱ መካከል ይሁኑ ፣ እንደየአሰፋፈራቸው እያንዳንዱ በየዓላማው እየተከታተሉ እንደዚሁ ይጓዙ (ጓዛቸውን ያንሡ) ። ዘኍ ፲ ፲፯ ፣ ዘዳግ ፳፫ ፲፪ ።

ከነርሱም ቀጥሎ ነገደ ኤፍሬም ከሠራዊቶቻቸው ጋር በምዕራብ በኩል ይሰፈሩ ፣ የኤፍሬም ልጆች አለቃም የአምዩድ ልጅ ኤልሳማ ነው ።

ከሠራዊቱም የተቈጠሩት አርባ ሺሕ ፣ አምስት መቶ ናቸው ።

ነገደ ምናሴም በጠገባቸው ይሰፈሩ ፣ የምናሴም ልጆች አለቃቸው የፈዳሱር ልጅ ገማልያል ነው ።

ከሠራዊቱም የተቈጠሩት ሦስት እልፍ ፣ ሁለት ሺሕ ፣ ሁለት መቶ ናቸው ።

በነርሱም አጠገብ የሚሰፍሩ ነገደ ብንያም ናቸው ፣ የብንያም ልጆች አለቃም የጋድዮን ልጅ አቢዳን ነው ።

ከሠራዊቱም የተቈጠሩት ሠላሳ አምስት ሺሕ ፣ አራት መቶ ናቸው ። መዝ ፸፰ ፳፯ ፣ ራእ ፯ ፰ ።

ከነገደ ኤፍሬም ከሠራዊቶቻቸው ጋር የተቈጠሩት ሁሉ አሥር እልፍ ፣ ስምንት ሺሕ ፣ አራት መቶ ናቸው ፣ እነሱም ሦስተኛ ሁነው ይጓዛሉ (ጓዛቸውን ያንሡ) ።

ነገደ ጋድ ከሠራዊቶቻቸው ጋር በሰሜን በኩል በጠገባቸው ይሰፈሩ ፣ የጋድ ልጆች አለቃም የአሚሳዴ ልጅ አክያዜር ነው ። ዘኍ ፲ ፳፪ ፣ ፳፫ ፳፬ ።

ከሠራዊቱም የተቈጠሩት ስሳ ሁለት ሺሕ ሰባት መቶ ናቸው ። ዘዳግ ፴፫ ፳፪ ።

ነገደ አሴርም በጐናቸው ይሰፈሩ ፣ የአሴር ልጆች አለቃም የአክራን ልጅ ፋግሔል ነው ።

ከሠራዊቱም ጋር የተቈጠሩት አርባ አንድ ሺሕ ፣ አራት መቶ ናቸው ። ራእ ፯ ፯ ።

ነገደ ንፍታሌምም በአጠገባቸው ይሰፈሩ ፣ የንፍታሌም ልጆች አለቃም የኤናን ልጅ አኪሬ ነው ።

ከሠራዊቱ ጋር የተቈጠሩት አምሳ ሦስት ሺሕ ፣ አራት መቶ ናቸው ። ዘዳ ፴ ፫ ፣ ፪ ነገ ፲፩ ፳፱ ።

ከዳን ሠራዊት ሁሉ የተቈጠሩት ሁሉ አሥራ አምስት እልፍ ሰባት ሺሕ ስድስት መቶ ናቸው ።

እነሱም እንደ ሥራታቸው በመጨረሻ ጓዛቸውን ያነሣሉ (ያንሡ) ። ዘኍ ፲ ፳፭ ፳፯ ።

በየአባቶቻቸው ወገኖች የተቈጠሩት የእስራኤል ልጆች ሠራዊት ሁሉ ቍጥር ስልሳ ሦስት ሺሕ አምስት መቶ አምሳ ነው ። ዘኍ ፩ ፵፯ ።

፴፫ ወሌዋውያንሰ ኢተኈለቁ ምስሌሆሙ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።
፴፬ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሉ ዘከመ አዘዘ እግዚአብ ሔር ለሙሴ ፣ ከማሁ ተዓየኑ በበሥርዐቶሙ ፣ ወከማሁ ያን ሥኡ በበነገዶሙ ዘዘዚአሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ።

ሌዋውያን ግን እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ከነ ሱ ጋር አልተቈጠሩም ። ምዕ፣ ፩ ፵፯፣ ፲፫ ፩ ።
የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ሁሉን አደረጉ ፣ እንደዚሁም በየሥርዓታቸው ሰፈሩ ፣ እን ደዚሁም በየነገዳቸው በየአባቶቻቸው ቤቶች ጓዛቸውን አነሡ ። ዘኍ፣ ፳፬ ፮ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

፩ ወከመዝ ይእቲ ልደቶሙ ለሙሴ ወለአሮን በዕለተ ተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና ።
፪ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ አሮን ፣ በኵሩ ናዳብ ወአብዩድ ወአልአዛር ወኢታምር ።
፫ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ አሮን ካህናት እለ ቀብዐን ወእለ ፍጹማን እደዊሆሙ ከመ ይኩኑ ካህናተ ።
፬ ወሞቱ ናዳብ ወአብዩድ በቅድመ እግዚአብሔር እስ መ አምጽኡ እሳተ ዘእምባዕድ ቅድመ እግዚአብሔር በሐ ቅለ ሲና ፣ ወአልቦሙ ውሉድ ፣ ወኮኑ አልአዛር ወኢታምር ካህናተ ምስለ አሮን አቡሆሙ ።
፭ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ንሥኦሙ ለነ ገደ ሌዊ ወአቅሞሙ ቅድመ አሮን ካህን ወይትለአክዎ ።
፮ ወይዕቀቡ ሕጎ ወሕጎሙ ለደቂቀ እስራኤል በቅድመ ደብተራ ዘመርጡል ወይግበሩ ምግባራቲሃ ለደብተራ ።
፯ ወይዕቀቡ ንዋያ ለደብተራ መርጡል ወኵሎ ሕጎሙ ለደቂቀ እስራኤል በኵሉ ምግባራቲሃ ለደብተራ ።
፰ ወታገብኦሙ ለሌዋውያን ኀበ አሮን እኁከ ወኀበ ደ ቂቁ ካህናት እስመ ሀብተ ተውህቡ ሊተ እሙንቱ እምደ ቂቀ እስራኤል ።
፱ ወትሠይሞሙ ለአሮን ወለደቂቁ ላዕለ ደብተራ ዘመ ርጡል ፣ ወይዕቀቡ ክህነቶሙ ወኵሎ ዘምሥዋዕ ወዘው ስጥ እመንጦላዕት ፣ ወእመቦ ዘገሠሠ ዘእምባዕድ ዘመድ ለይሙት ።
፲ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ናሁ አነ ነሣ እክዎሙ ለሌዋውያን እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ህየ ንተ ኵሉ በኵር ዘይፈትሕ ማኅፀነ ዘእምደቂቀ እስራኤል ቤዛ ዚአሆሙ ይኩኑኒ ሌዋውያን ።
፲፩ ይቤ እግዚአብሔር እስመ ኵሎ በኵረ ቀተልኩ በም ድረ ግብጽ ።
፲፪ ኵሉ በኵር ዘእምደቂቀ እስራኤል እምሰብእ እስከ እንስሳ ሊተ ውእቱ ፣ እስመ አነ እግዚአብሔር ።

፲፫ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ በሐቅለ ሲና ወይቤሎ ፣ ኈልቆሙ ለደቂቀ ሌዊ በበአብያተ አበዊሆሙ ወበበሕዘ ቢሆሙ ኵሎ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ።

፲፬ ወኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ።
፲፭ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሌዊ በበአስማቲሆሙ ጌድሶን ወቀዓት ወሜራሪ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

እግዚአብሔር በደብረ ሲና ሙሴን በተናገረበት ቀን የአሮንና የሙሴ ትውልዳቸው እንደዚህ ነበረ ።
የአሮን ልጆች ስማቸው ይህ ነው ፤ በኵሩ ናዳብ ፣ አብዩድ ፣ አልአዛር ፣ ይታምር ይባላሉ ። ዘፀ፣ ፮ ፳፫ ።
ካህናት ይሆኑ ዘንድ እጆቻቸውን የተቀቡት የአሮን ልጆች ስማቸው ይህ ነው ። ዘፀ፣ ፳፰ ፵፩ ።
በሲና ምድረ በዳ ከሌላ ጭረው እሳት አምጥተዋልና አብዩድና ናዳብ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሞቱ ፣ ልጅም አልነበራቸውም ፣ አልአዛርና ይታምር ግን ከአባታቸው ከአሮን ጋር ያገለግሉ ነበር ። ዘኍ፣ ፳፮ ፷፩ ።
የሌዊን ልጆች ያገለግሉት ዘንድ ወስደህ በአሮን ፊት አቁማቸው ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ።
ልዩ በሆነች ድንኳን የእስራኤልን ልጆች ሕግና የ ሱን ሕግ ይጠብቁ ፣ የደብተራ ኦሪትንም ሥራ ይሥሩ ።
የደብተራ ኦሪትንም ዕቃዋን ይጠብቁ በድንኳኑ በሚ ሠራው ሥራ ሁሉ የእስራኤልን ልጆች ሕግ ሁሉ ይጠብቁ ።
ከእስራኤል ልጆች ተለይተው ለኔ ፈንታ ሁነው ተሰጥተዋልና የሌዊን ልጆች ወደ ወንድምህ አሮንና ወደ ልጆቹ ካህናት አግባቸው ። ዘኍ፣ ፰ ፲፱፣ ፲፰ ፮ ።
አሮንንና ልጆቹን በደብተራ ኦሪት ላይ ሹማቸው ክህ ነታቸውንም ይጠብቁ ፣ ከመጋረጃው ውስጥ ያለውንና በመሠውያውም ያለውን ሁሉ ይጠብቁ ፣ ከሌላ የተወለደ ግን ንዋየ ቅድሳቱን የዳሰሰ ቢኖር ይሙት አለው ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ ከእስ ራኤል ልጆች ወገን መጀመሪያ ስለሚወለደው ሁሉ ፈን ታ ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይቼ ሌዋውያንን እነሆ ተቀበልኋቸው ። ፰ ፲፮ ፣ ፲፰ ፮ ።
እግዚአብሔር በግብጽ አገር በኵር በኵሩን ሁሉ ገድ ያለሁና (ሌዋውያን ቤዛ ይሁኑልኝ አለ) ። ዘኍ፣ ፫ ፵፩ ።
ይህን ያዘዝሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ከእስራኤል ል ጆች መጀመሪያ የሚወለደው ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ የኔ ገንዘብ ነው አለ ። ዘሌ፣ ፳፯ ፳፯ ፣ ሉቃ፣ ፪ ፳ ።
እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ምድረ በዳ እንዲህ ብሎ ነገረው ፣ የሌዊን ልጆች በየአባቶቻቸው ቤቶች በየወገኖ ቻቸው ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለውን ወንድ ወንዱን ቍጠራቸው አለው ። ዘኍ፣ ፩ ፵፮ ።
ሙሴና አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው በእግዚ አብሔር ቃል ቈጠሯቸው ። ፳፮ ፶፪ ።
በየስማቸው የሚቈጠሩ የሌዊ ልጆች ቀዓት ፣ ጌድሶ ንና ሜራሪ እሊህ ናቸው ። ዘፍ፣ ፵፮ ፲፩ ።

፲፮ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ጌድሶን በበሕዘቢሆሙ ሎቤን ወሴሜይ ።

በየወገኖቻቸው የሚጠሩ የጌድሶን ልጆች ስማቸው ሎቤን፡ ሴሜይ ነው ።

፲፯ ወደቂቁኒ ለቀዓት በበሕዘቢሆሙ፡ እንበረም ወይሰዓር ወኬብሮን ወአዛሔል ።

በየወገኖቻቸው የሚጠሩ የቀዓት ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤ እንበረም፡ ይሰዓር፡ ኬብሮን አዛሄል ነው ።

፲፰ ወደቂቁኒ ለሜራሪ በበሕዘቢሆሙ ሙሐሊ ወሐሙሲ ዝንቱ ውእቱ ነገደ ሌዋውያን በበአብያተ አበዊሆሙ ።

በየወገኖቻቸው የሚጠሩ የሜራሪም ልጆች ሙሐሊ ሐሙሲ ናቸው፡ በየወገኖቻቸው የሚጠሩ የሌዋውያን ነገድ ይህ ነው ።

፲፱ ዘጌድሶን ሕዝበ ጌድሶን፡ ዘሎቤን ሕዝበ ሎቤን፡ ዘሴሜይ ሕዝበ ሴሜይ፡ ዝንቱ ሕዝብ ዘጌድሶን ።

የጌድሶን ወገን ተብለው የሚጠሩ የጌድሶን ወገኖች የሎቤን ወገን ተብለው የሚጠሩ የሎቤን ወገኖች፡ የሴሜይ ወገን ተብለው የሚጠሩ የሴሜይ ወገኖች፡ የጌድሶን ነገድ ይህ ነው፡ (ይህ ነገድ የጌድሶን ነው) ።

፳ ወዘአስተፋቀዱ ኍልቈ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ኍላቌሆሙ ሰብዓ ምእት፡ ወአርበዕቱ ምእት ።

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ያቈጣጠሩዋቸው ወንዶች ሁሉ ቍጥራቸው ሰባት ሺሕ አራት መቶ ነው ።

፳፩ ወየኀብሩ ደቂቀ ጌድሶን ድኅረ ደብተራ መንገለ ገጸ ባሕር ።

የጌድሶን ልጆች ከደብተራ ኦሪት በስተኋላ በከበርው ቤት በምዕራብ በኩል ይሰፍራሉ (ይስፈሩ) ።

፳፪ ወመልአኮሙ ዘቤተ አበዊሆሙ ለሕዝበ ጌድሶን ኤልሳፍ ወልደ አዳሔል ።

የጌድሶን ወገን አባቶች አለቃ የአዳሔል ልጅ ኤልሳፍ ነው ። ዘኍ፡ ፫ ፳፱ ።

፳፫ ወዘይትሐበዩ ደቂቀ ጌድሶን እምደብተራ ዘመርጡል ደብተራ ወሠቃቲሃ ወመክደና ወመንጦላዕተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

የጌድሶን ልጆች በመገናኛው ድንኳን የሚሸከሙት ሸክማቸው ድንኳኑ (ሠቃት) አራቱን ኅብር ብስሙን (መክደና) ማእሰ መጋረጃ የደብተራ ኦሪት ደጃፍ መጋረጃ ነው።

፳፬ ወአልባሰ ዐፀድ ወመንጦላዕተ አንቀጽ ዘዐፀደ ደብተራ ወዘተርፈ ኵሉ ምግባራቲሃ ።

የአደባባዩ መጋረጆች በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ያለው መጋረጃ የቀረውም ዕቃዋ ሁሉ ነው ። ዘፀ፡ ፳፯ ፲፯ ።

፳፭ ወዘቀዓትኒ ሕዝበ እንበረም ወሕዝበ ኬብሮን ወሕዝበ አዛሔል እሉ ውእቶሙ ሕዝብ ዘቀዓት ።

የቀዓት ወገን ተብለው የሚቈጠሩት የእንበረም ወገኖች የአዛሔል ወገኖች የኬብሮን ወገኖች የይሰዓር ወገኖች በየወንዶቻቸው ቍጥር የቀዓት ወገኖች እነዚህ ናቸው ።

፳፮ በበኍልቈ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ሰማንያ ምእት ወሰብዐቱ ምእት፡ ወየዐቅቡ ሕጎሙ ለቅዱሳን ።

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው የተቈጠረው ወንድ ወንዱ ሁሉ ስምንት ሺሕ ሰባት መቶ ነው፡ የአሮንና የሙሴን ሕግ (ንዋየ ቅድሳቱን) ይጠብቃሉ ።

፳፯ ወየኀድሩ ሕዝበሙ ለደቂቀ ቀዓት እምገቦሃ ለደብተራ ዘመንገለ አዜብ ።

የቀንት ልጆች ወገኖችም በግራ በኩል በደብተራ ኦሪት አጠገብ ይስፈሩ ። ዘፀ፡ ፴ ፳፬፡ ዘኍ፡ ፫ ፴፰ ።

፳፰ ወመልአኮሙ ለቤተ አበዊሆሙ ለሕዝበ ቀዓት ኤልሳፍ ወልደ አዛሔል ።

የቀዓት ወገን አባቶች አለቃም የአዛሔል ልጅ ኤልሳፍ ነው ። ዘፀ፡ ፳፰ ፲፯ ።

፳፱ ወዘይትሐበዩ እሙንቱ ታቦተ ወማእደ ወመራናተ ወምሥዋዐ ወንዋያተ ዘቅድሳት ኵሉ ዘይገብሩ ቦቱ መክደኒ ወኵሎ ምግባራተ ።

እነዚህም የሚሸከሙት ታቦቱን፡ የማእድ ሰደቃውን ማብሪያውን ንዋየ ቅድሳቱን፡ ሥራ የሚሠሩበትን ዕቃ ሁሉ መሸፈኛውን መሣሪያውን የሚያገለግሉበትን ዕቃ ሁሉ ነው ። ዘፀ፡ ፳፮ ፩፡ ፴፩ ፳፮ - ፴፩ ።

፴ ወመልአክ ዘዲበ መሳፍንቲሆሙ ለሌዋውያን አልአዛር ወልደ አሮን ካህን ዘተሠይመ ይዕቀብ ሕጎሙ ለቅዱሳን ።

የአሮንና የሙሴን ሕግ ሊጠብቅ በሌዊ ልጆች ሹሞች ላይ የተሾመው አለቃም የካህኑ የአሮን ልጅ አልአዛር ነው ። ፪ ነገ፡ ፳፰ ፲፰ ።

፴፩ ወዘሜራሪኒ ሕዝበ ሙሐሊ ወሕዝበ ሐሙሲ እሉ እሙንቱ ሕዝበ ሜራሪ ።

የሙሐሊ ወገኖች የሐሙሲም ወገኖች የሜራሪ ወገኖች ተብለው የሚጠሩት እሊህ ናቸው ።

፴፪ ወኍላቌሆሙኒ በከመ አስተፋቀድዎሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ስሳ ምእት ።

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ እንደ አቈጣጠሩዋቸው ቍጥራቸው ስድስት ሺሕ ነው ።

፴፫ ወመልአኮሙ ለቤተ አበዊሆሙ ለሕዝበ ሜራሪ ሱራሔል ወልደ አቤኪያ ወየኀድሩ በገቦሃ ለደብተራ ዘመንገለ መስዕ ።

የሜራሪ ነገድ አባቶች አለቃም የአቤኪያ ልጅ ሱራሔል ነው፡ እነዚህም በደብተራ ኦሪት አጠገብ በሰሜን በኩል ይሰፍራሉ (ይስፈሩ) ።

| | | |
|---|---|---|
| ወዘይትሐበዩ ነገደ ደቂቀ ሜራሪ አርእስተ አዕማድ ዘደብተራ ወመናሥግቲሆን ወአዕማዲሃ ወመከየዲሆን ወኵሉ ንዋዮን ወምግባራቲሆን ። | ፴፬ | የሜራሪ ልጆች ነገድ የድንኳኑን ተራዳዎች ክባሶች፣ ማገሮቻቸውን ተራዳዎቹን ሰከተታቸውን ክስማዎችን ሁሉና መምቻውንም ። ዘፀ፣ ፳፯ ፲፭፣ ዘኍ፣ ፫ ፴፬ ። |
| ወአዕማደ ዘዐውደ ዐፀድ ወመከየዲሆን ወመታከሊሆን ወመታግሪሆን ። | ፴፭ | በአደባባዩ ዙርያ ያሉትን ምሰሶዎች ሰከተታቸውን ክስማዎችንና መምቻውንም ሁሉ ይሸከሙ (ይጠብቁ) ነበር ። |
| ወእለሰ የኀድሩ ቅድመ ደብተራ ዘመርጡል መንገለ ጽባሕ ሙሴ ወአሮን ወደቂቁ ከመ ይዕቀቡ ሕገ መቅደስ ወሕጎሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣ ወእመቦ ዘገሠሠ እምባዕድ ዘመድ ለይሙት ። | ፴፮ | የእስራኤልን ልጆች ሕግና የመቅደሱን ሕግ ይጠብቁ ዘንድ በስተምሥራቅ በኩል በደብተራ ኦሪት ፊት ለፊት የሚሰፍሩ ሙሴ አሮንና ልጆቹ ናቸው ፣ ከሌላ የተወለደ ንዋየ ቅድሳቱን የነካ ቢኖር ይገደል ። ዘኍ፣ ፩ ፶፫ ፣ ፪ ፲ ። |
| ወኵሉ ኈላቊሆሙ ለሌዋውያን ዘኈለቁ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር በበሕዘቢሆሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ክልኤቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ። | ፴፯ | ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሙሴና አሮን በየወገኖቻቸው የቈጠሩዋቸው የሌዋውያን ቍጥር ሁሉ ሃያ ሁለት ሺሕ ነው ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ኈልቍ ኵሎ በኵሮሙ ተባዕተ ለደቂቀ እስራኤል ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ፣ ወአእምር ኈላቊሆሙ በበአስማቲሆሙ ። | ፴፰ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው የእስራኤልን ልጆች መጀመሪያ የተወለደው ወንድ ወንዱን ሁሉ በየስማቸው ቈጥረህ ቍጥራቸውን ዕወቅ ። |
| ወታገብኦሙ ሊተ ለሌዋውያን ህየንተ ኵሉ በኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወእንስሳሆሙ ለሌዋውያን ህየንተ ኵሉ በኵረ እንስሳሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፴፱ | ስለ እስራኤል ልጆች የበኵር ልጅ ሁሉ ፈንታ ሌዋውያንን ለኔ አግባቸው ከብቶቻቸውንም ስለ እስራኤል ልጆች ከብት በኵር ሁሉ ፈንታ ለኔ ተቀበላቸው ። |
| ወኈለቆሙ ሙሴ ለኵሉ በኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ። | ፵ | ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው የእስራኤልን ልጆች በኵር በኵር ሁሉ ቈጠራቸው ። |
| ወኮነ ኵሉ በኵር ተባዕት በኈልቈ አስማቲሆሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ክነ ኈላቊሆሙ ክልኤቱ እልፈ ወዕሥራ ምእት ክልኤቱ ምእት ሰብዓ ወሠለስቱ ። | ፵፩ | ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው በየስማቸው ተቈጥረው የወንድ ወንዱ በኵር ሁሉ ቍጥራቸው ሃያ ሁለት ሺሕ፣ ሁለት መቶ፣ ሰባ ሦስት ሆነ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ንሥኦሙ ለሌዋውያን ህየንተ ኵሉ በኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፵፪ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ነገረው፤ ስለ እስራኤል ልጆች የበኵር ልጅ ሁሉ ፈንታ ሌዋውያንን ተቀበላቸው ። |
| ወእንስሳሆሙኒ ለሌዋውያን ህየንተ ኵሉ በኵረ እንስሳሆሙ ወይኩኑኒ ሊተ ሌዋውያን እስመ አነ እግዚአብሔር ። | ፵፫ | የሌዋውያንም ከብቶቻቸውን ስለ እስራኤል ልጆች ከብቶች በኵር ሁሉ ፈንታ ተቀበል ፣ ይህን ያዘዝኩ እኔ እግዚአብሔር ነኝና ሌዋውያን ለኔ ይሁኑኝ ። |
| ወቤዛሆሙኒ ለእልክቱ ክልኤቱ ምእት ወሰብዓ ወሠለስቱ ፣ እለ ፈድፈዱ እምሌዋውያን በኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣ ትነሥእ ለለአሐዱ በዲድርክም ዘቅዱስ ዕሥራ አቦሊ ዘሰቅሉ ። | ፵፬ | ከሌዋውያን በዝተው የተገኙት የነዚያን ሁለት መቶ ሰባ ሦስት የእስራኤል ልጆች ለውጣቸውን በቤተ መቅደሱ ሚዛን ከየአንድ አንዱ አምስት አምስት አቅመት ተቀበል ፣ ይኸውም የሰቅሉ ሚዛን ሃያ አቦሊ ነው ፣ (አቦሊ ፳ አበት ፣ ፳ ግርሽ ነው) አለው ። ግላ፡ ፬ ፩ ። |
| ወትሁቦሙ ወርቀ ለአሮን ወለደቂቁ ቤዛሆሙ ለእለ ፈድፈዱ እምኔሆሙ ። | ፵፭ | ከነሱ የተረፉት የእስራኤል ልጆች ቤዛ ወርቁን ለልጆቹና ለአሮን ስጣቸው ። |
| ወነሥአ ሙሴ ውእተ ወርቀ ዘቤዛሆሙ ለእለ ፈድፈዱ እምነ ቤዛሆሙ ለሌዋውያን ዘበኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፵፮ | ሙሴም ከሌዋ ልጆች የበዙ የእስራኤል የበኵር ልጆች ዋጋ የሚሆን ያንን ወርቅ ተቀበለ ። |
| ወነሥአ ወርቀ ዐሠርተ ምእተ ወሠለስተ ምእተ ወስሳ ወኀምስተ ሰቅሉ በሰቅል ቅዱስ ። | ፵፯ | በቤተ መቅደስ አዋቂ (ሚዛን) ሺሕ ሦስት መቶ፣ ስሳ አምስት ወርቅ ተቀበለ ። ዘኍ፣ ፫ ፵፯ ። |
| ወወሀቦሙ ሙሴ ውእተ ወርቀ ቤዛሆሙ ለእለ ፈድፈዱ ለአሮን ወለደቂቁ በቃለ እግዚአብሔር በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፵፰ | ከነዚያ የበዙት ልጆች ዋጋ የሚሆን ያንን ወርቅ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለአሮንና ለልጆቹ ሰጣቸው ። ዘኍ፣ ፫ ፵፰ ። |

## ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ፤ ፍልጥዎሙ ለደቂቀ ቀዓት እማእከሎሙ ለደቂቀ ሌዊ በበሕዘቢሆሙ ወበበቤተ አበዊሆሙ ።

፪ ዘእምዕሥራ ወኀምስቱ ዓም ወላዕሉ፤ እስከ ኀምሳ ዓም፤ ኵሉ ዘይበውእ ይግበር ግብረ ኵሉ ምግባር ዘውስተ ደብተራ ።

፫ ወዝንቱ ውእቱ ግብሮሙ ለደቂቀ ቀዓት በደብተራ ዘመርጡል ቅድስት ዘቅዱሳን ።

፬ ወይበውኡ አሮን ወደቂቁ ሶበ ይትነሣእ ትዕይንት ወያወርዱ መንጦላዕተ ዘይሜውር፤ ወይከድንዋ ቦቱ ለታቦት ዘመርጡል ።

፭ ወይወድዩ መልዕልቶ ክዳነ ዘማእሰ መጸጺት፤ ወይወድዩ መልዕልቶ ልብሰ ዘኵለንታሁ ያክንት ወይወድዩ መፃውርቲሃ ።

፮ ወዲበ ማእድኒ እንተ ሥርዐት ይወድዩ ልብሰ ዘኵለንታሁ ኅብረ ከብድ ወይወድዩ ላዕሌሃ መጻብሕቲሃ ወአጽሕልቲሃ ወመዳምኒሃኒ ወመዋጽሕቲሃ በዘቦቱ ያወጽሑ ወኅብስታኒ ዘይሠርፅ በኵሉ ጊዜ ላዕሌሃ ።

፯ ወይወድዩ ላዕሌሃ ልብሰ ለይ ወይከድንዋ መክደነ ዘማእሰ መጸጺት ወያስተዋድዱ መፃውርቲሃ ።

፰ ወይነሥኡ ልብሰ ያክንት ወይከድንዋ ለመራናት እንተ ላዕሌሃ፤ ያኀትዉ መኀትዊሃ ወጕጠታቲሃ በዘቦቱ ያሜንይዋ ወኵሎ ግምዔያቲሃ ዘቅብዕ ዘእምውስቴቱ ይገብርዋ ።

፱ ወይወድይዋ ላቲ ወለኵሉ ንዋያ ውስተ መክደና ዘእማእሰ መጸጺት ወያስተዋድዱ መፃውርቲሃ ።

፲ ወለምሥዋዕኒ ዘወርቅ ይገለብብዎ በልብስ ዘያክንት ወይከድንዎ እምላዕሉ በማእሰ መጸጺት፤ ወያስተዋድዱ መፃውርቲሁ ።

፲፩ ወይነሥኡ ኵሎ ንዋያተ ግብር ዘቦሙ ይገብሩ ወይወድይዎሙ ውስተ ልብስ ዘያክንት፤ ወይከድንዎ በማእሰ መጸጺት ወያነብሩ መፃውርቲሁ ወያሴስሉ ሐመደ ።

፲፪ ወመክደንሂ ያነብሩ ላዕለ ምሥዋዕ ወይከድኑ ላዕሌሁ ልብሰ ዘኅብረ ከብድ ።

፲፫ ወይወድዩ ውስቴቱ ኵሎ ንዋያቲሁ ዘቦሙ ይገብሩ ማዕጠንታተ ወመኀሥሣተ ወፍያላተኒ ወጸሕራተኒ ወምክዓዋተኒ ወኵሎ ንዋየ ምሥዋዕ ።

፲፬ ወይወድዩ ላዕሌሁ መክደነ ዘማእሰ መጸጺት ወያነብሩ መፃውርቲሁ ወያነሥኡ ልብሰ ዘኅብረ ከብድ ወይከድንዎ ለማእከክ ወለመከየዱ ወይወድዩ ላዕሌሁ መክደነ ዘማእሰ መጸጺት ወያነብሩ መፃውርቲሁ ።

፲፭ ወፈጺሞሙ አሮን ወደቂቁ ከዲነ ዘቅድሳት ወኵሎ ንዋያተ ቅድሳት ይትነሣእ ትዕይንት፤ ወእምዝ ይበውኡ

## ምዕራፍ ፬ ።

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፤ የቀነትን ልጆች በየአባቶቻቸው ቤትና በየወገኖቻቸው ከሌዊ ልጆች መካከል ለዩዋቸው ።

ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ ከዚያም እስከ አምሳ ዓመት የሆነውን በደብተራ ኦሪት የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ይሠራ ዘንድ የሚገባውን ሁሉ ለዩዋቸው ።

የቀዓትም ልጆች ልዩ በሆነች ድንኳን በቅድስተ ቅዱሳን የሚሠሩት ሥራቸው ይህ ነው ። ዘፀ፡ ፵ ፲ ።

ሰፈሩ በሚነሣበት ጊዜ አሮንና ልጆቹ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብተው ቅድስተ ቅዱሳኑን የሚሸፍነውን መጋረጃ አውርደው የምስክሩን ታቦት ይሸፍኗት ። ዘሌ ፲፮ ፪ ።

በላዩም የአስቆጣውን (ማእሰ መጸጺት) ሸፍነው ሁለንትናው ሰማያዊ የሆነ መጐናጸፊያን ያድርጉበት መሎጊያዎቹንም በቀለበቷ ያግቡ ። ዘፀ፡ ፳፭ ፲፫ ።

በተሠራች ማእድም ላይ ሁለንትናው ብጫ የሆነ ልብስ ይዘርጉበት፤ ታናናሽ ወጭቶቿን ታላላቅ ወጭቶቿን፤ ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱበት ጽዋዎቿን ማንከዎቿን በላይዋ ላይ ያድርጉ፤ በየጊዜው የሚሠሩትም ገጸ ኅብስት በርሷ ላይ ያኑሩት ። ዘፀ፡ ፳፭ ፳፫፤ ዘሌ፡ ፳፬ ፭ ።

በላይዋም ላይ ቀይ ልብስ፡ ቀለም የገባ ባሕረ ዓረብ ይሸፍኗት፤ መሎጊያዎቿንም በቀለበቷ ያግቡ ።

ሰማያዊ መጐናጸፊያንም አምጥተው በላይዋ መብራት የሚያበሩበት መቅረዝን ያልብሷት፤ የሚኰስትሩበት ወለባዎቿን ሁሉ የሚያበሩበት የዘይቱን ማሰሮዎችንም ሁሉ ይሸፍኑዋት ። ዘፀ፡ ፳፭ ፴፯ ።

እርሷን ከዕቃዋ ሁሉ ጋር ቀለም በገባ ባሕረ ዓረብ ይሸፍኗት፤ መሎጊያዎቿንም ያስማሙ ።

የወርቁንም መሠውያ በሰማያዊ ሐር ልብስ ይሸፍኑት በላዩም ላይ በማእሰ መጸጺት መሸፈኛ ይሸፍኑት መሎጊያዎቹንም ያስማሙ ። ዘፀ፡ ፴፩ ፭ ።

የሚሠሩባቸው የሥራ ዕቃዎችንም ሁሉ አምጥተው በሰማያዊ ሐር መጐናጸፊያ ሸፍነው በአስቆጣው ቍርበት ይሸፍኑት፤ በመሸከሚያዎቹም ላይ ያድርጉት፤ አመዱንም ከመሠውያው ላይ ይጥረጉት ።

መክደኛውንም በመሠዊያው ላይ ገጥመው በላዩ ቀይና ሰማያዊ የሆነ ሐምራዊ መጐናጸፊያ ያልብሱት ።

ሥራ የሚሠሩባቸው ዕቃዎችን ሁሉ ጥናዎቹን፤ ሥጋ የሚያወጡባቸው ሜንጦዎችን ደም የሚቀበሉባቸው ጣሳዎችን በገ ፈጅ ድስቶችን አመድ የሚያፈሱባቸው ዕንቅቦቹን የመሠውያውን ዕቃ ሁሉ በውስጡ ያስቀምጡ ።

ማእሰ መጸጺት መሸፈኛ በላዩ ላይ ያልብሱት መሎጊያዎችንም ያስማሙ፤ ቀይና ሰማያዊ መልክ ያለውን ሐምራዊ ልብስ አምጥተው ሰኑንና እግር ዛቁነውን ይሸፍኑት መሎጊያዎችንም በቀለበቱ ያግቡ፤ በላዩም የአስቆጣውን ቍርበት መሸፈኛ ይዘርጉበት ። ዘኍ፡ ፯ ፲፫ ።

አሮንና ልጆቹም ጽላቱን (መቅደሱን) ንዋየ ቅድሳቱን ሁሉ ሸፍነው ከጨረሱ በኋላ ጓዙ ይነሣ፤ ከዚህ በኋላ የቀ

ደቂቀ ቀዓት ይትመጠዉ ወኢይገሥሡ ዘቅድሳት ከመ ኢይሙቱ ዝንቱ ዘይፀውሩ ደቂቀ ቀዓት ዘእምውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፲፮ ወሥዩም ውእቱ አልአዛር ወልደ አሮን ካህን ላዕለ ቅብዐ ማኅቶት ወላዕለ ዕጣን ዘየዐጥኑ ወላዕለ መሥዋዕት ዘኵሉ አሚር ወላዕለ ቅብዕ ዘይትቀብዑ ወላዕለ ኵሉ ንዋየ ደብተራ ዘመርጡል ሥዩም ውእቱ፡ ወላዕለ ኵሉ ዘሀሎ ውስተ መቅደስ ወላዕለ ኵሉ ግብር ።

፲፯ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ኢትሥርውዎሙ ለነገደ ሕዝቡ ለቀዓት እማእከሎሙ ለሌዋውያን ።

፲፰ ወከመዝ ግበሩ ሎሙ ወየሐይዉ ወኢይመውቱ በበ ዊአቶሙ ውስተ ቅድስተ ቅዱሳን፡ አሮን ወደቂቁ ይባኡ ወያስተዳልዉ ሎሙ ያሮሙ ለለአሐዱ እምኔሆሙ ።

፲፱ ወኢይባኡ ግብተ ይርአዩ ቅድሳተ ወኢይሙቱ ።

፳ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ እኀዝ ኍልቆሙ ለደቂቀ ጌድሶን እምዮንቱ በበአብያተ አበዊሆሙ ወበበ ሕዘቢሆሙ ።

፳፩ ዘእምዕሥራ ወኀምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘሐምሳ ዓም ኍልቆሙ፡ ኵሉ ዘይበውእ ይግበር ግብረ በውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፳፪ ወዝንቱ ውእቱ ግብሮሙ ለነገደ ጌድሶን ዘይገብሩ ወይፀውሩ ።

፳፫ አዕፃዳተ ደብተራ ወሥቃተ ዘመርጡል መክደኒሁ ወመክደን ዘመጸጺት ዘዲቤሃ ዘእምላዕሉ፡ ወመክደነ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፳፬ ወመንጦላዕተ ዐፀድ፤ ወመክደነ አንቀጸ ዐፀድ፤ ዘደብተራ፡ ወኵሉ ንዋየ ግብሮሙ በዘቦቱ ይገብሩ ።

፳፭ ወይገብሩ በከመ አዘዝዎሙ አሮን ወደቂቁ ከማሁ ይኩን ግብሮሙ ለደቂቀ ጌድሶን በኵሉ ሕቢቶሙ ወበኵሉ ግብሮሙ፡ ወኍለቆሙ በበአስማቲሆሙ ለኵሉ ዘይፀውሩ ።

፳፮ ወዝንቱ ውእቱ ሕቢቶሙ ለደቂቀ ጌድሶን በውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወሊቆሙ ይታምር ወልደ አሮን ካህን ።

፳፯ ወለደቂቀ ሜራሪ በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ኍልቆሙ ።

፳፰ ዘእምዕሥራ ወኀምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘኀምሳ ዓም ኍልቆሙ ለኵሉ ዘይበውኡ ይግበሩ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ።

፳፱ ወዝንቱ ውእቱ ሕቢቶሙ ዘይፀውሩ እሙንቱ በኵሉ ግብሮሙ ዘውስተ ደብተራ ዘመርጡል አርእስቲሃ ለደብተራ ወአዕማዲሃ ወመናሥግቲሃ ወመከየዲሆን ።

፴ ወአዕማደ ዘብሩር ዘመንጦላዕተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወመከየዲሆን፡ ወአዕማደ ዓውደ ዐፀድ ወመከየዲሆን ወአዕማደ መንጦላዕት ዘአንቀጸ ዓፀድ ወመከየዲሆን፡

ዓት ልጆች ሸክማቸውን ሊቀበሉ ይግቡ፡ ነገር ግን እንዳ ይቀሠፉ ንዋየ ቅድሳቱን አይንኩ፡ በደብተራ ኦሪት የሚ ሸከሙት ይህ ነው ። ዘዳግ፡ ፴፩ ፱ ።

የካህኑም የአሮን ልጅ አልአዛር በመብራቱ ዘይት በሚያጥኑት ዕጣን፡ ሁሉ ጊዜ በሚሠዋው መሥዋዕት በሚቀቡትም ዘይት በደብተራ ኦሪት ውስጥ ባለው ዕቃ ሁሉ ላይ ሹም ነው፡ በመቅደሱ ውስጥ ባለው ዕቃ ሁሉ ላይና ሥራ በሚሠሩበትም ሁሉ ላይ ሹም ነው ።

የቀዓት የወገኖቹን ነገድ ከሌዋውያን መካከል አታጥ ፉዋቸው ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ነገራቸው ።

ነገር ግን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባታቸው እንዳ ይቀሠፉ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እንዲህ አድርጉላቸው አሮንና ልጆቹ ከነዚህ ላንዱም ላንዱ ሸክማቸውን ያዘጋ ጁላቸው ። ዘኍ፡ ፬ ፬ ።

ንዋየ ቅድሳቱን አይተው ድንገት እንዳይቀሠፉ ወደ ቅድስተ ቅድሳን አይግቡ ። ዘፀ፡ ፲፱ ፳፩ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ የጌድ ሰን ልጆች በየአባቶቻቸው ቤቶችና በየወገኖቻቸው ከበ ኵሩ ጀምረህ ቍጥራቸውን ያዝ ። ዘፀ፡ ፴፰ ፳ ።

በደብተራ ኦሪት ሥራ ይሠራ ዘንድ የሚገባውን ሁሉ ከሃያ አምስት ዓመት፡ ከዚያም በላይ እስከ አምሳ ዓመት ያሉትን ቍጠራቸው ። ዘፀ፡ ፰ ፳፬ ።

የጌድሶን ነገድ የሚሠሩት ሥራቸው የሚሸከሙት ሸክማቸው ይህ ነው ። ዘኍ፡ ፬ ፲፭፡ ፲፱ ፳፯ ።

የደብተራ ኦሪትን ፈርጅ የሚሸፍን ብስጥ፡ የመገናኛ ውን ድንኳን የሚሸፍን ቀለም የገባ ባሕረ ዓረብ የድን ኳኑ ደጃፍ መጋረጃ ። ዘፀ፡ ፳፯ ፩፡ ፴፯ ።

በአደባባዩ ያለውን መጋረጃ በደብተራ ኦሪትና በመሠ ውያ ዙርያ ያለውን የአደባባዩን ደጃፍ መጋረጃ ሥራ የሚ ሠሩበትን ዕቃ ሁሉ የሚያገለግሉበትን ሥራ ዕቃ ሁሉ ይሸከሙ ።

አሮንና ልጆቹ እንዳዘዙዋቸው ያድርጉ፡ የጌድሶን ልጆች ሥራቸውና አገልግሎታቸው ሁሉ በአሮንና በል ጆቹ ትእዛዝ ይሁን የሚሸከሙትን ሰዎች በየስማቸው ቁጠራቸው ። ዘኍ፡ ፬ ፴፯፡ ፫ ፲፯ ።

የጌድሶን ልጆች በደብተራ ኦሪት የሚሸከሙት ይህ ነው፡ አለቃቸውም የካህኑ የአሮን ልጅ ይታምር ነው ።

የሜራሪንም ልጆች በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገን ቍጠራቸው ።

ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ አም ሳ ዓመት የሆነውን በደብተራ ኦሪት ሥራ ይሠሩ ዘንድ የሚገባቸውን ሁሉ ቍጠራቸው ። ዘፍ፡ ፵፩ ፵፯ ።

በደብተራ ኦሪት የሚሠሩት ሥራቸው ሁሉ የሚሸከ ሙት ሸክማቸው ይህ ነው፡ የደብተራ ኦሪት ክባሶችዋን ተራዳዎቿን ማገሮቿንና ሰክተታቸውንም ።

የደብተራ ኦሪት ደጃፍ መጋረጃ የብር ምሰሶዎችን ሰክተታቸውን የዙርያውንም አድሞ ምሰሶዎች ሰክተታ ቸውን የደብተራ ኦሪት ደጃፍ መጋረጃ ምሰሶዎችን ሰክተ

ወኵሉ ንዋዮን ወመታክሊሆን ወመታግሪሆን ወኵሉ ንዋየ ግብሮሙ በበአስማቲሆሙ ትኌልቆሙ ወለኵሉ ንዋየ ሕቢቶሙ ዘይፀውሩ ።

ታቸውንና ዕቃዎቻቸውን ሁሉ ከስማዎቻቸውን መምቻዎቻቸውን የሥራቸውን ዕቃ ሁሉ ይህን ሁሉ ይሸከሙ፤ በየስማቸው ቍጠራቸው የሚሸከሙትንም ሸክማቸውን ሁሉ ቍጠር። ዘፀ፣ ፴፰ ፳፩።

፴፩ ወዝንቱ ውእቱ ሕቢቶሙ ለነገደ ደቂቀ ሜራሪ በኵሉ ግብሮሙ ዘውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወእሙንቱኒ ላዕለ ይታምር ወልደ አሮን ካህን ።

የሜራሪ ልጆች ነገድ በደብተራ ኦሪት የሚሠሩት ሥራቸው ሁሉ ይህ ነው፤ እነሳቸውም በካህኑ በአሮን ልጅ በይታምር የሚታዘዙ ናቸው ። ዘኍ፣ ፬ ፳፰ ።

፴፪ ወኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር ምስለ መላእክቲሆሙ ለእስራኤል ለደቂቀ ቀዓት በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ።

አሮንና ሙሴም ከእስራኤል አለቆች ጋር በእግዚአብሔር ቃል የቀዓትን ልጆች በየወገኖቻቸው፣ በየአባቶቻቸው የቤት አለቆች ቈጠርዋቸው ።

፴፫ ዘእምዕሥራ ወኃምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘኃምሳ ዓም ለኵሉ ዘይበውእ ከመ ይግበር ውስተ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ።

ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ አምሳ ዓመት ድረስ ያሉትን የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ የሚገቡትን ሁሉ ቍጠሩዋቸው ።

፴፬ ወኮነ ኍላቌሆሙ በበሕዘቢሆሙ ዕሥራ ምእት፣ ወሰብዓቱ ምእት ወኃምሳ ።

በየወገኖቻቸው የተቈጠሩት ቍጥራቸው ሁለት ሺሕ ሰባት መቶ አምሳ ሆነ። ፩ ሕፀ፣ ፳፫ ፳፬ ።

፴፭ ዝንቱ ውእቱ ኍላቌሆሙ ለደቂቀ ቀዓት ለኵሉ እለ ይበውኡ ይግበሩ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል. በከመ ኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር ወበእደ ሙሴ ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝና በሙሴ ቃል ሙሴና አሮን እንደቈጠሩዋቸው የደብተራ ኦሪትን ዕቃ የሚሸከሙ የጌድሶን ልጆች ሁሉ ቍጥራቸው ይህ ነው ።

፴፮ ወኈለቍዎሙ ለደቂቀ ጌድሶን በበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ።

የሜራሪንም ልጆች ነገዶች በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች የቤት አለቆች ቈጠሩዋቸው ።

፴፯ ዘእምዕሥራ ወኃምስቱ ዓም ወላዕሉ፣ እስከ ዘኃምሳ ዓም ኵሉ ዘይበውእ ውስተ ግብር ከመ ይግበር ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ።

የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት የሚገቡትን ሁሉ ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ አምሳ ዓመት ያሉትን ሁሉ ቈጠሩዋቸው።

፴፰ ወኮነ ኍላቌሆሙ ዘበበአብያተ አበዊሆሙ ዕሥራ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ወኃምሳ ።

በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ቤቶች የተቈጠሩት ቍጥራቸው ሁለት ሺሕ ሰባት መቶ አምሳ ሆነ።

፴፱ ወዝንቱ ውእቱ ኍላቌሆሙ ለደቂቀ ጌድሶን ኵሉ እለ ይፀውሩ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ዘኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር ወበእደ ሙሴ ።

እግዚአብሔር በሙሴ ቃል እንዳዘዘ ሙሴና አሮን የቈጠሩዋቸው በደብተራ ኦሪት የሚያገለግሉት የጌድሶን ልጆች ሁሉ ቍጥራቸው ይህ ነው ።

፵ ወኈለቍዎሙ ለነገደ ደቂቀ ሜራሪ በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ።

በየወገኖቻቸውና በየአባቶቻቸው የቤት አለቆች የሜራሪን ልጆች ነገድ ቈጠሩዋቸው ።

፵፩ ዘእምዕሥራ ወኃምስቱ ዓም ወላዕሉ፣ እስከ ዘኃምሳ ዓም ኵሉ ዘይበውእ ይግበር ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

በደብተራ ኦሪት ያገለግል ዘንድ ወደ ሥራ የሚገባው ሁሉ ከሃያ አምስት ዓመት ከዚያም በላይ እስከ አምሳ ዓመት ድረስ ያሉትን ቈጠራቸው ።

፵፪ ወኮነ ኍላቌሆሙ በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ሠላሳ ምእት ወክልኤቱ ምእት ።

በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው የቤት አለቆች የተቈጠሩት ቍጥራቸው ሦስት ሺሕ ሁለት መቶ ሆነ።

፵፫ ዝንቱ ውእቱ ኍላቌሆሙ ለነገደ ደቂቀ ሜራሪ ዘኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር ወበእደ ሙሴ ።

እግዚአብሔር በሙሴ ቃል አሮንና ሙሴ የቈጠሩዋቸው የሜራሪ ልጆች ነገድ ቍጥራቸው ይህ ነው ።

፵፬ ወኵሉ እለ ተኈለቁ ዘኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን ወመላእክቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወኵሎሙ እለ ተኈለቁ ሌዋውያን በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ።

አሮንና ሙሴ የእስራኤልም አለቆች በየወገኖቻቸውና በየአባቶቻቸው ቤቶች የቈጠሩዋቸው ሌዋውያን ሁሉ ።

፵፭ ዘእምዕሥራ ወኃምስቱ ዓም ወላዕሉ፣ እስከ ዘሐምሳ ዓም ኵሉ ዘይበውእ ውስተ ምግባረ ግብር ዘይፀውሩ ዘደብተራ መርጡል፣ ወኮኑ እለ ተኈለቁ ሰማንያ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ።

ከሃያ አምስት ዓመት ከዚያም በላይ እስከ አምሳ ዓመት ድረስ ያለውን ወደ ሥራ የሚገባው የደብተራ ኦሪትን ዕቃ የሚሸከሙ የሌዊ ልጆች ቍጥራቸው ስምንት ሺሕ ሰባት መቶ ሆነ ።

፵፮ ወበቃለ እግዚአብሔር ተኈለቁ ብእሲ ብእሲ በበምግባሪሆሙ ወበበፆሮሙ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እያንዳንዱ ሰው በየሸክማቸውና በየሥራቸው በእግዚአብሔር ቃል ተቈጠሩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፭ ። | | ምዕራፍ ፭ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ያውፅኡ እምውስተ ትዕይንት ኵሎ ዘለምጽ ፡ ወኵሎ ዘይትከዐዎ ዘርኡ ፡ ወኵሎ ዘበቱ ርኵስ ውእቱ ነፍስቱ እምተብዕት እስከ አንስት ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ ለምጽ የያዘውን ሁሉ ዘሩ የሚፈሰውን ሁሉ በሰውነቱ ኃጢአት ያለበትን ሁሉ ከወንድ ጀምሮ እስከ ሴት ድረስ ከሰፈር ያወጡ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ። |
| ወያውፅእዎሙ አፍአ እምትዕይንት ወኢያርኵሱ ተዓይኒሆሙ ዘውስቴቱ አንድርኦሙ ። | ፪ | ከከተማ ወደ ውጭ ያውጧቸው ፣ እኔ የማድርበት በፈራቸውንም አያርክሱ እሰው ። ዘሌዋ ፤ ፱ ፲፯ ። |
| ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል ወአውፅእዎሙ አፍአ እምትዕይንት በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል ። | ፫ | የእስራኤልም ልጆች እንዳዘዛቸው አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አድርገው የእስራኤል ልጆች እንዲሁ ከከተማ ወደ ውጭ አወጡዋቸው ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ እመኒ ብእሲ ወእመኒ ብእሲት እመቦ ዘገብረ እምኵሉ ኀጣውእ ዘይገብሩ ኵሉ እጓለ እመሕያው ተዐዊሮሙ ወእመኒ በኢያእምሮ ። | ፬ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ ወንድም ቢሆን ሴትም ብትሆን ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቸል ብለው በለማወቅም ቢሆን ከሚሠሩት ኃጢአት ሁሉ የሠራ ሰው ቢኖር ። ዘሌዋ ፤ ፮ ፩-፫ ። |
| ወነስሓት ይእቲ ነፍስ ወአይድዐት ኵሎ ኀጢአታ ዘገብረት ያገብእ ዘነሥአ ርእሰ ንዋዩ ። | ፭ | ያች ሰውነት ተጸጽታ ያደረገችውን ኃጢአት ሁሉ ብትናገር የወሰደውን ዓይነቱን ገንዘብ ለባለ ቤቱ ይመልስ ። |
| ወሐምስተ እዴሁ ይዌስክ ላዕሌሁ ወያገብእ ለበዓለ ንዋዩ ። | ፮ | በዓይነቱ ላይ አምስት እጅ ጨምሮ ለባለ ገንዘቡ ይመልስ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ። ዘሌ ፤ ፭ ፭ ። |
| ወእመ አልቦ ሰብእ ዘየኀሥሦ ወአልቦ ኀማሚ ዘይትፈደዮ ለእግዚአብሔር ውእቱ ዘንስሓሁ ወይሁብ ለካህን ዘእንበለ በግዕ ዘበቱ ያስተሠሪ ሎቱ ። | ፯ | ነገር ግን የወሰደውን ገንዘብ የሚፈልገው ሰው ባይኖር ፤ የሚከፈለውም ዘመድ ባይኖረው ፤ የንስሐው ገንዘብ ለእግዚአብሔር ይሁን ፤ ኃጢአቱን ከሚያስተሠርይለት ከበጉ ሌላ ለካህኑ ነው ፤ (ይስጠው) ። ፩ ሕፀ ፤ ፳፫ ፳ ። |
| ወኵሉ እምቀዳምያት ዘያበውእ ወኵሉ ብፅዓቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘያበውእ ለእግዚአብሔር ለካህን ውእቱ ። | ፰ | ከመጀመሪያ አዝመራቸው የሚያገቡት ሁሉ የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር የሚያገቡት ስለታቸውም ሁሉ ለካህኑ ነው ። ዘሌ ፤ ፯ ፯ ። ዘዳ ፤ ፲፰ ፬ ። |
| ወብፅዓቲሆሙ ለለአሐዱ አሐዱ ለካህን ዘተመጠዎ ሎቱ ውእቱ ። | ፱ | እያንዳንዱም ሰው ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ብጽዓት ለተቀበለው ካህን ይሁን ። ዘፀ ፤ ፳፱ ፳፰ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ብእሲ ብእሲ ለእመ ዘአበሰት ብእሲቱ ወተዐወረቶ ። | ፲ | እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው ፤ እንዲህም አለው ፤ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ፤ ሚስቱ ቸል ብላው የበደለችው አንዱም አንዱም ሰው ቢኖር ። |
| ወቦ ዘሰከበ ምስሌሃ ተዐዊሮ ወዘመወት ወኢያእመራ ምታ ወኀብአት እምኔሁ እንዘ ርኵስት ይእቲ ወአልቦ ስምዕ ዘይዘልፋ ወእመኒ ንጽሕት ይእቲ ። | ፲፩ | ባሏን ቸል ብላ ሰስና ከባሏ ዓይን ተሸሽጋ ከርሷ ጋር የተኛ ሰው ቢኖር ፤ ይህም ሥራቸው ከባሏ ዓይን ተሠውሮ ብትሰስን ፤ ባሏም ይህን ባያውቅ ረክሳም ሳለች ብትሸሽግ የሚመሰክርባት ምስክር ባይኖር ከዚህም ተግባር የራቀች ብትሆን ። ዮሐ ፤ ፰ ፩ ። |
| ወመጽአ ላዕሌሁ መንፈሰ ቅንእ ወቀንአ ላዕለ ብእሲቱ እንዘ ርኵስት ይእቲ ወእመኒ እንዘ ኢኮነት ርኵስተ ወመጽአ ላዕሌሁ መንፈሰ ቅንእ ወቀንአ ላዕለ ብእሲቱ ፤ ያመጽኣ ውእቱ ብእሲ ለብእሲቱ ኀበ ካህን ። | ፲፪ | ሚስቱ ረክሳ ሳለች ባትረክስም በባሏ ላይ የቅንአት መንፈስ ቢነሣበትና በሚስቱ ቢቀና ያ ሰው ሚስቱን ወደ ካህን ያምጣት ። ምሳ ፤ ፴፮ ፮ ፴፬ ፤ ሲራ ፤ ፲፱ ፲፩ ። |
| ወያመጽእ ቍርባና በእንቲአሃ ዓሥርተ እዴሃ ለመስፈርተ ኢፍ ሐሪጸ ሰገም ወኢይሠውጥ ላዕሌሁ ቅብዐ ወኢይወዲ ዲቤሁ ስኂነ እስመ መሥዋዕተ ቅንአት ውእቱ ወመሥዋዕተ ተዝካር ዘያዜክር ኃጢአተ ውእቱ ። | ፲፫ | ስለሷ የሚያቀርበውን ቍርባኑን የኢፍ መስፈሪያ አሥረኛ እጅ አንድ ላዳን የገብስ ዱቄት ያምጣ ፤ ኃጢአትን የሚያሳስብ የመታሰቢያና ስለ ቅንአት የሚሠዋ መሥዋዕት ነውና ቍንዶ በርበሬና ዘይት አይጨምርበት ። |
| ወያቀርብ ኀበ ካህን ወያቀውማ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፲፬ | ወደ ካህን ያቅርባት ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ያቁማት ። |
| ወይነሥእ ካህን ማየ ንጹሐ በግምዔ ልሕኵት ወይነሥእ መሬተ እምውስተ ደብተራ ዘመርጡል እምድሩ ወይወድዮ ውስተ ውእቱ ማይ ። | ፲፭ | ካህኑም ንጹሕ ውኃ በሸክላ ዕቃ ይዞ ከደብተራ ኦሪት ውስጥ አፈር ዘግኖ በዚያ ውኃ ውስጥ ይጨምረው ። |
| ወያቀውማ ካህን ለይእቲ ብእሲት ቅድመ እግዚአብሔር ወይከሥት ርእሳ ለይእቲ ብእሲት ወይሜጥዋ ውስተ | ፲፮ | ካህኑም ያችን ሴት በእግዚአብሔር ፊት አቁሞ ራሷን ይግለጣት ፤ የኃጢአት መታሰቢያ የሆነውን ያን የቅንአት |

| | | |
|---|---|---|
| እዴሃ ዝከተ መሥዋዕተ ተዝካር ወመሥዋዕተ ቅንአት ። | | መሥዋዕት በእጅዋ ይስጣት ። |
| ወውስተ እዴሁሰ ለካህን ዝክቱ ማየ ዘለፋ ዘመርገም ። | ፲፯ | ርግማን የሚያመጣውም ያን መራራው ውኃ ግን በካህኑ እጅ ይሁን ። |
| ወያምሕላ ካህን ለይእቲ ብእሲት ወይብላ ለእመ አልቦ ዘሰከበ ምስሌኪ ወኢተዐወርኪ ምተኪ ወኢያገመንኪ ርእሰኪ ንጽሕተ ኩኒ እምዝንቱ ማየ ዘለፋ ዘመርገም ። | ፲፰ | ካህን ያችን ሴት እንዲህ ብሎ ያምላት ፤ ከንቺ ጋር የተኛ ወንድ የሌለ እንደሆነ፡ ባልሽን ቸል ያላልሽ እንደ ሆነ ራስሽንም በኃጢአት አላሳደፍሽ እንደሆነ መርገምን ከሚያመጣ ከዚህ መራራ ውኃ ንጹሕ ሁኚ ይበላት ። |
| ወእመሰ ተዐወርኪ ምተኪ ወአገመንኪ ርእሰኪ ወቦ ዘሰከበ ምስሌኪ ባዕድ ዘእንበለ ምትኪ ፡ ርግምተ ኩኒ ። | ፲፱ | ነገር ግን ባልሽን ቸል ብትዪ ራስሽን ብታሳድፊ ከባልሽ በቀር የደረሰብሽ ሌላ ሰው ቢኖር የተረገምሽ ሁኚ ብሎ ያምላት ። ኢያ፡ ፯ ፳፮ ፡ ፩ ሳሙ፡ ፲፬ ፳፬ ። |
| ወያምሕላ ካህን ለይእቲ ብእሲት በዝንቱ መሐላ ዘመርገም ። | ፳ | ካህን ያችን ሴት በዚህ የመርገም መሐላ ያምላት ። |
| ወይብላ ካህን ለይእቲ ብእሲት ርግምተ ለይረሲኪ እግዚአብሔር ወይደምስስኪ እማእከለ ሕዝብኪ ከመ ያውድቆ እግዚአብሔር ለገቦኪ ወይሠዐሮ ለከርሥኪ ። | ፳፩ | ካህን ያችን ሴት እግዚአብሔር የተረገምሽ ያድርግሽ፡ ጐንሽን ያወድቀው ዘንድ ሆድሽንም ይሰነጥቃት ዘንድ ከወገንሽ ለይቶ ያጥፋሽ ይበላት ። ዘፍ፡ ፴፰ ፳ ። |
| ወይበአ ዝንቱ ማይ ዘመርገም ውስተ ከርሥኪ ወይሥዐሮ ለማኅፀንኪ ወይደቅ ገቦኪ ፡ ወትብል ይእቲ ብእሲት አሜን አሜን ። | ፳፪ | ይህ መርገም ያለበት ውኃ ከሆድሽ ገብቶ ማኅፀንሽን ይሰንጥቃት፡ ጐንሽም እርግፍግፍ ይበል ፡ ያችም ሴት አሜን አሜን ትበል ። መዝ፡ ፻፱ ፲፰ ፡ ዘዳ፡ ፳፯ ፲፭ ። |
| ወይጽሕፎ ካህን ለዝንቱ መርገም ውስተ መጽሐፍ ወየሐፅቦ በውእቱ ማየ ዘለፋ ዘመርገም ። | ፳፫ | ካህኑም ይህን ርግማን በብራና ጽፎ በዚያ መርገም ባለበት መራራ ውኃ ይጠበው፡ (ይደምስሰው)። |
| ወይትሜጦ ካህን እምውስተ እዴሃ ዝከተ መሥዋዕተ ቅንእ ወያነብሮ ለውእቱ መሥዋዕት ቅድመ እግዚአብሔር ወያቀርቦ ኀበ ምሥዋዕ ። | ፳፬ | ካህኑ ያንን ስለ ቅንአት የሚሠዋው መሥዋዕት ከእጅዋ ተቀብሎ ያንን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ያቅርበው፤ ወደ መሠውያም ያግባው ። ዘሌዋ፡ ፰ ፳፯ ። |
| ወይዘግን ካህን እምውስተ ውእቱ መሥዋዕት ዝክራ ወይወድዮ ላዕለ ምሥዋዕ ወእምድኅረ ዝንቱ ያሰትያ ለይእቲ ብእሲት ውእተ ማየ ። | ፳፭ | ካህኑ ከዚያ ከመታሰቢያዋ መሥዋዕት እፍኝ ሙሉ ዘግኖ በመሠውያው ላይ ያቃጥለው፤ ከዚህ በኋላ ለዚያች ሴት ያንን ውኃ ያጠጣት ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፬፡ ዘሌዋ፡ ፪ ፱ ። |
| ወለእመ አገመነት ርእሳ ወተዐወረቶ ለምታ ይበውእ ውእቱ ማየ ዘለፋ ዘመርገም ውስተ ከርሣ ወይሜዕሮ ለከርሣ ወይወድቅ ገቦሃ ወትከውን ይእቲ ብእሲት መርገመ ውስተ ሕዝባ ። | ፳፮ | ራሷን አሳድፋ ባሏን ቸል ብላ እንደሆነ በባሏም ላይ ያ ርግማን የሚሆን የስድብ መጽሐፍ የተደገመበት ውኃ ከሆድዋ ገብቶ ይሰነጥቀዋል ጐኗም እርግፍግፍ ይላል፤ ያችም ሴት በወገኖቿ ዘንድ የተረገመች ትሆናለች ። |
| ወእመሰ ኢያገመነት ርእሳ ወንጽሕት ይእቲ ያነጽሓ ወዘርአ ይከውና ። | ፳፯ | ራሷን ያላሳደፈች ከኃጢአትም የነጻች ብትሆን ግን (ማየ ዘለፋው) ያነጻታል ፡ ልጅም ይሆናታል ። ዘሌ፡ ፪ ፱ ። |
| ዝንቱ ሕገ ቅንአት ለብእሲት እንተ አበሰት ላዕለ ምታ ወአገመነት ርእሳ ። | ፳፰ | በባሏ ላይ አመንዝራ ራሷን በአሳደፈች ሴት ላይ የሚፈጸም የቅንአት ሕግ ይህ ነው ። ኢያ፡ ፯ ፳፮ ። |
| ወለብእሲኒ ዘመጽአ ላዕሌሁ መንፈሰ ቅንእ ወቀንአ ላዕለ ብእሲቱ ያመጽኣ ወያቀውማ ለብእሲቱ ቅድመ እግዚአብሔር ወይገብር ላቲ ካህን ኵሎ ዘንተ ሕገ ። | ፳፱ | የቅንአት መንፈስ ለተነሣበትም ሰው በሚስቱም ላይ ለሚቀና ሰው የሚፈጸም የቅንአት ሥርዓቱ የቅንአት ሕጉ ይህ ነው፤ ሚስቱንም አምጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ያቁማት ካህኑም ይህን ሁሉ ሕግ ያድርግላት ። ዘኍ፡ ፩ ፳ ። |
| ወንጹሕ ውእቱ ብእሲ እምኀጢአት ወይእቲሰ ብእሲት ትነሥእ ኀጢአታ ። | ፴ | ያም ሰው ከኃጢአት ንጹሕ ይሆናል፤ ያችም ሴት በኃጢአቷ የሚመጣባትን ፍዳ ትቀበላለች ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ብሎ ነገረው ። ዘዳ፡ ፳፯ ፲፭ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፮ ። | | ምዕራፍ ፮ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ብእሲ አው ብእሲት ዘአዕበየ በጺዐ ብፅዓት ከመ ያንጽሕ ርእሶ ለእግዚአብሔር ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ ወንድም ቢሆን ሴትም ብትሆን ራሱን ለእግዚአብሔር የተለየ ያደርግ ዘንድ ብጽዓቱን ከፍ ከፍ ያደረገ ቢኖር ። |
| እምወይን ወእሚስ ያንጽሕ ርእሶ ወእምብኒአ ወይን ወእምብኒአ ሚስ ኢይስተይ ። | ፪ | ራሱን ከወይን ጠጅና ከማር ጠጅ (ከሚያሰክር መጠጥ) የተለየ ያድርግ፡ ከወይን ከማር ጠጅ የተገኘውን ሆምጣጣ አይጠጣ ። ዘፍ፡ ፵፱ ፳፮ ፡ ዘሌ፡ ፳ ፯ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወእምኵሉ ዘይትገበር እምአስካል ኢይስተይ ወአስካለ ወዘቢብ ኢይብላዕ በኵሉ መዋዕለ ብፅዓቲሁ ። | ፫ | ከዘለላው ከተጠመቀውም ሁሉ አይጠጣ ፥ በተሳለበትም ወራት ሁሉ ደረቁንና እሸቱን አይብላ ። |
| እምኵሉ ዘይትገበር እምዐፀደ ወይን ወእምአስካል ልምሉም እስከ ዘቢብ ሕጉር ኢይብላዕ ፥ በኵሉ መዋዕለ ብፅዓቲሁ በዘያነጽሕ ርእሶ ። | ፬ | ራሱን የተለየ ባደረገበት ወራት ሁሉ ከወይን በታ ከመጣው ከእሸቱ ጀምሮ እስከ ደረቀው ዘቢብ ድረስ አይብላ ። ዘኍ፡ ፮ ፭ ፡ ፲፫ ፳፩ ፡ አሞ፡ ፪ ፲፪ ። |
| መመላጺ ኢያቅርብ ዲበ ርእሱ እስከ ይትፈጸማ ኵሉን መዋዕላት ዘበፅዐ ለእግዚአብሔር ቅዱሰ ይከውን ወያነውኅ ሥዕርተ ርእሱ ። | ፭ | ራሱን ለመለየት ብጽዓት ባደረገበት ወራት ሁሉ በራሱ ላይ ምላጭ አያድርስ ራሱን ለእግዚአብሔር ብፅዓት አድርጎ የተለየባቸው ወራቶች እስኪፈጸሙ ድረስ ከሁሉም የተለየ ይሁን የራሱንም ጠጉር ያሳድግ ። |
| ወበኵሉ መዋዕለ ብፅዓቲሁ ለእግዚአብሔር ላዕለ ነፍስ እንተ ሞተት ኢይባእ ። | ፮ | ለእግዚአብሔር በተለየበት ወራት ሁሉ ወደ ሞተች ነፍስ አይግባ ። ዘሌዋ፡ ፳፱ ፲፩ ፡ ዘኍ፡ ፲፱ ፲፩ ። |
| ኢላዕለ አቡሁ ፥ ወኢላዕለ እሙ ወኢላዕለ እኍሁ ወኢላዕለ እኅቱ ከመ ኢይርኩስ በሙ እምከመ ሞቱ እስመ ብፅዓተ አምላኩ ሀለወ ላዕለ ርእሱ ። | ፯ | ለፈጣሪው ያደረገው ስለት በራሱ ላይ አለና ፥ አባቱም ቢሆን እናቱም ብትሆን ወንድሙም ቢሆን እኅቱም ብትሆን ከሞቱ በኋላ በነሳቸው እንዳይረክስ አይግባ ። |
| በኵሉ መዋዕለ ብፅዓቲሁ ይትቄደስ ለእግዚአብሔር ። | ፰ | በተሳለበት ወራት ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ (የተቀደሰ) ይሁን ። |
| ወእመሰ ዘሞተ በቱ ግብተ በኀበ ሀለወ ውእቱ ይረኵስ ብፅዓተ ርእሱ ወይላጺ ርእሶ በዕለተ ይነጽሕ በሳብዕት ዕለት ይትላጸይ ። | ፱ | እርሱ ባለበት በታ ድንገት የሞተበት ሰው ቢኖር ግን የራሱ ስለት ይረክሳል ፥ በሚነጻበት በሰባተኛው ቀን ራሱን ይላጭ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፲፰ ፲፰ ፡ ፩ ቆሮ፡ ፱ ፰ ። |
| ወአመ ሰምንት ዕለት ያመጽእ ክልኤተ ማዕነቀ አው ክልኤተ እጕለ ርግብ ኀበ ካህን ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፲ | በስምንተኛውም ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች ከካህኑ ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ያምጣ ። ዘሌዋ፡ ፭ ፯ ፡ ፲፬ ፳፪ ፡ ፲፭ ፲፬ ። |
| ወይገብር ካህን አሐተ በእንተ ኀጢአት ወአሐተ ለመሥዋዕት ፥ ወያስተሠሪ ካህን በእንቲአሁ በበይነ ዘአበሰ በእንተ ነፍሱ ወይቄድስ ርእሶ በይእቲ ዕለት ። | ፲፩ | ካህኑም አንዲቱን ስለ ኃጢአት ፥ አንዲቱን ስለ መሥዋዕት ያቅርብለት ፤ ሁለተኛይቱንም የሞተ ሰው ወዳለበት በመግባቱ ስለ በደለ ካህን ስለ ርሱ መሥዋዕተ ኃጢአቱን ሠርቶ ያስተሥርይለት ፥ በዚያችም ቀን ራሱን ያንጻ ። |
| ወይትቄደስ ለእግዚአብሔር በኵሉ መዋዕለ ብፅዓቲሁ ወያመጽእ በግዐ ዘዓመት ዘኀስሐ ፥ ወመዋዕለ ቀዲሙሰ ኢይትኄለቍ ሎቱ እስመ ረኵሰ ብፅዓተ ርእሱ ። | ፲፪ | ብፅዓቱን ባደረገበት ወራት ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ያድርገው ፥ ዓመት የሆነውን የንስሐውን በግ ያምጣ ፥ ራሱን የለየበት ብፅዓቱ ፈርሶአልና ያለፈው ወራት አይቈጠርለትም ። ዘሌዋ፡ ፭ ፮ ፡ ሕዝ፡ ፲፰ ፳፩ ። |
| ወዝንቱ ሕጉ ለዘበፅዐ አመ ዕለተ ይትፌጸም መዋዕለ ብፃዓቲሁ ይመጽእ ሊሊሁ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፲፫ | ብፅዓት ላደረገ ሰው ሕጉ ይህ ነው ፤ የመለየቱ ወራት በተፈጸመ ጊዜ ሰውዬው ራሱ ሊሊት ወደ ደብተራ ኦሪት ይምጣ ። ግብ፡ሐዋ፡ ፳፩ ፳፮ ። |
| ወያበውእ ቍርበኖ ለእግዚአብሔር በግዐ ዘዓመት አሐደ ንጹሐ ለመሥዋዕት ወአሐተ በግዕተ ንጽሕተ ዘዓመት በእንተ ኀጢአት ወሐርጌ አሐደ ንጹሐ ለመሥዋዕተ መድኀኒት ። | ፲፬ | ለእግዚአብሔርም የሚያቀርበውን ቍርባን ዓመት የሆነውን አንድ ንጹሕ በግ ያምጣ ፥ ለመሥዋዕተ ኃጢአትም አንዲት ነውር የሌለባትን ዓመት የሆናት እንስት በግ ያምጣ ፤ ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ነውር የሌለበትን አንድ የበግ ጠቦት ያምጣ ። ዘሌዋ፡ ፬ ፴፬ ፡ ፫ ፮ ። |
| ወከፈረ ኅብስተ ሥንዳሌ ዘናእት ዘግቡር በቅብዕ ወጸራይቀ ናእት ዘግቡር በቅብዕ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ። | ፲፭ | በዘይት የታበቀ ከልዝብ ሥንዴ የተጋገረ አንድ መሶብ ዳቦ ያምጣ ፥ በዘይት የታሸም ስስ ቂጣ ያምጣ ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱት ወይናቸውንና መሥዋዕታቸውንም ያቅርብ ። ዘሌዋ፡ ፪ ፬ ፡ ዘፀ፡ ፳፬ ፪ ። |
| ወያበውእ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ወይገብር ካህን ዘበእንተ ኀጢአት ወመሥዋዕት ። | ፲፮ | ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ያቅርበው ስለ ኃጢአቱና ስለ ንስሐውም ያመጣውን በግ ይሠዋው ። |
| ወይገብር ሐርጌኒ ለመሥዋዕተ መድኀኒት ለእግዚአብሔር ምስለ ዝንቱ ከፈረ ዘናእት ፥ ወይገብር ካህን መሥዋዕቶ ወሞጻሕቶ ። | ፲፯ | በእንቅብ ካለው ከዚሁ ቂጣም ጋር መሥዋዕተ ኃጢአት የሚሆነውን የበግ አውራ ለእግዚአብሔር ያቅርብ ፥ ካህንም ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱት ወይናቸውንና መሥዋዕታቸውን በመሠውያው ላይ ያድርገው ። |
| ወይላጺ ውእቱ ዘበፅዐ በኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመር | ፲፰ | ያም የተሳለው ሰው የተለየበት የራሱን ጠጕር በደብ |

ጡል ርእሰ ብፅዓቲሁ ወይወዲ ሥዕርቶ ላዕለ እሳት ዘመ
ሥዋዕተ መድኀኒት ።
ወይነሥእ ካህን መዝራዕቶ በእንዳሁ እምሐርጌ ወኅብ ፲፱
ስተ ናእት አሐተ እምከፈር ወአሐተ ጸፊቀ ናእተ ወያነብር
ውስተ እደዊሁ ለዘበፅዐ እምድኅረ ተላጸየ ርእሰ ።
ወያበውእ ካህን ቍርባኖ ቅድመ እግዚአብሔር ፣ ወቅ ፳
ዱስ ይከውን ለካህን ተላዕ ዘቍርባን ወመዝራዕት ዘመበእ
ወእምድኅረ ዝንቱ ይሰቲ ወይነ ውእቱ ዘበፅዐ ።
ወዝንቱ ሕጉ ለዘበፅዐ እምከመ በፅዐ ዘያመጽእ ለእግ ፳፩
ዚአብሔር ቍርባኖ በእንተ ብፅዐቲሁ ዘረከበ ውስተ እዴ
ሁ በአምጣነ ይትከሀሎ ይግበር ለብፅዓቲሁ ዘበፅዐ በሕገ
አንጽሖ ።
ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤ ንግሮሙ ለአ ፳፪
ሮን ወለደቂቁ ወበሎሙ ፣ ከመዝ ትባርክዎሙ ለደቂቀ
እስራኤል ።
ወትብልዎሙ ለይባርከ እግዚአብሔር ወለይዕቀብከ ። ፳፫
ወለያስተርኢ እግዚአብሔር ገጾ ላዕሌከ ወይምሐርከ። ፳፬
ወለይሚም እግዚአብሔር ገጾ ኀቤከ ወየሀብከ ሰላመ ። ፳፭

ወይሰመይ ስምየ በላዕለ ደቂቀ እስራኤል ወአነ ዘእባ ፳፯
ርከሙ ።

ምዕራፍ ፯።

ወኮነ በዕለተ እንተ ፈጸመ ሙሴ ተኪሎታ ለደብተራ ፩
ወቀብዓ ወቀደሳ ወለኵሉ ንዋያ ወለምሥዋዕኒ ወለኵሉ
ንዋዩ ወቀብዖሙ ወቀደሶሙ ።
አምጽኡ መላእክተ እስራኤል ዐሠርቱ ወክልኤቱ ፪
መላእክት ዘዘአብያተ አበዊሆሙ እሉ ውእቶሙ መላእ
ክተ ነገዶሙ እለ ተሠይሙ ዲበ ምስፍናሆሙ ።
ወአምጽኡ ቍርባኖሙ ቅድመ እግዚአብሔር ስድስተ ፫
ሠረገላተ ሠናያነ፡ዐሠርተ ወክልኤተ አልሕምተ ለለአሐዱ
ሠረገላ ዘበክልኤቱ አልሕምት ፣ በበአሐዱ ሠረገላ እም
ክልኤቱ መላእክት ፤ ወሦረ እምኅበ አሐዱ አሐዱ ፣ ወአ
ምጽኡ ቅድመ ኆኅተ ደብተራ ።
ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ንሣእ እምኔ ፬
ሆሙ ወይኩን ዘይትቀነይ ለምግባረ ደብተራ ዘመር
ጡል ፣ ወሀበሙ ለሌዋውያን ለለአሐዱ እምኔሆሙ
በከመ ምግባሮሙ ።
ወነሥአሙ ሙሴ ለውእቶሙ አልሕምት ወለሠረገላት ፮
ወወሀበሙ ለሌዋውያን ።
ክልኤተ ሠረገላተ ወአርባዕተ አልሕምተ ወሀበሙ ፯
ለደቂቀ ጌድሶን በአምጣነ ግብሮሙ ።
ወአርባዕተ ሠረገላተ ወሰመንተ አልሕምተ ወሀበሙ ፰
ለደቂቀ ሜራሪ በአምጣነ ምግባሮሙ ወላዕለ ይታምር
ወልደ አሮን ካህን እሙንቱ ።
ወለደቂቀ፡ቀዓትሰ ኢወሀበሙ እስመ ግብረ ቅድሳት ፱
ሕቢቶሙ ወበመትከፍቶሙ ይፀውርዎ ።
ወአምጽኡ መላእክት ለመድቅሐ ምሥዋዕ በዕለት ፲

ተራ አሪት ደጃፍ ይላጨው ጠጕሩንም መሥዋዕተ ኃጢ
አቱ ካጤሰበት እሳት ውስጥ ይጣለው ።
ካህኑም ከሙክቱ ወርቹን በቁርበቱ ጠቅሎ ይውሰድ
አንዲት ያልበከች ድፎና በመሶብ ያለች የቂጣ ዳቦ ራሱን
ከተላጨ በኋላ እጁን በተሳለው ሰው እጆች ላይ ያኑር ።
ካህኑ ቍርባኑን በእግዚአብሔር ፊት ያቅርበው የመ
ባው ወርችና የቍርባኑ ፍሪምባም ለካህኑ የተለየ ይሁን
ከዚህ በኋላ ያ የተሳለው ሰው ወይን ይጠጣ ።
ስለት ለተሳለው ሰው ሕጉ ይህ ነው ፣ ከተሳለም በኋላ
ስለተሳለው ስለት ቍርባን አድርጎ ለእግዚአብሔር የሚያ
መጣውን ለብፅዓቱ የሚበቃውን ያህል በእጁ ያገኘውን
የተቻለውን ያህል ያምጣ ። ዘሌዋ፡ ፳፮ ፳፯ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ የእስ
ራኤልን ልጆች ስትመርቁዋቸው እንዲህ ብላችሁ መርቁ
ዋቸው ብለህ ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው ።
እግዚአብሔር ይባርክህ (ያክብርህ) ይጠብቅህ ።
እግዚአብሔር ፊቱን ይግለጥልህ ይቅርም ይበልህ ።
እግዚአብሔር ገጸ ረድኤቱን ያሳድርብህ ሰላምንም
(ደስታን) ይስጥህ ። መዝ፡ ፴፩ ፲፮ ፡ ፳ ፯ ።
ስሜም በእስራኤል ልጆች ይጠራ የማከብራቸው እኔ
ነኝ (አከብራቸውም አለሁ) አለ ብለህ ንገራቸው አለው ።

ምዕራፍ ፯ ።

ሙሴን ድንኳኑን ተክሎ በፈጸመበት ቀን ቀብቶም
ባከበራት ዕቃዋንም መሠውያውንም ዕቃውንም ሁሉ በቀ
ባበት እነዚህን ሁሉ ቀብቶ ባከበረባቸው ቀን እንዲህ ሆነ።
ዐሥራ ሁለት የእስራኤል አለቆች በየአባቶቻቸው ወገ
ኖች ቍርባናቸውን አመጡ ፣ በየሹመታቸው የተሾሙ
የነገዶቻቸውም አለቆች እነዚህ ናቸው ።
ቍርባናቸውን ያማሩ ስድስት ሠረገላዎች ፣ አሥራ ሁ
ለት ላሞች በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ ፣ ለያንዳንዱም
ሠረገላ ሁለት ሁለት ላሞች ፣ ለያንዳንዱም ሠረገላ ሁለት
ሁለት አለቆችን አንዱንም አንዱንም በሬ ከያንዳንዱ የነ
ገድ አለቆች በደብተራ አሪት ደጃፍ ፊት አመጡ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ ደብ
ተራ አሪትን የሚያገለግል ይሆን ዘንድ ከነርሱ ተቀብለህ
ለሌዋውያን ለያንዳንዳቸው እንደ አገልግሎታቸው መጠን
ስጣቸው አለው ። ኢሳ፡ ፷፮ ፳ ።
ሙሴም እነዚያን ዐሥራ ሁለት ላሞችና ስድስቱን ሠረ
ገሎች ተቀብሎ ለሌዊ ልጆች ሰጣቸው ።
ሁለቱን ሠረገሎችና አራቱን ላሞች ለጌድሶን ልጆች
እንደየ ድካማቸው መጠን ሰጣቸው ።
አራቱን ሠረገሎችና ስምንቱን ላሞች ለሜራሪ ልጆ
ች እንደየ አገልግሎታቸው መጠን ሰጣቸው ፣ እነሱም በአ
ሮን ካህን ልጅ በይታምር ሹመት ያሉ ናቸው ።
ለቀዓት ልጆች ግን ሸክማቸው ንዋየ ቅድሳት ነውና
አልሰጣቸውም ፤ በጫንቃቸው ይሸከሙት ነበር ።
አለቆቹም በቀባበት ቀን መሠውያውን ለማደስ (ለማስ

እንተ ባቲ ቀብዐ፣ ወአምጽኡ መላእክት ቍርባኖሙ ቅድመ ምሥዋዕ።

፲ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ አሐዱ አሐዱ መልአክ ለለዕለቱ ያብእ ቍርባኖ ለለአሐዱ መልአክ በበ ዕለቶሙ ለመድቅሐ ምሥዋዕ።

፲፩ ወዘያበውእ በቀዳሚት ዕለት ቍርባኖ ነአሶን ወልደ አሚናዳብ መልአኮሙ ለነገደ ይሁዳ።

፲፪ ወአብአ ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር አሐዱ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል፣ ወአሐደ ፍያለ ዘብሩር ዘሰብዓ በሰቅሎን ውእቱ በሰቅል ቅዱስ፣ ወክልኤሆሙ ምሉአነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት።

፲፫ ወጻሕለ አሐደ ዘዐሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ።

፲፬ ወላሕመ አሐደ እምአልሕምት ወበግዐ አሐደ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት።

፲፭ ወሐርጌ እምአጣሊ አሐደ በእንተ ኃጢአት።

፲፮ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤ እጕልተ ወኀምስተ አባግዐ ወኀምስተ አጣሌ ወኀምስተ አባግዐ እንስተ ዘዓመት፣ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለነአሶን ወልደ አሚናዳብ።

፲፯ ወበሳኒታ ዕለት አብአ ናትናኤል ወልደ ሰገር መልአኮሙ ለነገደ ይሳኮር ቍርባኖ፣ መጽብሐ ዘብሩር አሐዱ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል።

፲፰ ወፍያለ ዘብሩር አሐዱ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ፣ ወክልኤሆሙ ምሉአነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት።

፲፱ ወጻሕለ አሐደ ዘዐሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ።

፳ ወላሕመ አሐደ፣ ወበግዐ አሐደ ዘዓመት፣ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት።

፳፩ ወሐርጌ እምአጣሊ አሐደ በእንተ ኃጢአት።

፳፪ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤ እጕልተ፣ ወሐምስተ አባግዐ፣ ወሐምስተ አጣሌ፣ ወሐምስተ አባግዐ እንስተ፣ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለናትናኤል ወልደ ሰገር።

፳፫ ወበሣልስት ዕለት አብአ መልአኮሙ ለደቂቀ ዛብሎን ኤልያብ ወልደ ኬሎን ቍርባኖ፣ መጽብሐ አሐደ ዘብሩር ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል፣ ወፍያለ አሐደ ዘብሩር ሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ፣ ወክልኤሆሙ ምሉአነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት።

፳፬ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ።

፳፭ ወላሕመ አሐደ፣ ወበግዐ አሐደ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት።

መረቅ) ቍርባኑን አመጡ፣ አለቆችም ቍርባናቸውን በምሥዋው ፊት አቀረቡ። ዘፀ፡ ፵፪ ፲-፲፮።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ አንዱም አንዱም አለቃ በየቀኑ ቍርባኑን ያቅርብ፣ እያንዳንዱም አለቃ በየቀናቸው ለምሥዋው መቀደሻ (ማደሻ ማስመረቂያ) ዕለት ዕለት መባቸውን ያቅርቡ።

በመጀመሪያው ቀን ቍርባኑን የሚያገባ የይሁዳ ነገድ አለቃ የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው። ፩ ፯።

ያቀረበውም ቍርባኑ በቤተ መቅደሱ ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚሆን አንድ የብር ወጭት ነው፣ ሚዛኑም ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ጣሳ ነው፡ ሁለቱም ለሚቃጠል መሥዋዕት በዘይት የተለወሰ ሥንዴን የተሞሉ ናቸው።

ዋጋው አሥር ሰቅል የሆነ ዕጣን የተሞላ አንድ የወርቅ ጭልፋ ነው። ዘፀ፡ ፴ ፴፬፣ ዘሌዋ፡ ፲፮ ፲፪።

መሥዋዕት ሊሆን ከላሞች አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት አገባ።

ስለ ኃጢአት የሚሠዋም ከፍየሎች አንድ ሙክት አገባ። ዘሌዋ፡ ፬ ፳፬።

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት ፍየሎች፣ አንዳንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎችን አገባ፣ የአሚናዳብ ልጅ የነአሶን ቍርባኑ ይህ ነው። ዘሌዋ፡ ፩ ፫።

በሁለተኛውም ቀን የነገደ ይሳኮር አለቃ የሰገር ልጅ ቍርባኑን አገባ፣ (ያገባው ቍርባን) በቤተ መቅደስ ሚዛን መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ጣሳ ነው።

ሚዛኑ በቤተ መቅደሱ ሚዛን ሰባ ሰቅል አንድ የብር ድስት አገባ፣ እንዲሁም ሁለቱ መሥዋዕት ሊሆን በዘይት የታሸ የሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው።

ወርቁ አሥር ወቄት የሆነ ዕጣንም የተሞላ አንድ ትንሽ የወርቅ ጭልፋን አገባ። ዘፍ፡ ፰ ፳፣ ዘሌዋ፡ ፮ ፱።

ለሚጤሰውም መሥዋዕተ አሥምሮ ከላሞች ወገን አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት አገባ። መዝ፡ ፳ ፫፣ ሕዝ፡ ፵፩ ፵፮።

ስለ ኃጢአትም የሚሠዋ ከፍየሎች አንድ ሙክት።

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት ፍየሎች አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት ፍየሎችን አቀረበ፣ የሰገር ልጅ የናትናኤል ቍርባኑ ይህ ነበር። ዘሌዋ፡ ፯ ፲፫።

በሦስተኛውም ቀን የዛብሎን ልጆች አለቃ የኬሎን ልጅ ኤልያብ መባውን አገባ፣ በሚዛን መቶ ሠላሳ ወቄት የሆነ አንድ የብር ወጭት፣ በቤተ መቅደሱ ሚዛን ሰባ ሰቅሎን (ወቄት) የሚሆን አንድ የብር ጣሳ፣ ሁለቱም ለእኽል ቍርባን በዘይት የተለወሰ የንጹሕ ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው።

ወርቁ አሥር ወቄት የሆነ ዕጣን የተሞላ አንድ የወርቅ ጻሕል (ወጭት)። ዮሐ፡ ፩ ፳፱፣ ግ፡ ሐ፡ ፰ ፴፪።

ለሚቃጠልም መሥዋዕት አንድ ወይፈን፣ አንድ በግ አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት። ኢሳ፡ ፶፫ ፯።

፳፮ ወሐርጌ እምአጣሊ አሐደ በእንተ ኃጢአት ።
፳፯ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ፣ ወኃምስተ አባግዐ፣ ወሐምስተ አጣሌ፣ ወኃምስተ አባግዐ አንስተ፣ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለኤልያብ ወልደ ኬሎን ።

፳፰ ወበራብዕት ዕለት አብአ ኤሊሱር ወልደ ሴድዩር፣ መልአክሙ ለደቂቀ ሮቤል ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል፣ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ።
፳፱ ወክልኤሆሙ ምሉአን ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።
፴ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ፣ ወምሉእ ዕጣነ፣ ወላሕመ አሐደ፣ ወበግዐ አሐደ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።
፴፩ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።
፴፪ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ፣ ወሐምስተ አባግዐ፣ ወሐምስተ አጣሌ፣ ወሐምስተ አባግዐ አንስተ፣ ወዝ ውእቱ ቍርባኑ ለኤሊሱር ወልደ ሴድዩር ።

፴፫ ወበኃምስ ዕለት አብአ ሰላምያል ወልደ ሲሩሳዴ መልአክሙ ለደቂቀ ስምዖን ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል፣ ወፍያለ አሐደ ዘብሩር ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅልዘ ቅዱስ ።
፴፬ ወክልኤሆሙ ምሉአን ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።
፴፭ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ፣ ወምሉእ ዕጣነ ።

፴፮ ወላሕመ አሐደ፣ ወበግዐ አሐደ፣ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።
፴፯ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፴፰ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ ወኀምስተ አባግዐ፣ ወሐምስተ አጣሌ፣ ወኀምስተ አባግዐ አንስተ፣ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለሰላምያል ወልደ ሲሩሳዴ ።

፴፱ ወበሳድስት ዕለት አብአ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል መልአክሙ ለደቂቀ ጋድ ቍርባኖ፣ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል፣ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅል ዘቅዱስ ።

፵ ወክልኤሆሙ ምሉአን ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።
፵፩ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ ።

፵፪ ወላሕመ አሐደ፣ ወበግዐ አሐደ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።
፵፫ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

ስለ ኃጢአት የሚሠዋም ከፍየሎች አንድ ሙክት ።
ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት እንስት ፍየሎች፣ አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎችን አቀረበ፣ የኬሎን ልጅ የኤልያብ ቍርባኑ ይህ ነው ።

በአራተኛውም ቀን የሮቤል ልጆች አለቃ የሴድዩር ልጅ ኤሊሱር መባውን አገባ፣ (ያገባውም) ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደሱ አዋቂ ሚዛን ዋጋው ሰባሰቅል የሚሆን የብር ጣሳ ነው ።
ሁለቱም ለእኽል ቍርባን በዘይት የታሸ ልጦ ጉርዶ የወጣለት የሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።
ዕጣን የተሞላ ዋጋው አሥር ወቄት የሆነ አንድ የወርቅ ጭልፋ (ወጭት) መሥዋዕት ሊሆን አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ ዓመት የሆነው አንድ ንጹሕ የበግ ጠቦት ።
ስለ ኃጢአትም ከፍየሎች ወገን አንድ ሙክት ።
ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች፣ አምስት አውራ በጎች፣ አምስት አውራ ፍየሎች፣ አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎች አቀረበ፣ የሴድዩር ልጅ የኤሊሱር መባው ይህ ነበር ።

በአምስተኛውም ቀን የስምዖን ልጆች አለቃ የሲሩሳዴ ልጅ ሰላምያል መባውን አገባ፣ (ያገባው) ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደሱ ሚዛን አዋቂ ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ድስት ነው ።
ሁለቱም ለእኽል ቍርባን በዘይት የተለወሰ የሙልክም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።
ወርቁ ዐሥር ወቄት የሆነ ዕጣን የተሞላበት አንድ ታናሽ ወጭት ።
ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ ወይፈን፣ አንድ በግ መሥዋዕትም ሊሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ።
ስለ ኃጢአት የሚሠዋም ከፍየሎች ወገን አንድ አውራ ፍየል (ሙክት) ።
ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት ፍየሎች፣ አንዳንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎች ናቸው፣ የሴሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ቍርባኑ ይህ ነበር ።

በስድስተኛውም ቀን የጋድ ልጆች አለቃ የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ቍርባኑን አገባ፣ መባውም በሚዛን መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት ነው፣ ሚዛኑ በቤተ መቅደሱ ሚዛን ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ጣሳ ነው ።
ሁለቱም መሥዋዕት ሊሆን በዘይት የታሸ የሙልክም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።
ዕጣን የተሞላበት ተመኑ አሥር ወቄት የሆነ አንድ የወርቅ ወጭት ።
አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ መሥዋዕትም ሊሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ነው ።
ለመሥዋዕተ ኃጢአትም ከፍየሎች ወገን አንድ አውራ ሙክት ። መዝ፡ ፶፰ ፶፩ ፲፯፣ ኢሳ፡ ፩ ፲፩

፵፬ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ ፡ ወኀምስተ አባግዐ ፣ ወኀምስተ አጣሌ ፣ ወኀምስተ አባግዐ አንስተ ፣ ወዝውእቱ ቍርባኑ ለኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል ።

፵፭ <u>ወበሳብዕት ዕለት</u> አብአ ኤልሳማ ወልደ ኤምዩድ ፣ መልአከሙ ለደቂቀ ኤፍሬም ቍርባኖ ፡ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ፡ ወሠላሳ በሰቅል ።

፵፮ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ፣ ወክልኤሆሙ ምሉአነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።

፵፯ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ ።

፵፰ ወላሕመ አሐደ ፣ ወበግዐ አሐደ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።

፵፱ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፶ ወለመሥዋዕተ መድኀኒት ክልኤተ እጐልተ ፣ ወኀምስተ አባግዐ ፣ ወኀምስተ አጣሌ ፣ ወኀምስተ አባግዐ አንስተ ፣ ዝ ውእቱ ቍርባኑ ለኤልሳማ ወልደ ኤምዩድ ።

፶፩ <u>ወበሰምንት ዕለት</u> አብአ ገማልያል ወልደ ፈዳሱር መልአከሙ ለደቂቀ ምናሴ ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ፣ ወፍያለ አሐደ ዘብሩር ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ።

፶፪ ወክልኤሆሙ ምሉአነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።

፶፫ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ ።

፶፬ ወላሕመ አሐደ ፣ ወበግዐ አሐደ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።

፶፭ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፶፮ ወለመሥዋዕተ መድኀኒት ክልኤተ እጐልተ ፣ ወኀምስተ አባግዐ ፡ ወኀምስተ አጣሌ ፣ ወኀምስተ አባግዐ አንስተ ዘዘዓመት ፡ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለገማልያል ወልደ ፈዳሱር ።

፶፯ <u>ወበታስዕ ዕለት</u> አብአ አቢዳን ወልደ ጋድዮን መልአከሙ ለደቂቀ ብንያም ቍርባኖ ፡ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእተ ወሠላሳ በሰቅል ፡ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ።

፶፰ ወክልኤሆሙ ምሉአነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።

፶፱ ወጻሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣነ ።

፷ ወላሕመ አሐደ ፡ ወበግዐ አሐደ ፣ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።

፷፩ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፷፪ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ ፣ ወኀምስተ አባግዐ ፡ ወኀምስተ አጣሌ ፣ ወኀምስተ አባግዐ

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች ፣ አምስት ተባት በጎች ፡ አምስት አውራ ፍየሎች ፣ አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎች ናቸው ፣ የራጉኤል ልጅ የኤልሳፍ መባው ይህ ነው ።

<u>በሰባተኛውም ቀን</u> የኤፍሬም ልጆች አለቃ የኤምዩድ ልጅ ኤልሳማ መባውን አገባ ፣ በሚዛን መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት ።

በቤተ መቅደሱ ሚዛን ግምገማው ሰባ ወቄት የሆነ አንድ የብር ጣሳ ነው ፣ ሁለቱም መሥዋዕት ሊሆን በዘይት የታሸ የመልከም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።

ዕጣን የተሞላ ተመኑ አሥር ወቄት የሆነ አንድ የወርቅ (ጻሕል) ወጭት ነው ። ዘፀ፡ ፴፫ ፲ ፣ መዝ፡ ፷፯ ።

ለመሥዋዕትም አንድ ወይፈን ፣ አንድ አውራ በግ ፣ ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ነው ። ሚክ፡ ፮ ፮ ።

ስለ መሥዋዕተ ኃጢአትም ከፍየሎች ወገን አንድ ሙክት ።

ስለ መሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች ፡ አምስት ተባት በጎች ፡ አምስት አውራ ፍየሎች ፡ አንዳንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎች ናቸው ፣ የኤምዩድ ልጅ የኤልሳማ ቍርባኑ ይህ ነበር ።

<u>በስምንተኛው ቀን</u> የምናሴ ልጆች አለቃ የፈዳሱር ልጅ ገማልያል ቍርባኑን አቀረበ ፣ ቍርባኑም በቤተ መቅደሱ ሚዛን መቶ ሠላሳ ወቄት የሆነ አንድ የብር ወጭት በቅዱስ ሚዛን ሰባ ሰቅል የሆነ አንድ የብር ጣሳ ነው ።

ሁለቱም ለሚቃጠል መሥዋዕት ሊሆን በዘይት የታሸ የመልከም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።

ዕጣን የተሞላ ተመኑ አሥር ወቄት የሆነ አንድ የወርቅ ወጭት ።

አንድ ወይፈን ፣ አንድ በግ መሥዋዕት ሊሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ።

ስለ ኃጢአት የሚሠዋ ከፍየሎች ወገን አንድ ሙክት።

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች አምስት ተባት በጎች ፣ አምስት አውራ ፍየሎች አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎች ናቸው ፣ የፈዳሱር ልጅ የገማልያል ቍርባኑ ይህ ነበረ ። ዘሌ፡ ፫ ፩ ።

<u>በዘጠነኛው ቀን</u> የብንያም ልጆች አለቃ የጋድዮን ልጅ አቢዳን መባውን አገባ ፣ (መባውም) ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሆነ አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደሱ ሚዛን ዋጋው ሰባ ወቄት አንድ የብር ጣሳ ነው ።

ሁለቱም ለእኽሉ ቍርባን በዘይት የታሸ የመልከም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።

ዕጣን የተመላበት ሚዛኑ አሥር ወቄት የሆነ አንድ ጭልፋ ነው ። ራእ፡ ፭ ፰ ፣ ፰ ፩ ።

አንድ ወይፈን አንድ በግ ፣ መሥዋዕትም ሊሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ። ኢሳ፡ ፶፫ ፩ ።

ስለ መሥዋዕተ ኃጢአትም ከፍየሎች ወገን አንድ ሙክት ። ፪ ሕፀ፡ ፭ ፳፩ ።

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች አምስት ተባት በጎች ፣ አምስት ፍየሎች ፣ አምስት እንስት በጎችን

አንስተ ዘዘዓመት ፡ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለአቢዳን ወልደ ጋድዮን ።

፷፫ ወበአሥር ዕለት አብአ አክያዜር ወልደ አሚሳዴ መልአከሙ ለደቂቀ ዳን ፡ ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር ፡ አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ፡ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን ፡ በሰቅል ዘቅዱስ ።

፷፬ ወክልኤሆሙ ምሉአን ሥንዳሴ ፡ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።

፷፭ ወጸሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣን ።

፷፮ ወላሕመ አሐደ ፡ ወበግዐ አሐደ ፡ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።

፷፯ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፷፰ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤ እጐልተ ፡ ወኀምስተ አባግዐ ፡ ወኀምስተ አጣሌ ፡ ወኀምስተ አባግዐ አንስተ ዘዘዓመት ፡ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለአክያዜር ወልደ አሚሳዴ።

፷፱ ወአመ ዓሥሩ ወአሚሩ ዕለት አብአ ፋጌኤል ወልደ ኤክራን መልአከሙ ለደቂቀ አሴር ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ፡ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ።

፸ ወክልኤሆሙ ምሉአን ሥንዳሴ ፡ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።

፸፩ ወጸሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣን ።

፸፪ ወላሕመ አሐደ ፡ ወበግዐ አሐደ ፡ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።

፸፫ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፸፬ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ ፡ ወኀምስተ አባግዐ ፡ ወኀምስተ አጣሌ ፡ ወሐምስተ አባግዐ አንስተ ዘዘዓመት ፡ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለፋጌሔል ወልደ ኤክራን ።

፸፭ ወአመ ዓሡሩ ወሰኑዩ ዕለት ፡ አብአ አኪሬ ወልደ ኤናን መልአከሙ ለደቂቀ ንፍታሌም ቍርባኖ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ፡ ወፍያለ ዘብሩር አሐደ አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ።

፸፮ ወክልኤሆሙ ምሉአን ሥንዳሴ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ።

፸፯ ወጸሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቁ ወምሉእ ዕጣን ።

፸፰ ወላሕመ አሐደ ፡ ወበግዐ አሐደ ፡ ወማሕስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ።

፸፱ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

፹ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ እጐልተ ፡ ወኀምስተ አባግዐ ፡ ወኀምስተ አባግዐ አንስተ ዘዘዓመት ፡ ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለአኪሬ ወልደ ኤናን ።

አገባ ፡ የጋድዮን ልጅ የአቢዳን መባው ይህ ነበር ።

በአሥረኛው ቀን የዳን ልጆች አለቃ የአሚሳዴ ልጅ አክያዜር ቍርባኑን አገባ፡ መባውም ዋጋው በሚዛን መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደሱ ሚዛን ዋጋው ሰባ ወቄት የሆነ አንድ የብር ጣሳ ነው ።

ሁለቱም ለእኽል ቍርባን በዘይት የታሸ የመልካም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ። ዘፍ፡ ፲፫ ፲፫ ።

ዕጣን የተሞላ ዋጋው አሥር ወቄት የሆነ አንድ የብር ድስት ። መዝ፡ ፻፵፩ ፪፡ ኢሳ፡ ፷፮ ፫ ።

አንድ ወይፈን ፡ አንድ በግ መሥዋዕትም ሊሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ።

ስለ ኃጢአትም የሚሠዋ ከፍየሎች ወገን አንድ ሙክት ነው ።

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች አምስት አውራ በጎች ፡ አምስት አውራ ፍየሎች አንዳንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎችን አገባ ፡ የአሚሳዴ ልጅ አክያዜር መባው ይህ ነበር ።

በአሥራ አንደኛውም ቀን የአሴር ልጆች አለቃ የኤክራን ልጅ ፋጌሄል ቍርባኑን አቀረበ ፡ መባውም ዋጋው መቶ ሠላሳ ወቄት የሆነ አንድ የብር ወጭት ፡ በቤተ መቅደሱ ሚዛን ሰባ ወቄት የሆነ አንድ የብር ጣሳ ።

ሁለቱም ለእኽል ቍርባን በዘይት የተለወሰ ልጦ ጉርዶ የወጣለት የሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ።

ዕጣን የተሞላ ሚዛኑ አሥር ወቄት የሆነ አንድ የብር ጻሕል (ድስት) ነው ። ሚልክ፡ ፩ ፲፩፡ ሉቃ፡ ፩ ፲፩ ።

ለሚቃጠልም መሥዋዕት ከላሞች ወገን አንድ ወይፈን አንድ በግ፡ ዓሙት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ።

ለመሥዋዕተ ኃጢአትም ከፍየሎች ወገን አንድ አውራ ፍየል ነው ።

ለመሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች ፡ አምስት አውራ በጎች ፡ አምስት አውራ ፍየሎች ፡ አንዳንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎችን አገባ ፡ የኤክራን ልጅ የፋጌሔል ቍርባኑ ይህ ነው ።

በአሥራ ሁለተኛውም ቀን የንፍታሌም ልጆች አለቃ የኤናን ልጅ አኪሬ ቍርባኑን አገባ፡ መባውም ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሆነ አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደሱ ሚዛን ዋጋው ሰባ ወቄት የሆነ አንድ የብር ጣሳ ነው።

ሁለቱም ለእኽል ቍርባን በዘይት የታሸ የመልካም ሥንዴ ዱቄት የተሞሉ ናቸው ። ማቴ፡ ፲፬ ፲፰ ።

ዕጣን የተሞላ ዋጋው አሥር ወቄት የሆነ አንድ የብር ጭልፋ (ቃናሽ ወጭት)። ዘካ፡ ፲፬ ፳ ።

አንድ ወይፈን ፡ አንድ በግ ፡ መሥዋዕትም ሊሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት ።

ስለ ኃጢአት የሚሠዋ ከፍየሎች ወገን አንድ ሙክት።

ስለ መሥዋዕተ መድኃኒትም ሁለት ጊደሮች ፡ አምስት ተባት በጎች ፡ አምስት ፍየሎች ፡ አንዳንድ ዓመት የሆናቸው አምስት እንስት በጎችን አገባ ፡ የኤናን ልጅ የአኪሬ ቍርባኑ (መባው) ይህ ነው ።

፹፬ ወከመዝ ውእቱ መድቅሐ ምሥዋዕ ዘእምኀበ መላእክቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፡ ዘአመ ቀብዓ ለደብተራ መርጡል ፡ መጽብሕ ዘብሩር ዐሠርቱ ወክልኤቱ ፡ ወፍያላት ዘብሩር ዓሠርቱ ወክልኤቱ ፡ ወአጽሕልት ዘወርቅ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ።

ደብተራ ኦሪትን በቀባት ጊዜ ከእስራኤል ልጆች አለቆች የቀረበው የመሠውያው መቀደሻ (ማደሻ ማክበርያ) እንደዚህ ነበር ፡ አሥራ ሁለት የብር ወጭቶች ፡ አሥራ ሁለት የብር ጣሳዎች አሥራ ሁለት የወርቅ ጭልፋዎች ናቸው ። ዘኍ፡ ፯ ፲፩ ።

፹፭ ወለለአሐዱ መጽብሕ ምእት ወሠላሳ በሰቅሎን ፡ ወለለ አሐዱ ፍያል ሰብዓ በሰቅሎን ፡ ወኵሉ ብሩሮሙ ለውእቶሙ ንዋያት ዕሥራ ምእት ወአርባዕቱ ምእት በሰቅሎን ዘቅዱስ ።

እያንዳንዱም የብር ወጭት መቶ ሠላሳ ወቄት እያንዳንዱም ጣሳ ሰባ ሰቅል ነው ፡ የነዚህም ዕቃዎች ብር ሁሉ በቅዱስ ሰቅል ሚዛን ሁለት ሺሕ አራት መቶ ወቄት ነው ።

፹፮ ወዐሠርቱ ወክልኤቱ አጽሕልት ዘወርቅ ፡ ወኵሉ ወርቆሙ ለውእቶሙ አጽሕልት ምእት ወዕሥራ ።

አሥራ ሁለቱም ጭልፋዎች የወርቅ ናቸው ፡ የጭልፋዎቹም ወርቅ ሁሉ መቶ ሃያ ወቄት ነው ።

፹፯ ወኵሉ አልሕምት ዘመሥዋዕት ዐሠርቱ ወክልኤቱ ፡ ወአባግዕ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ፡ ወመሐስዐ አባግዕ ዐሠርቱ ወክልኤቱ ዘዘመዓት ለመሥዋዕትኒ ወለሞጻሕትኒ ።

ከእኽል ቍርባንና ከወይናቸውም ጋር ለሚቃጠል መሥዋዕት የቀረበ ሁሉ አሥራ ሁለት ወይፈኖች ፡ አሥራ ሁለት አውራ በጎች ፡ አንድ አንድ ዓመት የሆናቸውም የበግ ጠቦቶች አሥራ ሁለት ናቸው ።

፹፰ ወዓሠርቱ ወክልኤቱ ሐርጌያት እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ።

ለመሥዋዕተ ኃጢአትም ከፍየሎች ወገን የሚሠዉት ሙክቶች አሥራ ሁለት ናቸው ።

፹፱ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ዕሥራ ወአርባዕቱ እጐልት ፡ ወአባግዕኒ ስሳ፡ ወአጣሊኒ ስሳ ፡ ወአባግዕ አንስት ዘዘ ዓመት ንጹሐት ስሳ ፡ ከመዝ ውእቱ መድቅሐ ምሥዋዕ እምድኅረ ቀብዓ ።

ስለ መሥዋዕተ መድኃኒትም የሚሠዉ ጊደሮች ሃያ አራት ተባት በጎች ስሳ ፡ ፍየሎችም ስሳ፡ አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው ንጹሐን የሆኑ እንስት በጎችም ስሳ ፡ ናቸው ፡ ድንኳኑን ከቀባው በኋላ የቀረበው የምሥዋዑ መቀደሻ (ማክበሪያ) እንደዚህ ነበር ።

፺ ወሶበ ይበውእ ሙሴ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ይትናገሮ ይሰምዕ ቃለ እግዚአብሔር ፡ እንዘ ይትናገሮ እመልዕልተ ምስሐል ዘዲበ ታቦት ዘመርጡል እማእከለ ክልኤቱ ኪሩባት ወይትናገር ምስሌሁ ።

ሙሴም ሊነጋገረው ወደ ደብተራ ኦሪት በገባ ጊዜ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ባለ በታቦቱ መግጠሚያ ላይ ሁኖ ሲናገረው የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማ ነበር ፡ ከርሱም ጋር ይናገር ነበር ። ዘፍ፡ ፫ ፳፬ ፡ መዝ፡ ፲፰ ፲ ።

## ምዕራፍ ፰ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮ ለአሮን ወበሎ እምነ መንገለ ገበሃ ለገጻ አንብር መኃትዊሃ ለመራናት ወአኅትዎን ለሰቡዑ መኃትዊሃ ።

እግዚአብሔር ሙሴን በደብተራ ኦሪት አጠገብ የመቅረዝ መብራቶቹን አኑር ፡ ሰባቱ አዕዑቶቹን ሁሉም አብራቸው ብለህ ለአሮን ንገረው ብሎ ነገረው ።

፪ ወገብረ ከማሁ አሮን ፡ እምአሐዱ ገበሃ ዘመንገለ ገጻ ለመራናት አኅተወ መኅትዊሃ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

አሮንም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እንዲሁ አደረገ ፡ በድንኳኑ መግቢያ አጠገብ በኩች በመቅረዝ ጐን በአንድ ወገን መብራቶቹን አበራ ። ዘፀ፡ ፳፭ ፴፯ ።

፫ ወከመዝ ውእቱ ግብረታ ለመራት ፡ ወአዕጹቂሃኒ ጽኑዓን ዘወርቅ ኵለንታሆሙ ወጽጌያቲሃኒ ጽኑዓን ኵለንታሆሙ በከመ አርአያ ዘአርአዮ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብራ ለመራናት ።

የመቅረዝም ሥራዋ እንዲህ ነው ፡ ሁለንትናቸው ወርቅ የሆነ አጽቆቹም ሥረ - ወጽ ናቸው ፡ አበቦቹም ሁለንትናቸው ሥረ - ወጽ ናቸው ፡ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳሳየው አምሳል መቅረዚንም እንደዚያው አድርጎ ሠራት።

፬ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንሥኣሙ ለሌዋውያን እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአንጽሖሙ ።

እግዚአብሔር የሌዊን ልጆች ከእስራኤል ልጆች ለይተህ አንጻቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው ።

፭ ወከመዝ ትገብር ሎሙ ከመ ታንጽሖሙ ፡ ትነዝሖሙ በማየ አንጽሖ ወይላጽዩ ኵሎ ሥጋሆሙ ወይሕጽቡ አልባሲሆሙ ወንጹሐነ ይከውኑ ።

ታነጻቸውም ዘንድ እንዲህ አድርግላቸው በሚያነጻ ውኃ እርጫቸው ሰውነታቸውንም ሁሉ ይላጩ ፡ ልብሶቻቸውን ይጠቡ የነጹም ይሁኑ ። ዘሌዋ፡ ፲፬ ፱ ።

፮ ወይንሥኡ አሐደ ላሕመ እምአልሕምት ወሎቱኒ መሥዋዕተ ሥንዳሴ ዘግቡር በቅብዕ ወካልአ ላሕመ ዘዓመት ይንሥኡ በእንተ ኃጢአት ።

ከላሞችም አንድ ወይፈን ያምጡ ፡ ለሱም በቅቤ የታሸ ሕዕበ ጉርዶ የወጣ የሥንዴን መሥዋዕት ያምጡ ፡ ስለ ኃጢአትም ዓመት የሆነው ሁለተኛ ላም ያምጡ ።

፯ ወታመጽኦሙ ለሌዋውያን ቅድመ ደብተራ ዘመርጡል ወታስተጋብእ ኵሎ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

ሌዋውያንንም ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ አምጣቸው የእስራኤልን ልጆች ሠራዊት ሁሉ ሰብስብ ።

፲ ወታቀርቦሙ ለሌዋውያን ቅድመ እግዚአብሔር ወይወድዩ እደዊሆሙ ደቂቀ እስራኤል ላዕለ ሌዋውያን ።

ሌዋውያንን በእግዚአብሔር ፊት አቅርባቸው የእስራኤልም ልጆች እጆቻቸውን በሌዋውያን ላይ ያኑሩ ።

፲፩ ወይፈልጦሙ አሮን ለሌዋውያን ቅድመ እግዚአብሔር እምደቂቀ እስራኤል ወይከውኑ ለግብረ እግዚአብሔር እለ ይገብሩ ።

አሮንም የሌዊን ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ከእስራኤል ልጆች ይለያቸው የእግዚአብሔርንም ሥራ የሚሠሩ ይሁኑ ። ፰ ፲፫ ፣ ፩ ጢሞ ፭ ፳፪ ።

፲፪ ወሌዋውያን ይወድዩ እደዊሆሙ ዲበ አርእስተ አልሕምት ወይገብሩ አሐደ በእንተ ኀጢአት ወአሐደ ለመሥዋዕተ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ በእንቲአሆሙ ።

ሌዋውያን እጆቻቸውን በላሞች ራስ ላይ ያኑሩ ፣ አንዱን ስለ ኃጢአት ፣ አንዱን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያድርጉ ፣ ለነሳቸውም ኃጢአታቸውን ያስተሠርይላቸዋል ።

፲፫ ወታቀውሞሙ ለሌዋውያን ቅድመ አሮን ወቅድመ ደቂቁ ወታገብአሙ ሀብቶ ለእግዚአብሔር ።

ሌዋውያንንም በአሮንና በልጆቹ ፊት አቁማቸው ፣ የእግዚአብሔር ስጦታም አድርገህ አግባቸው ።

፲፬ ወትፈልጦሙ ለሌዋውያን እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይከውኑኒ ሊተ ።

ሌዋውያንን ከእስራኤል ልጆች መከከል ለያቸው ፣ ለኔም አገልጋዮች ይሁኑኝ ። ፫ ፵፭ ፣ ፲፯ ፱ ።

፲፭ ወእምድኅረ ዝንቱ ይበውኡ ሌዋውያን ይግበሩ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ወታነጽሖሙ ወታገብአሙ ቅድሜየ እስመ ሀብተ ገብኡ ሊተ እሙንቱ እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

ከዚህ በኋላ የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ሌዋውያን ይግቡ ፣ እነዚህ ከእስራኤል ልጆች መከከል ተለይተው ለኔ ስጦታ ተሰጥተዋልና አንጽተህ ወደኔ አግባቸው ።

፲፮ ህየንተ ኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ ዘእምኵሉ በኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ነሣእክዎሙ ሊተ ።

ከእስራኤል ልጆች በኵር ሁሉ መጀመሪያ ስለ ሚወለደው ሁሉ ፈንታ ስጦታ ሁነው ለኔ ተሰጥተዉኝ ተቀብያቸዋለሁ ። ዘኍ፣ ፫ ፲፪ ።

፲፯ እስመ ሊተ ውእቱ ኵሉ በኵር ዘእምደቂቀ እስራኤል እምነ ሰብእ እስከ እንስሳሁ ፣ በዕለት እንተ ባቲ ቀተልክዎሙ ለኵሎሙ በኵር ዘውስተ ምድረ ግብጽ ወቀደስክዎሙ ሊተ ።

ከእስራኤል ልጆች የተወለዱት በኵር በኵሩ ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ የኔ ነውና ፣ በግብጽ አገር ያለውን በኵር ሁሉ በጠፋሁበት ቀን ለኔ ለይቻቸው አለሁና ። ዘፀ፣ ፲፫ ፪ ።

፲፰ ወነሣእክዎሙ ለሌዋውያን ህየንተ ኵሉ በኵር ዘእምደቂቀ እስራኤል ።

ከእስራኤል ልጆች በኵር ሁኖ ስለሚወለደው ሁሉ ፈንታ ሌዋውያንን ተቀብልኋቸው ።

፲፱ ወአግባእክዎሙ ለሌዋውያን ሀብተ ተውህቡ ለአሮን ወለደቂቁ እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ይግበሩ ግብሮሙ ለደቂቀ እስራኤል በውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

ሌዋውያንን ስጦታ አድርጌ አገባኋቸው ፣ ልዩ በሆነች ድንኳን ውስጥ ከእስራኤል ልጆች መከከል ተለይተው የእስራኤልን ልጆች ሥራ ይሠሩ ዘንድ ለአሮንና ለልጆቹ ተሰጡ ።

፳ ወያስተሠርዩ በእንቲአሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣ ወአልቦ እምውስተ ደቂቀ እስራኤል ዘይቀርብ ኀበ ቅድሳት ።

የእስራኤልንም ልጆች ኃጢአት ያስተሠርዩላቸዋል ፣ ከእስራኤልም ልጆች ወደ ቤተ መቅደስ የሚቀርብ አይኑር ፣ አለው ። ዘኍ፣ ፫ ፬ ፣ ፰ ፲፮ ።

፳፩ ወገብሩ ሙሴ ወአሮን ወኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ላዕለ ሌዋውያን በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ በእንተ ሌዋውያን ከማሁ ገብሩ ሎሙ ደቂቀ እስራኤል ።

ሙሴና አሮን የእስራኤልም ልጆች ሠራዊት ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ሌዋውያን ሙሴን እንዳዘዘው በሌዋውያን ላይ እንዲሁ አደረጉ ።

፳፪ ወአንጽሑ ርእሶሙ ሌዋውያን ወሐጸቡ አልባሲሆሙ ወአግብእዎሙ ኀበ አሮን ሀብተ ቅድመ እግዚአብሔር ወአስተሥረየ በእንቲአሆሙ አሮን ከመ ያንጽሖሙ ።

ሌዋውያንም ራሳቸውን ንጹሕ አደረጉ ፣ ልብሶቻቸውንም አጥበው በእግዚአብሔር ፊት ስጦታ አድርገው ወደ አሮን አገቧቸው ፣ አሮንም ያነጻቸው ዘንድ ኃጢአታቸውን አስተሠረየላቸው ። ዘኍ፣ ፰ ፯ ፣ ፲፬ ፲፫ ።

፳፫ ወእምድኅረ ዝንቱ ቦኡ ሌዋውያን ይግበሩ ግብሮሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ አሮን ወቅድመ ደቂቁ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ በእንተ ሌዋውያን ከማሁ ገብሩ ሎሙ ።

ከዚህ በኋላ የሌዊ ልጆች ሥራቸውን ይሠሩ ዘንድ በልጆቹና በአሮን ፊት ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ ፣ እግዚአብሔር ሙሴን ስለ ሌዊ ልጆች እንዳዘዘው እንዲሁ አደረጉላቸው ። ፩ ዜና መ፣ ፳፫ ፣ ፫ ፳፬ - ፳፯ ።

፳፬ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ዝንቱ ውእቱ ዘበእንተ ሌዋውያን ።

ስለ ሌዋውያን የሚሠራ ሥርዓት ይህ ነው ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ።

፳፭ ዘእምዕሥራ ወኀምስቱ ዓም ወላዕሉ ይበውኡ ይግበሩ ግብሮሙ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል እስከ ዘኀምሳ ዓም ።

ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ አምሳ ዓመት ድረስ ያሉት ሌዋውያን የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት ይግቡ ።

| | | |
|---|---|---|
| ዘእምድኅረ ሐምሳ ዓም ይሰዐር እምግብረ ደብተራ ፡ ወኢይትቀነይ እንከ ውእቱ ። | ፴፬ | ከአምሳ ዓመት በኋላ ግን ከሹመቱ (ከሥራው) ይሻር እንግዲህ እሱ አያገልግል ። ዘኍ፡ ፬ ፫ ። |
| ወይትለአክ እኁሁ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወይዕቀብ ሕቢቶሙ ፡ ወተቀንዮ በሕቱ ኢይትቀነይ ፡ ወከመዝ ትገብር ሎሙ ለሌዋውያን በበሕቢቶሙ ። | ፴፭ | ስለሱ ፈንታ በደብተራ ኦሪት ውስጥ ወንድሙ ያገልግል ሰሞናቸውንም ይጠብቅ ፡ ነገር ግን (እንደሹመቱ ወራት) ማገልገሉን ይተው ፡ ለሌዊ ልጆች በየሰሞናቸው እንዲህ አድርግላቸው አለው ። ዘኍ፡ ፩ ፶፫ ። |
| **ምዕራፍ ፱ ።** | | **ምዕራፍ ፱ ።** |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ በገዳም ዘሲና ፡ በካልእ ዓመት እምዘ ወፅኡ ደቂቀ እስራኤል እምድረ ግብጽ በቀዳሚ ወርኅ ። | ፩ | የእስራኤል ልጆች ከግብጽ አገር በወጡ በሁለተኛው ዓመት በመጀመሪያ ወር በሲና ምድረ በዳ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ። ፩ ፩ ። |
| ወይቤሎ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ይግበሩ ፋሲካ አመ ጊዜሁ ። | ፪ | በጊዜው ጊዜ የፋሲካን በዓል ያደርጉ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፭ ። |
| አመ ዐሡሩ ወረቡዑ ለሠርቀ ወርኅ ቀዳሚ ወፍና ሠርክ ትገብርዎ አመ ጊዜሁ በከመ ሕጉ ወበከመ ትእዛዙ ትገብሮ ። | ፫ | በመጀመሪያው ወር በሚያዝያ በባተ በአሥራ አራተኛው ቀን በሠርክ ጊዜ እንደ ትእዛዙና እንደ ሕጉ አድርገው አለው ። ዘፀ፡ ፲፪ ፮ ፡ ዘኍ፡ ፱ ፭ ። |
| ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ይግበሩ ፋሲካ። | ፬ | ሙሴም የፋሲካን በዓል ያደርጉ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው ። ዘኍ፡ ፲፰ ፳፰ ። |
| ወአኀዙ ይግበሩ እምዕለተ ዐሡሩ ወረቡዑ ለሠርቀ ወርኅ በገዳም ዘሲና በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ፡ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል ። | ፭ | ሚያዝያ በባተ ከአሥራ አራተኛው ቀን ጀምረው በሲና ምድረ በዳ በዓሉን ያደርጉ ጀመር የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እንደዚሁ አደረጉ ። |
| ወመጽኡ ሰብእ እለ በሙ ርኩስ ውስተ ነፍስቶሙ ፡ ወስእኑ ገቢረ ፋሲካ በይእቲ ዕለት ፡ ወመጽኡ ቅድሜሆሙ ለሙሴ ወለአሮን በይእቲ ዕለት ። | ፮ | በሰውነታቸው ርኩሰት ያለባቸው ሰዎች መጡ ፡ በዚያች ቀን የፋሲካን በዓል ከማድረግ ተከለከሉ በዚያችም ቀን ወደ አሮንና ወደ ሙሴ መጡ ። ዘኍ፡ ፭ ፪ ። |
| ወይቤልዎሙ ውእቶሙ እደው ፡ ንሕነሰ ሰብእ ንሕነ እለ ብነ ርኩስ ውስተ ነፍስትነ ፡ ወኢንትኀደግ እምአብኦ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል በበዘመኑ ። | ፯ | እነዚያ ሰዎች እኛ በሰውነታችን ርኩሰት ያለብን እንደናንተ ሰዎች ነን ከእስራኤል ልጆች መካከል ተለይተን በየዘመኑ የእግዚአብሔርን መሥዋዕት ከማቅረብ አንከልከልም አሉ ። |
| ወይቤሎሙ ሙሴ ቁሙኒ እስማዕ ምንተ ይኤዝዝ እግዚአብሔር በእንቲአክሙ ። | ፰ | ሙሴም እግዚአብሔር ስለናንተ ምን እንደሚያዝዝ እሰማ ዘንድ ቆዩኝ አላቸው ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ። | ፱ | እግዚአብሔርም ሙሴን ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ብሎ ነገረው ። ፳፯ ፭ ። |
| ብእሲ ብእሲ ለእመቦ ዘወዕአ ርኩስ ውስተ ነፍስቱ ወለእመኒ ርኁቀ ብሔር ሀለወ ፡ ወለእመኒ ውስተ ሙላዲክሙ ይግበሩ ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር ። | ፲ | አንዱም አንዱም በሰውነቱ ርኩሰት የወጣበት ሰው ቢኖር ሩቅ አገር ያለም ቢሆን በተወለዳችሁበትም አገር ያለ ቢሆን የእግዚአብሔር በዓሉን (ፋሲካውን) ያድርጉ ። |
| በካልእ ወርኅ አመ ዐሡሩ ወረቡዑ ለሠርቅ ፍና ሠርክ ይግበርዎ በናእት ወበሐምለ ብኊእ ይብልዕዎ ። | ፲፩ | በሁለተኛው ወር ግንቦት በባተ በአሥራ አራተኛው ቀን ማታ ጊዜ በቂጣነቱ በአዘከል (ወመጻጻ) ይብሉት ። |
| ወኢያትርፉ እምኔሁ ለነግህ ፡ ወዐጽሞ ኢይሰብሩ እምኔሁ በሕጉ ለፋሲካ ይግበርዎ ። | ፲፪ | ከሱም ለነገ አያትርፉ (አያሳድሩ) አጥንቱንም አይስበሩት በበዓሉ ሥራት ያድርጉት ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲ ። |
| ወብእሲሰ ዘንጹሕ ውእቱ ወኢኮነ ርኁቀ ብሔረ ኀበ ሀለወ ለእመ ኀደገ ገቢረ ፋሲካ ለይሠሮ ውእቱ ነፍስ እምሕዝቡ ፡ እስመ ቍርባኖ ለእግዚአብሔር ኢያብአ በዘመኑ ፡ ኀጢአተ ይከውኖ ለውእቱ ብእሲ ። | ፲፫ | ንጹሕ የሆነ ያለበትም አገር ሩቅ ያልሆነ ሰው ግን በዓል ማድረግን ቢተው ያ ሰው ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ ፡ የእግዚአብሔር ቍርባኑ በዘመኑ አላገባምና በዚያ ሰው ኃጢአት ይሆንበታል ። ዘፍ፡ ፲፯ ፲፬ ፡ ዘፀ፡ ፲፪ ፲፭ ። |
| ወለእመኒ መጽአ ኀቤክሙ ግዩር ውስተ ምድርክሙ ይግበር ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር በሕጉ ለፋሲካ ወበከመ ትእዛዙ ወአሐዱ ውእቱ ሕጉ ለክሙ ለግዩርኒ ወለዘእም ፍጥረቱኒ ። | ፲፬ | መጻተኛም የእግዚአብሔርን በዓል በፋሲካ ሥርዓት ሊያደርግ ወደናንተ ቢመጣ እንደታዘዘው ያድርግ ፡ ለመጻተኛም ከናንተ ለተወለደም ሕጉ አንድ ነው በላቸው አለው ። ዘፀ፡ ፲፪ ፵፱ ። |

፲፭ ወበዕለት እንተ ባቲ ተከልዋ ለደብተራ ከደና ደመና ለደብተራ መርጡል ወሌሊተሰ ይመጽእ ዲበ ደብተራ ከመ ርእየተ እሳት እስከ ይጸብሕ ።

ደብተራ ኦሪትን በተከሉበት ቀን ደመና ደብተራ ኦሪትን ሸፈናት፣ በሌሊት ግን በደብተራ ኦሪት ላይ እንደ እሳት ያለ ዓምደ ብርሃን እስኪነጋ ድረስ ያበራ ነበር ።

፲፮ ወከመዝ ይከውን ለዘልፍ፡ ደመና ይከድና መዓልተ፣ ወርእየተ እሳት ሌሊተ ።

ዘወትር እንዲህ ይሆን ነበር፡ ቀን ደመና ይጋርዳት፣ ሌሊት ዓምደ ብርሃን ያበራላት ነበር ።

፲፯ ወእምከመ ሰሰለ ደመና እምደብተራ ይግዕዙ ደቂቀ እስራኤል፣ ወመከና ኀበ ቆመ ደመና ህየ ይትዐየኑ ደቂቀ እስራኤል ።

ደመናው ከደብተራ ኦሪት በወጣ ጊዜ የእስራኤል ልጆች ይጓዙ ነበር፡ ደመናው በቆመበት ቦታ የእስራኤል ልጆች ሲጓዙ ውለው በዚያው ይሰፍሩ ነበር ።

፲፰ ወበትእዛዙ ለእግዚአብሔር ይግዕዙ በኵሉ መዋዕል ዘቦቱ ይጼልላ ደመና ለደብተራ የኀድሩ ደቂቀ እስራኤል ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጓዙ ነበር፡ ደመናው ድንኳኒቱን በጋረደበት ወራት ሁሉ የእስራኤል ልጆች ይሰፍሩ ነበር ። ፩ ቆሮ፡ ፲ ፩ ።

፲፱ ወሰበ ይነብር ደመና ብዙኀ መዋዕለ ዲበ ደብተራ የዐቅቡ ደቂቀ እስራኤል መዓቅቢሁ ለእግዚአብሔር ወኢይግዕዙ ።

ደመናው በደብተራ ኦሪት ላይ ብዙ ቀን በሰነበተ ጊዜ የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር እስራኤልን የሚጠብቅበት ደመናን ይጠብቁ ነበር፣ (ደመናውም ሰፍሮ በሚሰነብትበት ጊዜ) አይጓዙም ነበር ። ዘኍ፡ ፱ ፳፪፡ ፩ ፶፫ ።

፳ ወበኍልቈ መዋዕል ዘይከድን ደመና ዲበ ደብተራ የኀድሩ ደቂቀ እስራኤል በቃለ እግዚአብሔር ወበትእዛዘ እግዚአብሔር ይግዕዙ ።

ደመናው በድንኳኑ ላይ በተጋረደበት ቀናት ቍጥር ሁሉ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ቃል ይሰፍሩ በእግዚአብሔርም ትእዛዝ ይጓዙ ነበር ። ኢዮብ ፲፯ ፳፪ ።

፳፩ ወሰበ ይነብር ደመና እምሠርክ እስከ ነግህ ወእመ ይሴስል ደመና በጽባሕ ይግዕዙ መዓልተ፣ ወእመኒ ሌሊተ እምከመ ሰሰለ ደመና ይግዕዙ ሌሊተ፣ በትእዛዘ እግዚአብሔር ይትዓየኑ ።

ደመናው ከማታ እስከ ጧት በደብተራ ኦሪት ላይ ሰፍሮ ሳለ አይጓዙም ነበር፣ ሲነጋም ደመናው በወጣ ጊዜ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በቀንም በሌሊትም ይጓዙ ይሠፍሩ ነበር ።

፳፪ ወለእመኒ አብዝኀ ነቢረ ደመና እንዘ ይጼልላ እስከ መዋዕለ ወርኅ ይትዓየኑ ደቂቀ እስራኤል ወኢይግዕዙ ።

ደመናው ድንኳኒቱን ጋርዶ እስከ ወር ድረስ ሰፍሮ ቢሰነብት የእስራኤል ልጆች ከሠፈሩ አይጓዙም ነበር ።

፳፫ እስመ በትእዛዘ እግዚአብሔር ይግዕዙ፣ ወሕገጊሁ ለእግዚአብሔር የዐቅቡ በትእዛዘ እግዚአብሔር ወበእዴሁ ለሙሴ ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጓዙ ነበርና እግዚአብሔር እስራኤልን የሚጠብቅበት ደመናንም በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ ቃል ይጠብቁ ነበር ። ዘኍ፡ ፱ ፲፱ ።

## ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ ግበር ለከ ክልኤተ መጣቅዕተ ዘብሩር ወዘዝብጦ ትገብሮሙ፡ ወይከውኑከ በዘቦቱ ትጼውዕ ተዓይነ ለኀዲር፣ ወበዘቦቱ ታንሥእ ተዓይነ ለሐዊር ።

እግዚአብሔር ሙሴን ቃየው ተነጋገረው፣ ተመትተው የተሠሩ ሁለት የብር ነጋሪቶችን ሥራ፣ ተመትተው የተሠሩም አድርጋቸው ሠራዊቱን የምትጠራባቸው ለመጓዝም የምታሥነሳባቸው ይሆኑሃል አለው ።

፪ ወትጠቅዕ በሙ ወይትጋብኡ ኵሉ ተዓይን ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

እነሱንም ምታቸው ሠራዊቱም ሁሉ ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ይሰብሰቡ ። ኤር፡ ፬ ፭፡ ኢዮብ ፪ ፲፭ ።

፫ ወለእመሰ በአሐዱ ጠቃዕከሙ ይመጽኡ ኀቤከ ኵሎሙ መላእክት ዘምስፍናሆሙ ለእስራኤል ።

በአንድ ስልት ነጋሪቱን ብትመታባቸው በእስራኤል ሹመት የተሾሙ አለቆች ሁሉ ወዳንተ ይመጣሉ ።

፬ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ ሠርቅ ።

(መጀመሪያ) በአንድ ስልት በመታችኋቸው ጊዜ በምሥራቅ በኩል የሰፈሩት ሠራዊት ይጓዙ፣ (ይሁዳ ይሳኮር ዛብሎን) ። ዘኍ፡ ፴፩ ፯ ።

፭ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ዳግመ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ አዜብ ።

ሁለተኛም በየስልታቸው በመታችኋቸው ጊዜ በደቡብ በኩል የሰፈሩት ሠራዊት ይጓዙ (ሮቤል ስምዖን ጋድ)።

፮ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ሣልስተ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ ባሕር ።

ሦስተኛም በየስልታቸው በመታችኋቸው ጊዜ በምዕራብ በኩል የሰፈሩ ሠራዊት ይጓዙ (ብንያም ምናሴ ኤፍሬም) ።

፯ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ራብዐተ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ መስዕ፣ ሶበ ለግዒዝ በትእምርት ትጠቅዑ፡ ወሰበ ለአስተጋብኦ ተዓይን ትጠቅዑ ዘእንበለ ትእምርት ።

አራተኛም በየስልታቸው በመታችኋቸው ጊዜ በሰሜን በኩል የሰፈሩ ሠራዊት ይጓዙ (አሴር ዳን ንፍታሌም) በምትጓዙበት ጊዜ በስልት ምቷቸው ሠራዊቱንም በመሰብሰብ በሆነ ጊዜ ያለ ስልት ምቱት ። ዘኍ፡ ፩ ፱ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወደቂቀ አሮን ካህናት እሙንቱ ይጠቅዕዎሙ ለመጣቅዕት ወይኩንክሙ ሕገ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ ። | ፰ | እነዚያም የአሮን ልጆች ካህናት ነጋሪቶቹን ይምቷቸው ፡ በዘመናችሁ ለዘለዓለም ሥራት ይሁናችሁ ። |
| ወለእመ ወፃእክሙ ፀብአ ላዕለ ፀርክሙ እለ አዕረሩ እምኔክሙ ትትኤመሩ በመጥቅዕ ወትዜክሩ በቅድመ እግዚአብሔር ወትድኅኑ እምፀርክሙ ። | ፱ | ግብር የአስቀሩባችሁ ጠላቶቻችሁን ልትወጉ ብትሮጡ በነጋሪቱ ትታወቃላችሁ በእግዚአብሔርም ፊት ትታሰባላችሁ ከጠላቶቻችሁም ትድናላችሁ ። ዘኍ፡ ፴፩ ፮ ። |
| ወበመዋዕለ ትፍሥሕትክሙ ወበዓላቲክሙ ወበሠርቀ ወርኅክሙ ትጠቅዑ በመጣቅዕት ላዕለ ቍርባንክሙ ወላዕለ መሥዋዕተ መድኃኒትክሙ ወይከውንክሙ ተዝካረ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወአነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ። | ፲ | በተድላ ደስታችሁና በበዓላችሁ ቀን ሠርቀ ወርኅም በሆነ ቀን ድኅነታችሁ የሚደረግበት መሥዋዕትንና ቍርባናችሁን በምታቀርቡበት ጊዜ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት መታሰቢያ ይሆናችኋል ፡ (ይህን ያዘዝኋችሁ) እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነኝ አለው ። |
| ወኮነ በካልእ ወርኅ ዘካልእት ዓመት አመ ኅሙሱ ለጽልመት ሰሰለ ደመና እምነ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፲፩ | በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር ጨረቃ ጨለማ በሆነች በአምስተኛው ቀን እንዲህ ሆነ ፡ ደመናው ከደብተራ ኦሪት ወገደ (ራቀ) ። ዘኍ፡ ፱ ፮ ። |
| ወተንሥኡ ደቂቀ እስራኤል ምስለ ገዓዞሙ ውስተ ገዳም ዘሲና ፡ ወቆመ ደመና ውስተ ገዳም ዘፋራን ። | ፲፪ | የእስራኤል ልጆች ከጓዛቸው ጋር ወደ ሲና ምድረ በዳ ለመሄድ ተነሡ ፡ ደመናውም በፋራን ምድረ በዳ ቆመ። |
| ወተንሥኡ እለ ይቀውሙ በቃለ እግዚአብሔር ወበእደ ሙሴ ። | ፲፫ | አስቀድመው የሚጓዙ ሠራዊት በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ ቃል ለጉዞ ተነሡ ። ዘኍ፡ ፪ ፱ ። |
| ወአንሥኡ በሕንሙ ትዕይንተ ደቂቀ ይሁዳ ቅድመ ምስለ ኀይሎሙ ወዘላዕለ ኀይሎሙ ነአሶን ወልደ አሚናዳብ ። | ፲፬ | የይሁዳም ልጆች እንደ ሥርዓታቸው አስቀድመው ከሠራዊቶቻቸው ጋር ጉዟቸውን አነሡ ፡ በሠራዊቶቻቸውም ላይ የተሾመው የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ይሳኮር ናትናኤል ወልደ ሰገር ። | ፲፭ | በይሳኮር ልጆች ነገድ ሠራዊትም ላይ የተሾመው የሰገር ልጅ ናትናኤል ነው ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ዛብሎን ኤልያብ ወልደ ኬሎን ። | ፲፮ | በዛብሎን ልጆች ነገድ ሠራዊት ላይ የተሾመው የኬሎን ልጅ ኤልያብ ነው ። |
| ወእምድኅረዝ ይነሥእዋ ለደብተራ ፡ ወያነሥእዋ ደቂቀ ጌድሶን ወደቂቀ ሜራሪ ወይፀውርዋ ለደብተራ ። | ፲፯ | ከዚህ በኋላ ድንኳኗን ነቅለው የጌድሶን ልጆችና የሜራሪ ልጆች ድንኳኗን አንሥተው ይሸከሟታል ። |
| ወይነሥኡ በሕንሙ ፡ ትዕይንተ ሮቤል ምስለ ኀይሎሙ ፡ ወዘላዕለ ኀይሎሙ ኤሊሱር ወልደ ሴድዩር ። | ፲፰ | የሮቤል ነገድ ከሠራዊቶቻቸው ጋራ በሥርዓታቸው ይነሡ ፡ በሠራዊቶቻቸውም ላይ የተሾመው የሴድዩር ልጅ ኢሊሱር ነው ። ዘኍ፡ ፪ ፲ - ፲፯ ፡ ፩ ፭ - ፲፬ ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ስምዖን ሰላምያል ወልደ ሲሩሳዴ ። | ፲፱ | በስምዖን ልጆች ነገድ ሠራዊት ላይ የተሾመውም የሲሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ነው ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ጋድ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል ። | ፳ | በጋድ ልጆች ነገድ ሠራዊት ላይ የተሾመውም የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ነው ። |
| ወያነሥኡ ደቂቀ ቀዓት ወይፀውሩ ዘቅድሳት ወያቀውምዋ ለደብተራ እስከ ይበጽሑ ። | ፳፩ | የቀዓት ልጆች ንዋየ ቅድሳቱን ይሸከማሉ ፡ የኋለኞቹ እስኪደርሱ ድረስ ደብተራ ኦሪትን ያቆሟት ነበር ። |
| ወይትነሥኡ በሕንሙ ትዕይንተ ኤፍሬም ምስለ ኀይሎሙ ወዘላዕለ ኀይሎሙ ኤልሳማ ወልደ ሴምዩድ ። | ፳፪ | የኤፍሬምም ልጆች ከሠራዊቶቻቸው ጋራ በሕጋቸው ይነሣሉ ፡ በሠራዊቶቻቸውም ላይ የተሾመው የሴምዩድ ልጅ ኤልሳማ ነው ። ዘኍ፡ ፪ ፲፰ ፡ ፩ ፲፩ ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ምናሴ ገማልያል ወልደ ፈዳሱር ። | ፳፫ | በምናሴ ልጆች ነገድ ሠራዊትም ላይ የተሾመው የፈዳሱር ልጅ ገማልያል ነው ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ብንያም አቢዳን ወልደ ጋድዮን ። | ፳፬ | በብንያም ልጆች ነገድ ሠራዊትም ላይ የተሾመው የጋድዮን ልጅ አቢዳን ነው ። |
| ወይትነሥኡ በሕንሙ ትዕይንተ ደቂቀ ዳን ድኅረ ኵሉ ተዓይን ምስለ ኀይሎሙ ወዘላዕለ ኃይሎሙ አክያዜር ወልደ አሚሳዴ ። | ፳፭ | የዳን ልጆች ሠራዊት ከሠራዊቱ ሁሉ በኋላ ከሠራዊቶቻቸው ጋራ በሥራታቸው ይነሣሉ ፡ የሠራዊቶቻቸውም አለቃ የአሚሳዴ ልጅ አክያዜር ነው ። ኢያ፡ ፮ ፱ ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ አሴር ፋጌሔል ወልደ ኤክራን ። | ፳፮ | በአሴር ልጆች ነገድ ሠራዊት ላይ የተሾመው የኤክራን ልጅ ፋጌሔል ነው ። |
| ወዘላዕለ ኀይሎሙ ለነገደ ደቂቀ ንፍታሌም አኪሬ ወልደ ኤናን ። | ፳፯ | በንፍታሌም ልጆች ነገድ ሠራዊት ላይ የተሾመውም የኤናን ልጅ አኪሬ ነው ። |

፳፰ ወከመዝ ውእቱ ግዓዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይግዕዙ
ምስለ ኀይሎሙ ።
፳፱ ወይቤሎ ሙሴ ለኢዮባብ ወልደ ራጉኤል መድናዊ ሐ
ሙሁ ፣ ንግዕዝ ንሕነሰ ውስተ መካን ኀበ ይቤለነ እግዚአ
ብሔር ኪያሁ እሁበክሙ ወነዓ ምስሌነ ወንገብር ሠናየ ላዕ
ሌከ እስመ እግዚአብሔር ነበበ ሠናየ ላዕለ እስራኤል ።

፴ ወይቤሎ ኢየሐውር፣ አላ ውስተ ብሔርየ ወውስተ
ሙላድየ እገብእ ።
፴፩ ወይቤሎ ሙሴ ኢትኅድገነ እስመ ነበርከ ምስሌነ ው
ስተ ገዳም ወልሀቀ በቤነ ።
፴፪ ወለእመ ሖርከ ምስሌነ እምዝንቱ ኵሉ ሠናይ እንተ
ይገብር እግዚአብሔር ላዕሌነ፣ ንገብር ሠናይተ ላዕሌከ ።
፴፫ ወግዕዙ እምኀበ ደብሩ ለእግዚአብሔር ምሕዋረ ሠ
ሉስ መዋዕል፡ ወታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ተሐውር
ቅድሜሆሙ ፍጽመ ምሕዋረ ሠሉስ መዋዕል ከመ ትር
አይ ሎሙ ምዕራፈ ።
፴፬ ወከነ ሶበ ግዕዘት ታቦት ይቤ ሙሴ፡ ተንሥእ እግዚአ
ወይዘረዉ ፀርከ ወይጕየዩ ኵሎሙ እለ ይጸልኡከ ።

፴፭ ወበማኅደሩሰ ይቤ፡ ተመየጥ እግዚአ በእልፍ ወበአእ
ላፍ ውስተ እስራኤል ።
፴፮ ወመጽአት ደመና ወጸለሎሙ መዓልተ እንዘ ይግዕዙ
እምትዕይንት ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወአንጐርጐሩ ሕዝብ በእኪት ቅድመ እግዚአብሔር፣
ወሰምዐ እግዚአብሔር ወተምዐ መዐተ ወነደት እሳት ላዕ
ሌሆሙ እምኀበ እግ፤አብሔር ወበልዐት አሐደ ኀብረ
እምትዕይንት ።
፪ ወጸርሑ ሕዝብ ኀበ ሙሴ ወጸለየ ሙሴ ኀበ እግዚአ
ብሔር ወኀደገት እሳት ።
፫ ወተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን መካነ ውዕየት እስመ
ነደት እሳት ላዕሌሆሙ እምኀበ እግዚአብሔር ።
፬ ወእለ ተደመሩሂ ምስሌሆሙ ፈተዉ ፍትወተ፡ ወነ
በሩ ወበከዩ ወደቂቀ እስራኤልኒ ይቤሉ መኑ ያበልዐነ
ሥጋ ።
፭ ተዘከርነ ዝክተ ዓሣተ ዘንበልዕ በብሔረ ግብጽ በከንቱ
ወቍስያቲሁ ወመልጶጶነ ወስጕርዶ ወበጸለ ወሰመተ ።

፮ ወይእዜሰ የብሰት ነፍስነ ዘአልብነ ባዕድ ዘንሬኢ ዘእ
ንበለ ዝ መና ።
፯ ወመናሰ ከመ ዘርአ ተቅዳ ውእቱ፡ ወርእየቱ ከመ ርእ
የተ በረድ ።
፰ ወየሐውሩ ሕዝብ ወይኤልዱ ሎሙ ወየሐርጽዎ በማ
ሕረጽ ወያደቀቅዎ በመድቀቅ ወያበስልዎ በመቅጹት ወገ
ብርዎ ዳፍንተኒ፣ ወጣዕሙኒ ከመ ጣዕመ መዓር ምስለ
ቅብዕ ።

የእስራኤል ልጆች ጉዞአቸው እንዲህ ነበር፣ ከሠራዊ
ቶቻቸው ጋር ይጓዙ ነበር ።
ሙሴም አማቹ ለሚሆን ለሚዶን ሰው የራጉኤል ልጅ
ኢዮባብን እንዲህ አለው፤ እኛ ግን እግዚአብሔር እሱን
እሰጣችኋለሁ ወዳለን በታ እንሄዳለን ከኛ ጋር ና እግዚአብ
ሔር ለእስራኤል በጎ ነገር አደርጋለሁ ብሎ ተናግሯልና
እኛም ላንተ በጎ ነገር እናደርግልሃለን አለው ።
ወደ ተወለድኩበት ወደ አገሬ እመለሳለሁ እንጂ አል
ሄድም አለው ። ዘፍ፣ ፲፪ ፯፣ ፴፪ ፲፪፣ ዘፀ፣ ፫ ፰ ።
ሙሴም በምድረ በዳ ከኛ ጋር ኑረሃልና በኛም ዘንድ
አርጅተሃልና አትለየን አለው ። ኢያሱ ፳፱ ፲፭ ።
ከኛ ጋር ብትሄድ፣ እግዚአብሔር ለኛ ከሚያደርግልን
በጎ ነገር ሁሉ ላንተም በጎ ነገር እናደርግልሃለን አለው ።
ከእግዚአብሔር ማደሪያ (ደብረ ሲና) የሦስት ቀን ጕ
ዳና ተጓዙ እግዚአብሔር እስራኤልን የሚጠብቅበት ደመ
ናም በታ ታዘጋጅላቸው ዘንድ የሦስት ቀን ጕዳና በፊታ
ቸው ቀድማ ትሄድ ነበር ። ዘፀ፣ ፫ ፩፡ ዘዳ፣ ፩ ፴፫ ።
ታቦቲቱም በተጓዘች ጊዜ እንዲህ ሆነ፣ ሙሴ አቤቱ፤
በረድኤት ተነሣ፡ ጠላቶችህ ይበተኑ፣ የሚጠሉህም ሁሉ
ይሸሹ ። ዘፀ፣ ፲፫ ፳፩ ።
በሰፈሩ ግን አቤቱ ከእልፍ አእላፍ (መላእክት ጋር
በረድኤት) ወደ እስራኤል ተመለስ እያለ ይጸልይ ነበር።
ደመናም ከሰፈር ሲጓዙ ቀን መጥታ ጋረደቻቸው ።

ምዕራፍ ፲፩ ።

ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት በክፉ አንጐራጐሩ እግ
ዚአብሔርም እንጐርጐሮአቸውን ሰምቶ ፈጽሞ ተቈጣ፣
ከእግዚአብሔርም ታዝዛ እሳት ነደደችባቸው፣ ከሰፈሩም
አንዱን ወገን አቃጠለች ። ዘዳ፣ ፱ ፳፪፣ መዝ፣ ፸፰ ፳፩ ።
ሕዝቡ ወደ ሙሴ ጮኹ፣ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር
ለመነ (ጸለየ) እሳቲቱም ማቃጠሏን ተወች ።
ከእግዚአብሔር ታዝዛ እሳት በነሳቸው ነዳለችና የዚያ
በታ ስም (እስራኤል) የተቃጠሉበት በታ ተባለች ።
ከነሳቸው ጋር በግቢ አንድ የሆኑም ሥጋን ማን ባበላን
ብለው ተቀምጠው አለቀሱ፡ የእስራኤልም ልጆች ሥጋ
ማን ባበላን፤ አሉ ። ዘፀ፣ ፲፪ ፴፰ ።
ሳንጽር ሳንግር በግብጽ አገር እንበላያው የነበረውን
ያን ዓሣ አሰብን፣ የዓሣውን ቋንጣ ዱባውን ቀይ ሽንኩር
ትን ነጭ ሽንኩርትን ኩራቱንም አሰብን ።
ዛሬ ግን ከዚህ ከመናው በቀር የምናየው የሌለ እኛ
ሰውነታችን ደረቀች አሉ ።
መናውም አካሉ እንደ ድንብላል መልኩም እንደ
በረድ ነጭ ነው ። ዘፍ፡ ፪ ፲ - ፲፪፣ ዘፀ፣ ፬ ፲፯ ።
ሕዝቡም ሂደው ሰብስበው በሙቀጫ ወቅጠው በወ
ፍጮ ፈጭተው በድስት ያበስሉት ነበር፣ ድፎ ዳቦ አድር
ገውም ይጋግሩት ነበር፣ ጣዕሙም ከቅቤ ጋር እንደ ተቀላ
ቀለ እንደ ማር ጣዕም ነበር ። ፪ ሳሙ፣ ፳፱ ፪ ።

፱ ወሶበ ይወርድ ጠል ውስተ ትዕይንት ሌሊተ ይወርድ
መናሂ ላዕሌሁ ።
፲ ወሰምዐ ሙሴ እንዘ ይበክዩ በበሕዘቢሆሙ አሐዱ
አሐዱ በኆበ ሞኆተ ደብተራሁ ወተምዐ መዐተ እግዚአብ
ሔር ጥቀ ወበቅድመ ሙሴኒ እኩየ ኮነ ።
፲፩ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ለምንት አሕመምኮ
ላዕለ ቍልዔከ፡ ወለምንት ኢረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ
ከመ ታግብእ ላዕሌየ መቅሠፍቶሙ ለእሉ ሕዝብ ።
፲፪ በኑ አነ ጸንስክዎሙ ለእሉ ሕዝብ፡ በኑ አነ ወለድክ
ዎሙ ከመ ትበለኒ፡ ንሥኦሙ ውስተ ኅፅንከ ከመ ይነሥ
እዎ ለዘየሐጽንዎ ውስተ ምድር ዘመሐልከ ለአበዊሆሙ ።

፲፫ እምአይቴ ሊተ ሥጋ ዘእሁብ ለእሉ ሕዝብ፡ እስመ
ናሁ ይበክዩ ላዕሌየ ወይብሉኒ ሀበነ ሥጋ ከመ ንብላዕ ።
፲፬ ወኢይክል አነ በሕቲትየ ፀዊሮቶሙ ለእሉ ሕዝብ
እስመ ይከብዱኒ ።
፲፭ ወለእመሰ ከመዝ ትሬስዮኒ ቀቲለ ቅትለኒ ለእመ ረከ
ብኩ ምሕረተ በቅድሜከ ከመ ኢይርአያ ለእኪትየ ።
፲፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አስተጋብእ ሊተ ሰብ
ዓ ብእሴ እምአእሩጊሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ተአምር
ለሊከ ከመ እሙንቱ ሊቃናቲሆሙ ለሕዝብ ወጸሐፍቶ
ሙኒ፡ ወታበውኦሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወይቁሙ
ህየ ምስሌከ ።
፲፯ ወእወርድ ወእትናገር በህየ ምስሌከ ወእነሥእ እመን
ፈስ ዘላዕሌከ ወእነብር ዲቤሆሙ፡ ወይፀውሩ ምስሌከ
ክበዶሙ ለእሉ ሕዝብ ወኢትሥራሕ በሕቲትከ ሎሙ ።

፲፰ ወትብሎሙ ለሕዝብኒ ያንጽሑ ርእሶሙ ለጌሠም ወት
በልዑ ሥጋ፡ እስመ በከይክሙ ቅድመ እግዚአብሔር
እንዘ ትብሉ መኑ ያበልዐነ ሥጋ፡ እስመ ይኄይሰነ ብሔረ
ግብጽ ወይሁበክሙ እግዚአብሔር ትብልዑ ሥጋ ።

፲፱ አኮ አሐተ ዕለተ ዘትበልዑ ወአኮ ሰኑየ፡ ወአኮ ኀሙ
ሰ መዋዕለ፡ ወአኮ ዐሠረ፡ ወአኮ ዕሥራ መዋዕለ ።
፳ ባሕቱ እስከ መዋዕለ ወርኅ ትበልዕዎ እስከ ይወፅእ
እምውስተ አእናፊክሙ፡ ወይከውነክሙ ኀምዘ እስመ ክሕ
ድክምዎ ለእግዚአብሔር ዘሀለወ ውስቴትክሙ ወበከይ
ክሙ በቅድሜሁ እንዘ ትብሉ፡ ለምንት ለነ አውፃእከነ እም
ብሔረ ግብጽ ።
፳፩ ወይቤ ሙሴ፡ ስሳ እልፍ አጋር ሕዝብ እለ ውስቴቶሙ
ሀለውኩ፡ ወአንተ ትቤለኒ እሁቦሙ ሥጋ፡ ወይበልዑ
መዋዕለ ወርኅ ።
፳፪ በኑ ኵሉ አባግዕ ወአልሕምት ይጠብሑ ሎሙ፡ አው
ኵሉ ዓሣተ ባሕር ይትጋብኡ ሎሙ ከመ ይእከሎሙ ።

፳፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በኑ ኢትክል እዴየ፡
ናሁ ትሬኢ እመ ትረክበ ለቃልየ ወእመ አልቦ ።

፳፬ ወወፅአ ሙሴ ወነገሮሙ ለሕዝብ ቃለ እግዚአብሔር

ጠልም ሌሊት በሰፈሩ በወረደ ጊዜ መናውም አብሮ
ይወርድ ነበር ። ዘፀ፡ ፲፮ ፲፫ ፲፬ ።
ሙሴም አንዱም አንዱም በየደጃፉ በየወገናቸው
ሲያለቅሱ ሰማ፡ እግዚአብሔርም ፈጽሞ ተቈጣ፡ በሙ
ሴም ፊት ክፉ ነገር ሆነ። ዘኍ፡ ፲፩ ፩ ።
ሙሴ እግዚአብሔርን በኔ በወዳጅህ ለምን ክፉ ነገር
አደረግህ፤ የነዚህንስ ወገኖች መከራ ወደኔ ትመልስ ዘንድ
በፊትህ ለምን ባለሟልነትን አላገኘሁ፤ አለው ።
የወለዱትን ልጅ ተከባክበው እንዲያሳድጉት ለአባቶ
ቻቸው ትሰጣቸው ዘንድ ወደ ማልሀላቸው ተከባክበህ
ውሰዳቸው ትለኝ ዘንድ በውኑ እኔ እነዚህን ወገኖች ጸንሼ
ወልጃቸዋለሁን፤። ኢሳ፡ ፵ ፲፩ ፡ ፵፱ ፳፫ ።
እንበላ ዘንድ ሥጋን ስጠን ብለው እነሆ በኔ ያለቅሳ
ሉና ለነዚህ ወገኖች የምሰጣቸው ሥጋ ከየት አገኛለሁ ።
ይበዙብኛልና እነዚህን ወገኖች እኔ ብቻዬን መጠ
በቅ አልችልም ። ዘፀ፡ ፲፰ ፲፰ ።
እንዲህስ ካደረግኸኝ በፊትህ ይቅርታን አግኝቼ እን
ደሆነ መከራዬን እንዳላይት እኔን ግደለኝ አለው ።
እግዚአብሔርም ሙሴን ከእስራኤል ልጆች ሽማግ
ሎች የሕዝቡ አለቆች እንዲሆኑ አንተ የምታውቃቸ
ውን ሰባ ሰዎች ሹማምንትንም ሰብስበህ ወደ ደብተራ ኦ
ሪት አግባቸው፥ ካንተም ጋር በዚያ ይቁሙ ።

ወርጄ በዚያ ካንተ ጋር እነጋገራለሁ፡ ባንተ ካደረው
መንፈስ ትንቢትንም ነሥቼ በነሳቸው አሳድርባቸዋለሁ፡
የነዚህን ወገኖች ብዛት ካንተ ጋር ይሸከሟሉ ለነሱ ብቻ
ህን አትድክም ። ዘፍ፡ ፲፩ ፫ ፡ ዘኍ፡ ፲፩ ፳፭ ።
ሕዝቡንም ለነገ ሰውነታቸውን ያነጹ ራሳቸሁን አንጹ
ማን ሥጋ ያበላናል ብላችሁ በእግዚአብሔር ፊት አልቅሳ
ችኋልና በግብጽም አገር መኖር ይሻለናል ብላችኋልና፡
ሥጋን ትበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ይሰጣችኋል ሥጋንም
ትበላላችሁ በላቸው ። ዘፀ፡ ፲፱ ፱ ፡ ዘኍ፡ ፲፩ ፭ ።
የምትበሉም አንድ ቀን፡ ሁለት ቀን፡ አምስት ቀን፡
አሥር ቀን፡ ሃያ ቀን፡ ብቻ አይደለም ።
በናንተ ያደረ እግዚአብሔርን ክዳችሁታልና ከግብጽ
አገርም ለምን አወጣኸን ብላችሁ በእግዚአብሔር ፊት
አልቅሳችኋልና በአፍንጫችሁ እስኪወጣ ድረስ መርዝም
ሁኖ እስኪጐዳችሁ ድረስ እስከ ወር ድረስ ትበሉታላችሁ
እንጂ ። ዘኍ፡ ፲፩ ፳፩ ፡ መዝ፡ ፸፰ ፳፱ ።
ሙሴም እኔ በመካከላቸው የምኖርባቸው ወገኖች ስሳ
እልፍ አርበኞች ናቸው፡ አንተም ሥጋ እሰጣቸዋለሁ፡
እስከ ወር ድረስ ሥጋን ይበላሉ አልከኝ ።
በውኑ ላሞችና በጎች ሁሉ ይታረዱላቸዋልን፤ ወይስ
ይበቃቸው ዘንድ የባሕር ዓሦች ሁሉ ይሰበሰቡላቸዋልን
አለ ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፳፮ ፡ መሳ፡ ፳፩ ፲፬ ።
እግዚአብሔርም ሙሴን በውኑ ሥልጣኔ ይህን ማድ
ረግ አትችልምን፤ ቃሌን ታምነው እንደሆነ አታምነውም
እንደሆነ እነሆ ታያለህ አለው ። ዘኍ፡ ፳፫ ፲፬ ።
ሙሴም ወጥቶ ለሕዝቡ የእግዚአብሔር ቃልን ነገራ

ወአስተጋብአ ሰብአ ብእሴ እምአእሩጊሆሙ ለሕዝብ ወአቀሞሙ ዐውደ ደብተራ ።

ቸው፣ ከሕዝቡም ሽማግሎች መርጦ ሰባ ሰው ሰብስቦ በድንኳኑ ዙርያ አቆማቸው ። ዘኍ፣ ፲፩ ፲፮ ።

፳፭ ወወረደ እግዚአብሔር በደመና ወተናገሮ፣ ወነሥአ እመንፈስ ዘላዕሌሁ ወሦጠ ላዕለ ሰብዓ ብእሲ ሊቃውንት፣ ወእምዝ አዕረፈ ላዕሌሆሙ መንፈስ ተነብዮ፣ ወተነበዩ ወኢተወሰኩ እንከ ።

እግዚአብሔርም በደመና ወርዶ ተነጋገረው፣ በሱ አድሮ ከለውም መንፈስ ትንቢት በሰባ ሊቃናት ላይ አሳደረው፣ ከዚህ በኋላ ትንቢትን የሚያናግር መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው ትንቢት ተናገሩ፣ ከሰባ ሊቃናት ግን አልተጨመሩም (አልተቈጠሩም)። ዘኍ፣ ፲፩ ፲፯ ።

፳፮ ወተርፉ ክልኤቱ አደው ውስተ ትዕይንት ስሙ ለአሐዱ ኤልዳድ፣ ወለካልኡ ሙዳድ ወአዕረፈ ላዕሌሆሙኒ መንፈሰ ትንቢት ወተነበዩ፣ ወእሙንቱኒ ተጽሕፉ ምስሌሆሙ ወኢመጽኡ ምስሌሆሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወተነበዩ በውስተ ትዕይንት ።

ሁለቱ ሰዎች በሰፈር ቀሩ፣ ያንዱ ስሙ ኤልዳድ የሁለተኛው ስሙ ሙዳድ ነው፣ በነሳቸውም ትንቢት የሚያናግር መንፈሰ ረድኤት አድሮ ትንቢት ተናገሩ፣ እነሱም ከነሳቸው ጋር ተቈጠሩ፣ ነገር ግን ከነሱ ጋር ወደ ደብተራ ኦሪት አልመጡም በከተማው ትንቢት ተናገሩ ።

፳፯ ወሮጸ አሐዱ ወሬዛ ወዜነዎ ለሙሴ ወይቤሎ ኤልዳድ ወሙዳድ ተነበዩ በውስተ ትዕይንት ።

አንድ ጐልማሳ ሮጦ ሄዶ ሙዳድና ኤልዳድ በከተማው ትንቢት ተናገሩ ብሎ ለሙሴ ነገረው ።

፳፰ ወይቤሎ ኢያሱ ዘነዌ ዘይቀውም ቅድሜሁ ለሙሴ ዘውእቱ ኅሩዩ እግዚእየ ሙሴ ክልአሙ ።

በፊቱ የሚቆም በለሚሉ የነዌ ልጅ ኢያሱ፣ ሙሴን ጌታዬ ከልክላቸው አለው ። ዘፀ፣ ፳፬ ፲፫ ።

፳፱ ወይቤሎ ሙሴ አንተኑ ትቀንእ ሊተ ወመኑ እምወሀበ ከመ ይትነበዩ ኵሉ ሕዝብ ለእግዚአብሔር ሶበ ወሀበ እግዚአብሔር መንፈሶ ላዕሌሆሙ ።

ሙሴም አንተ ለኔ ትቀናልኛለህን፤ ሕዝቡ ሁሉ ለእግዚአብሔር ትንቢት ይናገሩ ዘንድ ትንቢት የሚያናግር መንረሰ ረድኤት ማን በሳደረባቸው ነበር፤ እግዚአብሔር መንፈሰ ረድኤት ቢያሳድርባቸው እኔ እከለክላለሁን፤ አለው ።

፴ ወገብኡ ውስተ ትዕይንት ውእቱ ወአእሩጊሆሙ ለእስራኤል ።

እሱና የእስራኤል ሽማግሎችም ወደ ሰፈር ተመለሱ ።

፴፩ ወወፅአ መንፈስ እምኀበ እግዚአብሔር ወአዕደወ ፍርፍርተ እምባሕር፣ ወወረደ ውስተ ትዕይንት እስከ ምሕዋረ ዕለት እምዐውደ ትዕይንት እምለፌ ወእምለፌ፣ ወተወዋሐ ክዕበ እመተ መልዕልተ ምድር ።

ነፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዞ ወጥቶ (ታላቅ ታናሽ) ድርጭቶችን ከባሕር አወጣ፣ እስከ አንድ ቀን ጐዳናም ድረስ በከተማው ዙርያ በወድያና በወዲህ በምድር ላይ ሁለት ክንድ ተከመረ ። ዘፀ፣ ፲፮ ፲፫ ።

፴፪ ወተንሥኡ ሕዝብ ኵሎ መዓልተ ወኵሎ ሌሊተ በሳኒታ፣ ወአለዱ ሎሙ ፍርፍርተ፣ ወዘኅዳጠ አልዶ አለደ ዐሠርተ በመስፈርተ ቆሮስ፣ ወሰጥሑ ሎሙ ወአይበሱ ውስተ ዐውደ ተዓይኒሆሙ ።

ሕዝቡም በማግሥቱ ተነሥተው መላ ሌሊቱንና መዓልቱን ድርጭቶችን (የባሕር ዓሣና ዶሮ) ሰበሰቡ፣ አሳነሰሁ ያለ በላዩን አሥር ቆሮስ (፲፪ ጫን) ሰበሰበ፣ በሰፈሩም ዙርያ አስጥተው አደረቁ ። ዘፀ፣ ፲፮ ፲፮ ።

፴፫ ወእንዘ ሀለወ ሥጋ ውስተ ጥረሲሆሙ ዘእንበለ ያኅልቅዎ ተመዐ እግዚአብሔር ላዕለ ሕዝቡ ወቀተሎሙ በዐቢይ መቅሠፍት ጥቀ ።

ሥጋውም ገና በጥርሳቸው ሳለ (የቆረሱትን ሳይጐርሱት የጐረሱትን ሳያላምጡት) በልተው ሳይጨርሱ እግዚአብሔር፤በወገኖቹ ላይ ተቆጣ፣ እጅግ ጽኑ በሆነ መቅሠፍትም አጠፋቸው ። መዝ፣ ፸፰ ፴ ።

፴፬ ወተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን መቃብረ ፍትወት፣ እስመ ቀበርዎሙ ለሕዝብ እለ ፈተዉ፣ ወግዕዙ ሕዝብ እመቃብረ ፍትወት ውስተ አሴሮት ወነበሩ በአሴሮት ።

ሥጋን ግን ባበላን ብለው የተመኙት (የጐመጁ) ሕዝብ ቀብረዉበታልና የዚያ ቦታ ስም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ፣ ሕዝቡም ከምኞት መቃብር ወደ አሲሮት ተጉዘው በአሲሮት ተቀመጡ ። ዘዳግ፣ ፱ ፳፪ ።

## ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወሐመይዎ ለሙሴ ማርያም ወአሮን፣ በበይነ ብእሲት ኢትዮጵያዊት እንተ ነሥአ፣ እስመ ብእሲተ ኢትዮጵያዊተ ነሥአ ሙሴ ።

ሙሴ የኢትዮጵያን ሴት አግብቶአልና ስለ ኢትዮጵያይቱ ሴት አሮንና ማርያም (ወንድሞቹ) ሙሴን አሙት። ዘፀ፣ ፪ ፳፩ ።

፪ ወይቤሉ፣ ቦኑ ለሙሴ ባሕቲቱ ተናገሮ እግዚአብሔር አኮኑ ለነሂ ተናገረነ ወሰምዐ እግዚአብሔር ።

በውኑ እግዚአብሔር ሙሴን ብቻ ተናገረውን እኛንስ የተናገረን አይደለምን አሉ፣ እግዚአብሔርም ይህን ሰማ።

፫ ወሙሴሰ ብእሲ የዋህ ውእቱ ጥቀ እምኵሉ እጓለ እመሕያው ዘሀለወ ውስተ ምድር ።

ሙሴ ግን በዚህ ዓለም ካለው ሰው ሁሉ እጅግ የዋህ (ደግ) ነበር ። መዝ፣ ፸፯ ፬ ።

፬ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወለማር

እግዚአብሔርም ወድያው ሙሴን አሮንና እኅቱ ማር

| | | |
|---|---|---|
| ያም በጊዜሃ ንዑ አንትሙ ሠለስቲክሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፡ ወወፅኡ ሠለስቲሆሙ ። | | ያምን እናንተ ሦስታችሁ ወደ ደብተራ ኦሪት ኑ አላቸው ሦስቱም ሁሉ ወጡ ። ዘፍ፡ ፳፱ ፴፫፡ ሕዝ፡ ፴፭ ፲፪ ። |
| ወወረደ እግዚአብሔር በዐምደ ደመና ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወጸውዖሙ ለአሮን ወለማርያም፡ ወሖሩ ክልኤሆሙ ። | ፭ | እግዚአብሔር በዓምደ ደመና ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ወርዶ አሮንና ማርያምን ጠራቸው ሁለቱም ሄዱ ። ዘፀ፡ ፴፬ ፭ ። |
| ወይቤሎሙ ስምዑ ቃልየ፡ ለእመቦ ዘከነ ነቢየ እምኔክሙ ለእግዚአብሔር በራእይ እስተርኢ ሎቱ ወበሕልም እትናገሮ ። | ፮ | ቃሌን ስሙ ከናንተ ለእግዚአብሔር ነቢይ የሆነ ሰው ቢኖር በራእይ እታየዋለሁ፡ በሕልምም እነጋገረዋለሁ ። ኢዮብ ፴፫ ፲፭፡ ሉቃ፡ ፩ ፲፩ - ፳፪ ። |
| ወአኮ ከመ ቍልዔየ ሙሴ ምእመን ላዕለ ኵሉ ቤትየ ። | ፯ | ነገር ግን እንደ ወዳጄ እንደ ሙሴ አይደለም የምነጋገረው እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው ። መዝ፡ ፻፭ ፳፮። |
| አፈ በአፍ እትናገሮ ገሃደ ወአኮ በሥውር፡ ወርእየ ስብሐተ እግዚአብሔር፡ ወለምንት ኢፈራህክሙ ሐምዮቶ ለቍልዔየ ሙሴ ። | ፰ | እኔ በሥውር ያይደለ በግልጥ ቃል ለቃል እነጋገረዋለሁ የእግዚአብሔርንም ጌትነቱን አይቷል፡ ወዳጄ ሙሴን ማማትን ያልፈራችሁ ለምንድነው! አላቸው ። |
| ወኮነ ላዕሌሆሙ መንሱተ መዐቱ ለእግዚአብሔር ወሖሩ ። | ፱ | እግዚአብሔር ተቈጥቶ ያመጣው መከራ በነሳቸው ላይ ወርዶባቸው ሄዱ ። ዘፀ፡ ፴፫ ፲፩፡ ዕብ፡ ፫ ፭ ። |
| ወሰሰለ ደመና እምደብተራ ዘመርጡል ወአኀዛ ለምጽ ለማርያም ወፃዕደወት ኵለንታሃ ከመ በረድ፡ ወተመይጠ አሮን ኀበ ማርያም ወናሁ አኀዛ ለምጽ ። | ፲ | ደመናውም ከደብተራ ኦሪት ተነሣ (ወገደ) ማርያምን ለምጽ ያዘት (ወጣባት) ሁለንተናዋ እንደ በረድ ነጭ ሆነ፡ አሮንም ወደ ማርያም ተመለሰ እነሆም ለምጽ ወጥቶባት አገኛት ። ዘሌዋ፡ ፲፫ ፲፡ ዘዳግ፡ ፳፬ ፱ ። |
| ወይቤሎ አሮን ለሙሴ ብቍዐኒ እግዚእየ ኢትረስያ ለነ ኃጢአተ እስመ ኢያእመርነ ከመ አበስነ ። | ፲፩ | አሮንም ሙሴን ጌታዬ በጅ በለን እንደ በደልን አላወቅንምና በኛ ኃጢአት አታድርግብን አለው ። |
| ወኢንኩን ትዕሬራነ ለሞት ከመ ፃእፃእ ዘይወፅእ እማኅፀነ እሙ ወተበልዐ መንፈቀ ሥጋሃ ። | ፲፪ | ከናቱ ማኅፀን እንደ ወጣ ጭንጋፍ በሞት የተለቀምን አንሁን፡ የማርያም እኩሌታ አካሏም በለምጽ ተበላ (ነደደ) ። |
| ወጸርሐ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ፡ እግዚአ ብቍዐኒ አሕይዋ ። | ፲፫ | ሙሴም አቤቱ! በጅ በለኝ ማርያምን ከለምጽዋ አድናት ብሎ ወደ እግዚአብሔር ለመነ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሶበ አቡሃ ተፍአ ትፍአቶ ውስተ ገጻ እምኢኀፍረትኑ ሰቡዐ መዋዕለ ለትትገኀሥ አፍአ እምትዕይንት ሰቡዐ መዋዕለ፡ ወእምዝ ትባ ውእ ውስተ ትዕይንት ። | ፲፬ | እግዚአብሔርም ሙሴን አባቷ በፊቷ ምራቁን እንትፍ ቢልባት ሰባት ቀን በላፈረች ነበርን፤ (አሁንም) ከከተማ ወደ ውጭ ወጥታ ሰባት ቀን ትቀመጥ፡ ከዚያ በኋላ ወደ ከተማው ትግባ አለው ። ዘሌ፡ ፲፫ ፵፮፡ ዘዳግ፡ ፳፭ ፱ ። |
| ወትግኀሠት ማርያም አፍአ እምትዕይንት ሰቡዐ መዋዕለ ወኢግዕዙ ሕዝብ እስከ ንጽሐት ማርያም ። | ፲፭ | ማርያምም ከከተማው ወደ ውጭ ወጥታ ሰባት ቀን ተቀመጠች፡ ሕዝቡም ማርያም ከለምጽ እስክትነጻ ድረስ አልተጓዙም ። ሉቃ፡ ፲፯ ፲፪፡ ፱ ዜና መ፡ ፳፩ ፳፩ ። |
| ወእምድኅረ ዝንቱ ግዕዙ ሕዝብ እምአሴሮት ውስተ ገዳም ዘፋራን ። | ፲፮ | ከዚሁ በኋላ ሕዝቡ ከአሴሮት ወደ ፋራን ምድረ በዳ ተጓዙ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፲፫ ። | | ምዕራፍ ፲፫ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ፈኑ እደወ ሰብእ ዐይነ እለ ይሬእይዋ ለምድረ ከነአን ዘአነ እሁበሙ ለደቂቀ እስራኤል ይኩንንዋ ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ተነጋገረው፡ ይገዙዋት ዘንድ ለእስራኤል ልጆች የምሰጣቸው የከነዓንን ምድር ያዩዋት ዘንድ ጉበኞች ሰዎችን ስደድ አለው ። |
| አሐዱ አሐዱ ብእሲ እምነገዶሙ ወእምሕዘቢሆሙ ዘዘአብያተ አበዊሆሙ ትፌኑ ኵሎ ዐበይቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፪ | በየአባቶቻቸው ወገኖች ከየወገኖቻቸውና ከየነገዶቻቸው አንድ አንድ ሰው ከእስራኤል አለቆች ሁሉ ላክ ። |
| ወፈነዎሙ ሙሴ እምገዳም ዘፋራን በቃለ እግዚአብሔር ወእሉ ኵሎሙ እደው ዐበይቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እሙንቱ ። | ፫ | ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ከፋራን ምድረ በዳ ሰደዳቸው፡ እነዚህም ሰዎች ሁሉ የእስራኤል ልጆች አለቆች ናቸው ። ዘኍ፡ ፴፪ ፰፡ ዘዳ፡ ፩ ፳፪ ። |
| ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ዘእምነገደ ሮቤል ስሙ ወልደ ዝኩር ። | ፬ | ስማቸው ይህ ነው፤ ከነገደ ሮቤል የተላከው የዝኩር ልጅ (ወልደ ዝኩር) ነው ። |

፭ ወዘእምነገደ ስምዖን ሰፈጥ ወልደ ሱሪ ።
፮ ወዘእምነገደ ይሁዳ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ።
፯ ወዘእምነገደ ይሳኮር ኤጋል ወልደ ዮሴፍ ።
፰ ወዘእምነገደ ኤፍሬም አውሴ ወልደ ነዌ ።

፱ ወዘእምነገደ ብንያም ፈልጢ ወልደ ራፉው ።
፲ ወዘእምነገደ ዛብሎን ጉድዬል ወልደ ሰዲ ።
፲፩ ወዘእምነገደ ዮሴፍ ዘእምነገደ ደቂቀ ምናሴ ጋዲ ወልደ ሱሲ ።
፲፪ ወዘእምነገደ ዳን አሚሔል ወልደ ገማሊ ።
፲፫ ወዘእምነገደ አሴር ሳቱር ወልደ ሚካኤል ።
፲፬ ወዘእምነገደ ንፍታሌም ናቤ ወልደ ያቢ ።
፲፭ ወዘእምነገደ ጋድ ጉድያል ወልደ ማኪ ።
፲፮ ዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለእደው እለ ፈነወ ሙሴ ከመ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር ።
፲፯ ወሰመዮ ሙሴ ለአውሴ ወልደ ነዌ ኢያሱ ።
፲፰ ወፈነዎሙ ሙሴ ከመ ይርአይዋ ለይእቲ ምድረ ከነዓን፤ ወይቤሎሙ ሐሩ ውስተ ውእቱ ገዳም ወእምዝ ተዐርጉ ውስተ ደብር ።
፲፱ ወርእይዋ ለይእቲ ምድር እንተ ከመ እፎ ይእቲ ወሕዝብኒ እለ ይነብሩ ውስቴታ እመ ጽኑዓን እሙንቱ፤ ወእመ ድኩማን፤ ወእመ ውኁዳን ወእመ ብዙኃን እሙንቱ ።
፳ ወእንተ ከመ እፎ ይእቲ ምድራ እንተ ውስቴታ ይነብሩ እሙንቱ እመ ሠናይት ይእቲ ወእመ እኪት ወዘከመ እፎ ውእቶን አህጉሪሆሙ እለ ውስቴቶን ይነብሩ እሙንቱ፤ ወለእመ ቦቶን ቅጽር ወለእመ አልቦ ።
፳፩ ወእንተ ከመ እፎ ይእቲ ምድራ ለእመ ጥልልት ይእቲ፤ ወለእመ ይብስት ለእመ ቦ ውስቴታ እእዋም ወለእመ አልቦ፤ ወርእየክሙ ንሥኡ እምፍሬሃ፤ ወመዋዕሊሁ መዋዕለ ማእረር ዘእንበለ ይቅሥሙ ወይነ ።
፳፪ ወሐሩ ወርእይዋ ለይእቲ ምድር እምገዳም ዘሲን እስከ ሮአብ እንዘ የሐውሩ ለኤማት ።
፳፫ ወዐርጉ እንተ አዜብ ወበጽሑ እስከ ኬብሮን ወሀየ ውእቱ አኪሚ ወሴሲ ወተላሚ ትውልዱ ለኤናቅ ወኬብሮንሂ እንተ በሰብዐቱ ዓመት ተነድቀት እምቅድመ ሀገረ ጣኒ ዘግብጽ ።
፳፬ ወበጽሑ እስከ ቈላተ እጽቅ ወርእይዋ ወገመዱ እምሀየ ሐረገ ወይን ወውስቴቱ አሐዱ አስካል ወፆርዎ በምዝላል፤ ወእምሮማንሂ ወእምበለስሂ ።

፳፭ ወሰመይዎ ለውእቱ መካን ቈላ ሐረግ፤ በእንተ ሐረግ ዘገመዱ እምህየ ደቂቀ እስራኤል ።
፳፮ ወገብኡ እምህየ ርእዮሙ ይእተ ምድረ በአርባዓ ጽብሕ ።
፳፯ ወሐዊሮሙ በጽሑ ኀበ ሙሴ ወአሮን ወኀበ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ገዳም ዘፋራን ዘቃዴስ ወነገርዎሙ ዜናሆሙ ለኵሉ ተዓይኒሆሙ ወአርአይዎሙ ፍሬሃ ለይእቲ ምድር ።
፳፰ ወነገርዎሙ ወይቤሉ በጻሕነ ውስተ ይእቲ ምድር ኀበ

ከነገደ ስምዖን የተላከው የሱሪ ልጅ ሰፈጥ ነው ።
ከነገደ ይሁዳ የተላከው የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ነው ።
ከነገደ ይሳኮር የተላከው የዮሴፍ ልጅ ኤጋል ነው ።
ከነገደ ኤፍሬም የተላከው የነዌ ልጅ አውሴ (ኢያሱ) ነው ።
ከነገደ ብንያም የተላከው የራፉው ልጅ ፈልጢ ነው ።
ከነገደ ዛብሎን የተላከው የሰዲ ልጅ ጉድዬል ነው ።
ከምናሴም ልጆች ነገድ ከተወለደው ከነገደ ዮሴፍ የተላከው የሱሲ ልጅ ጋዲ ነው ።
ከነገደ ዳን የተላከው የገማሊ ልጅ አሚሔል ነው ።
ከነገደ አሴር የተላከው የሚካኤል ልጅ ሳቱር ነው ።
ከነገደ ንፍታሌም የተላከው የያቢ ልጅ ናቤ ነው ።
ከነገደ ዳን የተላከው የማኪ ልጅ ጉድያል ነው ።
ያችን ምድር ያዩዋት ዘንድ ሙሴ የላካቸው ሰዎች ስማቸው ይህ ነው ። ዘኍ፡ ፴፩ ፲፱፣ ፲፫ ፴ ።
ሙሴ የነዌ ልጅ አውሴን ኢያሱ አለው ።
ሙሴን ያችን የከነዓን ምድር እንዲያዩዋት ላካቸው፤ ወደዚያ ምድረ በዳም ሂዱ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ተራራው ውጡ አላቸው ። ዘፍ፡ ፲፬ ፲፣ ፲፱ ፲፯ ።
ያችንም ምድር ምን እንደሆነች እዩዋት፤ በውስጧ የሚኖሩ ሰዎች የጸኑም የደከሙም እንደሆኑ ጥቂቶችም ብዙዎችም እንደሆኑ ።
እነሳቸው የሚኖሩባት አገርነቷ ምን እንደሆነች መልካምም ክፉም እንደሆነች እነሱ የሚኖሩባቸው አገሮችም ምን እንደሆኑ ቅጥርም እንዳለባቸውና እንደሌለባቸውም ። ነህ፡ ፱ ፳፫፣ ሕዝ፡ ፴፬ ፲፬ ።
ምድርነቷም ምን እንደሆነች ግጪም ጭንጫም እንደሆነች በውስጧም ዛፎች እንዳሉባት ወይም እንደሌሉባት ሂዳችሁ አይታችሁ ከፍሬዋ አምጡ አላቸው፤ ወራቱም ወይኑን ሳይለቅሙ የአዝመራ ወራት ነበር ።
ወደ ኤማት ሲሄዱ ያችን ምድር ከሲን ምድረ በዳ ጀምሮ እስከ ሮአብ ድረስ ሂደው አዩዋት ።
ወደ አዜብ ወጡ እስከ ኬብሮንም ደረሱ በዚያም የኤናቅ ልጆች ሱሲ አኪሚና ተላሚ ነበሩ፤ ኬብሮንም በግብጽ አገር ካለች ከጣኒ አገር አስቀድማ ሰባት ዓመት የተሠራች ነበረች ። ዘፍ፡ ፲፫ ፲፰፣ ኢያ፡ ፲፬ ፲፭ ።
የወይን ሐረግ እስካለበት ቈላ ደርሰው አዩዋት፤ ከዚያም የወይን ሐረግ ቈረጡ፤ በውስጡም አንድ የወይን ዘለላ ነበረበት፤ በሳንሳም ተሸክመው ከሮማኑም ከበለሱም አመጡ ። ዘዳግ፡ ፩ ፳፭፣ ፪ ፲፫ ።
ያነንም ቦታ የእስራኤል ልጆች ከዚያ ስለቈረጡት ሐረግ፤ "የወይን ሐረግ ያለበት ቈላ„ አሉት ።
ያችንም ምድር አይተው በአርባ ቀን ተመለሱ ።

ሂደውም ከአሮንና ከሙሴ ከእስራኤል ልጆች ሠራዊቱም ሁሉ ዘንድ ወደ አሉበት የቃዴስ ክፍል ወደ ሆነች ወደ ፋራን ምድረ በዳ ደረሱ፤ የሠራዊቶቻቸውንም ሁሉ ወሬ ነገሩዋቸው፤ የዚያችንም ምድር ፍሬዋን አሳዩዋቸው።
አኗኗራቸውን ነገርዋቸው ወደ ላክኸን ወደዚያች

ፈነውከነ ምድር እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ወናሁ ፍሬሃ ።

፳፱ ወሕዝብኒ እለ ይነብሩ ውስቴታ ለይእቲ ምድር ጽኑዓን ወአህጉሪሆሙኒ ጽኑዓት ጥቀ ወዓበይት ወበሙ ቅጽር ወትውልዶሂ ለኤናቅ ርኢነ በህየ ።

፴ ወዐማሌቅ ኅዱራን ውስተ ምድር እንተ መንገለ አዜብ ወኬጤዎን ወአሞሬዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ኅዱራን ውስተ አድባሪሃ ወከነዓን ኅዱራን መንገለ ባሕር ወመንገለ ፈለገ ዮርዳኖስ ።

፴፩ ወአዘዘ ካሌብ ያርምሙ ሕዝብ በኀበ ሙሴ ወይቤ አልቦ አላ ዐሪገ ነዐርግ ወንወርሳ እስመ ክሂለ ንክህሎሙ።

፴፪ ወይቤሉ እልክቱ እደው እለ ዐርጉ ምስሌሁ ኢነዐርግ እስመ ኢንክል ዐሪገ ኀበ እሙንቱ ሕዝብ እስመ ይጸንዑ እምኔነ ፈድፋደ ።

፴፫ ወግርምተ ረሰይዋ ለይእቲ ምድር እንተ ርእይዋ በኀበ ደቂቀ እስራኤል እንዘ ይብሉ ምድር እንተ ሖርነ ከመ ንርአያ ምድር ይእቲ እንተ ተዐቅበሙ ለእለ ይነብሩ ውስቴታ ወኵሉ ሕዝብ ዘሀለዉ ውስቴታ ዘርኢነ እደው እሙንቱ እለ ፈድፈደ ኑኆሙ ።

፴፬ ወርኢነ በህየ እለ ያርብሕ፥ ወኮነ ቅድሜሆሙ ከመ አናብጥ እለ ከማሆሙኒ ቅድሜሆሙ ።

## ምዕራፍ ፲፬ ።

፩ ወነብሩ ኵሉ ተዓይን ወጸርሑ በዓቢይ ቃል ወበከዩ ሕዝብ ኵላ ሌሊተ ።

፪ ወአንጐርጐሩ ላዕለ ሙሴ ወላዕለ አሮን ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ወይቤልዎሙ ኵሉ ትዕይንት እምኀየሰነ ሶበ ሞትነ በምድረ ግብጽ እምንሙት በዝንቱ ገዳም ።

፫ ወለምንት ይወስደነ እግዚአብሔር ውስተ ይእቲ ምድር ከመ ንደቅ በውስተ ቀትል ወአንስትያነኒ ወደቂቅነኒ ይከውኑ ሕብልያ፥ ወይእዜኒ ይኄይሰነ ንግባእ ውስተ ብሔረ ግብጽ ።

፬ ወተባሀሉ በበይናቲሆሙ ሀቡ ናንግሥ ለነ ንጉሠ ወንግባእ ውስተ ብሔረ ግብጽ ።

፭ ወወድቁ ሙሴ ወአሮን በገጾሙ ቅድመ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፮ ወኢያሱ ወልደ ነዌ፥ ወካሌብ ወልደ ዮፎኒ እለ እምኔሆሙ ለእለ ርእይዋ ለይቲ ምድር ሠጠጡ አልባሲሆሙ ።

፯ ወይቤልዎሙ ለኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ምድርሰ እንተ ርኢነ ሠናይት ጥቀ ወፈድፋደ ።

፰ ወለእመሰ እግዚአብሔር ኀረየነ ከመ ያብእነ ውስተ ይእቲ ምድር ይሁበነ ለነ ይእተ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ።

፱ ወባሕቱ አንትሙ ኢትኩኑ ከሐድያነ እግዚአብሔር ወኢትፍርህዎሙ አንትሙ ለሕዝበ ለይእቲ ምድር እስመ ንሕነ ናጠፍኦሙ እስመ ኀለፈ መዋዕሊሆሙ እስመ እግዚአብሔር ሀሎ ምስሌነ ኢትፍርህዎሙ ።

ምድር ደረስን፣ ምድሪቱ ማርና ወተት የምታፈስ ናት፣ እነሆ ፍሬዋም ይህ ነው አሉ ። ዘኁ፡ ፲፬ ፰ ።

በዚያች አገር የሚኖሩም ሰዎች አርበኞች ናቸው፣ አምባዎቻቸውም እጅግ የጸኑና ታላላቆች ናቸው፡ ቅጥር አላቸው፣ የኤናቅንም ልጆች በዚያ አየን ።

አማሌቅም በአዜብ በኩል ባለችው አገር ሰፍረዋል፣ አሞሬዎንና፣ ኬጤዎን፣ ኤዌዎንና፡ ኢያቡሴዎን በደጋዎችዋ ሰፍረዋል፣ የከነዓንም ሰዎች በባሕርና በዮርዳኖስ ፈለግ ሰፍረዋል ብለው ነገሯቸው ። ዘፀ፡ ፲፯ ፰ ።

ካሌብ በሙሴ ዘንድ ያሉ ወገኖች ዝም ይሉ ዘንድ አዘዘ፣ እነሱን ማጥፋት እንችላለንና ወጥተን እንወርሳታለን እንጂ አንወርሳትም እንዳላችሁት አይደለም አላቸው።

ከሱ ጋር የወጡ እነዚያም ሰዎች ከኛ የሚጸኑ ስለሆኑ ወደነዚያ ወገኖች መውጣት አንችልምና አንወጣም አሉ ።

ያዩዋትንም ያችን ምድር በእስራኤል ልጆች አስፈራርተው ተናገሩ ልናያት የሄድንባት አገር በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች የምትጠብቃቸው ምድር ናት በውስጧ ያሉ ያየናቸውም ሰዎች ሁሉ ቁመታቸው እጅግ የረዘመ ነው።

በዚያም አርበኞችን አየን በፊታቸውም እንደ አንበጣ ሆነን፣ እንደነሳቸውም ያሉ አሕዛብ በፊታቸው እንደ አንበጣ ሆኑ አሉ ። ዘፍ፡ ፮ ፬፣ ዘሌዋ፡ ፲፩ ፳፪ ።

## ምዕራፍ ፲፬ ።

ሠራዊቱ ሁሉ ተባብረው ቃላቸውን አሰምተው ጮኹ ሕዝቡም ሁሉ ሙሉ ሌሊቱን አለቀሱ ። ዘኁ፡ ፲፩ ፬ ።

የእስራኤል ልጆች ሁሉ በሙሴና በአሮን ላይ አንጐራጐሩ፣ ሠራዊቱም ሁሉ በዚህ ምድረ በዳ ከምንሞት፡ በግብጽ አገር በሞትን በተሻለን ነበር አሉዋቸው ።

በጦር እንሞት ዘንድ እግዚአብሔር ወደዚያች አገር ለምን ይወስደናል፡ ልጆቻችንና ሚስቶቻችንም ብዝበዛ ይሆናሉ፡ አሁን ወደ ግብጽ አገር ብንመለስ ይሻለናል አሉዋቸው ።

እርስበርሳቸውም ኑ ንጉሥ አንግሠን ወደ ግብጽ አገር እንመለስ ተባባሉ ። ነሀ፡ ፬ ፲፯፣ ዘዳግ፡ ፲፰ ፲፯ ።

ሙሴና አሮንም በእስራኤል ልጆች ጉባኤ ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ወደቁ ።

ያችን አገር ካዩዋት ወገኖች የሆኑ የዮፎኒ ልጅ ካሌብና የነዌ ልጅ ኢያሱ ልብሳቸውን ቀደዱ ።

የእስራኤል ልጆች ሠራዊትን ሁሉ ያየናትስ ምድር ፈጽማ ያማረች የለመለመች ናት አሉዋቸው ።

ወደዚያች አገር ያገባን ዘንድ እግዚአብሔር ከመረጠንስ ማርና ወተት የምታፈስ (ተድላ ደስታ የሚገኝባት) ያችን አገር ለኛ ይሰጠናል ። ዘፀ፡ ፫ ፰፣ ዘዳግ፡ ፲ ፲፫ ።

እናንተ ግን እግዚአብሔርን የምትክዱ አትሁኑ እናንተ የዚያችን አገር ወገኖች ዘመናቸው ስለ አለፈባቸው አትፍሩዋቸው፣ እግዚአብሔርም (በረድኤት) ከኛ ጋር ስለ ሆነ እኛ እናጠፉቸዋለንና አትፍሩዋቸው አሉዋቸው ።

፲ ወይቤሉ ኵሉ ተዓይን ከመ ይውግርዎሙ በእብን፤ ወአስተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር በደመና ኀበ ደብተራ ዘመርጡል ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ።

፲፩ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ እስከ ማእዜኑ ይሤሁ ኩኒ እሉ ሕዝብ፤ ወእስከ ማእዜኑ ኢየአምኑኒ በኵሉ ተአምርየ ዘገበርኩ ሎሙ ።

፲፪ እቀትሎሙኑ በሞት ወአጥፍኦሙ ወእሬስየከ ለከ ወለቤተ አቡከ ውስተ ሕዝብ ዐቢይ ዘይበዝኅ እምእሉ ፈድፋደ ።

፲፫ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ይሰምዑ ግብጽ እለ እምኔሆሙ አውፃእኮሙ ለእሉ ሕዝብ በኀይልከ ።

፲፬ ወይሰምዑ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ ለይእቲ ምድር ከመ አንተ እግዚአብሔር ሀለውከ ውስተ እሉ ሕዝብ፤ ወአንተሰ እግዚአ ታስተርኢ ሎሙ ከመ ዘበዐይነ በዐይን ይትረአይ ወደመናከ ቆመት መልዕልቴሆሙ ወበዓምደ ደመና አንተ ሖርከ ቅድሜሆሙ መዓልተ ወበዓምደ እሳት ሌሊተ ።

፲፭ ወለእመ ቀጥቀጥኮሙ ለእሉ ሕዝብ ከመ ዘአሐዱ ብእሲ ይብሉ አሕዛብ እለ ይሰምዑ ስመከ፤ እስመ ስእነ እግዚአብሔር አብኦቶሙ ውስተ ምድር ዘመሐለ ሎሙ ቀተሎሙ በውስተ ገዳም ።

፲፮ ወይእዜኒ ይትለዐል ኀይልከ እግዚእ በከመ ትቤ እንዘ ትብል፤ እግዚአብሔር ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት ወጻድቅ ዘየኀድግ ዐመፃ ወኀጢአተ ወጌጋየ ወአንጽሖኒ ኢያነጽሖ ለመአብስ ወይኄልቆ ኃጣይአ ወላዲ ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ።

፲፯ ኅድግ ሎሙ ኃጣውኢሆሙ ለእሉ ሕዝብ በከመ ዕበየ ምሕረትከ ወበከመ መሐሬ ኮንከ ሎሙ እምብሔረ ግብጽ እስከ ይእዜ ።

፲፰ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ መሐርክዎሙ በከመ ትቤ፤ አላ ሕያው አነ ወሕያው ስምየ ።

፲፱ ወይመልእ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ኵሉ ምድረ ።

፳ ኵሎሙ እደው እለ ርእይዎ ለስብሐትየ ወለተአምርየ ዘገበርኩ በብሔረ ግብጽ ወበገዳም ወአምኀዙ አመከሩኒ ናሁ ዓሥር ዝንቱ ወኢሰምዑ ቃልየ ።

፳፩ ከመ ኢይሬእይዋ ለይእቲ ምድር እንተ መሐልኩ ለአበዊሆሙ ዘእንበለ ለውሉዶሙ እለ ሀለዉ ምስሌየ ዝየ ኵሎሙ እለ ኢየአምሩ ሠናየ ወእኪተ፤ ኵሉ ንኡስ ዘአልበ ዘየአምር ሎሙ እሁብ ለይእቲ ምድር፤ ወኵሎሙ እለ ወሀኩኒ ኢይሬእይዋ ።

፳፪ ወለቍልዔየ በሕቱ ካሌብ እስመ ኮነ ካልእ መንፈስ ላዕሌሁ ወተለወኒ፤ አበውኦ ውስተ ይእቲ ምድር እንተ ውስቴታ ቦአ ህየ ወዘርኡ ይወርሳ ።

ሕዝቡ ሁሉ በደንጊያ ይደበድቡዋቸው ዘንድ እንደ ብድባቸው አሉ፤ የእግዚአብሔርም ብርሃን በደብተራ ኦሪት ዘንድ በደመና ሁኖ ለሺል ልጆች ሁሉ ታያቸው ።

እግዚአብሔርም ሙሴን እነዚህ ወገኖች የሚያውኩኝ እስከ መቼ ድረስ ነው፤ ባደረግሁላቸው ተአምራቴስ ሁሉ የሚያምኑኝ እስከ መቼ ድረስ ነው፤ አለው ።

ፈጽሜ በሞት ላጥፋቸውን አንተንና ያባትህን ወገኖች ከነዚህ እጅግ ፈጽመው በሚበዙ ወገኖች አሾማችኋለሁ ። ዘፀ፡ ፴፪ ፲ ።

ሙሴም እግዚአብሔርን ከነሱ ለይተህ በከሃሊነትህ ያወጣኻቸው እነዚህን ወገኖች አጠፋቸው ሲሉ የግብጽ ሰዎች ይሰማሉ ። ዘፀ፡ ፴፪ ፲፪፤ ዘዳ፡ ፱ ፳፯ ።

በዚያች አገር የሚኖሩ ሰዎችም ሁሉ አንተ እግዚአብሔር በኒህ ወገኖች ዘንድ በረድኤት እንዳለህ ይሰማሉ፤ አቤቱ! አንተ ግን ሰው ከሰው ጋር ዓይን ለዓይን እንዲተያይ እንደታየሃቸው በፊታቸውም በሄድክበት ሁሉ ደመናህ ቀን የብርሃን ምሰሶ ሌሊት የእሳት ምሰሶ ሁና እንደ ቆመችላቸው ይሰማሉ ። ዘፀ፡ ፲፫ ፲፬፤ ፲፫ ፳ ።

እነዚህን ወገኖች እንደ አንድ ሰው ብታጠፋቸው ስምህን (ዝናህን) የሚሰሙ አሕዛብ እግዚአብሔር ወደ ማለላቸው አገር ማግባት ተስኖታልና በምድረ በዳ አጠፋቸው ይላሉ ። ዘዳግ፡ ፲፰ ፫፤ ኢያ፡ ፰ ፩ ።

አቤቱ! አሁንም ከሃሊነትህ ይገለጥ ዘንድ እግዚአብሔር ከመዓት የራቀ ቸርነቱ የበዛ፤ እውነተኛ ኃጢአትንና በደልን ክሕደትን ይቅር የሚል በደለኛውንም ከፍዳ የማያነፃ ያባትን ኃጢአት እስከ ሦስት እስከ አራት ትውልድ ድረስ በልጆች የሚያመጣ ነው ብለህ እንደተናገርህ።

እንደ ቸርነትህ ብዛት ከግብጽ አገር ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይቅር እንዳልኻቸው የነዚህን ወገኖች ኃጢአት ይቅር በላቸው ።

እግዚአብሔርም ሙሴን (ተአምራቴን አይተው የተፈታተኑኝ ሰዎች እንዳይድኑ) ሕያው ነኝ፤ ስሜም ሕያው ነው እንጂ ማራቸው እንዳልከኝ አሁን ማርኳቸው አለው ።

(ሙሴም) የእግዚአብሔር ክብሩ ጌትነቱ ምድሩን ሁሉ ይምላ አለ ። መዝ፡ ፸፪ ፲፱ ።

በግብጽ አገርና በምድረ በዳ ያደረግሁት ተአምራቴን ያዩ፤ ከዩም በኋላ የተፈታተኑኝ ቃሌንም ያልሰሙኝ ሰዎች ሁሉ፤ እነሆ ብዙ ጊዜ ነው ።

በዚህ ከኔ ጋር ያሉ ልጆቻቸው ናቸው የሚወርሷት እንጂ እኔ የማልሁላቸው አባቶቻቸው ይህችን ምድር እንዳይወርሷት ሕያው ነኝ ከኔ ጋራ ያሉ ክፉውንና በጎውን ለይተው ለማያውቁ ለትልቁም ለትንሹም ልጆቻቸው ይህችን ምድር እሰጣታለሁ እንጂ ለማልኩላቸው ለአባቶቻቸው እንዳልሰጣት ሕያው ነኝ፤ የተፈታተኑኝም ሁሉ አያዩዋትም ። ዘኍ፡ ፴፪ ፲፩፤ ፲፬ ፲፫ ።

ወዳጄ ካሌብን ግን ልዩ ዕውቀት አድሮበት ተከትሎኛልና ወደገባበት ወደዚያች አገር አገባዋለሁ፤ ልጁም ይወርሳታል አለው ። ዘኍ፡ ፲፫ ፯፤ ፴፪ ፲፩ ።

፳፭ ወአማሌቅ ወከነዓን ኅዱራን ውስተ ቈላት አውርዮን ወአንትሙሰ ገዐዙ ወግብኡ ውስተ ገዳም ዘፍኖተ ባሕረ ኤርትራ ።

ከነዓንና አማሌቅም አውርዮን በሚባለው ቈላ ሰፍረው ነበር ፤ እናንተ ግን በኤርትራ ባሕር መንገድ ተመልሳችሁ ተጓዙ አላቸው ።

፳፮ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን እንዘ ይብል ፤ እስከ ማእዜኑ እሰምዕ ንጕርጓሮሙ ለእሉ ትዕይንት ዘያንጐረጕሩ እሙንቱ እኮ ላዕሌክሙ እላ ላዕሌየ ።

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ሲል ተናገራቸው ፤ እነዚህ የሚያጕረጕሩት የሠራዊቱን እንጕርጕሮ እስከ መቼ ድረስ እሰማለሁ ፤ የሚያንጐራጕሩትም እንጕርጕሮአቸው በኔ ላይ እንጂ በናንተ ላይ አይደለም ።

፳፰ በሎሙ ሕያው አነ ይቤ እግዚአብሔር እመ አኮ ዳእሙ በከመ ነበብክሙ ውስተ ዕዝንየ ከማሁ እገብረክሙ ውስተ ዝንቱ ገዳም ።

ብቻ መመለሱ ካልሆነ በጆሮዬ ስሰማ እንደ ተናገራችሁ በዚህ ምድረ በዳ እንዳጠፋችሁ ሕያው ነኝ አላቸው ። ዘኍ፡ ፲፬ ፪ ።

፳፱ ወይወድቁ አብድንቲክሙ ወኵልክሙ እለ ተፈቀድክሙ ወእለ ተኈለቅክሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵልክሙ እለ አንጐርጐርክሙ ላዕሌየ ።

ሬሳችሁም ይወድቃሉ ፤ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያ በላይ የሆነው ፈጽማችሁ የተቈጠራችሁ በኔ ላይ ያንጐራጐራችሁም ሁሉ ። ዕብ፡ ፫ ፲፯ ።

፴ ከመ ኢትበውእዋ ለይእቲ ምድር ዘሰፋሕኩ እዴየ ከመ አንብርክሙ ውስቴታ ዘእንበለ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ወኢያሱ ወልደ ነዌ ።

ከነዌ ልጅ ከኢያሱና ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር በርሷ አኖራችሁ ዘንድ እጄን ዘርግቼ ያሳየኋችሁ ያችን አገር እንዳትገቡዋት ሕያው ነኝ አለ በላቸው ። ዘፀ፡ ፮ ፰ ።

፴፩ ወለደቂቅኒ እለ ትብልዎሙ ሕብልያ ይከውኑ አነ አበውኦሙ ውስተ ይእቲ ምድር ወይወርስዋ ለይእቲ ምድር እንተ አንትሙ ርኅቅሙ እምኔሃ ።

ብዝበዛ ይሆናሉ ያላችኋቸው ልጆቻችሁን ግን እኔ ወደዚያች አገር አገባቸዋለሁ ፤ እናንተ የራቃችኋት ያችን አገር ይወርሷታል ። ዘዳ፡ ፩ ፴፱ ፤ መዝ፡ ፻፮ ፳፬ ።

፴፪ ወይወድቁ አብድንቲክሙ ውስተ ዝንቱ ገዳም ወይትረዐዩ ደቂቅክሙ አርብዓ ዓመ ውስተ ዝንቱ ገዳም ።

ሬሳችሁም በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ ፤ ልጆቻችሁም በዚህ ምድረ በዳ አርባ ዓመት ይሠማራሉ (ይቅበዘበዛሉ) ።

፴ በከመ ኍላቌሆሙ ለእልክቱ መዋዕል እለ በሙ ርእይዋ ለይእቲ ምድር አርብዓ ዕለተ ፤ እምአርብዓ አሐቲ ዕለት ዓመተ ትከውን ብክሙ በእንተ ኀጢአትክሙ ወይኩንክሙ አርብዓ ዓመ ፤ ወተአምሩ እንከ መንሱተ መዐትየ ።

ያችን አገር እንዳዩባቸው እንደነዚያ ቀኖች ቍጥር አርባው ቀን ፤ አርባ ዘመን ፤ አንዲቱ ቀን ስለ ኃጢአታችሁ አንድ ዓመት ትሆንባችኋለች ፤ አርባው ቀን ፤ አርባ ዘመን ይሁንባችሁ ፤ ከዚያ በኋላ ፈርጄ የመጣሁባችሁ መቅሠፍቴን ታውቃላችሁ ። ዘሌ፡ ፳ ፭ ፤ ሕዝ፡ ፬ ፮ ።

፴፭ እስመ አነ እግዚአብሔር ዘነበብኩ ከመዝ እገብራ ለዛቲ ትዕይንት እኪት እንተ ኀብረት ላዕሌየ በዝንቱ ገዳም ለይጠፍኡ ወበህየ ለይሙቱ ።

እንዲህ ብዬ የተናገርኩ እኔ እግዚአብሔር ነኝና [illegible]ኔ የተባበረችብኝ ክፉ ወገን የምትሆን ይህችን ወገን እንዲህ አድርጌ አጠፋታለሁ ፤ በዚህ ምድረ በዳ ይጥፉ በዚያም ይሙቱ ። መዝ፡ ፻፮ ፳፬ ፤ ምሳ፡ ፩ ፳፫ ።

፴፮ ወእልክቱኒ እደው ዘፈነዎሙ ሙሴ ከመ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር እመ ገብኡ ወአንጐርጐሩ በእንቲአሃ ኀበ ኵሉ ትዓይን ወአውፅኡ ነገረ እኩየ በእንተ ይእቲ ምድር ።

ያችን ምድር ያዩዋት ዘንድ ሙሴ የላካቸው እነዚያ ሰዎች ተመልሰው በሕዝቡ ዘንድ አንጐራጐሩ ስለዚያችም አገር ከልቡናቸው አውጥተው ክፉ ነገር የተናገሩ ።

፴፯ ይመውቱ ውእቶሙ እደው እለ ይቤልዋ ለይእቲ ምድር እኪት ወምድርሰ ሠናይት ይእቲ በቅድመ እግዚአብሔር ።

ያችን አገር ክፉ ናት ያሉ እነዚያ ሰዎች ይሞታሉ አገሪቱ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ያማረች የተወደደች ናት ። ምሳ፡ ፳፫ ፲፱ ፤ ፲፫ ፴፭ ።

፴፰ ወኢያሱ ወልደ ነዌ ፤ ወካሌብ ወልደ ዮፎኒ ፤ የሐይዉ እምኔሆሙ ለውእቶሙ እደው እለ ሖሩ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር ።

ያችን አገር ለመጎብኘት ከተላኩት ከነዚያ ሰዎች ተለይተው የዮፎኒ ልጅ ካሌብና የነዌ ልጅ ኢያሱ ግን ይድናሉ አላቸው ። ኢያ፡ ፲፬ ፯ ፤ ይሁ፡ ፭ ።

፴፱ ወነገሮሙ ሙሴ ዘንተ ነገረ ለደቂቀ እስራኤል ወላሐዉ ሕዝብ ጥቀ ።

ሙሴም ይህንን ነገር ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው ሕዝቡም ፈጽመው አለቀሱ ።

፵ ወጌሡ በጽባሕ ወዐርጉ ውስተ ርእሰ ደብር ወይቤሉ ናሁ ንሕነ ነዐርግ ውስተ ውእቱ መካን ዘይቤለነ እግዚአብሔር እስመ አበስነ በእንቲአሁ ።

እሱን በድለናልና ፤ እግዚአብሔር ትወጣላችሁ ወዳለን በታ እነሆ እኛ እንወጣለን ብለው ሲነጋ ገሥግሠው ወደ ተራራው ራስ ላይ ወጡ ። ዘዳ፡ ፩ ፵፩ ።

፵፩ ወይቤሎሙ ሙሴ ለምንት ትትዓደዉ ቃለ እግዚአብሔር ኢኮነ ሠናየ ለክሙ ከመዝ ።

ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃል ለምን ትተላለፋላችሁ እንዲህ ያለ ነገር ለናንተ በጎ አይደለም አላቸው ።

፵፪ ኢትዕርጉ አንትሙ እስመ ኢሀለወ እግዚአብሔር ምስሌክሙ ወትወድቁ ቅድመ ፀርክሙ ።

እግዚአብሔር (በረድኤት) ከናንተ ጋር የለምና እናንተ አትውጡ በጠላቶቻችሁ ፊት ትወድቃላችሁ ።

፵፫ እስመ አማሌቅ ወከነናን ሀለዉ ሀየ ቅድሜክሙ ወትወድቁ በሐፂን እንበይነ ዘተመየጥክሙ ወክሕድክምዎ ለእግዚአብሔር ወኢሀለወ እግዚአብሔር ምስሌክሙ ።

የከነዓን ሰዎችና አማሌቅ በዚያ በፊታችሁ አሉና ወደ ግብጽ እንመለስ ስለ አላችሁ እግዚአብሔርን አሉተኛ ስለ አደረጋችሁት እግዚአብሔርም በረድኤት ከናንተ ጋር ስላልሆነ በጦር ተደብድባችሁ ትወድቃላችሁ አላቸው ።

፵፬ ወተኀይሎሙ ዐርጉ ውስተ ርእሰ ደብር ወታቦተ ሕጉሰ ለእግዚአብሔር ወሙሴኒ ኢተሐውሱ እማእከለ ትዕይንት ።

እምቢ ብለውም ወደ ተራራው ወጡ ፤ ሙሴና የእግዚአብሔር ሕጉ የተጻፈበት ታቦተ ጽዮን ግን ከሰፈሩ አልተነቃነቁም ። ዘዳ፡ ፩ ፵፫ ፡ ፩ ሳሙ፡ ፬ ፫ ።

፵፭ ወወረዱ አማሌቅ ወከናኔን እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ደብር ወሰደድዎሙ እስከ ኤርሚ ወገብኡ ውስተ ትዕይንት።

በዚያች ተራራ የሚኖሩ ከነዓንና አማሌቅም ወርደው እስከ ኤርሚ ድረስ አባረሩዋቸው ወደ ሰፈር ተመለሱ ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ፡ አመ በእክሙ ውስተ ይእቲ ምድር እንተ ውስቴታ ትነብሩ ዘአነ እሁበክሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ እኔ ወደ ምሰጣችሁ ወደ ምትኖሩበት አገር በገባችሁ ጊዜ ።

፪ ወትገብሩ ፍሬ ለእግዚአብሔር ቍርባነ አው መሥዋዕተ ፤ ወታፀብዩ ብፅዓተ እመኒ ዘበፈቃድክሙ ወእመኒ በበዓላቲክሙ ትገብሩ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር እመኒ እምአልሕምት ወእመኒ እምአባግዕ ።

ፍሬውን ለእግዚአብሔር ቍርባን ወይም መሥዋዕት አድርጉ ፤ በፈቃዳችሁም ቢሆን በበዓላቶቻችሁም ቢሆን እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ስለቱን አብዝታችሁ አድርጉ ፤ ከላሞችም ቢሆን ከበጎችም ወገን ቢሆን ያምጣ ።

፫ ወያመጽእ ዘያበውእ ቍርባኖ ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ ሥንዳሴ ዓሥራተ እዴሃ ለመስፈርተ ኢፍ ዘልዉስ በቅብዕ በራብዕተ እዴሃ ለመስፈርተ ኢን ።

ለእግዚአብሔር ቍርባኑን የሚያመጣ ሰው የኢን መስፈሪያ አራተኛ እጅ በሆነ ዘይት የተለወሰ የኢን መስፈሪያ አሥረኛ እጅ የሆነ የመልክም ሥንዴ ዱቄት ያምጣ ።

፬ ወወይነ ለሞጻሕት ራብዕተ እዴሃ ለመስፈርተ ኢን ይገብር ዲበ ቍርባን ወእመኒ ዲበ መሥዋዕት ፤ ለአሐዱ ማሕስእ በግዕ ይግበር ዘመጠነዝ ቍርባነ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ፍልቅ አድርገው አፍሰው ሊጠጡት የገንቦ አርበኛ ወይን በቍርባኑ ላይ ያድርግ ፤ በመሥዋዕቱም ላይ ቢሆን ለአንድ የበግ ጠቦት እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ይህን ያህል ቍርባን ያድርግ ። ሽጅ ፯ ፲፬ ።

፭ ወለበግዕኒ ሰበ ትገብርዎ ቍርባነ አው መሥዋዕተ ሥንዳሴ ክልኤተ ዓሥራተ ዘግቡር በቅብዕ በሣልስተ እዴሃ ለመስፈርተ ኢን ።

በጉንም ቍርባን ወይም መሥዋዕት አድርጋችሁ በምታቀርቡት ጊዜ በገንቦ ሢሶ ዘይት የታሸ የሁለት ላዳን ሥንዴ ድፎ መሥዋዕት አድርጉ ። ሽጅ ፲፪ - ፲፬ ።

፮ ወወይነ ለሞጻሕት ሣልስተ እዴሃ ለመስፈርተ ኢን ታበውእ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ፍልቅ አድርገው ሊጠጡት የገንቦ ሢሶ ወይንን ያግባ ።

፯ ወለእመሰ እምውስተ አልሕምት ገበርክሙ ቍርባነ ፤ አው መሥዋዕተ ፤ አው አዕበይክሙ ብፅዓተ መድኀኒትክሙ ለእግዚአብሔር ።

ከላሞች ወገን መሥዋዕትን ብትሠዉ ወይም ብትበሉት ፤ ወይም ድኅነትን የሚያሰጥ ስለትን ለእግዚአብሔር አብዝታችሁ ብታደርጉ ። ዘሌዋ፡ ፯ ፲፩ ።

፰ ወያመጽእ ላዕለ ውእቱ ላሕም መሥዋዕተ ሥንዳሴ ሠለስተ ዓሥራተ ዘልዉስ በቅብዕ በመንፈቃ ለመስፈርተ ኢን ።

በዚያ በላሙ ላይ በገንቦ እኩሌታ ዘይት የታሸ ሦስት ላዳን የመልክም ዱቄት ሥንዴ መሥዋዕት ያምጣ ።

፱ ወወይነ ለሞጻሕት መንፈቃ ለመስፈርተ ኢን ቍርባነ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ፍልቅ አድርገው አፍሰው ሊጠጡት የገንቦ እኩሌታ ወይን ቍርባን አምጣ ።

፲ ከማሁ ትገብር ለአሐዱ ላሕም ፤ አው ለአሐዱ በግዕ ፤ አው ለአሐዱ ማሕስአ በግዕ ፤ እምአባግዕ ወእመኒ እምአጣሊ ።

ለአንድ በሬ ፤ ለአንድ በግ ፤ ወይም ከበጎቹ ለይተው ላመጡት የበግ ጠቦት ከፍየሎችም ወገን ቢሆን እንዲህ አድርግ ።

፲፩ በኍላቌሆሙ ለእለ ገበርክሙ ከመዝ ትገብር ለለአሐዱ አሐዱ በአምጣነ ኍላቌሆሙ ።

በሠዋችኋቸው ቍጥር ላንዱም ላንዱም በቍጥራቸው መጠን እንደዚህ አድርጉ ።

፲፪ ኵሉ ዘእምፍጥረቱ ከመዝ ይገብር ፤ ወከመዝ ያበውእ ቍርባኖ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ትውልዱ ከእስራኤል ወገን የሆነ ሁሉ እንደዚህ ያድርግ ፤ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ቍርባኑን እንደዚህ ያቅርብ ።

፲፫ ወለእመሰ ግዩር ዘከነ ውስቴትክሙ ወፈለሰ ውስተ ምድርክሙ ወእመኒ ዘከነ ውስተ ሙላዲክሙ ይግበር

ከናንተ ጋር ያለ ወደ አገራችሁ የተሰደደ መጻተኛ ቢኖር ወይም በተወለዳችሁበት አገር ያለ ቢሆን አይገባ

| | | |
|---|---|---|
| ቍርባነ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር በከመ ትገብሩ አንትሙ ። | | ኛም ብሎ ዝም አይበል፤ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው እናንተ እንደምታደርጉት ያድርግ ። |
| አሐዱ ውእቱ ሕጉ ለክሙ ወለግዩራን እለ ሀለዉ ውስቴትክሙ ሕገ ዘለዓለም በመዋዕሊክሙ ይኩንክሙ በከመ ትገብሩ አንትሙ ከማሁ ይገብሩ ግዩራን ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፲፬ | ለናንተ ከናንተም ጋር ላሉ መጻተኞች ሕጉ ሥርዓቱ ይህ ነው፤ በዘመናችሁ የዘለዓለም ሥርዓት ይሁናችሁ፤ እናንተ እንደምታደርጉት መጻተኞችም በእግዚአብሔር ፊት እንደዚሁ ያድርጉ ። |
| አሐዱ ውእቱ ሕጉ ወአሐዱ ኵነኔሁ ለክሙ ወለግዩር ዘሀለወ ውስቴትክሙ ። | ፲፭ | ለናንተና ከናንተ ጋር ላሉ መጻተኞች ሕጉ (ቅጣቱ) አንድ ነው ። ዘፀ፡ ፲፪ ፵፱፤ ዘሌዋ፡ ፫ ፲፯ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ። | ፲፮ | እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው ። |
| እመ ትበውኡ ውስተ ይእቲ ምድር ዘአነ እወስደክሙ ህየ ። | ፲፯ | እኔ ወደምወስዳችሁ ወደዚያች አገር በገባችሁ ጊዜ ። |
| ሶበ በላዕክሙ እምእክላ ለይእቲ ምድር ትፈልጡ መባአ ፍሉጠ ለእግዚአብሔር እምቀዳሚ ሐሪጽክሙ ። | ፲፰ | ከዚያች አገር እኽል በበላችሁ ጊዜ ከዱቄታችሁ መጀመሪያ ለእግዚአብሔር የተለየ መባውን ስጡ ብለህ ንገራቸው ። |
| ኅብስተ መባእ ትፈልጡ ሎቱ ከመ መባእ ዘእምውስተ ዐውደ እክል ከማሁ ትፈልጡ ሎቱ እምውስተ ቀዳሚ ሐሪጽክሙ፤ ወትሁቡ ለእግዚአብሔር መባአ በመዋዕሊክሙ ። | ፲፱ | ከዱቄታችሁ መጀመሪያ እንድትሰጡ የእንጀራውንም መጀመሪያ ስጡ፤ ከእኽሉ ዐውድማ እንድትለዩት መባ እንደዚሁም ከመጀመሪያው ዱቄታችሁ ለይታችሁ ባለ ዘመናችሁ ለእግዚአብሔር መባውን ስጡ ። |
| ወለእመ አበስክሙ ወአበይክሙ ወኢገበርክሙ ዘንተ ኵሎ ትእዛዘ ዘይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፳ | እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ይህን ትእዛዝ እምቢ ብላችሁ ብትበድሉ (እንሰጥም) ብትሉ ግን ። |
| በከመ አዘዘክሙ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ እምአመ አዘዘክሙ እግዚአብሔር ወእምቅድሜሁ በመዋዕሊክሙ ። | ፳፩ | እግዚአብሔር በሙሴ ቃል እንዳዘዛችሁ እግዚአብሔር ካዘዛችሁ ጀምሮ ከዚያም አስቀድሞ ባለ ዘመናችሁ፤ ያዘዛችሁን ሁሉ ባታደርጉ ። ዘዳግ፡ ፳፯ ፲ ፥ ፩ - ፲፬ ። |
| ወለእመሰ ዘኢተአውቆሙ ውስተ አዕይንቲሆሙ ለትዕይንት ወትገብር ኵላ ይእቲ ትዕይንት አሐደ ላሕመ እምአልሕምት ንጹሐ ለመሥዋዕት ወለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር፤ ወመሥዋዕቱኒ ለዝንቱ ወሞጻሕቱሂ በከመ ሕጉ ወአሐዱ ሐርጌ እምአጣሊ በእንተ ኀጢአት ። | ፳፪ | ለሠራዊቱም በፊታቸው ያልታወቃቸው ኃጢአት ቢኖር፤ ያች ሁሉ ሠራዊት እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ከላሞች ንጹሕ የሆነ አንድ ወይፈን ለመሥዋዕት ታቅርብ የዚህም መሥዋዕት ፍልቅ አድርገው አፍሰው ሊጠጡት የሚያቀርቡት ወይኑም እንደሥራቱ ነው፤ ከፍየሎችም አንድ ሙክት ለመሥዋዕት ታቅርብ። ዘሌ፡ ፬ ፲፫ ። |
| ወያስተሠሪ ካህን በእንተ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይትኀደግ ሎሙ እስመ በኢያእምሮ ውእቱ ወእሙንቱኒ ያመጽኡ ቍርባኖሙ ወመሥዋዕቶሙ ለእግዚአብሔር በእንተ ኀጢአቶሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወበእንተ ኢያእምሮቶሙ ። | ፳፫ | ካህኑም የእስራኤልን ልጆች ሠራዊት ሁሉ ኃጢአት በለማወቅ የተሠራ ነውና ያስተሠርይላቸዋል፤ እነሳቸውም በለማወቅ ስለ ሠሩት ኃጢአታቸው በእግዚአብሔር ፊት ቍርባናቸውንና መሥዋዕታቸውን ያምጡ ። |
| ወይትኀደግ ለኵሉ ትዕይንቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወለግዩርኒ ዘይመጽእ ኀቤክሙ እስመ ለኵሉ ሕዝብ በኢያእምሮ ኮነ ። | ፳፬ | የእስራኤል ልጆች ሠራዊት ሁሉ ኃጢአት በዚህ ይሠረያል ወደናንተ የመጣውም መጻተኛ ኃጢአት በዚህ ይሠረያል፤ ለሕዝቡ ሁሉ ባለማወቅ የተሠራ ነውና ። |
| ወለእመሰ አሐዱ ብእሲ አበሰ በኢያእምሮ፤ ያመጽእ አሐተ ጠሊተ እንተ ዓመት በእንተ ኀጢአት ። | ፳፭ | አንድ ሰው ባለማወቅ ቢበድል ግን ስለ ኃጢአቱ ዓመት የሆናት አንዲት ፍየል ያምጣ። ዘሌ፡ ፬ ፳፯ ። |
| ወያስተሠሪ ካህን በእንተ ውእቱ ብእሲ እንተ በኢያእምሮ አበሰ ቅድመ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ ካህን በእንቲአሁ ። | ፳፮ | ካህን ባለማወቅ በእግዚአብሔር ፊት ስለ በደለ ስለ ዚያ ሰው በዚሁ መሥዋዕት ኃጢአቱን ያስተሥርይለት ። |
| ዘእምፍጥረቱሂ ውስተ ደቂቀ እስራኤል ወለግዩራንሂ ዘሀለወ ውስቴትክሙ አሐዱ ውእቱ ሕጉ ሎሙ ወለክሙ እምከመ በኢያእምሮ ገብሩ ። | ፳፯ | ትውልዱ ከእስራኤል ልጆች ወገን ለሆነና ከናንተ ጋር ላሉ መጻተኞችም ካህኑ ኃጢአታቸውን ያስተሥርዩላቸው ባለማወቅ ከሠሩ የነሱም የናንተም ሥርየቱ አንድ ነው ። ዘዳ፡ ፯ ፲፪፤ መዝ፡ ፲፱ ፲፫ ። |
| ወብእሲ እንተ ገብረ በእዴሁ ትዕቢተ እመኒ እለ እምፍጥረቶሙ ወእመኒ እምግዩራኒሁ ለእግዚአብሔር ወእም | ፳፰ | በቃሉ ትዕቢት ያደረገ (አምላክ ነኝ ያለ) ሰው ትውልዳቸው ከእስራኤል ወገን ከሆኑ ሰዎችም ቢሆን ከእግዚ |

ዕፀ በዝንቱ ለይሠሮ ውእቱ ብእሲ እምሕዝቡ ።

፴፩ እስመ ላዕለ ቃለ እግዚአብሔር አበሰ ወዐለወ ትእ
ዛዞ ተቀጥቅጦ ለይትቀጥቀጥ ውእቱ ብእሲ ወኀጢአቱሂ
ላዕሌሁ ።
፴፪ ወሀለዉ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ገዳም ወረከቡ ብእሲ
እንዘ ይኤልድ ዕፀወ በዕለተ ሰንበት ።
፴፫ ወአምጽእዎ እለ ረከብዎ ኀበ ሙሴ ወአሮን ወኀበ
ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።
፴፬ ወአውዐልዎ ውስተ ሙዓል እስመ አልቦ ዘከሠቶ ዘከ
መ ይሬስይዎ ።
፴፭ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ሞተ ለይሙት
ውእቱ ብእሲ ወይውግርዎ በእብን ኵሉ ትዕይንት ።
፴፮ ወአውፅእዎ አፍአ ኵሉ ተዓይን እምትዕይንት ወወገ
ርዎ በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ።
፴፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤ ንግሮሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ይግበሩ ዘፈረ ውስተ ጽንፈ አል
ባሲሆሙ በመዋዕሊሆሙ ወይደዩ ውስተ ዘፈረ ጽንፈሁ
ደርከኖ ፍቱለ ።
፴፰ ወይኩንክሙ ውስተ ዘፈሩ ወትሬእይዎ ወትዜክሩ
ኵሉ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር ወግበርዎን ።
፴፱ ወኢትትልዉ ድኅረ ሕሊናክሙ ወድኅረ አዕይንቲ
ክሙ በዘበቱ ትዜምዉ አንትሙ ድኅሬሆሙ ።
፵ ከመ ትዘከሩ ወትግበሩ ኵሉ ትእዛዝየ ወትኩኑ ቅዱ
ሳነ ለአምላክክሙ ።
፵፩ ዘአውፅአኩክሙ እምድረ ግብጽ ከመ እኩንክሙ
አምላከ ወአነ እግዚአብሔር አምላክክሙ ።

ምዕራፍ ፲፮ ።

፩ ወተናገረ ቆሬ ወልደ ይስአር ወልደ ቀዓት ፤ ወልደ
ሌዊ ወዳታን ወአቤሮን ደቂቀ ኤልያብ ወአውናን ወልደ
ፋሌቅ ወልደ ሮቤል ።
፪ ወተቃወምዎ ቅድሜሁ ለሙሴ ፤ ወእደው እምደቂቀ
እስራኤል ክልኤቱ ምእት ወኃምሳ ዐበይተ ተዓይን ኅሩ
ያን በውስተ ምክር ወእደው ስሙያን ።
፫ ወተንሥኡ ዲበ ሙሴ ወዲበ አሮን ወይቤልዎሙ
ይኩንክሙ ለክሙ ፤ እስመ ኵሉ ተዓይን ቅዱሳን ኵሎሙ
ወእግዚአብሔር ሀለወ ውስቴቶሙ ፤ ወለምንት ትቀውሙ
ዲበ ትዕይንቱ ለእግዚአብሔር ።

፬ ወሰሚዖ ሙሴ ወድቀ በገጹ ፤ ወይቤሎ ለቆሬ ወለ
ኵሉ ትዕይንቱ ለይርአይ እግዚአብሔር ወያእምሮሙ ለእ
ሊአሁ ወያስተጋብአሙ ኀቤሁ ለቅዱሳኒሁ ።
፭ ወከመዝ ግበሩ አንትሙ ወንሥኡ ለክሙ ማዕጠንተ
ቆሬ ወኵሉ ትዕይንቱ ።
፮ ወደዩ ውስቴቱ እሳተ ወደዩ ዲቤሁ ዕጣነ ቅድመ እግ
ዚአብሔር ጌሠመ ወይኩን ዝንቱ ብእሲ ዘኀረዮ እግዚአ
ብሔር ቅዱሰ ይኩኖሙ ለደቂቀ ሌዊ ።

አብሔር መጻተኞችም ቢሆን በዚህ ትዕቢቱ እግዚአብ
ሔርን ቢያሰዝን ያ ሰው ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ ።
በእግዚአብሔር ሕግ ላይ በድሏልና ፤ ትእዛዙንም አፍ
ርሷልና ያ ሰው በደንጊያ ተወግሮ ይሙት ፤ የኃጢአቱም
ፍዳ በራሱ ላይ ነው በላቸው አለው ። ፪ ሳሙ፡ ፲፪ ፱ ።
የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ሳሉ አንድ ሰው ቅዳ
ሜ ቀን ዕንጨት ሲለቅም አገኙ ።
ያገኙትም ሰዎች ወደ ሙሴ ወደ አሮንና ወደ እስራ
ኤል ልጆች ሁሉ አመጡት ። ዘፀ፡ ፴፭ ፫ ፤ ፩ ፳ ።
ምን እንደሚያደርጉት የፈረዱበት የለምና በግዞት
ቤት አኖሩት ። ዘሌዋ፡ ፳ ፲፩ ።
እግዚአብሔርም ያ ሰው ፈጽሞ ይሙት ፤ ሠራዊቱም
ሁሉ በደንጊያ ይውገሩት ብሎ ለሙሴ ነገረው ።
ሠራዊቱም ሁሉ ከከተማው ውጭ አውጥተው እግዚ
አብሔር ለሙሴ እንዳለው በደንጊያ ወግረው ገደሉት ።
እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላ
ቸው ብሎ ነገረው ፤ ባለ ዘመናቸው በልብሶቻቸው ጫፍ
ምልክት ያደርጉ ዘንድ በዘሩም የተፈተለ ሰማያዊ ሐር
ያደርጉ ዘንድ አድርጉ በላቸው ። ዘሌዋ፡ ፬ ፳፩ - ፳፫ ።
በዘሩም ምልክት ይሁናችሁ እሱንም አይታችሁ የእ
ግዚአብሔርን ትእዛዝ እያሰባችሁ አድርጓቸው ።
እናንተ እነሷቸውን በምታመልኩ ገንዘብ በዓይናችሁ
ያያችሁትን በልባችሁ ያሰባችሁትን ሁሉ አትከተሉ ።
አስባችሁም ትእዛዜን ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ለኔ ለፈጣ
ሪያችሁ የተለያችሁ ሁኑ ።
ገዥ ፈጣሪ እሆናችሁ ዘንድ ከግብጽ አገር ያወጣኋ
ችሁ እኔ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነኝ በላቸው አለው ።

ምዕራፍ ፲፮ ።

ከሌዊ የተወለደ የቀዓት ልጅ የይስዓር ልጅ ቆሬ የሮ
ቤል ልጅ ከሚሆን ከፋሌቅ ልጅ ፤ ከአውናንና ከኤልያብ
ልጆች ከአቤሮንና ከዳታን ጋራ ተናገረ ። ዘፀ፡ ፮ ፲፰ ።
ከእስራኤልም ልጆች ለምክር በተመረጡ ሠራዊት
ላይ የተሾሙ ስማቸውም የተጠራ ሁለት መቶ አምሳ ሰዎ
ች እሊህ ሁሉ ሙሴን ፊት ለፊት ተቃወሙት ።
በአሮንና በሙሴ ላይ በጠላትነት ተነሥተው ሠራዊቱ
ሁሉ ንጹሐን (ለሹመት የበቁ) ናቸውና እግዚአብሔርም
በረድኤት አድሮባቸዋልና እንግዲህስ ሹመት በቃችሁ
በእግዚአብሔርም ሠራዊት ላይ ለምን ትሾማላችሁ አሉ
ዋቸው ። መዝ፡ ፻፮ ፲፯ ። ዘኍ፡ ፲፯ ፮ ።
ሙሴም ይህን በሰማ ጊዜ በግንባሩ ወደቀ ፤ ቆሬንና
ሠራዊቱን ሁሉ እግዚአብሔር ለይቶ ወገኖቹን ይወቃቸው
ለሹመት የበቁትንም ወደሱ ይሰብስባቸው አለው ።
እናንተ እንዲህ አድርጉ የሠራዊቱ ሁሉና ቆሬ ጥና
ቶቻችሁን ያዙ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፫ - ፳፯ ።
በውስጡም እሳት አድርጋችሁ ነገ በእግዚአብሔር
ፊት በላዩ ዕጣን ጨምሩ ፤ እግዚአብሔር የመረጠውም ያ
ሰው ለሌዊ ልጆች የተለየ (ቡም) ይሁናቸው አለው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎ ሙሴ ለቆሬ ስምዑኒ ደቂቀ ሌዊ ። | ፯ | ሙሴ ቆሬን የሌዊ ልጆች ስሙኝ አለው ። |
| ታስተንእስዎኑ አንትሙ ለዝንቱ ዘንረየክሙ አምላከ እስራኤል እምትዕይንቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአቅረበክሙ ኀቤሁ ከመ ትግበሩ ምግባረ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር ወትቁሙ ቅድመ ትዕይንት ወትትለአክዎ ። | ፰ | የእግዚአብሔር ማደሪያ የደብተራ ኦሪትን ሥራ ትሠሩ ዘንድ ወደሱ ያቀረባችሁን ማቅረብ በሠራዊቱም ፊት ቁማችሁ ታገለግሉት ዘንድ የእስራኤል ፈጣሪ ከእስራኤል ልጆች ሠራዊት ለይቶ የመረጣችሁን መምረጥ ታሳንሱታላችሁን፤ ። ዘኍ፡ ፲፮ ፲፫ ፤ ፩ ሳሙ፡ ፲፰ ፳፫ ። |
| ወአቅረበከ ለከ ወለአኀዊከ ደቂቀ ሌዊ ምስሌከ ወትፈቅዱ ትኩኑ ካህናተ ። | ፱ | አንተን ያቀረበህን ወንድሞችህ የሌዊ ልጆችንም ካንተ ጋር ያቀረባቸውን ማቅረብ አሳነሳችሁትን (እንደ አሮን) ካህናት ልትሆኑ ትወዳላችሁን፤ ። |
| ወበእንተ ዝንቱ አንተኒ ወኵሉ ትዕይንትከ እንተ አንገለገት ላዕለ እግዚአብሔር ወአሮን፣ ምንት ውእቱ ከመ ታንጐርጕሩ ላዕሌሁ ። | ፲ | ስለዚህ በእግዚአብሔርና በአሮን ላይ የዶለተች ሠራዊትህ ሁሉና አንተም በሱ ላይ የምታንጐረጕሩት እንጐንጕሮ ምንድር ነው ። |
| ወለአከ ሙሴ ይጸውዕዎሙ ለዳታን ወለአቤሮን ደቂቀ ኤልያብ ወይቤሉ ኢንመጽእ ። | ፲፩ | ሙሴ የኤልያብን ልጆች አቤሮንና ዳታንን ይጠሩዋቸው ዘንድ ላከ፤ ነገር ግን አንመጣም አሉ ። |
| ታስተንእስኑ ዘንተ ዘአግባእከነ ውስተ ምድር እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ዘቀተልከነ ውስተ ገዳም ከመ ትትመልአክ ላዕሌነ ። | ፲፪ | በምድረ በዳ ያጠፋኸን አንተ በኛ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ ተድላ ደስታ ወደሚገኝበት አገር ያገባኸንን ማግባት ታሳንሰዋለንህ፤ ። ዘፀ፡ ፪ ፲፬ ፣ ዘኍ፡ ፲፱ ፱ ። |
| መልአክኑ አንተኒ ከዐበ ውስተ ምድርኑ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ አበእከነ ዘንተ ዘወሀብከነ መክፈልተ ውስተ ገዳም፣ ወአዕየደ ወይነ አዕይንቲሆሙ ለእሉ እደውታውጽእኑ ኢንመጽእ ። | ፲፫ | ዳግመኛ ተድላ ደስታን በምታስገኝ አገር አንተ አለቃ ነህን፣ በምድረ በዳ ይህንን ርስታችንን የወይኑንም ቦታ የሰጠኸን አንተ አገባኸን እክ! የነዚህን ሰዎች ዓይኖቻቸውን ታወጣለህን፤ አንመጣም አሉት ። ፩ ነገ፡ ፲፪ ፳፩ ። |
| ወአክበደ ሙሴ ተክዞ ጥቀ ወይቤሎ ለእግዚአብሔር ኢትነጽር መሥዋዕቶሙ አልቦ ዘነሣእኩ ወኢዘአሐዱ እምኔሆሙ ፈቲውየ፣ ወአልቦ ዘአኅሠምኩ ወኢላዕለ አሐዱ እምኔሆሙ ። | ፲፬ | ሙሴም ይህን በሰማ ጊዜ ፈጽሞ አዘነ፣ እግዚአብሔርንም መሥዋዕታቸውን (በዓይነ ምሕረት) አትመልከት፣ ከነሳቸው የአንዱን ወድ፟ጂ የተቀበልኩት የለም፣ ከነሳቸውም በአንዱ ላይ ክፉ ነገር ያደረግሁት የለም፣ አለው ። |
| ወይቤሎ ሙሴ ለቆሬ፣ ቀድስ ትዕይንተከ ወኩኑ ድልዋነ ቅድመ እግዚአብሔር አንተ ወእሙንቱ ወአሮን ለጌሠም ። | ፲፭ | ሙሴ ቆሬን ሠራዊትህን ለይ አንተም እነሱም በእግዚአብሔር ፊት የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ አሮንም ለነገ የተዘጋጀ ይሁን ። ዘፀ፡ ፲፮ ፱ ። |
| ወይንሣእ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶ ወይደይ ዕጣነ ወያብእ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፲፮ | አንዱም አንዱም ሰው ጥናውን ይዞ፣ ዕጣኑን ይጨምር፣ አንዱም አንዱም ማጠኛውን በእግዚአብሔር ፊት ያግባ አለው ። ዘኍ፡ ፲፮ ፯ ። |
| ወነሥአ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶ ወወደዩ ውስቴቱ እሳተ ወወደዩ ውስቴቱ ዕጣነ፣ ወቆሙ ሙሴ ወአሮን ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፲፯ | አንዱም አንዱም ጥናውን ያዘ በውስጡም እሳት አደረጉ፣ ዕጣኑንም ጨመሩ አሮንና ሙሴም በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ቆሙ ። |
| ወሮዶሙ ቆሬ ምስለ ኵሉ ትዕይንቱ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወአስተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር ለኵሉ ትዕይንት ። | ፲፰ | ቆሬም ከሠራዊቱ ሁሉ ጋራ በድንኳኑ ደጃፍ ከበባቸው፣ የእግዚአብሔርም ብርሃን ለሠራዊቱ ሁሉ ታየ ። |
| ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ፣ ተገኀሡ እማእከሎሙ ለእሉ ትዕይንት ወአጠፍኦሙ በምዕር ። | ፲፱ | እግዚአብሔር አንድ ጊዜ አጠፋቸዋለሁና ከነዚህ ሠራዊት መካከል ተለዩ፣ ብሎ ለአሮንና ለሙሴ ነገራቸው ። |
| ወወድቁ በገጾሙ ወይቤሉ፣ እግዚኦ አምላኩ ለኵሉ ዘሥጋ ወለኵሉ ዘነፍስ፣ ለእመ አሐዱ ብእሲ አበሰ ዲበ ኵሉ ትዕይንት ይከውን መዓተ እግዚአብሔር ። | ፳ | የሥጋዊ የደማዊ ፈጣሪ አቤቱ አንድ ሰው ቢበድል የእግዚአብሔር ቁጣ በሠራዊቱ ሁሉ ላይ ይሆናልን ብለው በግንባራቸው ወደቁ ። ዘኍ፡ ፲፬ ፲፭ - ፳፯ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ ንግሮሙ ለትዕይንት ይትገኀሡ እምበውደ ትዕይንተ ቆሬ ። | ፳፩ | እግዚአብሔርም ከቆሬ ሰፈር አደባባይ ይርቁ ዘንድ ለሠራዊቱ ንገራቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው ። |
| ወተንሥአ ሙሴ ወሖረ ኀበ ዳታን ወአቤሮን፣ ወሖሩ ምስሌሁ ኵሎሙ አእሩገ እስራኤል ። | ፳፪ | ሙሴም ተነሥቶ ወደ ዳታንና ወደ አቤሮን ሄደ፣ የእስራኤልም ሽማግሎች ከሱ ጋራ ሄዱ ። |
| ወነገሮሙ ለትዕይንት ወይቤሎሙ ተገኀሡ እምዓውደ ተዓይኒሆሙ ለእሉ ሰብእ እኩያን፣ ወኢትግሥሡ እም | ፳፫ | በኃጢአታቸው ሁሉ እንዳትጠፉ ከነዚህ ከክፉዎች ሰዎች አደባባይ ራቁ፣ ከነሱም ገንዘብ ሁሉ አትንኩ ብሎ |

| | | |
|---|---|---|
| ኵሉ ዘዚአሆሙ ከመ ኢትትኀጕሉ በኵሉ ኃጣውኢሆሙ። | | ለሠራዊቱ ነገራቸው። ዘፍ፡ ፲፱ ፲፪፡ ፪ ቆሮ፡ ፮ ፲፯። |
| ወተግኅሡ እምዐውደ ትዕይንተ ቆሬ ወወፅኡ ዳታን ወአቤሮን ወቆሙ ኅበ ሆኅተ ደብተራሆሙ፡ ወአንስትያሆሙኒ ወደቂቆሙኒ ወንዋዮሙኒ። | ፳፬ | እነሱም ከቆሬ ሰፈር ዙርያ ሁሉ ራቁ፡ አቤሮንና ዳታንም ከልጆቻቸው ከሚስቶቻቸውና ከንዛቸው ጋራ ወጥተው በድንኳኖቻቸው ደጃፍ ቆሙ። |
| ወይቤ ሙሴ፡ በዝንቱ ተአምሩ ከመ እግዚአብሔር ፈነወኒ ከመ እግበር ዘንተ ኵሎ ግብረ ከመ አኮ እምልብየ። | ፳፭ | ሙሴም ይህን ሁሉ ሥራ እሠራ ዘንድ እግዚአብሔር እንደላከኝ ይህን የደረግሁ ከልቤ አንቅቼ እንዳይደለ በዚህ ታውቃላችሁ አለ። ዘኍ፡ ፳፬ ፳፫። |
| ወእመ ኢይመውቱ ከመ ሞተ ሰብእ፡ ወከመ ኢኮነ መቅሠፍቶሙ ከመ መቅሠፍተ ሰብእ ለእሉ፡ አኮ እግዚአብሔር ፈነወኒ ከመ እግበር፡ እንበለ በተርኅወተ ምድር ዘያርኢ እግዚአብሔር። | ፳፮ | እግዚአብሔር በሚያሳየው ተአምራት ምድር ተከፍታ ትውጣቸዋለች እንጂ እንደሰው ሞት እንዳይሞቱ የነዚህም መቅሠፍት እንደሰው መቅሠፍት እንዳይደለ እግዚአብሔር ልኮኛልና። ዘፀ፡ ፳፭ ፳፫ - ፴፩። |
| ወታብቁ ምድር አፉሃ ወትውኅጦሙ ሎሙ ወለአብያቲሆሙ ወለደብተራሆሙኒ ወለኵሉ ዘዚአሆሙ። | ፳፯ | እነሳቸውን ወገኖቻቸውን ድንኳኖቻቸውንና ገንዘባቸውን ሁሉ ምድር ተከፍታ ትውጣቸዋለች። |
| ወይወርዱ ሕያዋኒሆሙ ውስተሲኦል፡ ወየአምሩ ከመ አምዐዕዎ እሉ ሰብእ ለእግዚአብሔር። | ፳፰ | አለን አለን ሲሉም ወደ መቃብር ይወርዳሉ፡ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር እንዳሳዘኑት ያውቃሉ አላቸው። |
| ወሶበ አኅለቀ ተናግሮ ዘንተ ኵሎ ነገረ ተሠጥቀት ምድር በታሕተ እገሪሆሙ። | ፳፱ | ይህንን ነገር ሁሉ ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ የቆሙበት ምድር ተሰነጠቀች (ተከፈተች)። ዘኍ፡ ፳፯ ፲። |
| ወተርኅወት ምድር ወውኅጠቶሙ ሎሙ ወለአብያቲሆሙ ወለኵሉ ሰብእ እለ ሀለዉ ምስሌሆሙ ወለቆሬሂ ወለአንስትያሆሙሂ። | ፴ | ምድር ተከፍታ እነሳቸውንና ወገኖቻቸውን ከነሳቸው ጋር ያሉትም ሰዎች ሁሉ ቆሬንም ሚስቶቻቸውን ዋጠቻቸው። ዘኍ፡ ፲፯ ፲፯፡ ፳፯ - ፲፩፡ ፩ ነገ፡ ፯ ፳፱። |
| ወወረዱ እሙንቱ ወኵሉ ዘዚአሆሙ ሕያዋኒሆሙ ውስተ ሲኦል፡ ወከደነቶሙ ምድር ወተኀጕሉ እማእከለ ትዕይንት። | ፴፩ | እነሳቸው ከወገኖቻቸው ሁሉ ጋራ አለን አለን ሲሉ ወደ መቃብር ወረዱ፡ ምድር ደፈነቻቸው ከሠራዊቱም መካከል ተለይተው ጠፉ። |
| ወኵሉ ትዕይንተ እስራኤል እለ ዐውዶሙ ጐዩ እምቃሎሙ እንዘ ይብሉ ከመ ኢትኅጠነ ለነሂ ምድር። | ፴፪ | በዙርያቸው ያሉ የእስራኤል ወገኖች ሁሉ ከጩኸታቸው የተነሣ እኛንም ምድር እንዳትውጠን ብለው ሸሹ። |
| ወወፅአት እሳት እምኀበ እግዚአብሔር ወበልዐቶሙ ለእልክቱ ክልኤቱ ምእት ወኃምሳ እደው እለ አብኡ ዕጣነ። | ፴፫ | ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት ወጥታ ሊያጥኑ የገቡትን እሊያን ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች በላቻቸው። |
| ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአልአዛር ወልደ አሮን ካህን አሰስሉ ማዕጠንቃተ ዘብርት እማእከሎሙ ለእለ ውዕዩ። | ፴፬ | እግዚአብሔር የካህኑ የአሮን ልጅ አልአዛርና ሙሴን ከተቃጠሉት ሰዎች መካከል የናስ ጥናዎችን አውጡ። |
| ወዘንተ እሳተ ዘአምበዕድ ዝርዉ ከሓ እስመ ተቀደሱ ማዕጠንቃቲሆሙ ለእሉ ኃጥአን በነፍሶሙ። | ፴፭ | ከጉረቤት ያመጡትንም [illegible] እሳት ወድያ በትኑት፡ የነዚህ ኃጢአተኞች ጥናዎቻቸው በሰውነታቸው ጥፋት ከብረዋልና። ዘኍ፡ ፫ ፴፪፡ ፬ ፲፯ ፲፱ ፫። |
| ወግበሮሙ ሰሌዳተ ዘዝብጦ ወይኩኑ ለምግባረ ምሥዋዕ እስመ ቦኡ ቅድመ እግዚአብሔር ወተቀደሱ ወኮኑ ተአምረ ለደቂቀ እስራኤል። | ፴፮ | ተመትተው የተሠሩ መጫፊያዎች አድርጋቸው ወደ እግዚአብሔር ገብተው ከብረዋልና ለመሠውያው መሥሪያ ይሁኑ ለእስራኤልም ልጆች ምልክት ይሁኑ አላቸው። |
| ወነሥአ አልአዛር ወልደ አሮን ካህን እሉንተ ማዕጠንቃተ ዘብርት ኵሎ ዘአብኡ እለ ውዕዩ ወረሰዮሙ ለምግባረ ምሥዋዕ። | ፴፯ | የአሮን ልጅ አልአዛርም እሊያ የተቃጠሉት ሰዎች ያገቧቸው እነዚያን የናስ ጥናዎች ሁሉ ለመሠውያው ሥራ አደረጋቸው። ዘፍ፡ ፩ ፯፡ ዘፀ፡ ፴፱ ፫። |
| ተዘከረ ለደቂቀ እስራኤል ከመ አልበ ዘይበውእ እምባዕድ ዘመድ ዘኢኮነ እምዘርአ አሮን ከመ ይደይ ዕጣነ ቅድመ እግዚአብሔር፡ ወከመ ኢይኩኑ ከመ ቆሬ ወከመ ተቃውሞቱ በከመ ነበበ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ። | ፴፰ | ከአሮን ልጆች ወገን ያልተወለደ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሊያጥን የሚገባ እንዳይኖር እንደ ቆሬም እንደ ክርክሩም እንዳይሆን ለእስራኤል ልጆች መታሰቢያ ሊሆኑ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል እንደተናገረ ለመሠውያው አደረጋቸው። ዘኍ፡ ፫ ፲፡ ፪ ነገ፡ ፳፮ ፲፰። |
| ወበሣኒታ አንጐርጐሩ ደቂቀ እስራኤል ዲበ ሙሴ ወዲበ አሮን፡ ወይቤልዎሙ አንትሙ ቀተልክምዎሙ ለሕዝበ እግዚአብሔር። | ፴፱ | (የቆሬ ልጆች በሞቱ) በማግሥቱም የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔርን ወገኖች እናንተ ገደላችኋቸው ብለው በአሮንና በሙሴ ላይ አንጐራጐሩ። |
| ወከነ ሶበ ተጋብኡ ትዕይንት ላዕለ ሙሴ ወአሮን ወሮድዎሙ ኀበ ሆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፡ ወበጊዜሃ ከደና | ፵ | ሠራዊቱም በአሮንና በሙሴ ላይ ተሰብስበው በደብተራ አሪት ደጃፍ በከበቡዋቸው ጊዜ እንዲህ ሆነ በዚያን |

ደመና ወአስተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር ።

ጊዜ ደመና ድንኳኒቱን ጋረዳት የእግዚአብሔርም ብርሃን ታየ ። ዘፀ፡ ፵ ፴፬ ፣ ዘኁ፡ ፲፮ ፲፱ ፣ ፲፬-፲ ።

፵፩ ወበእ ሙሴ ወአሮን እንተ ኀበ ገጸ ደብተራ ዘመርጡል ።

ሙሴና አሮንም ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ገቡ ።

፵፪ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ፤ ተገኀሡ እማእከላ ለዛቲ ትዕይንት ወአጠፍኦሙ በምዕር ወወድቁ በገጾሙ ሙሴ ወአሮን ።

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን ከዚያች ሰፈር መካከል ወግዱ (ተለዩ) አንድ ጊዜ አጠፋቸዋለሁ ብሎ ለአሮንና ለሙሴ ነገራቸው ፤ ሙሴና አሮንም በግንባራቸው ወደቁ ። ዘኁ፡ ፲፮ ፳፩-፳፬ ።

፵፫ ወይቤሎ ሙሴ ለአሮን ንሣእ ማዕጠንተ ወደይ ውስቴቱ እሳተ እምሥዋዕ ፣ ወደይ ላዕሌሁ ዕጣነ ወሰድ ፍጡነ ውስተ ትዕይንት ፤ ወአስተሥሪ በእንቲአሆሙ ፣ እስመ ወድአ ወፅአ መንሱት እምቅድመ እግዚአብሔር ወአኀዘ ያጥፍኦሙ ለሕዝብ ።

ሙሴም አሮንን ጥናውን ይዘህ ከመሠውያው እሳት አምጥተህ በውስጡ አድርግ በላዩም ዕጣን ጨምረህ ፈጥነህ ወደ ሠፈሩ ውሰድ ፤ መቅሠፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈጽሞ መጥቷልና ሕዝቡንም ሊያጠፋቸው ጀምሯልና ስለነሱ አማልድ (አጥነህ አስተሥርይላቸው) ።

፵፬ ወነሥአ አሮን በከመ ይቤሎ ሙሴ ወሮጸ ፍጡነ ውስተ ትዕይንት ፣ ወበጽሐ ወበአ ብድብድ ውስተ ሕዝብ ፣ ወወደየ አሮን ዕጣነ ውስተ ማዕጠንት ወአስተሥረየ በእንተ ሕዝብ ።

አሮንም ሙሴ እንደ ተናገረው ጥናውን ይዞ ፈጥኖ ወደ ሰፈር ሄዶ ደረሰ ፣ ቸነፈሩም ወደ ሕዝቡ ገባ ፣ አሮንም በጥናው ውስጥ ዕጣን ጨምሮ ስለ ሕዝቡ አማለደ ።

፵፭ ወቆመ ማእከለ ምዉታን ፣ ወማእከለ ሕያዋን ወኀደገ ብድብድ ።

በሞቱትና በሕያዋኑ መካከል ቆመ ፣ ቸነፈሩም ጸጥ አለ (ቲወ) ። ዘኁ፡ ፲፮ ፳፩ ።

፵፮ ወኮኑ እለ ሞቱ በብድብድ እልፍ ወአርባዕ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ፣ ዘእንበለ እለ ሞቱ ምስለ ቆሬ ።

ከቆሬ ጋር ከሞቱት ሰዎች በቀር ፤ በቸነፈሩ የሞቱት እልፍ አራት ሺሕ ከሰባት መቶ ሆኑ ።

፵፯ ወገብአ አሮን ኀበ ሙሴ ወኀበ ደብተራ ዘመርጡል ።

አሮንም ወደ ሙሴና ወደ ደብተራ ኦሪት ተመለሰ ፣ ቸነፈሩም ጸጥ አለ (ተከለከለ) ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወንሣእ በኀቤሆሙ በትረ ለለአብያተ አበዊሆሙ እምኀበ ኵሉ መላእክቲሆሙ ዘዘአብያተ አበዊሆሙ ዐሠርተ ወክልኤተ አብትረ ወለለአሐዱ ጸሐፍ ስሞ ውስተ በትሩ ።

እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው ብሎ ነገረው ፣ በነሳቸው ዘንድ ያለ የየአባቶቻቸውን በትር አምጣ ፤ ከየአባቶቻቸው አለቆች ሁሉ አሥራ ሁለቱን በትሮች ተቀብለህ የያንዳንዱም ስሙን በበትሩ ላይ ጻፍ ።

፪ ወጸሐፍ ስሞ ለአሮን ውስተ በትረ ሌዊ እስመ ለለሕዝበ ቤተ አበዊሆሙ አሐተ በትረ ይሁቡ ።

በየአባቶቻቸው ወገን አንድ አንድ በትር ይሰጣሉና ፣ የአሮንንም ስም በሌዊ በትር ላይ ጻፍ ።

፫ ወታነብሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ ታቦት በዘበቱ እስተርአ ለከ በህየ ።

በዚያ በምገለጽልህ በታቦቱ ፊት ለፊት በደብተራ ኦሪት ውስጥ አኑራቸው ።

፬ ወለዝክቱ ብእሲ ዘአነ ኀረይክዎ ትሠርጽ በትሩ ወአሴስል እምኔክ ነጐርጓሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘያንጐረጕሩ እሙንቱ በላዕሌክሙ ።

እኔ የመረጥሁት የዚያ ሰው በትር ትለመልማለች ፤ እነሳቸው በናንተ ላይ የሚያንጐራጕሩትን የእስራኤል ልጆች ሁሉ እንጕርጕሮ ካንተ አርቃለሁ አለው ።

፭ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ወወሀብዎ ኵሎሙ መላእክቲሆሙ በትረ ለለአሐዱ መልአክ ።

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው አለቆቻቸውም ሁሉ እያንዳንዱ አለቃ በትርን ሰጡት ።

፮ ወለለመልአክ በትር ዘዘአብያተ አበዊሆሙ ዐሠርቱ ወክልኤቱ አብትር ወበትረ አሮንሂ ማእከለ አብትሪሆሙ ።

በየአባቶቻቸው ወገኖች የተሾሙ ያንዱም ያንዱም አለቃ በትር አሥራ ሁለት ናቸው ፣ የአሮንም በትር በበትሮቻቸው መካከል ነበረች ።

፯ ወአንበሮን ሙሴ ለውእቶን አብትር ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ።

ሙሴም እነዚያን በትሮች በእግዚአብሔር ፊት በደብተራ ኦሪት አኖራቸው ። ዘኁ፡ ፲፯ ፳ ።

፰ ወኮነ በሳኒታ በአ ሙሴ ወአሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወናሁ ሠረፀት በትረ አሮን እንተ ቤተ ሌዊ ወአውፅአት ቈጽለ ወጸገየት ጽጌ ወፈረየት ከርካዐ ።

በማግሥቱም እንዲህ ሆነ አሮንና ሙሴ ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ ፣ እነሆም ከሌዊ ወገን የተወለደ የአሮን በትር ለምልማ ተገኘች ቅጠልንም አወጣች ፤ አበባም ለውዝ ገውዝ አፈራች ።

፱ ወአውፅአን ሙሴ ለኵሎን አብትሪሆሙ እምቅድመ

ሙሴም በትሮቻቸውን ሁሉ ከእግዚአብሔር ፊት ወደ

እግዚአብሔር ኀበ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ወርእዩ ፡ ወነሥአ አሐዱ አሐዱ በትሮ ።

፲ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ አንብር በትሮ ለአሮን ቅድመ መርጡል ከመ ትትዐቀብ ለትእምርት ለደቂቆሙ ለእለ አልበሙ ትእምርት ወምስማዐት ወይትኀደግ ነጐርጓሮሙ እምላዕሌየ ከመ ኢይሙቱ ።

፲፩ ወገብሩ ሙሴ ወአሮን ኵሎ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

፲፪ ወይቤልዎ ደቂቀ እስራኤል ለሙሴ ፡ ናሁ ተወዳእነ ወንትኀጐል እንዘ ንኀልቅ ።

፲፫ እስመ ኵሉ ዘገሠሠ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር ይመውት ለተገምሮትኑ እስከ ንመውት ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለአሮን ወይቤሎ ፡ አንተ ወደቂቅከ ወቤተ አቡከ ምስሌከ ትነሥኡ ኀጣይአ ክህነትክሙ ።

፪ ወአኀዊከኒ ደቂቀ ሌዊ ሕዝበ አቡከ አስተጋብእ ኀቤከ ወይትወሰኩ ለከ ወይትለአኩከ ወአንተ ወደቂቅከ ምስሌከ ላዕለ ደብተራ ዘመርጡል ።

፫ ወይዕቀቡ ሕገከ ወሕጋ ለደብተራ ባሕቱ ኀበ ንዋይ ዘቅድሳት ወኀበ ምሥዋዕ ኢይባኡ ወኢይሙቱ እሙንቱኒ ወአንትሙኒ ።

፬ ወይትወሰኩ ኀቤከ ወይዕቀቡ ሕጋ ለደብተራ ዘመርጡል በኵሉ ግብራ ወዘእምነ ባዕድ ኢይባእ ኀቤከ ።

፭ ወተዐቀቡ ሕገ መቅደስ ወሕገ ምሥዋዕ ፡ ኢይምጻእ እንከ መንሱት ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ።

፮ ወአነ ነሣእክምሙ ለአኀዊከ ሌዋውያን እማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ሀብተ ተውህቡ ለእግዚአብሔር ከመ ይግበሩ ግብራ ለደብተራ መርጡል ።

፯ ወአንተ ወደቂቅከ ምስሌከ ዕቀቡ ክህነተክሙ በከመ ኵሉ ሕጉ ለምሥዋዕ ወዘውሥጥ እምነ መንጦላዕት ፡ ወግበሩ ግብረ ሀብታ ለክህነትክሙ ወዘእምባዕድ ዘመድ ዘቦአ ለይሙት ።

፰ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአሮን ፡ ናሁ አነሂ ወሀብኩክሙ ትዕቀቡ ዘያቀድሙ አብእ ሊተ እምኵሉ ዘይትቄደሱ እምደቂቀ እስራኤል ፡ ለከ ወሀብኩከ እስከ ትረስዖ ወእምድኅሬከ ለደቂቅከ ሕግ ዘለዓለም ።

፱ ወዝንቱ ይኩንክሙ ለክሙ እምዘይትቄደስ ለቅዱሳን ወእምዘምሥዋዕ እምኵሉ ቍርባኖሙ ወእምኵሉ መሥዋዕቶሙ ወእምኵሉ ዘንስሐሆሙ ፡ ወእምኵሉ ዘኀጣይኢሆሙ ፡ ኵሉ ዘያመጽኡ ሊተ እምኵሉ ዘቅዱሳን ለከ ወለደቂቅከ ውእቱ ።

፲ በቅዱሰ ቅዱሳን ብልዕዎ ወኵሉ ተባዕት ለይብልዖ እስመ ቅዱስ ውእቱ ለከ ።

እስራኤል ልጆች ሁሉ አወጣቸው ፡ አይተውም አንዱም አንዱም በትሩን አነሣ ።

ምስክርና ምልክት ለሌላቸው ለልጆቻቸው ትጠበቅ ዘንድ የአሮንን በትር ወደ ደብተራ ኦሪት ውስጥ አኑር ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ፡ እንዳይሞቱም (እንዳይቀሠፉ) አንጐርጕርአቸው ከኔ ይቀራል ። ዘኍ ፲፯ ፮ ።

ሙሴና አሮንም እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ ።

የእስራኤል ልጆች ሙሴን እነሆ አለቅን ጥቂት ጥቂት እያልን እንጠፋለን ።

የእግዚአብሔርን ድንኳን የነካ ሰው ሁሉ ይሞታልና ዝም ማለትህ ጥቂት ጥቂት እያልን እስክንፈጸም ድረስ ነውን፣ አሉት ። ዘፀ ፳፱ ፳፱ ፡ ፵ ፲፫ ።

## ምዕራፍ ፲፰ ።

አንተና ልጆችህ ካንተም ጋር ያሉ የአባትህ ወገኖች የክህነታችሁን ኃጢአት ፍዳ ትቀበላላችሁ ብሎ እግዚአብሔር ለአሮን ነገረው ። ዘኍ ፲፮ ፴፰ ፡ ፲፰ ፲፩ ።

ያባትህ ወገኖች የሚሆኑ የሌዊ ልጆች ወንድሞችህንም ወዳንተ ሰብስብ ፡ ተጨምረውም ያገለግሉሃል አንተና ካንተ ጋር ያሉ ልጆችህም ልዩ በሆነች ድንኳን አገልግሉ ። ዘኍ ፲፰ ፩ ፡ ፫ ፮ - ፲ ።

ያንተን ሕግና የደብተራ ኦሪትን ሥራት ይጠብቁ ፡ ነገር ግን እነሳቸውና እናንተም እንዳትቀሠፉ ወደ ንዋየ ቅድሳቱና ወደ መሠውያው አትግቡ ።

ካንተ ጋራ ተጨምረው በሥራዋ ሁሉ የደብተራ ኦሪት ሕጓን ይጠብቁ ከሌላ ወገን የተወለደ ሰው ግን ወዳንተ አይግባ ። ዘኍ ፲፮ ፲፫ ።

እንግዲህ በእስራኤል ልጆች ላይ ጥፋት እንዳይመጣ የመሠውያውንና የቤተ መቅደሱን ሥርዓት ጠብቁ ።

የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ለእግዚአብሔር ፈንታ ተሰጥተዋልና ወንድሞችህ ሌዋውያንን ከእስራኤል ልጆች ለይቼ እኔ ተቀበልኋቸው ። ዘኍ ፱ ፫ ።

ካንተ ጋር ያሉ ልጆችህና አንተም እንደ መጋረጃ ውስጥ ሥርዓትና እንደ መሠውያው ሥርዓት ክህነታችሁን ጠብቁ ፡ የክህነታችሁ የሃብቷን ሥራ ሥሩ ፡ ከሌላ ተወልዶ የገባ ሰው ግን ይሙት አለው ። ዘኍ ፫ ፲ ።

እግዚአብሔር አሮንን እንዲህ አለው ፡ አስቀድመው ለኔ የሚያገቡትን ትጠብቁ ዘንድ እነሆ እኔ ሰጠኋችሁ ፡ ከእስራኤል ልጆች የሚለዩትን ሁሉ ለዘለዓለም ሥርዓት ይሆን ዘንድ እስክታረጅ ድረስ ላንተ ሰጠሁህ ካንተም በኋላ ለልጆችህ ሰጠኋቸው ። ዘፀ ፵ ፲፫ ፡ ዘሌ ፯ ፴፫ ።

ይህ ከሚለየው የተረፈው ለናንተ ለካህናት ይሁናችሁ በመሠውያው ካለ ቍርባናቸው ሁሉ ከመሥዋዕተ ንስሐቸውም ሁሉ ከመሥዋዕተ ኃጢአትም ሁሉ ለይተው የሚያመጡት ሁሉ ለካህናቱ ከተለየው ሁሉ ላንተና ለልጆችህ ነው ። ዘፀ ፵ ፲ ፡ ዘሌዋ ፪ ፫ ፡ ፬ ፳፪ ፡ ፯ ፳፭ ።

በቅድስተ ቅዱሳን ሁናችሁ ብሉት፣ ላንተ የተለየ ነውና ወንዱ ወንዱ ሁሉ ይብላው ። ዘሌ ፯ ፲፮ ።

፲፩ ወዝንቱ ይኩንከሙ ለከሙ እምቀዳሚ ሀብቶሙ ወእ
ምኵሉ ዘያበውኡ ደቂቀ እስራኤል ለከ ወሀብኩከ ወለደ
ቂቅከ ወለአዋልዲከኒ ምስሌከ፥ ሕግ ዘለዓለም ፥ ኵሉ ዘን
ጹሕ በውስተ ቤትከ ለይብልዖ ።

፲፪ ኵሉ ቀዳምያቲ ቅብዕ ወኵሉ ቀዳምያቲ ወይን ወዘ
ሥርናይ ወኵሎ ዘያበውኡ ለእግዚአብሔር ለከ ወሀብኩከ።

፲፫ ወኵሎ ቀዳሚ እክል ዘበኵሉ ምድሮሙ ወኵሉ ዘያ
መጽኡ ለእግዚአብሔር ለከ ወሀብኩከ፥ ኵሉ ዘንጹሕ በው
ስተ ቤትከ ይብልዖ።

፲፬ ኵሉ ዘያሐርሙ በውስተ ደቂቀ እስራኤል ለከ ውእቱ።

፲፭ ወኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እምኵሉ ዘሥጋ ወኵሉ ዘያ
መጽኡ ለእግዚአብሔር እምሰብእ እስከ እንስሳ ለከ ውእቱ
ባሕቱ በኵረ ሰብእ በቤዛ ይትቤዘው ወበኵረ እንስሳኒ ዘር
ኩስ ታቤዞ ።

፲፮ ወቤዛሁ ለዘአሐዱ ወርኅ ኀምስቱ ሰቅል በሰቅል ዘቅ
ዱስ ዕሥራ አበሊ ውእቱ ።

፲፯ ዘእንበለ በኵረ አልሕምት ወበኵረ አባግዕ ወበኵረ
አጣሊ ዘኢታቤዞ እስመ ቅዱስ ውእቱ ፥ ወትክዑ ደሞሙ
ኀበ ምሥዋዕ ወሥብሖሙ ትገብር መሥዋዕተ ለእግዚአብ
ሔር ለመዐዛ ሠናይ ።

፲፰ ወሥጋሁ ይኩንከ ለከ በከመ ተላዕ ዘያበውኡ፥ ወበ
ከመ መዝራዕት ዘየማን ይኩንከ ለከ ።

፲፱ ኵሉ መባእ ዘቅዱስ ወኵሎ ዘይፈልጡ ደቂቀ እስራ
ኤል ለእግዚአብሔር ወሀብኩከ ለከ ወለደቂቅከ ወለአዋል
ዲከ ምስሌከ፥ ሕግ ዘለዓለም ወሥርዐት ለዝሉፉ እንተ
ለዓለም ይእቲ ቅድመ እግዚአብሔር ለከ ወለዘርእከ እም
ድኅሬከ ።

፳ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአሮን፥ እምድሮሙ ኢትረስ
ወአልብከ ክፍል ምስሌሆሙ እስመ አነ ውእቱ ክፍልከ
ወርስትከ በማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፳፩ ለደቂቀ ሌዊኒ ናሁ ወሀብክዎሙ ዓሥራተ ዘደቂቀ እስ
ራኤል ክፍሎሙ ህየንተ ግብሮሙ ኵሎ ዘይገብሩ እሙ
ንቱ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ።

፳፪ ወኢይበውኡ እንከ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ደብተራ
ዘመርጡል ከመ ኢይኩኖሙ አበሳ ዘለሞት ።

፳፫ ወይግበርዎ ለዝንቱ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ሌዋ
ውያን ወእሙንቱ ይረክቡ ኀጢአቶሙ ሕግ ዘለዓለም
በመዋዕሊሆሙ፥ ወኢይወርሱ ርስተ በማእከሎሙ ለደቂቀ
እስራኤል ።

፳፬ እስመ ዓሥራቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ መባእ
ዘይፈልጡ ለእግዚአብሔር ወሀብክዎሙ ለሌዋውያን ክፍ
ሎሙ፥ ወበበይነ ዝንቱ እቤሎሙ ኢትወርሱ ርስተ በማ
እከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

ይህ ሥርዓት ለናንተ ይሁናችሁ የእስራኤል ልጆች
የሚያገቡትን ሁሉና የመጀመሪያ ስጦታቸውን የዘለዓለም
ሥርዓት ሊሆን ላንተ ሰጠሁህ ከንተም ጋር ላሉ ለሴቶችና
ለወንዶች ልጆችህ ሰጠኋቸው በቤትህ ያለ ንጹሕ ሁሉ
ይብላው ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፯፥ ዘሌዋ፡ ፯ ፴፥ ፲ - ፲፩ ።

የወይኑን መጀመሪያና የዘይቱን መጀመሪያ ሁሉ የሥ
ንዴውንም መጀመሪያ ለእግዚአብሔር የሚያገቡትን
ሁሉ ላንተ ሰጠሁህ ። ዘፍ፡ ፵፭ ፲፰፥ ዘዳ፡ ፲፰ ፬ ።

በምድራቸውም ሁሉ ያለ የእኽሉን መጀመሪያ የደረ
ሰውን ለእግዚአብሔር የሚያመጡትንም ሁሉ ላንተ ሰጠ
ሁህ፥ በቤትህ ያለ ንጹሕ ሁሉ ይብላው ። ዘፀ፡ ፴፬ ፳፯ ።

በእስራኤል ልጆች ዘንድ የሚከለከለው ሁሉ ላንተ
ነው ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፳፰ ።

ከሥጋዊ ከደማዊ ወገን ለናቱ በኵር ሁኖ የሚወለ
ደው ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ ለእግዚአብ
ሔር የሚያገቡት ሁሉ ላንተ ነው ነገር ግን የበኵርን ልጅ
በገንዘብ ይበዠት ከማይበላውም ከብት በገንዘብ ታስቤ
ዠዋለህ ። ዘፀ፡ ፲፫ ፬፥ ፲፫ ፲፪ ።

አንድ ወር የሆነው ልጅ ዋጋው በቤተ መቅደስ ሚዛን
አምስት ወቄት ነው፥ ይኸውም ሃያ መሐልቅ ነው ።

ንጹሕ ነውና ከማትቤዠው ከበጎች ከላሞችና ከፍየ
ሎች መጀመሪያ ከተወለደው በቀር የማይበላውን በገንዘብ
አስበዠው፥ ደማቸውንም በመሠውያው ላይ አፍስሰው ስባ
ቸውንም ወደ ሊቀበለው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
አድርገው ። ዘሌዋ፡ ፫ ፪ - ፭፥ ዘዳግ፡ ፲፭ ፲፱ ።

ሥጋውም እንደ ፍሪምበውና እንደ ቀኝ ወርቹ ላንተ
ይሁንህ ። ዘፀ፡ ፳፱ ፳፮ - ፳፰፥ ዘሌዋ፡ ፴፭ ፴፬ ።

የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር ብለው የሚለዩት
የተቀደሰው መባ ሁሉ ለዘለዓለም ሕግ ሊሆን ላንተ ሰጠ
ሁህ ከንተም ጋር ላሉ ለሴቶችና ለወንዶች ልጆችህም ሰጠ
ኋቸው ይህችውም ላንተ ከንተም በኋላ ለልጆችህ በእግ
ዚአብሔር ፊት ለዘወትር ሥርዓት ናት አለው ።

እግዚአብሔር አሮንን በእስራኤል ልጆች መካከል ርስ
ትህና ፈንታህ እኔ ነኝና ከምድራቸው አትውረስ ከነሱ
ጋር ፈንታ የለህም ። ዘኍ፡ ፲፱ ፲፪ ።

ለሌዊ ልጆችም የደብተራ ኦሪትን ሥራ እነሱ ስለሚ
ሠሩት ሥራቸው ሁሉ ፈንታ የእስራኤል ልጆች ለይተው
የሚያመጡትን አሥራት ዕድል ፈንታ አድርጌ እነሆ ሰጠ
ኋቸው ። ዘሌዋ፡ ፳፯ ፴፥ ዘኍ፡ ፫ ፯ ።

ለሞት የሚያበቃ በደል እንዳይሆንባቸው የእስራኤል
ልጆች እንግዲህ ወደ ደብተራ ኦሪት አይግቡ ።

ሌዋውያን ይህን የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሥሩት፥
እነሳቸው ይህን ባይሠሩት ግን የኃጢአታቸውን ፍዳ ይቀ
በላሉ፥ ይኸውም በዘመናቸው የዘለዓለም ሥራት ነው፥
(ይሁን) በእስራኤልም ልጆች መካከል ርስት አይውረሱ ።

የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር መባ አድርገው
የሚለዩት አሥራት ሁሉ ለሌዋውያን ፈንታ አድርጌ ሰጥ
ቻቸዋለሁና ስለዚህ በእስራኤል ልጆች መካከል ርስት
አትውረሱ አልኋቸው ። ዘኍ፡ ፲፰ ፲፱፥ ፳፯ - ፳፱ ።

፳፮ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ ንግሮሙ ለሌዋውያን ወበሎሙ እንዘ ትብሉ ለእመ ነሣእክሙ እምደቂቀ እስራኤል ዓሥራተ ዘወሀብኩክሙ እምኀቤሆሙ ክፍለክሙ ትፈልጡ አንትሙሂ እምኔሁ መባአ ለእግዚአብሔር ዓሥራቶ ለዓሥራት ።

እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው ከእስራኤል ልጆች የሰጠኋችሁን አሥራት ከነሳቸው ብትቀበሉ እናንተም ዕድል ፈንታ አድርጌ ከሰጠኋችሁ መባ የአሥራቱን አሥራት ለእግዚአብሔር ለዩ ብለህ ለሌዋውያን ንገራቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው ።

፳፯ ወይትኋለቍ ለክሙ መባእክሙ ከመ ሥርናይ ዘእምውስተ ዐውደ እክል ወከመ መባእ ዘእምውስተ ምክያደ ወይን ።

መባችሁም በዐውድማ እንዳለ እንደ ሥንዴው መባና በአኽሉ ውድማ እንዳለ እንደ ሥንዴው መባ ይቈጠርላችኋል ። ዘኍ፣ ፲፰ ፴ ።

፳፰ ወከማሁ ፍልጡ አንትሙሂ እምኵሉ መባአ ለእግዚአብሔር እምኵሉ ዓሥራቲክሙ ዘትነሥኡ እምደቂቀ እስራኤል ወትሁቡ እምኔሁ ለአሮን ካህን መባአ ለእግዚአብሔር ።

መባውን ለእግዚአብሔር ለይተው እንዲሰጡ እናንተም እንዲሁ ከእስራኤል ልጆች ከምትቀበሉት አሥራታችሁ ሁሉ ለካህኑ ለአሮን ስጡ ።

፳፱ ወእብኡ ለእግዚአብሔር ኵሎ ዘይቀድሙ አብአ እምኔሁ ዘይትቀደስ ።

ከአሥራቱ አስቀድመው ለይተው የሚያገቡትን መባ ሁሉ ለእግዚአብሔር ስጡ ። ዘኍ፣ ፲፰ ፲፪ ፣ ፴ - ፴፪ ።

፴ ወበሎሙ ሰበ ትፈልጡ እምኔ ቀዳምያት ወይትኋለቍ ለክሙ ከመ እክል ዘእምውስተ ዐውዱ ወከመ ወይን ዘእምውስተ ምክያዱ ።

ከቀዳምያቱ ለይታችሁ በሰጣችሁ ጊዜ ከዓውድማ እንዳለ እኽልና ከመጭመቂያው እንዳለ ወይን ይቈጠርላችኋል ። ዘኍ፣ ፲፰ ፳፯ ።

፴፩ ወትበልዕዎ በኵሉ መካን አንትሙ ወአብያቲክሙ እስመ ዝንቱ ዐስብክሙ ለክሙ ውእቱ ህየንተ ግብርክሙ ዘደብተራ መርጡል ።

በደብተራ ኦሪት ስለ ምትሠሩት ሥራችሁ ፈንታ የናንተ ደመወዛችሁ ይህ ነውና፤ በቦታው ሁሉ ሁናችሁ ብሉት ። ሉቃ፣ ፲ ፯ ፣ ፩ ቆሮ፣ ፱ ፩ ።

፴፪ ወኢይከውነክሙ በእንቲአሁ ኀጢአተ እስመ ታወፅኡ እምኔሁ ቀዳምያቲሁ ወኢታርኵሱ ቅድሳቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ኢትሙቱ ።

ከሱ ቀደምያቱን ታወጣላችሁና ስለሱ ዕዳ በደል አይሆንባችሁም፣ ነገር ግን እንዳትቀሠፉ የእስራኤል ልጆች ለይተው ያመጡትን አታሳድፉ (አታስቀፉ) ።

## ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ዝንቱ ውእቱ ትእዛዙ ኵሉ ሕግ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ወይቤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ያምጽኡ ለከ እሐተ እጐልተ ቀይሕተ ንጽሕተ እንተ አልቦቲ ላዕሌሃ ነውር ወእንተ ኢተወድየ ላዕሌሃ አርዑት ።

እግዚአብሔር ያዘዘው የሕጉ ሁሉ ትእዛዝ ይህ ነው ነውር የሌለባት ያልተጠቃች ቀንበር ያልተጫነባት አንዲት ቀይ ጊደር ያመጡልህ ዘንድ አምጡ በላቸው አለ ብላችሁ ለእስራኤል ልጆች ንገሩዋቸው ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ነገራቸው ።

፪ ወትሁብ ለአልዓዛር ካህን ወይወስድዋ አፍኣ እምትዕይንት ውስተ መካን ንጹሕ ወይጠብሕዋ በቅድሜሁ ።

ለካህኑ ለአልዓዛር ስጠው ከከተማው ወደ ውጭ ወስደው በንጹሕ ቦታ በፊቱ ይረዷት ። ዘሌ፣ ፬ ፲፬ ።

፫ ወይነሥእ አልዓዛር እምደማ በአፃብዒሁ ወይነዝኃ ቅድመ ገጸ ለደብተራ መርጡል ስብዐ ።

አልዓዛርም ጣቶቹን ከደሟ ነክሮ በደብተራ ኦሪት ፊት ለፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው ። ዘሌ፣ ፯ ፲፯ ፣ ፲፯ - ፲፱ ።

፬ ወያውዕይዋ በቅድሜሁ ወማእሰኒ ወሥጋሃኒ ወደማኒ ምስለ ክዕሴሃ ያውዕዩ ።

በፊቱ ያቃጥሏት፣ ሥጋዋን ቁርበቷንና ደሟን ከሰገራ ጋር ያቃጥሉ ። ዘፀ፣ ፳፱ ፲፬ ፣ ዘሌ፣ ፩ ፲፫ ።

፭ ወይነሥእ ካህን ዕፀ አርዝ ወቈጽለ ሁስጱ ወለየ ወይወድዮ ማእከለ እሳታ ለይእቲ እጐልት ።

ካህኑም የዝግባ ዕንጨት፣ አሽክት፣ ቀይ ሐር ወስዶ በዚያች ጊደር እሳት መካከል ይጨምረው ።

፮ ወየሐፅብ አልባሲሁ ካህን ወይትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወእምድኅረ ዝንቱ ይበውእ ውስተ ትዕይንት፣ ወርኩስ ውእቱ ካህን እስከ ሠርክ ።

ካህኑ ልብሱን ይጠብ፣ ሰውነቱንም በውኃ ይታጠብ፣ ከዚህ በኋላ ወደ ከተማ ይግባ፤ ካህኑም እስከ ሠርክ (ማታ) ድረስ ርኩስ ነው ። ዘሌ፣ ፲፩ ፳፭ ፣ ፲፭ - ፭ ፣ ዘኍ፣ ፲፱ ፳ ።

፯ ወዘአውዓያ የሐፅብ አልባሲሁ በማይ ወይትሐፀብ ሥጋሁ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።

ያቃጠላትም ሰው ልብሱን በውኃ ይጠብ፣ ሰውነቱንም ይታጠብ፣ እስከ ሠርክም ድረስ ርኩስ ነው ።

፰ ወያስተጋብእ ብእሲ ንጹሕ ሐመዳ ወያነብሮ አፍአ እምትዕይንት ውስተ መካን ንጹሕ ወይከውን ዕቅበ ለትዕይንቶሙ ለደቂቀ እስራኤል፣ ለማየ መንዘኅ የዐቅብዎ እስመ ቦቱ ይነጽሑ ።

ንጹሕ ሰው አመዷን ሰብስቦ ከከተማ ውጭ አውጥቶ በንጹሕ ቦታ ያኑረው ለእስራኤል ልጆች ሠራዊት የተጠበቀ ይሁን፣ ይነጹበታልና የሚረጩበትን ውኃ ይጠብቁት።

፱ ወዝኩ ዘያስተጋብእ ሐመዳ ለይእቲ እጐልት የሐፅብ አልባሲሁ ወየሐፅብ ሥጋሁ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ

ያም የዚያች ጊደር አመድ የሚሰበስብ ሰው ልብሱን ይጠብ፣ ገላውንም ይታጠብ እስከ ማታም ርኩስ ነው፣

ወይኩኖሙ ለደቂቀ እስራኤል ወለግዩራን እለ ሀለዉ
ውስቴትክሙ ማእከሌክሙ ሕገ ዘለዓለም ።
፲ ወዘገሠሠ በድነ ዘኵሉ ነፍስ ሰብእ ርኩስ ውእቱ ሰቡ
ዐ መዋዕለ ።
፲፩ ወከመዝ ያነጽሕ ርእሶ በሣልስት ዕለት ወበሳብዕት
ዕለት ወይከውን ንጹሐ ፤ ወለእመሰ ኢያንጽሐ ርእሶ በሣ
ልስት ዕለት ወበሳብዕትኒ ዕለት ኢይነጽሕ ።
፲፪ ኵሉ ዘገሠሠ በድነ ዘኵሉ ነፍስ እንለ እመሕያው
ዘሞተ ወኢያንጽሐ ርእሶ ወአርኰሰ ደብተራሁ ለእግዚአብ
ሔር ለይትቀጥቀጥ ውእቱ ብእሲ እምእስራኤል ፤ እስመ
ኢተነዝኀ ላዕሌሁ ማየ መንዝኅ ርኩስ ውእቱ ወዓዲሁ
ርኵሱ ሀለወ ላዕሌሁ ።
፲፫ ወከመዝ ውእቱ ሕጉ ለሰብእ ለእመበ ዘሞተ በውስተ
ቤት ፤ ኵሉ ዘበአ ውስተ ውእቱ ቤት ወኵሉ ዘሀለወ ውስተ
ውእቱ ቤት ርኩስ ውእቱ ሰቡዐ መዋዕለ ።
፲፬ ወኵሉ ንዋይ ዘክሡት ወዘኢከነ እሱረ በማእሰር ፤
ርኩስ ውእቱ ።
፲፭ ወኵሉ ዘገሠሠ በውስተ ምድር እመኒ ቅቱለ ወእመኒ
በድነ እው ዐፅመ ሰብእ እው መቃብረ ፤ ርኩስ ውእቱ
ሰቡዐ መዋዕለ ።

፲፮ ወያመጽኡ ሎቱ ለዝክቱ ርኩስ እምሐመዳ ለእንቃክቲ
እንተ አውዐዩ ለአንጽሖ ወይሰውጡ ውስቴቱ ማየ ጥዑመ
በውስተ ግምዔ ።
፲፯ ወያመጽኡ ቈጽለ ሁስጱ ወይጠምዖ ብእሲ ንጹሕ ው
ስተ ውእቱ ማይ ወይነዝኃ ላዕለ ውእቱ ቤት ወላዕለ ንዋይ
ወላዕለ ኵሉ ነፍስ ዘሀለወ ህየ ወዲበ ኵሉ ዘገሠሠ ዐፅመ
ሰብእ እመኒ ቅቱለ ወእመኒ በድነ ወእመኒ መቃብረ ።

፲፰ ወይነዝኅዎ ንጹሕ ለርኩስ በሣልስት ዕለት ወበሳብዕት
ዕለት ወይነጽሕ በሳብዕት ዕለት ወየሐፅብ አልባሲሁ ወይ
ትሐፀብ ሥጋሁ በማይ ወርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፲፱ ወብእሲ ርኩስ ዘኢያንጽሐ ርእሶ ለይሠሮ እምሕዝቡ
ወእማእከለ ትዕይንት እስመ አርኰሰ ቅድሳቲሁ ለእግዚአ
ብሔር ፤ እስመ ማየ መንዝኅ ኢተነዝኀ ላዕሌሁ ርኩስ ው
እቱ ወይኩንክሙ ሕገ ዘለዓለም ።

፳ ወዘይነዝኅ ማየ መንዝኅ የሐፅብ አልባሲሁ ፤ ወዘገሠሦ
ለማየ መንዝኅ ርኩስ ውእቱ እስከ ሠርክ ።
፳፩ ወኵሉ ዘገሠሦ ለርኩስ ይረክስ ወነፍስ እንተ ገሠሠቶ
ርኵሰት ይእቲ እስከ ሠርክ ።

ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወኵሉ ተዓይኒሆሙ እምገ
ዳም ዘፂን በቀዳሚ ወርኅ ፤ ወበጽሑ ውስተ ቃዴስ ወበ
ህየ ሞተት ማርያም ወተቀብረት ።
፪ ወእልቦቱ ማይ ለትዕይንት ወተጋብኡ ሕዝብ ላዕለ
ሙሴ ወላዕለ አሮን ።

በመካከላችሁ ላሉ መጻተኞችና ለእስራኤል ልጆች ለዘለ
ዓለም ሥርዓት ይሁናቸው ።
የሰውን ሁሉ ሰውነት ሬሳ የነካ ሰው እስከ ሰባት ቀን
ድረስ ርኩስ ነው ። ዘኍ፣ ፲፱ ፲፮ ።
እንደዚህ አድርጎ በሦስተኛው ቀን በሰባተኛው ቀን
ራሱን ንጹሕ ያድርግ ፤ በሦስተኛው በሰባተኛው ቀን ራሱ
ን ንጹሕ ባያደርግ ግን ንጹሕ አይሆንም ።
የሞተውን ሰው ሬሳ የነካ ሰው ሁሉ ራሱን ንጹሕ
ካላደረገና የእግዚአብሔር ማደሪያን ቢያረክስ ያ ሰው ከእ
ስራኤል ተለይቶ በደንጊያ ተወግሮ ይሙት ፤ የሚረጩ
ትን ውኃ አልተረጨምና የረከሰም ነው ፤ ኃጢአቱም ገና
በሱ ላይ አለ ። ዘኍ፣ ፲፱ ፳፣ ፴፩ - ፲፱ ።
የሰው ሁሉ ሥርዓቱ እንደዚህ ነው በቤት ሳለ የሞተ
ሰው ቢኖር ወደዚያ ቤት የገባ ሰው ሁሉ በዚያም ቤት
ያለ ዕቃ ሁሉ ሰባት ቀን የረከሰ ነው ።
የተከፈተ ዕቃ (ማድጋ) ሁሉ በማሠሪያ ያልታሰረም
(አቍማዳ ዳውላ) ርኩስ ነው ። ዘኍ፣ ፴፩ ፳ ።
በጦር የሞተም ቢሆን ታሞ የሞተም ቢሆን ወይም
የሰው አጥንት ቢሆን ወይም መቃብር ያፈለሰ (በድን
የዳሰሰ) ቢሆን በምድር የነካ ሰው ሁሉ ሰባት ቀን የረ
ከሰ ነው ።
ለዚያም ለረከሰ ሰው ለማንጻት ከቃጠሏት ከዚያች
ጊደር አመድ ያምጡለት በማሰሮም ጥሩ ውኃ ይጨምሩ ።

አሸክትን አምጥተው ንጹሕ የሆነ ሰው በዚያ ውኃ
ውስጥ ነክሮ ያነን ቤት ይርጨው ፤ ዕቃውንም በዚያ ሰው
በሞተበት ቤት ያለው ሰውነት ላይ የሰውንም አጥንት
በዳሰሰ ሰው ሁሉ ላይ ተወግቶ የሞተው ቢሆን ታሞ
የሞተ ሰውም ቢሆን መቃብር ያፈለሰውንም የነካ ሰውን
ሁሉ ይርጭ ። ዘፀ፣ ፲፬ ፳፪ ።
ንጹሑ የረከሰውን ሰው በሦስተኛው ቀን በሰባተኛው
ቀን ይርጨው ፤ በሰባተኛው ቀን ይነጻል ፤ ልብሱን ይጠብ ፤
ሰውነቱንም በውኃ ይታጠብ እስከ ሠርክ ድረስ ርኩስ ነው ።
ርኩስ የሆነ ራሱን ያላነጻ ሰው በሦስተኛው በሰባተ
ኛው ቀን የእግዚአብሔርን ንዋየ ቅድሳት አሳድፏልና
ከሠራዊቱ ተለይቶ ይጥፋ ፤ የሚረጩትንም ውኃ አልተረ
ጨምና የረከሰ ነው ፤ ይህ የዘለዓለም ሕግ ሥራት ይሁ
ናችሁ ። ዘኍ፣ ፲፱ ፲፫ ።
ማየ መንዝኅ የሚረጨውም ልብሱን ይጠብ ፤ የሚረ
ጨውንም ውኃ የነካ ሰው እስከ ሠርክ ድረስ የረከሰ ነው ።
ርኩሱን የነካ ሰው ይረክሳል ፤ የነካችውም ሰውነት
እስከ ሠርክ የረከሰች ናት ። ሐጌ፣ ፪ ፲፫ ።

ምዕራፍ ፳ ።

የእስራኤል ልጆችና ሠራዊቶቻቸው ሁሉ በመጀመ
ሪያ ወር ጺን የሚባል ዕንጨት ካለበት ምድረ በዳ ተጉ
ዘው ወደ ቃዴስ ደረሱ ፤ ማርያምም በዚያ ሞታ ተቀበረች ።
ለሠራዊቱም ውኃ አልነበረምና ፤ ሕዝቡ በአሮንና
በሙሴ ላይ ተሰበሰቡ ። ዘፀ፣ ፲፯ ፩ ፤ ዘኍ፣ ፲፯ ፲፱ ።

## ኦሪት ዘኍልቍ ፡ ምዕራፍ ፳ ።

፫ ወጸአልዎ ለሙሴ ወይቤልዎ እምኀየሰነ ንሙት በሞተ አበዊነ በቅድመ እግዚአብሔር ።

ሙሴንም ነቀፉት ፡ በእግዚአብሔር ፊት እንደ አባቶቻችን ብንሞት በተሻለን ነበር አሉት ። ዘፀ፡ ፲፯ ፪ ።

፬ ወለምንት አውፃእክሙ ትዕይንቶ ለእግዚአብሔር ውስተ ዝንቱ ገዳም ከመ ትቅትሉነ ወለእንስሳነ በጽምእ ።

ከብቶቻችንም እኛንም በውኃ ጥም ትገድሉን ዘንድ የእግዚአብሔርን ሠራዊት ለምን ወደዚህ ምድረ በዳ አወጣችሁ ፤ ።

፭ ወለምንት ዝንቱ ዘአውፃእክሙነ እምግብጽ ከመ ታምጽኡነ ውስተ ዝንቱ መከን እኩይ ዘኢይዘራእ ወዘአልቦ በለስ ወአዕፃደ ወይን ወሮማን ወአልቦ ማይ ለሰትይ ።

ዘር ወደ ማይዘረበት ፡ በለስ ወደሌለበት የሮማንና የወይን በታ ወደሌለበት ፡ ለመጠጣትም ውኃ ወደሌለበት ወደዚህ በታ ታመጡን ዘንድ ከግብጽ ያወጣችሁን ለምንድር ነው ፤ አሉት ።

፮ ወሖሩ ሙሴ ወአሮን እምቅድመ ገጸሙ ለትዕይንት ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፡ ወወድቁ በገጾሙ ወአስተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር ሎሙ ።

ሙሴና አሮንም ከሠራዊቱ ፊት ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሄደው በግንባራቸው ወደቁ ፡ የእግዚአብሔርም ብርሃን ተገለጠላቸው ። ዘኍ፡ ፲፬ ፭ ፤ ፲፯ - ፳፱ ።

፯ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንሥእ ለእንታክቲ በትር ።

እግዚአብሔር ያችን በትር ያዝት ብሎ ለሙሴ ነገረው ።

፰ ወአስተጋብኡ ትዕይንተ አንተ ወአሮን እኁከ ወበልዋ ለኰኵሕ በቅድሜሆሙ ወትሁብ ማየ ፡ ወታወፅኡ ሎሙ ማየ እምኰኵሕ ወታሰትዩ ትዕይንተ ወእንስሳሆሙ ።

አንተና ወንድምህ አሮን ሠራዊቱን ሰብስባችሁ ደንጊያይቱን በፊታቸው እዘዙዋት ፡ ውኃን ታስገኛለች ፡ ከደንጊያ ውኃ አፍልቃችሁ ሠራዊቱን ከብቶቻቸውንም ውኃ ታጠጣላችሁ አለው ። ዘፀ፡ ፲፯ ፭ ፡ ኢሳ፡ ፵፫ ፳ ።

፱ ወነሥአ ሙሴ ለእንታክቲ በትር እንተ እምቅድሜሁ ለእግዚአብሔር በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ።

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ያችን በትር ከእግዚአብሔር ፊት አነሣት ። ዘኍ፡ ፲፯ ፲ ።

፲ ወአስተጋብእዎሙ ሙሴ ወአሮን ለትዕይንት ቅድሜሃ ለይእቲ ኰኵሕ ወይቤሎሙ ስምዑኒ ከሐድያን ቦኑ እምዛቲ ኰኵሕ ናወፅእ ለክሙ ማየ ።

አሮንና ሙሴም በዚያች በትር ፊት ሠራዊቱን ሰብስበው እናንተ ከሐድያን ስሙኝ በውኑ ከዚች ደንጊያ ውኃ እናፈልቅላችሁ ነበርን ፤ አላቸው ። መዝ፡ ፻፭ ፴፪ - ፴፫ ።

፲፩ ወአልዐለ ሙሴ በትሮ በእዴሁ ወዘበጣ ለይእቲ ኰኵሕ በእንታክቲ በትር ክዕበ ወወፅአ ማይ ብዙኅ ወአስተዩሙ ለትዕይንት ወለእንስሳሆሙኒ ።

ሙሴ በትሩን በእጁ አንሥቶ ያችን ደንጊያ በዚያች በትር ሁለት ጊዜ መታት ፡ ብዙ ውኃም ወጣ፡ ሠራዊቱንም ከብቶቻቸውንም አጠጣቸው ። ዘፀ፡ ፲፯ ፯ ።

፲፪ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ፡ እስመ ኢአመንክሙኒ ከመ ትቀድሱኒ ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል በበይነ ዝንቱ ኢታበውእዎሙ አንትሙ ለእሉ ትዕይንት ውስተ ምድር ዘአነ ወሀብክዎሙ ።

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን ተናገራቸው ፡ በእስራኤል ልጆች ፊት ታመሰግኑኝ ዘንድ አላመናችሁኝምና ፡ ስለዚህ ነገር እናንተ እነዚህን ሠራዊት እኔ ወደ ሰጠኋቸው አገር አታገቡዋቸውም አላቸው ። ዘኍ፡ ፳፯ ፲፬ ።

፲፫ ወዝንቱ ማይ ዘቅስት ውእቱ እስመ ተዋቀሡ ደቂቀ እስራኤል ቅድመ እግዚአብሔር ።

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ተከራከረው በቃሉና ይህ ውኃ "የክርክር ውኃ" ተባለ ። ዘዳ፡ ፴፩ ፰ ።

፲፬ ወፈነወ ሙሴ መላእክተ እምቃዴስ ኀበ ንጉሠ ኤዶም እንዘ ይብል ከመዝ ይቤ እኁከ እስራኤል ለሊከ ተአምር ኵሎ ሕማመነ ዘረከበነ ።

ሙሴ ከቃዴስ ወደ ኤዶም ንጉሥ እንዲህ ሲል መላክተኛን ላከ፤ ወንድምህ እስራኤል እንዲህ አለ ያገኘንን መከራ ሁሉ አንተ ታውቃለህ አለ ብሎ ።

፲፭ ወረዱ አበዊነ ውስተ ግብጽ ወነበሩ ህየ ብዙኀ መዋዕለ ወሣቀዩነ ግብጽ ወለአበዊነ ።

አባቶቻችን ግብጽ ወርደው በዚያ ብዙ ዘመን ኖሩ ፡ የግብጽም ሰዎች እኛንም አባቶቻችንም መከራ (ሥቃይ) አጸኑብን ። ዘፍ፡ ፵፮ ፯ ፡ ዘዳ፡ ፲፯ ፯ ።

፲፮ ወጸራሕነ ኀበ እግዚአብሔር ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለነ ወፈነወ መልአከ ወአውፅአነ እምግብጽ ወይእዜኒ ሀለውነ ውስተ ቃዴስ ጥቃ ደወለ ብሔርከ ።

እኛም ወደ እግዚአብሔር ጮኽን ፡ እግዚአብሔርም ጩኽታችንን (ልመናችንን) ሰምቶ መልአኩን ልኮ ከግብጽ አወጣን ፡ አሁንም በአገርህ አውራጃ ባለ ቃዴስ በሚባል አገር አለን ። ዘፀ፡ ፪ ፳፫ ።

፲፯ ወአኅልፈነ እንተ ብሔርከ ወሀገርከ ወኢነኀልፍ እንተ ላዕለ ገራሀትከ ወኢላዕለ ዐፀደ ወይንከ ወኢንሰቲ እምዐዘቅትከ ማየ ፡ ፍኖተ መንግሥት ነሐውር ወኢንትገኀሥ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም እስከ ነኀልፍ እምደወልከ ።

በአገርህና በአውራጃህ አሳልፈን በእርሻህና በወይንህ በታ ላይ አንሄድም ከጉድጓድህም ውኃን አንጠጣም በጥርጊያው ጐዳና እንሄዳለን ፡ ከአውራጃህ እስክናልፍ ድረስ ወደ ቀኝ ወደ ግራ አንልም አለው ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፱ ።

፲፰ ወይቤሎ ንጉሠ ኤዶም ኢተኀልፍ እንተ ላዕሌየ ወእመ አኮሰ ንትቃተል ወእወፅእ እትቀበልከ ።

የኤዶምም ንጉሥ በኔ ላይ አታልፍም ይህስ ካልሆነ እንዋጋለን ፡ በጦር እቀበልህ ዘንድ እወጣለሁ አለው ።

፲፱ ወይቤልዎ ደቂቀ እስራኤል እንተ መንገለ አድባር ነኅልፍ ወለእመኒ ሰተይነ እማይከ ንሕነ ወእንስሳነ ሜጠ ንሁበከ ወዝንቱሰ ኢኮነ ወኢምንተኒ እንተ መንገለ አድባር ነኅልፍ ።

የእስራኤልም ልጆች ደጋ ደጋውን እንሄዳለን እኛም ከብቶቻችንም ከጉድጓድህ ውኃ ብንጠጣ ዋጋውን እንሰጥሃለን፤ ይህስ ምንም አይሆንም (መንገዱን መክከል) ደጋ ደጋውን እናልፋለን አሉት ። ፪ ሳሙ፤ ፳ ፲፫ ።

፳ ወይቤ ኢተኀልፍ እንተ ላዕሌየ፤ ወወፅአ ንጉሠ ኤዶም ወተቀበሎሙ ለእስራኤል ምስለ ብዙኅ ሰራዊት ወበእደ ጽንዕት ።

የኤዶም ንጉሥ አንተ በኔ ላይ አታልፍም ብሎ እስራኤልን በብዙ ሠራዊት ጋር በጸናች ኃይል ተቀበላቸው (ገጠማቸው) ።

፳፩ ወኢፈቀደ ንጉሠ ኤዶም የሀበሙ ምኅላፈ እንተ ደወሉ ወተግኅሠ እስራኤል እምኔሁ ።

የኤዶም ንጉሥ በአውራጃው መተላለፊያን ሊሰጣቸው አልወደደም እስራኤልም ከሱ ፈቀቅ አሉ ።

፳፪ ወግዕዙ እምቃዴስ ወኀደሩ ኵሉ ትዕይንት ውስተ ደብረ ሆር ።

ከቃዴስም ተጕዘው ሠራዊቱ ሁሉ ሖር በሚባል ተራራ ሰፈሩ ። ዘፀ፤ ፳፩ ፬፤ ዘኍ፤ ፴፫ ፴፯ ።

፳፫ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሆር በመንገለ ደወለ ምድሩ ለኤዶም እንዘ ይብል ።

እግዚአብሔር ሙሴን በኤዶምያስ ምድር ዳርቻ ባለው በሖር ተራራ እንዲህ ሲል ተናገረው ።

፳፬ ለይትወሰክ አሮን ኀበ ሕዝቡ፤ እስመ ኢትበውኡ ውስተ ይእቲ ምድር ዘእነ እሁቦሙ ለደቂቀ እስራኤል እስመ አምዓዕክሙኒ በኀበ ማየ ቅስት ።

ጠብ ክርክር በተደረገበት ውኃ ስለ አሳዘናችሁኝ እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣቸው ወደዚያች አገር አትገቡምና አሮን ወደ ወገኖቹ ይጨመራል ።

፳፭ ወንሥኦሙ ለአሮን ወለአልአዛር ወልዱ ወአዕርጎሙ ውስተ ደብረ ሆር በቅድመ ኵሉ ትዕይንት ።

አሮንንና ልጁ አልአዛርን በሠራዊቱ ሁሉ ፊት ወስደህ ወደ ሖር ተራራ አውጣቸው ።

፳፮ ወንሣእ አልባሲሁ ለአሮን እምላዕሌሁ ወአልብሶ ለአልአዛር ወልዱ ወይትወሰክ አሮን ወይሙት በህየ ።

የአሮንንም ልብስ አውጥተህ ለልጁ ለአልአዛር አልብሰው አሮንም በዚያው ተራራ ሙቶ በሞት ወደ ወገኖቹ ይጨመር አለው ። ዘኍ፤ ፳ ፳፬ ።

፳፯ ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ወአዕረጎሙ ውስተ ደብረ ሆር በቅድመ ኵሉ ትዕይንት ።

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አድርጎ በሠራዊቱ ሁሉ ፊት ወደ ሖር ተራራ አወጣቸው ።

፳፰ ወነሥአ አልባሲሁ ለአሮን እምላዕሌሁ ወአልበሶ ለአልአዛር ወልዱ፤ ወተወሰከ አሮን ወሞተ በህየ በውስተ ርእሰ ደብር፤ ወወረዱ ሙሴ ወአልአዛር እምደብር ።

የአሮንን ልብስ ወስዶ ለልጁ ለአልአዛር አለበሰው፤ አሮንም በዚያ በተራራው ራስ ላይ ሙቶ በሞት ከወገኖቹ ጋር ተጨመረ አልአዛርና ሙሴም ከተራራው ወረዱ ።

፳፱ ወርእዩ ኵሉ ትዕይንት ዘከመ ኀለፈ አሮን ወበከይዎ ሠላሳ መዋዕለ ኵሉ ቤተ እስራኤል ።

ሠራዊቱም ሁሉ አሮን እንደ ሞተ አይተው የእስራኤል ወገኖች ሁሉ ሠላሳ ቀን አለቀሱለት ።

## ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወሰምዐ ከነአን ንጉሠ አራድ ዘይነብር ውስተ አዜብ ከመ መጽአ እስራኤል እንተ ፍኖተ አታርን ወተቃተሎሙ ወማኅረከ እምኔሆሙ ፄዋ ።

በአዜብ የሚኖር የአራድ ንጉሥ ከነዓን እስራኤል በአታርን ጐዳና እንደመጡ ተዋጋቸው፤ ከነሳቸውም ምርኮን ማረከ ። ዘኍ፤ ፴፫ ፵፤ ዘዳ፤ ፲፫ ፳፩ ።

፪ ወበፅዑ እስራኤል ብፅዓተ ለእግዚአብሔር ወይቤሉ ለእመ አግብኦ እግዚአብሔር ለዝንቱ ሕዝብ ለነ ነበልሎሙ ወለአህጉሪሁ ።

እግዚአብሔር ይህን ወገን በእጃችን ቢጥልልን ሰዉንም አገሩንም ጕልት እናደርጋቸዋለን ብለው ስለትን ተሳሉ ። ዘፍ፤ ፳፰ ፳፤ ዘሌ፤ ፳፯ ፳፰፤ መሳ፤ ፲፩ ፴ ።

፫ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃሎሙ ለእስራኤል ወአግብአሙ ለከነአን ውስተ እደዊሆሙ ወአለልምሙ ሎሙ ወለአህጉሪሆሙ ወሰመዩ ስሞ ለውእቱ መካን ማዕለልት ።

እግዚአብሔር የእስራኤል ልመናቸውን ሰምቶ የከነዓንን ሰዎች በእጃቸው ጣለላቸው፤ ሰዎቹንም አገራቸውንም ጕልት አደረጉዋቸው፤ የዚያንም ቦታ ስም "ጕልት" አሉት ። ዘኍ፤ ፲፬ ፲፭፤ ኢያ፤ ፲፱ ፬ ።

፬ ወግዕዙ እፍአ እምደብረ ሆር መንገለ ፍኖተ ባሕረ ኤርትራ ወዖድዋ ለምድረ ኤዶም ወተቈጥዐ ሕዝብ በፍኖት ።

ከሖር ተራራ አደባባይ ወጥተው ወደ ኤርትራ ባሕር ጐዳና ተጓዙ፤ የኤዶምያስን ምድር ዞሯት ሕዝቡም በጐዳና ተበሳጩ ። ዘኍ፤ ፳ ፳፱፤ መሳ፤ ፲፩ ፲፰ ።

፭ ወሐመይዎ ለእግዚአብሔር ወለሙሴ ወይቤልዎ ለምንት አውፃእከነ እምድረ ግብጽ ከመ ትቅትለነ በውስተ ዝንቱ ገዳም እስመ አልቦቱ እክል ወአልቦቱ ማይ፤ ወተቈጥዐት ነፍስነ በዝንቱ ኅብስት ዘአልቦቱ በቍዕ ።

እኽል ውኃ የለበትምና ሰውነታችንም ረብሕ ጥቅም የሌለው የዚህ ኅብስቱን ስልችታለችና በዚህ ምድረ በዳ ታጠፉን ዘንድ ለምን ከግብጽ አወጣኸን ብለው እግዚአብሔርን አሙት ሙሴንም ነቀፉት ። መዝ፤ ፸፰ ፲፱ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወፈነወ እግዚአብሔር አራዊተ ምድር ላዕለ ሕዝብ ዘይነስኮ ወይቀትሉ ፡ ወሞቱ ሕዝብ ብዙኃን እምደቂቀ እስራኤል ። | ፮ | እግዚአብሔር እየነደፉ የሚገድሉ የምድር እባቦችን በሕዝቡ ላይ ለቀቀባቸው ፡ ከእስራኤልም ልጆች ብዙ ወገኖች ሞቱ ። ዘዳ፡ ፰ ፲፭ ፡ ፩ ቆሮ፡ ፲ ፱ ። |
| ወመጽኡ ሕዝብ ኀበ ሙሴ ወይቤሉ አበስነ እስመ ሐመይናሁ ለእግዚአብሔር ወለከኒ ፡ ጸሊ እንከሰ ኀበ እግዚአብሔር የሰስል እምኔነ አራዊተ ምድር ። | ፯ | ሕዝቡም ከሙሴ ዘንድ መጥተው እግዚአብሔርን እም ተነዋልና አንተንም ነቅፈንሃልና በደልን እባቦችን ያጠ ፋልን ዘንድ እንግዲህ እግዚአብሔርን ለምንልን አሉት። |
| ወጸለየ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ሕዝብ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ግበር ለከ አርዌ ምድር ዘብርት ወአንብሮ ኀበ ይትኤመሩ ወእምከመ ነሰከ አርዌ ምድር ሰብአ ኵሉ ዘተነስከ ለይርአዮ ወይሕየው ። | ፰ | ሙሴም ስለ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ለመነ ፡ እግዚ አብሔርም ሙሴን የናስ እባብ ሠርተህ በሚሰፍሩበት በታ ላይ አኑረው የምድር እባብ ሰውን በነደፈው ጊዜ የተነደ ፈው ሰው ሁሉ አይቶት ይዳን አለው ። |
| ወገብረ ሙሴ አርዌ ምድር ዘብርት ወአቀሞ ኀበ ይት ኤመሩ ወእምከመ ነሰከ አርዌ ምድር ሰብአ ይኔጽሮ ለዝ ኩቱ አርዌ ዘብርት ወየሐዩ ። | ፱ | ሙሴም ከናስ የተሠራ የምድር እባብን ሠርቶ በሚት ያዩበት በታ ሰቀለው ፡ የምድር እባብ ሰውን በነደፈው ጊዜ ያንን ከናስ የተሠራው የምድር እባብ አይቶ ይድን ነበር ። ዮሐ፡ ፫ ፲፬ - ፲፭ ። |
| ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወኀደሩ ውስተ አጋቦት ። | ፲ | የእስራኤልም ልጆች ተጉዘው በአጋቦት ሰፍረው አደሩ ። ዘኍ፡ ፴፫ ፵፫ ። |
| ወግዕዙ እምአጋቦት ወኀደሩ ውስተ ጌልጋይ ማዕዶተ ገዳም እንተ አንጻረ ገጸ ለሞአብ መንገለ ምሥራቀ ፀሐይ ። | ፲፩ | ከአጋቦትም ተጉዘው በፀሐይ መውጫ በኩል በሞአብ አንጻር በለችው ምድረ በዳ ማዶ በጌልጋይ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምህየ ወኀደሩ ውስተ ቈላተ ዛሬት ። | ፲፪ | ከዚያም ተጉዘው በዛሬት ቈላ አደሩ (ሠፈሩ) ። |
| ወግዕዙ እምህየ ወኀደሩ ውስተ ማዕዶተ አርኖን ዘይ ከሁ ማይ እምአድባር ዘአሞሬዎን ፡ እስመ ደወሎሙ ው እቱ ለሞአብ ፡ ወማእከለ ሞአብ ወማእከለ አሞሬዎን ውእቱ ። | ፲፫ | ከዚያም ተጉዘው ውኃውን ከአሞሬዎን ደጋ በሚያፈ ሰው በአርኖን ማዶ ሠፈሩ ፡ ይኸውም በአሞሬዎንና በሞ አብ መካከል ያለ የሞዓባውያን ወሰናቸው ነው ። |
| ወበበይነ ዝንቱ ይብል ውስተ መጽሐፍ ፀብኡ ለእግ ዚአብሔር ዞውግያ ለዛእሙ ወአቀመ ወኀይዝተ አርኖን ዘሀለወ ውስተ ኤር ዘይሰመይ ደወለ ሞአብ ። | ፲፬ | ስለዚህ በወግ (በታሪክ) የእግዚአብሔር ሰልፉ ዘአሙ የምትባል አገርን አጠፋት ይላል ፡ የሞዓብ ድምበር በሚ ባል በኤር ያለ የአርኖንን ፈሳሾች አቆመ ። |
| ወእምህየ ውስተ ዐዘቅት ዘይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አስተጋብእ ሕዝበ ወእሁቦሙ ማየ ዘይሰትዩ ። | ፲፭ | ከዚያም ተጉዘው እግዚአብሔር ለሙሴ ሕዝቡን ሰብስብ የሚጠጡትን ውኃ እሰጣቸዋለሁ ብሎ በነገረው በታ አደሩ ። |
| ወይእተ አሚረ ኀለዩ እስራኤል ዛተ ማኅሌተ በኀበ ይእቲ ዐዘቅት ። | ፲፮ | ያን ጊዜ እስራኤል በዚያች ጉድጓድ ይህን ምስጋና አመሰገኑ (መዝሙር ዘመሩ) ። |
| አቅደሙ ሎሙ ዐዘቅተ ፡ እንተ ከረይዋ መላእክት ወወቀርዋ ነገሥቱ አሕዛብ በምሕናኖሙ ወእምይእቲ ዐዘቅት ውስተ ምንትናይን ። | ፲፯ | አለቆች አስቀድመው በቈፈርዋት የአሕዛብም ነገሥ ታት በግዛታቸው መትተው የቈፈሩዋትን ጉድጓድ እስራ ኤል ፈጥነው አገኙ ብለው ዘመሩ ። ከዚያችም ጉድጓድ ወጥተው ወደ ምንትናይን አደሩ ። |
| ወእምንትናይን ውስተ ነሐልያል ፡ ወእምነሐልያል ውስተ ባሞት ። | ፲፰ | ከምንትናይንም ተጉዘው ወደ ነሐልያል ፡ ከነሐልያ ልም ተጉዘው በባሞት አደሩ ። |
| ወእምባሞት ውስተ ኢያጺን እንተ ገዳም ዘሞአብ እምኀበ ርእሱ ለፋስጋ ዘይኔጽር መንገለ ገጸ ገዳም ። | ፲፱ | ከባሞትም ተጉዘው በምድረ በዳ አንጻር በፋስጋ ራስ መያያዣ በሞዓብ ምድረ በዳ በኢያጺን አደሩ ። |
| ወፈነወ እስራኤል ተናብልተ ኀበ ሴዎን ንጉሠ አሞ ሬዎን በቃለ ሰላም እንዘ ይብል ። | ፳ | እስራኤል ወደ አሞሬዎን ንጉሥ ወደ ሴዎን በፍቅር ቃል እንዲህ ብሎ መልእክተኛን ላከ ። |
| ንኅልፍ እንተ ምድርከ መንገደ ንኅልፍ ወኢንትገኀሥ ኢ ውስተ ገራህትከ ወኢ ውስተ ዐፀደ ወይንከ ፡ ወኢን ሰቲ ማየ እምውስተ ዐዘቃቲከ ፍኖተ መጽያሕቲ ነሐውር እስከ ንኅልፍ እምደወልከ ። | ፳፩ | ከወሰንህ እስክናልፍ ድረስ ጥርጊያውን ጐዳና እንሄ ዳለን እንጂ ወደ እርሻህና ወደ ወይን በታህም አንገባም ከጉድጓዶችህም ውኃ አንጠጣም ። ዘኍ፡ ፳ ፲፯ ። |
| ወኢያብሖሙ ሴዎን ለእስራኤል ይኅልፉ እንተ ደወሉ ወአስተጋብአ ሴዎን ኵሎ ሰብአ ወወፅአ ይትቃተሎሙ ለእስራኤል ውስተ ገዳም ወበጽሐ ውስተ ኢያሶን ወተቃ ተሎሙ ለእስራኤል ። | ፳፪ | ሴዎን ግን በአገሩ ይሄዱ ዘንድ እስራኤልን አላሰናበ ታቸውም ፡ ሴዎን ሰውን ሁሉ ሰብስቦ እስራኤልን ለመው ጋት ወደ ምድረ በዳ ወጣ ፡ ወደ ኢያሶን ደርሰም እስራኤ ልን ተዋጋቸው ። ዘዳ፡ ፳፱ ፯ ፡ መሳ፡ ፲፩ ፳ ። |

፳፬ ወቀተልዎሙ እስራኤል ቀትለ ኅቢየ በሐፂን፣ ወገብአ ሎሙ ብሔሩ እምአርኖን እስከ ኢያቦቅ ወእስከ ደቂቀ አሞን እስመ ኢያዜር ደወሎሙ ውእቱ ለደቂቀ አሞን።

እስራኤልም ጽኑ ሰልፍ አድርገው በጦር ወጉዋቸው ከአርኖን ጀምሮ እስከ አሞን ልጆች አገርና እስከ ኢያቦቅ ድረስ በእስራኤል እጅ ገባላቸው፤ ኢያዜርም ለአሞን ልጆች ወሰናቸው (አውራጃቸው) ነው ። ዘዳ፣ ፱ ፴፫ ።

፳፭ ወነሥአ እስራኤል ኵሎን ውእቶን አህጉረ ወነበረ እስራኤል ውስተ ኵሉን አህጉረ አሞሬዎን በሐሴቦን ወበኵሉ ደወሉ ።

እስራኤል እነዚያን አገሮች ሁሉ እጅ አድርጎ በአሞሬዎን አገሮች ሁሉ በሐሴቦንና በአውራጃዎቿ ሁሉ ኖረ ።

፳፮ እስመ ቦቅ በሐሴቦን አህጉረ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ወውእቱ ዘፀብአ ቀዲሙ ለንጉሠ ሞአብ ወነሥአ ኵሎ ምድሮ እምአሮኤር እስከ አርኖን ።

የአሞሬዎን ንጉሥ ሴዎን በሐሴቦን ከተሞች ነበሩት፤ ይኸውም አስቀድሞ የሞዓብን ንጉሥ የወጋው ነው፤ ከአሮኤር ጀምሮ እስከ አርኖን ድረስ አገሩን ሁሉ ወግቶ እጅ ያደረገ ነው ።

፳፯ ወበእንተ ዝንቱ ይብሉ ሰብአ ንግምስጥስጤ ሖሩ ውስተ ሐሴቦን ከመ ትትነደቅ ወይትገበር አህጉረ ሴዎን ።

ስለዚህ የሞዓብ አገር የሴዎን አገር ተብላ ትሠራ ትቀጸርም ዘንድ (ሰብአ ንግምስጥስጤ) የወግ የታሪክ ሰዎች ከሐሴቦን ወደ ሞዓብ ሂዱ አሉ ።

፳፰ እስመ እሳት ወፅአት እምሐሴቦን ወነድ እምአህጉረ ሴዎን ወበልዐት እስከ ሞአብ ወውኅጠት ሐውልተ አርኖን ።

ከሐሴቦንና ከሴዎን ከተሞች (እሳት) ጦር ወጥታ እስከ ሞዓብ ድረስ አጥፍታለችና፤ የአርኖንም ኃያላን አጥፍታለችና ወደ ሞዓብ ሂዱ አሉ ። ኢዮብ ፳፯ ፩ ።

፳፱ አሌ ለከ ሞአብ አኅጕልኪዮሙ ለሕዝበ ከሞስ አስገብኡ ደቂቆሙሰ አድኅንክሙ ወአዋልዲክሙ ተፄወዋ ኀበ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ።

ሞዓብ ወዮ ድካም የተመለሱ የጣኦቱን ወገኖች አጥፍተሸዋልና ወዮልሽ ልጆቻቸውን ግን አዳናችሁ፤ ሴቶች ልጆቻችሁም ተማርከው ወደ አሞሬዎን ንጉሥ ወደ ሴዎን ሂዱ ። መሳ፣ ፲፩ ፳፬፤ ፪ ነገ፣ ፳፫ ፲፫ ።

፴ ወዘርእሙኒ ደምሰሰሙ እምሐሴቦን እስከ ዲቦን ወአንስቲያሆሙኒ ዓዲ አንደዱ እሳተ ላዕለ ሞአብ ።

ልጆቻቸውንም ከሐሴቦን እስከ ዲቦን ድረስ አጠፋቸው፤ ሚስቶቻቸውም ዳግመኛ በሞዓብ ላይ (እሳት አነደዱ) ጠብ አነሡ ። ዘኍ፣ ፴፬ ፫፤ ኢሳ፣ ፲፭ ፪ ።

፴፩ ወነበረ እስራኤል ውስተ ኵሉ አህጉረ አሞሬዎን ።

እስራኤልም በአሞሬዎን አገሮች ሁሉ ኖረ (ተቀመጠ)።

፴፪ ወፈነወ ሙሴ ይርአይዋ ለኢያዜር ወእምዝ አስተጋብእዋ ምስለ አህጉራሂ ወአውፅእዎሙ ለአሞሬዎን እለ ሀለዉ ህየ ።

ሙሴም ኢያዜርን ያዩዋት ዘንድ ሰላዮችን ሰደደ፤ ከዚህ በኋላ ከአውራጃዎቿ ጋር እጅ አደረጉዋት፤ በዚያ የነበሩ አሞሬዎንንም አበረሩዋቸው ። ዘኍ፣ ፴፪ ፫ ።

፴፫ ወተመይጡ ወዐርጉ ውስተ ፍኖተ ባሳን፤ ወወፅአ ዖግ ንጉሠ ባሳን ወተቀበሎሙ ምስለ ኵሉ ሕዝቡ ከመ ይትቃተሎሙ በአድራዒን ።

ተመልሰውም በባሳን ጐዳና ወጡ፤ የባሳን ንጉሥ ዓግም ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፎ ይወጋቸው ዘንድ በአድራይን ተቀበላቸው ። ዘዳ፣ ፩ ፬፤ ፫ - ፩ ።

፴፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ኢትፍርሆ፤ እስመ ውስተ እዴከ አገብአ ወለኵሉ ሕዝቡ ወለኵሉ ምድሩ፤ ወትገብሮ ከመ ገበርከሁ ለሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ።

እግዚአብሔርም ሙሴን በእጅህ እጥለዋለሁና ሠራዊቱንም ሁሉ ምድሩንም ሁሉ በእጅህ እጥልልሃለሁና በሐሴቦን የሚኖር የአሞሬዎንን ንጉሥ ሴዎን እንዳደረግኸው ታደርገዋለህና አትፍራው አለው ። ዘዳ፣ ፫ ፪ ።

፴፭ ወቀተሉ ሎቱ ወለደቂቁ ወለኵሉ ሕዝቡ እስከ ኢያትረፈ ሎቱ ነፋሴ ተ፤ ወወረሱ ምድሮሙ ።

እሱን ልጆቹን ሕዝቡንም ሁሉ ሽሽታ ሳያስቀር አጠፉቸው፤ አገራቸውንም ወረሱ ። ኢያሱ ፲ ፳፰ ።

## ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወኀደሩ መንገለ ዐረበ ለሞአብ ኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ።

የእስራኤል ልጆች ተጕዘው በኢያሪኮ በዮርዳኖስ ማዶ ባለው በሞዓብ ሜዳ ሠፈሩ ። ዘኍ፣ ፳፯ ፫፤ ፴፫ - ፵፰ ።

፪ ወሰበ ርእየ ባላቅ ወልደ ሰፎር ኵሎ ዘገብሩ ፳ል በአሞሬዎን ፈርህዎሙ ሞአብ ለሕዝብ ጥቀ እስመ ብዙኃን እሙንቱ ወተሀውኩ እምቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

የሰፎር ልጅ ባላቅም ፳ል በአሞሬዎን ያደረጉትን ሁሉ በሰማ ጊዜ እነሱ ብዙ ናቸውና የሞዓብ ወገኖች እስራኤልን እጅግ ፈሩዋቸው፤ ከእስራኤል ልጆች ፊትየተነሣ ታወኩ።

፫ ወይቤሎሙ ሞአብ ለአእሩገ ምድያም፤ ይእዜ ያኀልቅሙ ዛቲ ትዕይንት ለኵሎሙ እለ ዐውድነ ከመ ያኀልቅ ላሕም ሣዕረ ዘውስተ ገዳም፤ ወባላቅ ወልደ ሰፎር ንጉሠ ሞአብ ውእቱ በውእቱ መዋዕል ።

ሞዓብም (የሰፎር ልጅ ባላቅ) የምድያምን ሽማግሎች ይህች ሠራዊት በሬ በምድረ በዳ ያለውን ሣር በልቶ እንዲጨርስ በዙርያችን ያሉትን ሁሉ አሁን ትጨርሳቸዋለች አላቸው፤ በዚያም ወራት የሰፎር ልጅ ባላቅ የሞዓብ ንጉሥ ነበር ። ዘኍ፣ ፳፬ ፯፤ ፳፭ - ፲፰፤ ኢያ፣ ፲፫ ፳፩ ።

፬ ወፈነወ ተናብልተ ኀበ በለዓም ወልደ ቤዖር ዘፋቱራ ዘሀለወ ኀበ ፈለገ ምድሮሙ ለደቂቀ ሕዝቡ ።

በወገኖቹ ልጆች አገር ወንዝ ወዳለው ሟርተኛ ወደ ሚሆን ወደ ቤዖር ልጅ ወደ በለዓም መልእክተኛን ላከ ።

፭ ወጸውዖ እንዘ ይብል ፡ ናሁ ሕዝብ ዘወፅአ እምግብጽ ከደኖ ለገጸ ምድር ወሀለዉ ይነብሩ ቅሩብየ ።

እነሆ ከግብጽ የወጣ ወገን የምድሪቱን ፊት በብዛት አለበሳት ፤ በአቅራብያዬም ይኖራሉ ። ዘዳ፡ ፳፫ ፬ ።

፮ ወይእዜኒ ነዓ ርግሞሙ ሊተ እስመ ይጸንዑ እምኔየ ለእመ እክል ቀቲሎቶሙ ወአውፅኦቶሙ እምድርየ እስመ አአምር ከመ ዘአንተ ባረከ ቡሩክ ይከውን ወዘአንተ ረገምከ ርጉመ ይከውን ።

ከኔ ይበረታሉና ማጥፋታቸው ይቻለኝ እንደሆነ ከአገሬም አውጥቼ አሰዳቸው እንደሁ አንተ የመረቅኸው የተመረቀ እንዲሆን አንተ የረገምከው የተረገመ እንዲሆን አውቃለሁና አሁንም መጥተህ ርገምልኝ ብሎ ጠራው ።

፯ ወሖሩ አዕሩገ ሞአብ ወአዕሩገ ምድያም ፡ ወነሥኡ መቃስምቲሆሙ ምስሌሆሙ ወበጽሑ ኀበ በለዓም ወነገርዎ ቃለ ባላቅ ።

የምድያምና የሞዓብም ሽማግሌዎች የሚያሟርቱበትን ከነሳቸው ጋር ይዘው ከበለዓም ዘንድ ደርሰው የባላቅን ነገር ነገሩት ። ዘኁ፡ ፳፪ ፲፱ ።

፰ ወይቤሎሙ ቢቱ ዝየ ሌሊተ ወአየድአክሙ ቃለ ዘይቤለኒ እግዚአብሔር ወኀደሩ መላእክተ ሞአብ ኀበ በለዓም ።

በዚች ሌሊት እደሩ ፤ እግዚአብሔር የሚለኝን ነገር እነግራችኋለሁ አላቸው ፤ የሞዓብ አለቆችም ከበለዓም ዘንድ አደሩ ።

፱ ወመጽአ እግዚአብሔር ኀበ በለዓም ወይቤሎ ምንተ ይግበሩ መጽኡ እሉ ሰብእ ኀቤከ ።

እግዚአብሔርም ወደ በለዓም መጥቶ እኒህ ሰዎች ምን ሊያደርጉ ወዳንተ መጡ አለው ። ዘኁ፡ ፳፬ ፳ ።

፲ ወይቤሎ በለዓም ለእግዚአብሔር ባላቅ ወልደ ሰፎር ንጉሠ ሞአብ ፈነዎሙ ኀቤየ እንዘ ይብል ።

በለዓምም እግዚአብሔርን የሞዓብ ንጉሥ የሰፎር ልጅ ባላቅ እንዲህ ሲል ወደኔ ልኮአቸዋል አለው ።

፲፩ ናሁ ሕዝብ ዘወፅአ እምግብጽ ከደነዋ ለገጸ ምድር ወሀለዉ ንቡራነ ቅሩብየ ወይእዜኒ ነዐ ርግሞሙ ሊተ ለእመ እክል ቀቲሎቶሙ ወአወፅኦቶሙ እምድርየ ።

እነሆ ከግብጽ የወጡ መላዋን ምድር ሸፈኑዋት ፤ በአቅራቢያዬም ተቀምጠዋል ፤ አሁንም ማጥፋት ይቻለኝ እንደሁ ከአገሬም አስወጣቸው እንደሁ መጥተህ ርገምልኝ ።

፲፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለበለዓም ኢትሖር ምስሌሆሙ ወኢትርግሞሙ እስመ ቡሩካን እሙንቱ ።

እግዚአብሔርም በለዓምን ከነሱ ጋር አትሂድ የተመረቁ ናቸውና ፤ አትርገማቸው አለው ። ዘኁ፡ ፳፫ ፳ ።

፲፫ ወተንሥአ በለዓም በጽባሕ ወይቤሎሙ ለመላእክተ ባላቅ ሑሩ ኀበ እግዚእክሙ ግብኡ እስመ ኢኀደገኒ እግዚአብሔር ከመ እሑር ምስሌክሙ ።

በለዓምም ማለዳ ተነሥቶ የሞዓብን መልእክተኞች ከናንተ ጋር እሄድ ዘንድ እግዚአብሔር አላሰናበተኝምና ተመልሳችሁ ወደ ጌታችሁ ሂዱ አላቸው ።

፲፬ ወተንሥኡ መላእክተ ሞአብ ወሖሩ ኀበ ባላቅ ወይቤልዎ አበየ በለዓም መጺአ ምስሌነ ።

የሞዓብም መልእክተኞች ተነሥተው ወደ ባላቅ ሄደው በለዓም ከኛ ጋር መምጣትን እምቢ አለ አሉት ።

፲፭ ወደገመ ዳግመ ባላቅ ወፈነወ መላእክተ እለ ይበዝኁ ወእለ ይከብሩ እምእልክቱ ።

ባላቅም ዳግመኛ ከነሱ የሚበዙና የሚከብሩ መልእክተኞችን ላከ ።

፲፮ ወበጽሑ ኀበ በለዓም ወይቤልዎ ከመዝ ይቤ ባላቅ ወልደ ሰፎር ብቍዐኒ ኢትትሀከይ መጺአ ኀቤየ ።

ከበለዓም ዘንድ ደርሰው የሰፎር ልጅ ባላቅ እንዲህ አለ በጅ በለኝ ወደኔ መምጣትንም ቸል አትበል ።

፲፯ እስመ አክብሮ አከብረከ ወኵሎ ዘትቤለኒ እገብር ለከ ወነዓ ርግሞሙ ሊተ ለእሉ ሕዝብ ።

ማክበሩን አከብርሃለሁና ያልከኝንም ሁሉ አደርግልሃለሁና ፤ እነዚህን ወገኖች መጥተህ ርገምልኝ አለ አሉት ።

፲፰ ወአውሥአሙ በለዓም ወይቤሎሙ ለመላእክተ ባላቅ ምልአ ቤት ወርቀ ወብሩረ ለእመ ወሀበኒ ባላቅ ኢይክል ተዓውሮ ቃለ እግዚአብሔር ከመ እግበር ንኡሰ አው ዐቢየ እምልብየ ።

በለዓምም የባላቅን መልእክተኞች ቤት ሙሉ ወርቅና ብር ቢሰጠኝ ከልቤ አንቅቼ ታላቁን ታናሹንም አደርግ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ቸል አልልም ብሎ መለሰላቸው ። ዘዳግ፡ ፳፬ ፴፰ ፤ ፳፫ - ፳፮ ።

፲፱ ወይእዜኒ ቢቱ ዝየ ሌሊተ አንትሙ ምንተ ይገብር እግዚአብሔር ዘከመ ይቤለኒ ።

እግዚአብሔር የሚያደርገው ምን ይታወቃል አሁንም እናንተ በዚች ሌሊት እደሩ ፤ እግዚአብሔር ያለኝን እነግራችኋለሁ አላቸው ። ፳፬ ፳ ።

፳ ወመጽአ እግዚአብሔር ኀበ በለዓም በዛቲ ሌሊት ወይቤሎ ከመ ይጸውዑከ መጽኡ እሉ ሰብእ ተንሥእ ወትልዎሙ አላ ቃለ ዘእቤለከ ኪያሁ ተዓቂብ ለነቢብ ።

እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት ወደ በለዓም መጥቶ እኒህ ሰዎች ሊጠሩህ መጡን ፤ እኔ የምነግርህን ነገር ለመናገር ተጠበቅ እንጂ ተነሥተህ ተከተላቸው አለው ።

፳፩ ወተንሥአ በለዓም በጽባሕ ወረሐነ እድግቶ ወሖረ ምስለ መላእክተ ባላቅ ።

በለዓም ማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጭኖ ከባላቅ መልእክተኞች ጋራ ሄደ ። መሳ፡ ፭ ፲ ፤ ፩ ሳሙ፡ ፲፭ ፳፱ ።

፳፪ ወተምዐ መዐተ እግዚአብሔር እስመ ሖረ ውእቱ ወተንሥአ መልአከ እግዚአብሔር ያዕቅፎ ወውእቱሰ ይጼ

እሱ ሄዶአልና እግዚአብሔር ፈጽሞ ተቈጣ ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ያሰነክለው ዘንድ ተነሣ ፤ እሱ ግን

ዓን ዲበ እድግቱ ወክልኤቱ ደቂቁ ምስሌሁ ።

፳፫ ወሶበ ርእየቶ ይእቲ እድግት ለመልአከ እግዚአብሔር ይቀውም ውስተ ፍኖት ወሰይፍ ምሉሕ ውስተ እዴሁ ተግኅሠት ይእቲ እድግት እምፍኖት ወሖረት ውስተ ገዳም ወዘበጣ በበትር ለይእቲ እድግት ከመ ያግብኣ ውስተ ፍኖት ።

፳፬ ወቆመ መልአከ እግዚአብሔር ማእከለ ፀቈን ዘዓፀደ ወይን ፤ ፀቈን እምለፌ ወፀቈን እምለፌ ።

፳፭ ወሶበ ርእየቶ ይእቲ እድግት ለመልአከ እግዚአብሔር ተጠውቀት በፀቈን ወመለጦቶ እግሮ ለበለዓም ወደገመ ዘቢጦታ ።

፳፮ ወደገመ ዓዲ መልአከ እግዚአብሔር ወሖረ ወቆመ ውስተ መካን ጸቢብ ኀበ አልቦ ምግኃሥ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም ።

፳፯ ወሶበ ርእየቶ ይእቲ እድግት ለመልአከ እግዚአብሔር በረከት በታሕቴሁ ለበለዓም ወዘበጣ በበትር ለይእቲ እድግት ።

፳፰ ወፈትሐ እግዚአብሔር አፉሃ ለይእቲ እድግት ፤ ወትቤሎ ለበለዓም ምንተ ረሰይኩከ ከመዝ ዘትዘብጠኒ ናሁ ሣልስከ ዝንቱ ።

፳፱ ወይቤላ በለዓም ለይእቲ እድግት እስመ ተሣለቂ ላዕሌየ ሶበሰ ብየ መጥባሕት ውስተ እዴየ እምወዳእኩ እምረገዝኩኪ ።

፴ ወትቤሎ ይእቲ እድግት ለበለዓም አኮኑ አነ ይእቲ እድግትከ እንተ ትጼዐነኒ እምንእስከ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ፤ ቦኑ እመ ተዐውሮ ተዐወርኩከ ወገበርኩ ላዕሌከ ከመዝ ወይቤላ አልቦ ።

፴፩ ወከሠተ እግዚአብሔር አዕይንቲሁ ለበለዓም ወርእዮ ለመልአከ እግዚአብሔር እንዘ ይቀውም ውስተ ፍኖት ፤ ወመጥባሕት ምልሕት ውስተ እዴሁ ወደነነ ወሰገደ ሎቱ በገጹ ።

፴፪ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ለምንት ዘበጥካሃ ለእድግትከ ወናሁ ሣልስከ ዝንቱ ወናሁ አነ መጻእኩ ከመ አዕቅፍከ እስመ ኢኮነት ርትዕተ ፍኖትከ ቅድሜየ ፤ ወሶበ ርእየተኒ እድግትከ ተግኅሠት እምኔየ ናሁ ሣልስከ ዝንቱ ።

፴፫ ሶበሰ ኢተግኅሠት እምኔየ እምወዳእኩ እምቀተልኩከ ይእዜ ፤ ወኪያሃሰ እምአሕየውክዋ ።

፴፬ ወይቤሎ በለዓም ለመልአከ እግዚአብሔር አበስኩ እስመ ኢያእመርኩ ከመ አንተ ተቃወምከኒ ቅድሜየ ውስተ ፍኖት ወይእዜኒለእመ ኢትፈቅድ እገብእ ።

፴፭ ወይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር ሑር ምስለ እሉ ሰብእ ወባሕቱ ቃለ ዘእቤለከ ኪያሁ ተዐቀብ ለነቢብ ወሖረ በለዓም ምስለ መላእክተ ባላቅ ።

፴፮ ወሶበ ሰምዐ ባላቅ ከመ መጽአ በለዓም ወፅአ ወተቀበሎ ውስተ ሀገረ ሞአብ እንተ ደወለ አርኖን እንተ ሀለወት ውስተ አሐዱ ኀብር እምደወሎሙ ።

፴፯ ወይቤሎ ባላቅ ለበለዓም አኮኑ ለአክኩ ኀቤከ ይጸውዑከ ለምንት ኢመጻእከ ኀቤየ እምኢክህልኩኑ አክብሮተከ ።

በአህያው ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ሁለቱም ብላቴኖቹም አብረዉት ነበሩ ። ዘፀ ፬ ፳፬ ።

ያችም አህያ የእግዚአብሔርን መልአክ በጐዳና ቁሞ የያዘውም ሰይፍ በጁ ተመዝዞ ባየችው ጊዜ ከጐዳና ወጥታ ወደ ምድረ በዳ ሄደች፤ ወደ ጐዳናም ሊመልሳት አህያዋን በበትር መታት ።

ከእግዚአብሔር የተላከውም መልአክ በቀኝ በግራ የወይን ቅጥር ባለበት ቦታ መካከል ቆሞ ።

ያችም አህያ የእግዚአብሔርን መልአክ ባየችው ጊዜ የወይን ቅጥር ባለበት ቦታ መካከል ተጠግታ የበለዓምን እግሩን መለጠችው ዳግመኛም መታት ።

የእግዚአብሔር መልአክ ዳግመኛ ሂዶ በቀኝም በግራም መታላለፊያ በሌለበት በጠባብ ቦታ ቆመ ።

ያችም አህያ የእግዚአብሔርን መልአክ ባየችው ጊዜ ከበለዓም በታች ተንበርከከች ያችንም አህያ በበትር መታት ።

እግዚአብሔርም ያችን አህያ አፉዋን ፈታ (እንድትናገር አደረጋት) በለዓምንም እነሆ ይህ ሦስተኛህ ነው፤ እንዲህ የምትደበድበኝ ምን አደረግሁህ፤ አለችው ።

በለዓምም ያችን አህያ ዘብተሽብኛልና በእጄ ሾተል ቢኖረኝ ፈጽሜ በወጋሁሽ ነበር አላት ።

ያችም አህያ በለዓምን ከሕፃንነትህ ጀምሮ እስከ አሁን እስከዚህችም ቀን ድረስ የምትቀመጠኝ አህያህ አይደለሁምን አንተን ቸል ያልኩበት ባንተስ እንዲህ ያደረግሁበት ጊዜ አለን፤ አለችው፤ እሱም የለም አላት ።

እግዚአብሔርም የበለዓም ዓይነ ልቡናውን ገልጦለት መልአከ እግዚአብሔርን በጐዳናው ቁሞ የተመዘዘች ሰይፍ በእጁ ተይዞ አየው፤ በግምባሩም ተደፍቶ ሰገደለት ።

እግዚአብሔር የላከው መልአክም አህያህን ለምን መታሃት፤ እነሆ ሦስተኛህ ነው፤ ጐዳናህ በፊቴ የቀናች አይደለችምና እነሆ እኔም ላሰነክልህ መጣሁ፤ አህያህም ባየችኝ ጊዜ ከኔ ሸሸች እነሆ ይህ ሦስተኛህ ነው ።

ከኔ ባትሸሽ አሁን ፈጽሜ በገደልኩህ ነበር፤ እሷን ግን ባዳንኋት ነበር አለው ።

በለዓምም የእግዚአብሔርን መላክተኛ አንተ በጐዳና እንደተቃወምከኝ አላወቅሁምና በደልሁ፤ አሁን መሄዴን ካልወደድከ ልመለስን፤ አለው ። ፩ ሳሙ፤ ፲፭ ፳፬ ።

መልአከ እግዚአብሔርም ከነዚህ ሰዎች ጋር ሂድ፤ ነገር ግን እኔ ተናገር ያልኩህን ነገር ለመናገር ተጠበቅ በለዓምም ከባላቅ መልእክተኞች ጋራ ሄደ ።

ባላቅም በለዓም እንደመጣ በሰማ ጊዜ ከአውራጃቸው በአንድ ወገን ባለች በአርኖን ዳርቻ በሞዓብ አገር ወጥቶ ተቀበለው ። ዘኍ ፳፩ ፲፫ ።

ባላቅም በለዓምን ይጠሩህ ዘንድ ወዳንተ የላክሁ አይደለምን፤ ለምን ወደኔ ያልመጣህ፤ አንተን ማክበርህን ባልቻልሁ ነበርን፤ አለው ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ ናሁ መጻእኩ ኀቤከ ይእዜኒ ኢይክል ነቢበ ቃል ምንተኒ ዳዕሙ ዘወደየ እግዚአብሔር ውስተ አፉየ ወኪያሁ እትዓቀብ ለነቢብ ። | ፴፰ | በለዓምም ባላቅን እነሆ ወዳንተ መጣሁ ፤ አሁንም እግዚአብሔር በአንደበቴ ተናገር ያለኝን ያንን ለመናገር እጠበቃለሁ እንጂ ምንም ቃልን ለመናገር አልችልም አለው። |
| ወሖረ በለዓም ምስለ ባላቅ ወበኡ ውስተ ሀገረ ንድቅ ። | ፴፱ | በለዓምም ከባላቅ ጋር ሄዶ በኖራ ወደ ተቀጸረች ግንብ ገቡ ። ዘፍ፡ ፴፭ ፳፯ ፡ ኢያሱ ፲፭ ፲፫ ፡ ፲፬ - ፲፭ ። |
| ወጠብሐ ባላቅ አበግዐ ወአልሕምተ ወፈነወ ለበለዓም ወለመላእክት እለ ምስሌሁ ። | ፵ | ባላቅም ላሙን በጉን አርዶ ለበለዓምና ከሱም ጋር ላሉ አለቆች ላከላቸው ። |
| ወኮነ ሰበ ጸብሐ ነሥአ ባላቅ ለበለዓም ወአዕረጎ ውስተ ትእምርተ በዓአል ፡ ወአርአዮ እምህየ አሐደ ኀብረ እም ሕዝብ ። | ፵፩ | በነጋም ጊዜ እንዲህ ሆነ ፡ ባላቅ በለዓምን በበላአል ወዳለ ጣኦት ይዞት ወጣ ፡ ከዚያም ከሕዝቡ አንድ ወገኑን አሳየው ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳ ፡ ዘዳግ፡ ፲፪ ፪ ። |

ምዕራፍ ፳፫ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ ንድቅ ሊተ ዝየ ሰብዐተ መሣውዓተ ወአስተዳሉ ሊተ ዝየ ሰብዓተ አልሕምተ ወሰብዓተ አበግዐ ። | ፩ | በለዓም በዚህ ሰባት መሠውያዎችን ሥራልኝ፡ በዚህም ሰባት በሬችን ሰባት ላሞችን አዘጋጅልኝ አለው ። |
| ወገብረ ባላቅ በከመ ይቤሎ በለዓም ወአዕረገ ላሕመ ወበግዐ ላዕለ ምሥዋዕ ። | ፪ | ባላቅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ በመሠውያውም ላይ በጉንና ላሙን ሠዋ ። ዘኍ፡ ፳፫ ፬ ፡ ፲፬ - ፴ ። |
| ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ ቁም ኀበ መሥዋዕትከ ወአሑውር እመ ያስተርእየኒ እግዚአብሔር ቅድሜየ ወቃለ ዘአስተርአየኒ አየድዐከ ወቆመ ባላቅ ኀበ መሥዋዕቱ ። | ፫ | በለዓም ባላቅን በመሥዋዕትህ አጠገብ ቁም እግዚአብሔር ቢገልጽልኝ የነገረኝን ነገር እነግርሃለሁ አለው፡ ባላቅም በመሥዋዕቱ አጠገብ ቆመ ። |
| ወበለዓምሰ ሖረ ይሰአሎ ለእግዚአብሔር ወሖረ ርቱዐ፡ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለበለዓም ፡ ወይቤሎ በለዓም ለእግዚአብሔር ናሁ አስተዳለውኩ ለከ ሰብዓተ መሣውዓተ ወአዕረጉ ለከ ሰብዓተ አልሕምተ ወሰብዓተ አበግዐ ላዕለ ምሥዋዕ ። | ፬ | በለዓም ግን እግዚአብሔር ሊጠይቀው አቅንቶ ሄደ ፡ እግዚአብሔርም በለዓምን ታየው ተነጋገረው፡ በለዓም እግዚአብሔርን እነሆ ሰባት መሠውያዎችን አዘጋጀሁልህ በመሠውያዎቹም ላይ ሰባት በሬችንና ሰባት ላሞችን ሠዋሁልህ አለው ። |
| ወወደየ እግዚአብሔር ቃለ ውስተ አፉሁ ለበለዓም ፡ ወይቤሎ ግባእ ኀበ ባላቅ ወከመዝ በል ። | ፭ | እግዚአብሔር በለዓምን አናገረው ወደ ባላቅ ተመልሰህ እንዲህ ብለህ ተናገር አለው ። ዘዳ፡ ፲፰ ፲፰ ። |
| ወገብአ ኀቤሁ ወረከቦ ይቀውም ኀበ መሥዋዕቱ ወኵሎሙ መላእክተ ሞአብ ምስሌሁ ፡ ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ምስለ ነገር ። | ፮ | ወደሱም ተመልሶ በመሥዋዕቱም አጠገብ ቁሞ አገኘው ፡ የሞዓብም አለቆች ከሱ ጋር ቁመው ነበር፡ ትንቢት ከመናገር ጋርም መንፈስ ቅዱስ ወደሱ መጣ ። |
| ወይቤ እመስጴጦምያ ጸውዐኒ ባላቅ ንጉሠ ሞአብ እምደወለ ጽባሕ እንዘ ይብል ፡ ነዐ ርግሞ ሊተ ለያዕቆብ ወነዓ ጸአሎ ሊተ ለእስራኤል ። | ፯ | የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ መጥተህ ያዕቆብን ርገምልኝ እስራኤልንም ስደብልኝ ብሎ የምሥራቅ አውራጃ ከምትሆን ከመስጴጦምያ ጠራኝ አለ ። ዘኍ፡ ፳፬ ፫ ፡ ፳፪ - ፯ ። |
| ምንተ እጼእል ዘእግዚአብሔር ኢጸአለ ወምንተ እረግም ዘእግዚአብሔር ኢረገመ ። | ፰ | እግዚአብሔር ያልረገመውን ምን ብዬ እረግማለሁ፤ እግዚአብሔር ያልሰደበውን ምን ብዬ እሰድበለሁ፤ ። |
| እስመ እምአርእስተ አድባር እሬእዮ፡ ወእምአውግር እሔብዮ ፡ ናሁ ሕዝብ ዘበሕቲቱ የኀድር ወኢይትኌለቍ ውስተ አሕዛብ ። | ፱ | ከመኳንንቱና ከነገሥታቱ በላይ ሁኖ አየዋለሁና እነሆ ይኸውም ተዘልሎ የሚኖር ወገን ነው፡ በአሕዛብ ዘንድ አይቈጠርም ። |
| መኑ የአምሮ ለዘርአ ያዕቆብ ወመኑ ይኌልቆ ለሕዝበ እስራኤል ወትሙት ነፍስየ ምስለ ነፍሶሙ ለጻድቃን ወይኩን ዘርእየ ከመ ዘርኦሙ ለእሉ ። | ፲ | የያዕቆብን ልጅ ማን ያውቀዋል፤ የእስራኤልንስ ወገን ማን ይቈጥረዋል፤ ሰውነቴ ከእስራኤል (ጻድቃን) ሰውነት ጋር ትሙት ልጄም እንደነሱ ልጆች ይሁኑ አለ ። |
| ወይቤሎ ባላቅ ለበለዓም ለምንት ረሰይከኒ ከመዝ አኮኑ ትርግሞ ሊተ ፀርየ ጸዋዕኩከ ወናሁ ባርኮ ባረከ ። | ፲፩ | ባላቅም በለዓምን ለምን እንዲህ አደረግኸኝ ጠላቶቼን እንድትረግምልኝ ጠራሁ ፡ እነሆ ምርቃትን ትመርቃለህ፤ አለው ። ዘኍ፡ ፳፪ ፲፩ ። |
| ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ አኮኑ ኵሎ ቃለ ዘወደየ እግዚአብሔር ውስተ አፉየ ኪያሁ እትዓቀብ ለነቢብ ። | ፲፪ | በለዓምም ባላቅን እግዚአብሔር በአንደበቴ ተናገር ያለኝን ሁሉ ቃል መናገር እጠበቅ ዘንድ ያልኩህ አይደለምን አለው ። ዘኍ፡ ፳፪ ፴፰ ። |
| ወይቤሎ ባላቅ ነዓ ዓዲ ምስሌየ ካልአ መካነ ኀበ ኢት | ፲፫ | ባላቅም ከኔ ጋር ና ፡ ዳግመኛ ከነሱ ከምታየው ከንዱ |

ሬእዮሙ በሀየ ዘእንበለ አሐዱ ኅብር ዘትሬኢ እምኔሆሙ ወኵሎሙሰ ኢትሬኢ ወርግሞሙ ሊተ በሀየ ።
፲፬ ወነሥኦ ወአዕርጎ ውስተ ገዳም ውስተ ርእሰ ደብር ዘውቅሮ ወነደቀ ሰብዐተ ምሥዋዓተ ወአዕረገ ላሕመ ወበግዐ ላዕለ ምሥዋዕ ።
፲፭ ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ ቁም ኀበ ምሥዋዕ ፡ ወአንሰ አሐውር እሰአሎ ለእግዚአብሔር ።
፲፮ ወተራከቦ እግዚአብሔር ለበለዓም ወወደየ ቃለ ውስተ አፉሁ ወይቤሎ ግባእ ኀበ ባላቅ ወከመዝ በል ።
፲፯ ወገብአ ኀቤሁ ወረከቦ ይቀውም ኀበ ምሥዋዕ ወኵሎሙ መላእክተ ሞአብ ምስሌሁ ፡ ወይቤሎ ባላቅ ለበለዓም ፡ ምንተ ይቤ እግዚአብሔር ምስለ ነገር ።
፲፰ ወይቤ ተንሥእ ወስማዕ ወአፅምእ ባላቅ ወልደ ሰፎር ።
፲፱ አኮ ከመ ሰብእ ዘይትዔዋሀ እግዚአብሔር ወአኮ ከመ እጓለ እመሕያው ዘይትሜኣክ አንተሰ ትቤ ኢይገብር ወኢይነብበኒ ወኢያበጽሕ ።
፳ ናሁ ለበርኮ መጻእኩ እባርክ ፡ ወኢይትመየጥ ።
፳፩ አልቦ ፃማ ውስተ ያዕቆብ ወኢያስተርኢ ሕማም ላዕለ እስራኤል ፡ እግዚአብሔር አምላኩ ምስሌሁ ወክብረ መላእክት ሎቱ ።
፳፪ እግዚአብሔር ዘአውፅኦ እምብሔረ ግብጽ ከመ ክብረ ዘአሐዱ ቀርኑ ።
፳፫ አልቦ ሰገል ውስተ ያዕቆብ ወአልቦ መቅስም በውስተ እስራኤል ወለለመዋዕሊሁ ይትበሀል ለያዕቆብ ወለእስራኤል ምንተ ይገብር እግዚአብሔር ።
፳፬ ናሁ ሕዝብ ዘይትነሣእ ከመ እጓለ አንበሳ ወይትሔር ከመ አንበሳ ዘኢይነውም እስከ ይበልዕ ዘነሠአ ወይሰቲ ደመ ዘቀተለ ።
፳፭ ወይቤሎ ባላቅ ለበለዓም ኢ መርገመ ትረግሞሙ ሊተ ወኢ በርኮ ትባርኮሙ ።
፳፮ ወአውሥኦ በለዓም ለባላቅ ወይቤሎ ኢይቤለከኑ እንዘ እብል ቃለ ዘይቤለኒ እግዚአብሔር ኪያሁ እገብር ።
፳፯ ወነሥኦ ባላቅ ለበለዓም ውስተ ርእሰ ፌጎር ዘየዐውድ ውስተ ገዳም ።
፳፰ ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ ንድቅ ሊተ ዝየ ሰብዐተ ምሥዋዓተ ፡ ወአስተዳሉ ሊተ ዝየ ሰብዐተ አልሕምተ ወሰብዐተ አባግዐ ።
፳፱ ወገብረ ባላቅ በከመ ይቤሎ በለዓም ወአዕረገ ላሕመ ወበግዐ ላዕለ ምሥዋዕ ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

፩ ወሶበ ርእየ በለዓም ከመ ሠናይ ውእቱ ቅድመ እግዚአብሔር በርኮቶ ለእስራኤል ፡ ኢሖረ በከመ ያለምድ መንገሬ ቅድሜሁ ለአስተቃስሞ ወሜጠ ገጾ መንገለ ምሥራቅ ዘገዳም ።

ወገን በቀር ሌላ ወደማታይበት በታ ልውሰድህ ፡ ሁሉን ግን አታይም በዚያው ርገምልኝ አለው ።

የኖራ ግምብ ወዳለበት ተራራ ይዞ አዘረው ፡ ሰባት መሠውያንም ሠራ ፡ በመሠውያውም ላይ በጉንና ላሙን ሠዋ ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፱፡ ፳፫ - ፬ ።

በለዓም ባላቅን በመሠውያው አጠገብ ቁም ፡ እኔ እግዚአብሔርን እጠይቀው ዘንድ እሄዳለሁ አለው ።

እግዚአብሔርም በለዓምን ተገናኘው እንዲናገርም አደረገው ፡ ወደ ባላቅ ተመልሰህ እንዲህ ብለህ ተናገር አለው ። ዘኍ፡ ፳፪ ፴፭ ።

ወደሱም ተመልሶ በመሠውያው አጠገብ ቆሞ አገኘው የሞዓብም አለቆች ሁሉ ከርሱ ጋር ቆመው ነበሩ ፡ ባላቅም ነገርን ከመናገር ጋራ እግዚአብሔር ምን አለ አለው።

የሰፎር ልጅ ባላቅ! ተነሥተህ ስማ አለ ።

እግዚአብሔር እንደሰው የሚታለል አይደለምና እንደሰውም የሚቈጣ አይደለምና አንተ ግን ነገሬን ላያደርግልኝ አደርግልሃለሁ ይለኛል ፡ ወደ እግዚአብሔርም እያደርስልኝም ትላለህ አለው ።

እነሆ ለመመረቅ መጥቻለሁ (እስራኤልን ከመመረቅ) አልመለስም ። ዘፍ፡ ፲፪ ፫ ፡ ዘኍ፡ ፳፬ ፲፱ ።

በያዕቆብ ድካም የለም በእስራኤልም ላይ ደዌ አይታይም ፈጣሪው እግዚአብሔር (በረድኤት) ከሱ ጋር አለ የመላእክትም ክብር ለሱ ነው ። መዝ፡ ፺ ፲፬ ፡ ፹፱ ፲፭ ።

እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር ያወጣው እሱ በአንድ ቀንዱ ክብሮ እንደሚኖር አንድ ርኤም ነው ።

በእስራኤል ጥንቈላ የለም ፡ በእስራኤል ሟርት የለም እየወራቱ እስራኤል ለተባለ ያዕቆብ እግዚአብሔር ምን ያደርግለት ይሆን፣ ይባላል ። ዘዳ፡ ፲፰ ፲ ።

እነሆ እስራኤል እንደ አንበሳ ግልገል በማስፈራራት ይነሣል ፡ ያደነውን እስኪበላ የገደለውንም ደም እስኪጠጣ ድረስ እንደማይተኛ እንደ አንበሳ ይደነፋል አለ ።

ባላቅም በለዓምን ምርቃትን ትመርቃቸዋለህ እንጂ ርግማንን አትረግምልኝም ፣ አለው ።

በለዓምም ለባላቅ እግዚአብሔር ያለኝን ቃል እናገራለሁ ብዬ የነገርኩህ አይደለምን ብሎ መለሰለት ።

ባላቅ በለዓምን በምድረ በዳ ዙሮ ወደ ሚገቡበት ጣኦት ወደ ቆመበት ተራራ አወጣው ። ዘኍ፡ ፳፫ ፲፫ ።

በለዓምም ባላቅን በዚህ ሰባት መሠውያዎችን ሥራልኝ ፡ በዚህ ሰባት በጎችንና ሰባት ላሞችን አዘጋጅልኝ አለው ። ዘዳ፡ ፬ ፫ ፡ መዝ፡ ፻፮ ፳፰ ።

ባላቅም በለዓም እንዳለው አደረገ፣ በጉንና ላሙን በመሠውያው ላይ ሠዋ ። ዘዳ፡ ፫ ፲፯ ፳፯ ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

በለዓም በእግዚአብሔር ዘንድ እስራኤልን መመረቅ በጎ እንደሆነ በየ ጊዜ ፡ ለማሟረት እንደ ልማዱ አቅንቶ አልሄደም ፡ ፊቱንም ወደ በሐይ መውጫ ምድረ በዳ መለሰ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወአልዐለ አዕይንቲሁ ወርእዮሙ ለእስራኤል እንዘ ይግዕዙ በበሕዘቢሆሙ ወመጽአ ላዕሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር ምስለ ነገር ። | ፪ | ዐይኖቹን አቅንቶ በተመለከተ ጊዜ እስራኤልን በየ ወገኖቻቸው ሲጓዙ አያቸው ፣ ነገር ከማናገር ጋራ የእግዚ አብሔር መንፈስ ረድኤት ወደሱ መጣ ። ዘኍ፡ ፪ ፪ ። |
| ወይቤ በለዓም ወልደ ቢዖር ብእሲ ራትዕ ይቤ ዘይሬኢ ራእየ እምእግዚአብሔር ዘክሡታት አዕይንቲሁ እንዘ ይነውም ። | ፫ | ቅን ሰው የሚሆን የእግዚአብሔርን ራእይ የሚያይ ተኝቶ ሳለ ዓይኖቹን የገለጠው የቤዖር ልጅ በለዓም ። |
| እፎ ሠናይ አብያቲከ ያዕቆብ ወተዓይኒከ እስራኤል ። | ፬ | ያዕቆብ ወገንህ ምን ያምር ! እስራኤል ሰፈርህ (ሠራዊትህ) ምን ያምር ! አለ ። |
| ከመ አእዋም ዘይጼልሉ ወከመ ገነት ዘኀበ ፈለግ ወከመ ትዕይንት ዘተከለ እግዚአብሔር ወከመ አርዝ ዘኀበ ማይ ። | ፭ | እንደሚጋርዱ ዛፎች በውኃ ዳር ያለ ዛፍም ያማረ እንደሆነ እግዚአብሔር እንደተከለው ከተማ በፈሳሽ አጠገብ እንደ ያለም ተክል ደስ እንደሚያሰኝ ምን ያምር ! ። |
| ወይወጽእ ብእሲ እምዘርኡ ወይቀኒ ብዙኀነ አሕዛበ ወትትሌዐል እምአጋግ መንግሥቱ ወተዐቢ ። | ፮ | ከልጁ (ከዳዊት) ሰሎሞን (ክርስቶስ) ይወለዳል ፣ ብዙ አሕዛብን ይገዛል ፣ መንግሥቱም ከአጋግ መንግሥት ከፍ ይላል ይበልጣልም ። ኤር፡ ፶፩ ፲፫ ። |
| ወእግዚአብሔር መርሖ እምግብጽ ከመ ክብረ ዘአሐዱ ቀርኑ ውእቱ ሎቱ ፣ ወይበልዖሙ ለአሕዛብ ፀሩ ወያስተና ንዖ ስብሖሙ ወይነድፎሙ በአሕፃሁ ለፀሩ ። | ፯ | እግዚአብሔር ከግብጽ መርቶ ያወጣቸው እስራኤል ቀንዱ አንድ እንደሆነ በቀንዱ ተከብሮ እንደሚኖር እንደ ርኤም ነው ፣ ጠላቶቹ አሕዛብን ያጠፋቸዋል የአሕዛብ ገን ዘባቸውን ይበላል ፣ ጠላቶቹንም በጦር ይወጋቸዋል ። |
| ይሰክብ ወየዐርፍ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ መኑ ያነቅሆ ። | ፰ | አበት አንበሳና ግልገል አንበሳ በልቶ ጠጥቶ ዐርፎ ይተኛል ፣ ከተኛበትም የሚቀሰቅሰው እንደሌለ እስራኤልን ማን ነው ! የሚነካው ። |
| እለ ይባርኩከ ቡሩካነ ይኩኑ ! ወእለ ይረግሙከ ርጉማነ ይኩኑ ። | ፱ | የሚመርቁህ የተመረቁ ይሁኑ ፣ የሚረግሙህም የተረገሙ ይሁኑ አለ ። ዘፍ፡ ፲፪ ፱ ፣ ፲፪ - ፫ ። |
| ወተምዐ ባላቅ ላዕለ በለዓም ወአስተጣፍሐ እደዊሁ ፣ ወይቤሎ ባላቅ ለበለዓም ከመ ትርግሞሙ ሊተ ለጸላእትየ ጸዋዕኩከ ወናሁ ባርኮ ትባርክ ሣልስከ ዝንቱ ። | ፲ | ባላቅም በበለዓም ተቈጥቶ እጁን አጨበጨበ ፣ ባላቅ በለዓምን ጠላቶቼን እንድትረግምልኝ ጠርቼህ ነበር ፣ እነሆ ግን ትመርቃቸዋለህ ፣ ይህም ሦስተኛህ ነው አለው ። |
| ወይእዜኒ እቱ ቤተከ እቤ ከመ አክብሮ አክብርከ ፣ ወይእዜሰ ኢወሀበከ እግዚአብሔር ክብረ ። | ፲፩ | አሁንም ወደ ቤትህ ግባ ማክበርን እንዳከብርህ ተና ግሬህ ነበር ፣ አሁን ግን እግዚአብሔር ክብሩን አልሰጠ ህም አለው ። |
| ወይቤሎ በለዓም ለባላቅ አኮኑ ለወዓልትከኒ እለ ለአክ ኀቤየ እቤሎሙ እንዘ እብል ፣ ለእመ ወሀበኒ ባላቅ ወርቀ ወብሩረ ምልአ ዝንቱ ቤት ኢይክል ተዐድዎ ቃለ እግዚ አብሔር ከመ እግበር ሠናየ አው እኩየ እምኀቤየ ኵሎ ዘይቤለኒ እግዚአብሔር ኪያሁ እብል ። | ፲፪ | በለዓም ባላቅን እንዲህ አለው ! ሙሉ ቤት ወርቅንና ብርን ቢሰጠኝ እግዚአብሔር ያለኝን ሁሉ እናገራለሁ እን ጂ ከልቤ አንቅቼ ክፉውንም በጎውንም አደርግ ዘንድ የእ ግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍ አልችልም ብየ ወደኔ ለላክሃቸው አሽከሮችህ የነገርኳቸው አይደለምን ። |
| ወይእዜኒ ናሁ አአቱ ቤትየ ፣ ወነዐ አይድዕከ ዘይገብሩ እሉ ሕዝብ ላዕለ ሕዝብከ በደኃሪ መዋዕል ምስለ ነገር ። | ፲፫ | አሁንም እነሆ ወደቤቴ እገባለሁ እነዚህ ወገኖች ትን ቢት ከመናገር ጋራ በኋላ ዘመን በወገኖችህ የሚያደርጉ ትን ና ልንገርህ አለው ። ዘፍ፡ ፵፱ ፭ ፣ ሚክ፡ ፮ ፭ ። |
| ወይቤ በለዓም ወልደ ቢዖር ብእሲ ራትዕ ይቤ ዘይሬኢ ። | ፲፬ | ቅን ሰው የሚሆን ራእይ የሚያይ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ ። |
| ወይሰምዕ ቃለ እግዚአብሔር ዘየአምር መዝራዕቶ ለልዑል ወርእየ ራእየ እግዚአብሔር ክሡታት አዕይንቲሁ እንዘ ይነውም እሬእዮ ። | ፲፭ | የልዑል እግዚአብሔርን ኃይል የሚያውቅ የእግዚአ ብሔርን ራእይ የሚያይ ተኝቶ ሳለ ዓይኖቹ ተገልጠው የሚያይ የቤዖር ልጅ በለዓም እስራኤልን ክብሮ አየዋ ለሁ አለ ። |
| ወአኮ ይእዜ አስተበፅዖ ወአኮ ዘይነውም ወይቀርብ ፣ ይሠርቅ ኮከብ እምያዕቆብ ወይትነሣእ እምእስራኤል ወያ ጠፍአሙ ለመሳእክተ ሞአብ ወይጼውዎሙ ለኵሎሙ ደቂቀ ሴት ። | ፲፮ | ነገር ግን ዛሬ አይደለም አደንቀዋለሁ ሳይደረግ የሚ ቀር አይደለም ፈጥኖ የሚደረግም አይደለም ፣ "ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል (ዳዊት ኮከብ ክርስቶስ ይወለዳል) ከእስራ ኤል ተወልዶ ንጉሥ ሁኖ ይነሣል" ፣ የሞአብን አለቆች ያጠፋቸዋል ፣ የሴትን ልጆች ሁሉ ይማርካቸዋል ። |
| ወይከውኖ ኤዶም ርስቶ ወይከውኖ ርስቶ ኤሳው ፀሩ | ፲፯ | ኤዶም ርስቱ ይሆነዋል ፣ ጠላቱ ዔሳውም ርስቱ ይሆ |

ወእስራኤልሰ ገብረ በኀይል ።

፲፰ ወይትነሣእ ብእሲ ኃያል እምያዕቆብ፣ ወያጠፍኦሙ ለእለ ድኅኑ እምሀገር ።

፲፱ ወርእዮሙ ለአማሌቅ ምስለ ነገር ወይቤ ቀዳሚሁ ለአሕዛብ አማሌቅ ወይጠፍእ ዘርኦሙ ።

፳ ወርእዮሙ ለቄኔዎን ምስለ ነገር ወይቤ ጽኑዕት አብይትከ፣ ወለእመሂ ውስተ ኰኵሕ አንበርከ እንጒሊከ ።

፳፩ ወለእመሂ ኮነ ለቤዖር እጕለ ጕሕሉት፣ አሶር ይፄውወከ ።

፳፪ ወርእዮ ለአግ ምስለ ነገር፣ ወይቤ አ፣ አ፣ መኑ የሐዩ አመ ይገብሮ እግዚአብሔር ለዝንቱ ።

፳፫ ወይወፅእ እምእዴሆሙ ለቀጥያዎን ወየአክዩ አሶር ለዕብራውያን፣ ወዕብራውያን የአክዩ በአሶር ወእሙንቱሰ ኅቡረ ይጠፍኡ ።

፳፭ ወተንሥአ በለዓም ወሐረ ወገብአ ውስተ ቤቱ፣ ወባላቅሂ አተወ ቤቶ ።

ምዕራፍ ፳፭ ።

፩ ወኀደሩ እስራኤል ውስተ ሰጢን ወተገመኑ ሕዝብ ወዘመዉ በአዋልደ ሞአብ ።

፪ ወጸውዕዎሙ ውስተ መሥዋዕተ አማልክቲሆን ወበልዑ ሕዝብ መሥዋዕቶን ወሰገዱ ለአማልክቲሆን ።

፫ ወተፈጸሙ እስራኤል በብዔል ፌጎር ወተምዐ፣ መዐተ እግዚአብሔር ላዕለ እስራኤል ።

፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ንሥኦሙ ለመላእክተ ሕዝብ ወተዘለፎሙ በእንተ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር ፀሐይ ይሴስል እምቅድመ መንሱተ መዐቱ ለእግዚአብሔር እምእስራኤል ።

፭ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል፣ ቅትሉ አሐዱ አሐዱ እምኔክሙ ሰብአ ቤትክሙ፣ እለ ገብሩ በብዔል ፌጎር ።

፮ ወናሁ አሐዱ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል መጽአ ወወሰዶ ለእኁሁ ኀበ መድናዊት በቅድመ ሙሴ ወበቅድመ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወእሙንቱሰ ሀለዉ ይበክዩ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ።

፯ ወሰበ ርእየ ፊንሐንስ ወልደ አልአዛር ወልደ አሮን ካህን ተንሥአ እማእከለ ትዕይንት ወነሥአ ረምሐ በእዴሁ።

፰ ወቦአ ወተለዎ ለውእቱ ብእሲ እስራኤላዊ ውስተ እቶን ወረገዞሙ ለክልኤሆሙ ለውእቱ ብእሲ እስራኤላዊ መንገለ ሐቌሁ፣ ወለይእቲ ብእሲት መድናዊት ወግአ እንተ መንገለ ኃፍረታ ወኀደገ መቅሠፍት እምእስራኤል ።

፱ ወኮኑ እለ ሞቱ በውእቱ መቅሠፍት ክልኤቱ እልፍ ወአርባዕ ምእት ።

፲ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣ ፊንሐስ ወልደ አልአዛር ወልደ አሮን ካህን አኀድጎ መዐትየ እምደቂቀ እስራኤል ።

ነዋል እስራኤል ግን ኃይልን አደረገ (በኃይሉ ሠራ) ።

፲፰ ከያዕቆብ ኃይለኛ ሰው (ዳዊት) ተነሥቶ ከአገር የዳኑትን ያጠፋቸዋል ።

፲፱ አማሌቅን ከነገር ጋራ አያቸው፣ የአሕዛብ ደገኛቸው (አለቃቸው) አማሌቅ ነው፣ ዘራቸውም ይጠፋል አለ ።

፳ ቄኔዎንንም ነገር ከማናገር ጋራ አያቸው ከፍትህ የጸናች ናት፣ ልጆችህን በዋሻ ውስጥ ብታኖር (ብታጸና) ።

፳፩ ለቤዖርም ተንኰል ያለኝ እኔ ብኖረው፣ ባቢሎናዊ ይማርክሃል ።

፳፪ አግንም ነገር ከማናገር ጋራ አየው፣ እግዚአብሔር ይህን ነገር ባደረገው ጊዜ ማን ይድናል ወዮ! ወዮ! አንክሮ ይገባል ።

፳፫ እስራኤል ከቀጥያዎን (ፅርዓውያን) እጅ ይድናል፣ ዕብራውያን በአሶራውያን አሶራውያንም በዕብራውያን ይከፋሉ፣ እነሳቸው ግን አንድነት ይጠፋሉ አለ ።

፳፭ በለዓም ተነሥቶ ወደ ቤቱ ሄደ፣ ባላቅም ወደ ቤቱ ገባ ። ዘኍ፣ ፴፩ ፰ ።

ምዕራፍ ፳፭ ።

፩ እስራኤል በሰጢን አደሩ (ሰፈሩ) ሕዝቡም ተዳደፈ፣ በሞዓብ ልጆችም ረከሰ (ሰሰነ) ። ዘኍ፣ ፴፫ ፵፱ ።

፪ ለጣኦቶቻቸው ወደ ሠዉት መሥዋዕት ጠሯቸው፣ መሥዋዕታቸውንም በልተው ለጣኦቶቻቸው ሰገዱ ።

፫ ጣኦቱንም በማምለካቸው እስራኤል ፈጽመው ጠፉ፣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ቍጣን ተቈጣ ።

፬ እግዚአብሔር ሙሴን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላፈረሱ የወገኖችን አለቆች ይዘህ ውቀሳቸው እግዚአብሔር ፈርዶ ካመጣው መዓት የተነሣ ረድኤቱም ከእስራኤል ይርቃል አለው ። ዘዳ፣ ፬ ፫፣ ኢያሱ ፳፪ ፲፯ ።

፭ ሙሴም የእስራኤልን ወገኖች ከናንተ አንዱም አንዱም በጣኦቱ ኃጢአትን የሠሩ የቤታችሁን ሰዎች ግደሉ አላቸው ። ዘፀ፣ ፴፪ ፳፯፣ ዘኍ፣ ፲፩ ፲፯፣ ፳፩ - ፳፰ ።

፮ እነሆ ከእስራኤል ልጆች የተወለደ አንድ ሰው መጥቶ በእስራኤል ልጆች ወገኖች ፊት ወንድሙን ወደ መድናዊት (ምድያም) ሴት ወሰደው እነሱ ግን በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሁነው ያለቅሱ ነበር ። ኢዮብ ፬ ፲፯ ።

፯ የካህኑ የአሮን ልጅ የአልአዛር ልጅ ፊንሐስ ይህን በየ ጊዜ ከሠራዊቱ መካከል ተነሥቶ በእጁ ዘገሩን ይዘ ።

፰ ከእስራኤል ወገን የተወለደ ያንን ሰው ተከትሎት ወደ ማደሪያ ቤት ድንኳን ገብቶ ሁለቱን ያንን ከእስራኤል የተወለደ ሰው ዳሌውን ወጋው ያችንም ሴት ማኅፀኗን ወጋት መቅሠፍቱም ከእስራኤል ጸጥ አለ ። ዘኍ፣ ፲፯ ፵፰ ።

፱ በዚያም መቅሠፍት የሞቱ ሰዎች ሁለት እልፍ ከራትሺሕ ሆኑ ። ፩ ቆሮ፣ ፲ ፰ ።

፲ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፣ አገልጋይ የሚሆን የአሮን ልጅ የአልአዛር ልጅ ፊንሐስ በእስራኤል ልጆች የተቈጣሁትን ቁጣ አስተወኝ (አበረደልኝ)።

፲፩ እስመ ቀንአ ሊተ ቅንአትየ ላዕሌሆሙ ወኢያጥፋእክ
ዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በቅንአትየ ።
፲፪ ወከመዝ አቤ ናሁ አነ እሁብ ሕገ ሰላም ።

፲፫ ወይኩኖ ሎቱ ወለዘርኡ እምድኅሬሁ ሕገ ክህነት ዘለ
ዓለም ፣ እስመ ቀንአ ለአምላኩ ወአስተስረየ ለደቂቀ እስ
ራኤል ።
፲፬ ወስሙ ለውእቱ ብእሲ እስራኤላዊ ዘተቀትለ ምስለ
መድናዊት ዘንበሪ ወልደ ሰሎ ፣ መልአክሙ ለሕዝበ
ስምዖን ።
፲፭ ወስማ ለይእቲ ብእሲት መድናዊት እንተ ተቀትለት
ክስቢ ወለተ ሱር መልአክሙ ለሕዝበ ሳሞት ዘቤተ አበዊ
ሆሙ ውእቱ ለምድያም ።
፲፮ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፣ ንግሮሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ተፃረርዎሙ ለሚድናውያን ወቅ
ትልዎሙ እስመ እሙንቱኒ ይፃረሩክሙ በጕሕሉት ።
፲፯ ወሁሉ ዘይትጐሐለወክሙ በእንተ ፌጎር ወበእንተ
ክስቢ ወለተ መልአክ ምድያም እኅቶሙ እንተ ተቀትለት
አመ ዕለተ መቅሠፍት በበይነ ፌጎር ።

## ምዕራፍ ፳፮ ።

፩ ወከነ እምድኅረ መቅሠፍት ነበቦሙ እግዚአብሔር
ለሙሴ ወለአልአዛር ካህን ።
፪ ወይቤሎሙ ንሥኡ እምጥንቱ ወኍልቈ ኵሎ ተዓይ
ኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ በበ
አብያተ አበዊሆሙ ኵሎ ዘይወፅእ ፀብአ እምውስተ እስ
ራኤል ።
፫ ወነገርዎሙ ሙሴ ወአልአዛር በአራቦት ዘሞአብ በኀበ
ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ።
፬ ወይቤልዎሙ ተፋቀዱ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ
በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ።
፭ ወደቂቀ እስራኤል እለ ወፅኡ እምግብጽ ሮቤል በኵሩ
ለእስራኤል ፤ ወደቂቀ ሮቤል ሄኖኅ ወነገደ ሄኖኅ ዘፋሉሊ
ነገደ ፋሉይ ።

፮ ዘአስሮንኒ ነገደ አስሮኒ ፣ ወዘከርም ነገደ ከርሚ ፤
እሉ ሕዝብ ዘሮቤል ።

፯ ወከነ ኍላቌሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወሰ
ብዓቱ ምእት ወሠላሳ ።
፰ ወደቂቀ ፋሉ ኤልያብ ፣ ወደቂቀ ኤልያብ ናሙኤል
ወዳታን ወአቤሮን ።
፱ እሉ ዐበይተ ትዕይንት እለ ቆሙ ላዕለ ሙሴ ወአሮን
ውስተ ትዕይንት ዘቆሬ አመ ተቃወሙ ላዕለ እግዚአብሔር ፤

፲ ወአብቀወት ምድር አፉሃ ወውኅጠቶሙ ወለቆሬኒ
ወሞቱ ወለትዕይንቲሆሙኒ ከልኤቱ ምእት ወሐምሳ በል
ዐቶሙ እሳት ወኮኑ ለተአምር ።

እኔ ለነሳቸው የምቀናውን ቅንአት ቀንቶልኛልና ስለ
ምላክነቱ ቀንቶ የእስራኤልን ልጆች አላጠፋኋቸውም ።
እንዲህም አልሁ እነሆ እኔ ሕገ ሰላምን (ሕገ ክህ
ነትን) እሰጠዋለሁ ። ሚል፡ ፪ ፭ ።
ለፈጣሪው ቀንቶአልና ለእስራኤልም ልጆች ኃጢአታ
ቸውን አቀሏልና ለርሱ ከርሱም በኋላ ለልጅ ልጆቹ ይሆ
ነው ዘንድ የዘለዓለም ሕገ ክህነትን እሰጠዋለሁ አልሁ ።
የሞተው የለዩ እስራኤላዊ ሰው ስሙ የስምዖን ወገ
ኖች አለቃ የሚሆን የሰሎ ልጅ ዘንበሪ ይባላል ።

ከምድያም የተወለደች የዚያች የተገደለችው ሴት
ስም የምድያም አባቶች ወገን የሚሆን የሳሞት ወገኖች
አለቃ የሱር ልጅ ክስቢ ይባላል ። ዘኍ፡ ፴፩ ፰ ።
እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው የሚድናውያንን ሰዎ
ች ተጣሏቸው ግደሏቸውም ፣ እነሱ በተንኰል ይጣሏች
ኋልና ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው ።
ስለ ጣኦቱ የሚሸነግላችሁ ሁሉ ጣኦት ስላመለኩ
መቅሠፍት በታዘዘበት ቀን ስለ ሞተችው እኅታቸው ስለ
ምድያም አለቃ ልጅ ስለ ክስቢ ይጣሏችኋልና ተጣሏቸው
በላቸው አለው ። ዘኍ፡ ፴፪ ፲፯ ፣ ራእ፡ ፪ ፲፬ ።

## ምዕራፍ ፳፮ ።

ከመቅሠፍት (እስራኤል ከጠፉ) በኋላ እንዲህ ሆነ
ለካህኑ ለአልአዛርና ለሙሴ እግዚአብሔር ተናገራቸው ።
ከሃያ ዓመት ጀምሮ ያለውን ከዚያም በላይ የሆነውን
በየ አባቶቻቸው ወገኖች ከእስራኤል ወደ ጦር የሚወ
ጣውን ሁሉ የእስራኤልን ልጆች ሠራዊት ሁሉ ከመጀመ
ሪያው (ከሮቤል) ጀምራችሁ ቍጠሩ አላቸው ።
አልአዛርና ሙሴም በዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ አጠገብ
ባለች በሞዓብ አውራጃ በአራቦት ነገሩዋቸው ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ከሃያ ዓመት ጀምሮ
ያለውን ከዚያም በላይ የሆነውን ተቈጣጠሩ አሏቸው ።
ከግብጽም የወጡ የእስራኤል ልጆች እኒህ ናቸው ፣
የያዕቆብ የበኩር ልጁ ሮቤል ነው ፣ የሮቤልም ልጆች የሄ
ኖኅ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሄኖኅ ወገኖች የፋሉሊ
ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የፋሉይ ወገኖች ።
የአስሮኒ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአስሮኒ ወገኖች
የከርሚ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የከርሚ ወገኖች የሮ
ቤል ወገኖች እሊህ ናቸው ።
ቍጥራቸውም አራት እልፍ ሦስት ሺሕ ሰባት መቶ
ሠላሳ ሆነ ። ዘኍ፡ ፩ ፳፩ ።
የፋሉ ልጅ ኤልያብ ነው ፣ የኤልያብም ልጆች ናሙ
ኤል ዳታን አቤሮን ናቸው ።
እግዚአብሔርን በተቃወሙ ጊዜ ከቆሬ ወገኖች ጋራ
በአሮንና በሙሴ ላይ በጠላትነት የተነሡ የሠራዊቱ አለ
ቃዎች እሊህ ናቸው ። ዘኍ፡ ፪ ፲፮ ፣ ፲፯ - ፪ ።
ምድርም አፏዋን ከፍታ ዋጠቻቸው ፣ ቆሬንም ዋጠ
ችው ሞቱም ሁለት መቶ አምሳ (ካህናት) ሰዎች እሳት
በላቻቸው ለምልክትም ሆኑ ። ዘኍ፡ ፲፮ ፴፪ ።

፲፩ ወደቂቀ ቆሬስ ኢሞቱ ።

(ከነገሩ ያልገቡ) የቆሬ ልጆች ግን አልሞቱም ።

፲፪ ወደቂቀ ስምዖንሂ ዘናሙሔል ውስተ ነገደ ደቂቀ ናሙሔል ፤ ወዘኢያምንሂ ውስተ ነገደ ደቂቀ ኢያምኒ ፤ ወዘኢያክንሂ ውስተ ነገደ ደቂቀ ኢያክኒ ።

የስምዖንም ልጆች የናሙሔል ልጆች ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የናሙሔል ወገኖች ፤ የኢያምን ልጆች ተብለው የሚቈጠሩ የኢያምኒ ልጆች የኢያክንም ልጆች ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የኢያክኒ ልጆች ።

፲፫ ወዘዛሬሂ ውስተ ነገደ ደቂቀ ዛሬይ ፤ ወዘሰውልሂ ውስተ ነገደ ሳውል ።

የዛሬ ልጆች ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የዛራይ ልጆች የሳውል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሳውል ወገኖች ።

፲፬ እሉ ሕዝብ ዘስምዖን ወኍላቈሆሙ ክልኤቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወክልኤቱ ምእት ።

የስምዖን ወገኖች እነህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም ሁለት እልፍ ሁለት ሺሕ ሁለት መቶ ነው ። ዘኍ ፩ ፳፫ ።

፲፭ ወደቂቀ ይሁዳ ዔር ወአውናን ወሴሎን ወፋሬስ ወዛራ ፤ ወሞቱ ዔር ወአውናን በምድረ ከነአን ።

የይሁዳም ልጆች ኤር አውናን ፋሬስ ሴሎንና ዛራ ናቸው ፤ አውናንና ኤር በከነዓን ምድር ሞቱ ።

፲፮ ወኮኑ ደቂቀ ይሁዳ በበሕዘቢሆሙ ዘሴሎን ውስተ ነገደ ሴሎኒ ፤ ወዘፋሬስ ውስተ ነገደ ፋሬስ ፤ ወዘዛራ ውስተ ነገደ ዛራይ ።

በየወገኖቻቸው የሚቈጠሩ ፤ የይሁዳ ልጆች እንዲህ ሆኑ ፤ የሴሎም ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሴሎሚ ወገኖች የፋሬስ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የፋሬስ ወገኖች ፤ የዛራ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የዛራይ ወገኖች ፤ እሊህ ናቸው ።

፲፯ ወኮኑ ደቂቀ ፋሬስ ዘአሴሮን ውስተ ነገደ አሴሮኒ ፤ ወዘያሙሔልሂ ውስተ ነገደ ያሙሔሊ ።

የፋሬስም ልጆች እንዲህ ሆኑ የአሴሮን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአሴሮኒ ወገኖች የያሙሔል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የያሙሔሊ ወገኖች ።

፲፰ እሉ ሕዝብ ዘይሁዳ ወኍላቈሆሙ ሰብዓቱ እልፍ ወስሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት ።

የይሁዳ ወገኖች እነህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም ሰባት እልፍ ስድስት ሺሕ አምስት መቶ ነው ። ዘኍ ፩ ፳፯ ።

፲፱ ወደቂቀ ይሳኮርሂ በበሕዘቢሆሙ ዘቶላ ውስተ ነገደ ቶላይ ፤ ወዘፎሐ ውስተ ነገደ ፎሐይ ።

በየወገኖቻቸው የሚቈጠሩ የይሳኮር ልጆች እሊህ ናቸው ፤ የቶላ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የቶላይ ወገኖች የፎሐ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የፎሐይ ወገኖች ።

፳ ወዘያሱብ ውስተ ነገደ ያሱብ ፤ ወዘሠምራ ውስተ ነገደ ሠምራይ ።

የያሱብ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የያሱብ ወገኖች ፤ የሠምራ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሠምራይ ወገኖች ።

፳፩ እሉ ሕዝብ ዘይሳኮር ወኍላቈሆሙ ሰብዓቱ እልፍ ወአርባዕ ምእት ወሠለስቱ ምእት ።

የይሳኮር ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም ሰባት እልፍ አራት ሺሕ ሦስት መቶ ነው ።

፳፪ ወደቂቀ ዛብሎንሂ በበሕዘቢሆሙ ዘሳሬድ ውስተ ነገደ ሳሮድይ ፤ ወዘአሎ ውስተ ነገደ አሎኒ ፤ ወዘአሎኒ ውስተ ነገደ አሎልይ ።

በየወገኖቻቸው የሚቈጠሩ የዛብሎን ልጆች የሳሬድ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሳሮድይ ወገኖች ፤ የአሎ ወገኖች ተብለው የሚቈጠሩ የአሎኒ ወገኖች ፤ የአሎልይ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአሎልይ ወገኖች ።

፳፫ እሉ ሕዝብ ዘዛብሎን ወኍላቈሆሙ ሰብዓቱ እልፍ ወሐምስቱ ምእት ።

የዛብሎን ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም ሰባት እልፍ አምስት መቶ ነው ። ዘፍ ፵፮ ፲፫ ፤ ፩ ዜና ፯ ፩ ።

፳፬ ወደቂቀ ጋድሂ በበሕዘቢሆሙ ዘሳፎን ነገደ ሳፎኒ ፤ ወዘሐግ ውስተ ነገደ ሐጊ ፤ ወዘሱኒ ነገደ ሱኒይ ።

በየወገኖቻቸው የጋድ ልጆች የሳፎኒ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሳፎኒ ወገኖች የሐጊ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሐጊ ወገኖች ፤ የሱኒ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሱኒይ ወገኖች ። ዘፍ ፵፮ ፲፫ ።

፳፭ ወዘአዜን ውስተ ነገደ አዜኒ ፤ ወዘሰደፍ ውስተ ነገደ ሰድፍይ ።

የአዜን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአዜን ወገኖች ፤ የሳደፍ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሰድፍይ ወገኖች ።

፳፮ ወዘአሩሐድ ውስተ ነገደ አሩሐዲ ፤ ወዘአሩሔል ውስተ ነገደ አሩሔሊ ።

የአሩሐድ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአሩሐዲ ወገኖች ፤ የአሩሔል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአሩሔሊ ወገኖች ። ዘፍ ፵፮ ፲፫ ።

፳፯ እሉ ሕዝብ ዘጋድ ወኍላቈሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሐምስቱ ምእት ።

የጋድ ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም አራት እልፍ አምስት መቶ ነው ። ዘኍ ፩ ፴፩ ።

፳፰ ወደቂቀ አሴርሂ በበሕዘቢሆሙ ዘኢያምን ውስተ ነገደ ኢያምኒ ፤ ወዘኢያሱ ውስተ ነገደ ኢያሱይ ፤ ወዘበርያ ውስተ ነገደ በራይ ።

በየወገኖቻቸው የሚቈጠሩ የአሴር ልጆች የኢያምኒ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የኢያምኒ ወገኖች የኢያሱ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የኢያሱይ ወገኖች ፤ የበርያ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የበራይ ወገኖች ። ዘፍ ፵፮ ፳ ።

፳፱ ወዘኮበር ውስተ ነገደ ኮበሬ ፤ ወዘምልክያል ውስተ

የኮበር ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የኮበሬ ወገኖች የም

| | | |
|---|---|---|
| ነገደ ምልክያል ። | | ልክያል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የምልክያል ወገኖች። |
| ወስማ ለወለተ አሴር፣ ሳራ ። | ፴ | የአሴር ልጅ ስሟ ሣራ ይባላል ። ኢያሱ ፲፯ ፪ ። |
| እሉ ሕዝበ አሴር ወኍላቌሆሙ ሐምስቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወአርበዐቱ ምእት ። | ፴፩ | የአሴር ወገኖች እሊህ ናቸው፣ ቍጥራቸውም አምስት እልፍ፣ ሦስት ሺሕ አራት መቶ ነው ። |
| ወደቂቀ ዮሴፍ በበሕዘቢሆሙ ምናሴ ወኤፍሬም ። | ፴፪ | በየወገኖቻቸው የሚቈጠሩ የዮሴፍ ልጆች ኤፍሬምና ምናሴ ናቸው ። |
| ወደቂ ምናሴ ዘማኪር ነገደ ማኪሬ፣ ወማኪር ወለዶ ለገለአድ፣ ወዘገለአድ ነገደ ገለአዲ ። | ፴፫ | የምናሴም ልጆች የማኪሬ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የማኪር ወገኖች፣ ማኪርም ገለአድን ወለደው የገለአድ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የገለአዲ ወገኖች ። |
| እሉ ደቂቀ ገለአድ ዘአክያዜር ነገደ አክያዜር፣ ወዘኬሌግ ነገደ ኬሌጊ ። | ፴፬ | የገለአድ ልጆች እሊህ ናቸው፣ የአክያዜር ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአክያዜር ወገኖች ። ዘኍ፣ ፩ ፴ ። |
| ወዘኢሳርያል ነገደ ኢሳርያሊ፣ ወዘሴኬም ነገደ ሴኬሚ ፤ | ፴፭ | የኢሳርያል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የኢሳርያሊ ወገኖች፣ የሴኬም ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሴኬሚ ወገኖች። |
| ወዘሲማኤር ነገደ ሲማኤሬ፣ ወዘዖፌር ነገደ ዖፌሬ ። | ፴፮ | የሲማኤር ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሲማኤሬ ወገኖች፣ የዖፌር ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የዖፌሬ ወገኖች። |
| ወለሰለጰአድ ወልደ ዖፌር አልቦቱ ደቂቀ ዘእንበለ አዋልድ፣ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆን መሐላ፣ ወኑሓ፣ ወሔግላ፣ ወሚልካ፣ ወቴርሳ ። | ፴፯ | ለዖፌር ልጅ ለሰለጰአድ ግን ከሴቶች ልጆች በቀር ወንድ ልጅ አልነበረውም ፤ ስማቸውም ይህ ነው መሐላ፣ ኑሓ፣ ሔግላ፣ ሚልካ፣ ቴርሳ፣ ናቸው ። ዘኍ፣ ፳፯ ፩ ። |
| ዝንቱ ሕዝበ ምናሴ ወኍላቌሆሙ ሐምስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወሰብዐቱ ምእት ። | ፴፰ | የምናሴ ወገን ይህ ነው ፤ ቍጥራቸውም አምስት እልፍ ሁለት ሺሕ ሰባት መቶ ነው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፷፬ ። |
| ወእሉ ደቂቀ ኤፍሬም ዘሱታላ ነገደ ሱታላይ፣ ወዘጣናሕ ነገደ ጣናሒ ። | ፴፱ | የኤፍሬም ልጆች እሊህ ናቸው ፤ የሱታላ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሱታላይ ወገኖች የጣናህ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የጣናሒ ወገኖች ። ፩ ዜና ፳ ፫ ። |
| እሉ ደቂቀ ሱታላ፣ ወዘአዴን ነገደ አዴኒ ። | ፵ | የሱታላ ልጆች እሊህ ናቸው ፤ የአዴን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአዴኒ ወገኖች ። ዘኍ፣ ፩ ፴፮ ። |
| እሉ ሕዝብ ዘኤፍሬም፣ ወኍላቌሆሙ ሠለስቱ እልፍ ወሰሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት ። | ፵፩ | የኤፍሬም ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም ሦስት እልፍ ስድስት ሺሕ አምስት መቶ ነው ። ዘኍ፣ ፳፮ ፷፫ ። |
| ወእሉ ሕዝብ ዘደቂቀ ዮሴፍ በበነገዶሙ፣ ወደቂቀ ብንያም በበነገዶሙ፣ ዘበዓል ነገደ በዓሊ፣ ወዘአሴቤር ነገደ አሴቤሬ፣ ወዘአኪራን ነገደ አኪራኒ፣ ወዘሰፈን ነገደ ሰፈኒ ። | ፵፪ | በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የብንያም ልጆችና በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የዮሴፍ ልጆች ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ የበዓል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የበዓል ወገኖች፣ የአሴቤር ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአሴቤሬ ወገኖች፣ የአኪራን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአኪራኒ ወገኖች፣ የሰፈን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሰፈኒ ወገኖች ። |
| ወኮኑ ደቂቀ በዓል አዴር ወኑሐሚን ነገደ ኑሐሚኒ ። | ፵፫ | የበዓል ልጆች እንዲህ ሆኑ (እሊህ ናቸው) አዴርና ኑሐሚን ናቸው፣ የኑሐሚን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የኑሐሚኒ ወገኖች ። |
| እሉ ደቂቀ ብንያም በበነገዶሙ ወኍላቌሆሙ አርበዕቱ እልፍ፣ ወሐምሳ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ። | ፵፬ | በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የብንያም ወገኖች እኒህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም አራት እልፍ አምስት ሺሕ ሰባት መቶ ነው ። |
| ወደቂቀ ዳንኒ በበነገዶሙ ዘዓሣ ነገደ ዓሣ እሉ ሕዝብ ዘዳን፣ በበነገዶሙ ወኍላቌሆሙ ስሱሉ ነገደ ዳን፣ ሰብዓቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት፣ ወአርበዐቱ ምእት ። | ፵፭ | በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የዳን ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ የዓሣ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የዓሣ ወገኖች፣ በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የዳን ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ የዳን ነገዶች ሁሉ ቍጥራቸው ሰባት እልፍ፣ አምስት ሺሕ አራት መቶ ነው ። ዘኍ፣ ፩ ፵፩ ። |
| ወደቂቀ ንፍታሌምኒ በበነገዶሙ ዘአሴሔል ነገደ አሴሔሊ፣ ወዘጉኒን ነገደ ጉኒኒ ። | ፵፮ | በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የንፍታሌም ልጆች የአሴሔል ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የአሴሔሊ ወገኖች፣ የጉኒን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የጉኒኒ ወገኖች ። |
| ወዘዴሴር ነገደ ዴሴሬ፣ ወዘሴሌም ነገደ ሴሌሚ ። | ፵፯ | የዴሴር ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የዴሴሬ ወገኖች፣ የሴሌም ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሴሌሚ ወገኖች ። |

፵፰ እሉ ሕዝብ ዘንፍታሌም ወኍላቌሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሐምስ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ።

የንፍታሌም ወገኖች እሊህ ናቸው ፤ ቍጥራቸውም አራት እልፍ ፡ አምስት ሺሕ አራት መቶ ነው ።

፵፱ ወዝንቱ ኍላቌሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፡ ስሳ እልፍ ወዓሠርቱ ምእት ፡ ወሰብዓቱ ምእት ወሠላሳ ።

የእስራኤል ልጆች ቍጥራቸው ይህ ነው ፡ ስድስት መቶ አንድ ሺሕ ሰባት መቶ ሠላሳ ነው ። ዘኍ ፩ ፵፮ ።

፶ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ እሉ እለ ይወርስዋ ለይእቲ ምድር በበመክፈልቶሙ ወበበኍልቈ አስማተ አበዊሆሙ ።

እግዚአብሔርም በየአባቶቻቸው ስምና በየዕፃቸው የትን ምድር የሚወርሷት እሊህ ናቸው ብሎ ለሙሴ ነገረው ። ኢያ፡ ፲፩ ፳፫ ፡ ፲፬ ፩ ።

፶፩ ለእለ ይበዝኁ ታበዝኅ መክፈልቶሙ ወለእለ ይውኅዱ ታውሕድ መክፈልቶሙ ወለለአሐዱ እምኔሆሙ በአምጣነ ኍልቆሙ ትሁቦሙ ወበዕፃሆሙ ይረክቡ መክፈልቶሙ እለ ተሰምዩ በበነገደ አበዊሆሙ ።

የብዙዎቹን ፈንታ አብዛላቸው የጥቂቶቹንም ፈንታ አሳንስባቸው ፡ ከነሳቸውም ለአንዱም ለአንዱም በቍጥራቸው ልክ ስጣቸው ። ዘኍ ፴፫ ፶፬ ፡ ፴፬ ፲፫ ።

፶፪ ወይወርስሙ እመክፈልቶሙ አበዊሆሙ ዘይረክቡ ርስቶሙ ማእከለ ብዙኃን ወውኁዳን ።

በየአባቶቻቸው ስም የተጠሩት እነዚህ ፈንታቸው በዕጣ ይድረሳቸው ፡ ከአባቶቻቸው የሚደርሳቸው ርስታቸውን በጥቂቶቹና በብዙዎቹ መካከል ይውረሱ ።

፶፫ ወደቂቀ ሌዊ በበነገዶሙ ዘጌድሶን ነገደ ጌድሶኒ ፡ ወዘቀዓት ነገደ ቀዓቲ ፡ ወዘሜራሪ ነገደ ሜራሪ ።

በየነገዳቸው የሚቈጠሩ የሌዊም ልጆች የጌድሶን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የጌድሶኒ ወገኖች የቀዓት ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የቀዓቲ ወገኖች የሜራሪ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሜራሪ ወገኖች ። ዘፍ፡ ፵፮ ፲፩ ።

፶፬ እሉ ሕዝብ ነገደ ደቂቀ ሌዊ ፡ ነገደ ሎቤኒ ፡ ወነገደ ኬብሮን ፡ ወነገደ ሙሐሊ ፡ ወነገደ ሐሙሲ ፡ ወነገደ ቆሬ ፡ ወነገደ ቀዓት ፡ ወቀዓት ወለዶ ለእንበረም ።

የሌዊ ልጆች ነገድ እነዚህ ናቸው ፤ የኬብሮን ነገድና የሎቤኒ ነገድ የሐሙሲ ነገድና የሙሐሊ ነገድ ፡ የቆሬ ነገድና የቀዓት ነገድ ፡ እነዚህ ናቸው ፡ ቀዓትም እንበረምን ወለደው ።

፶፭ ወስማ ለብእሲተ እንበረም ዮካብድ ወለተ ሌዊ ዘወለደቶሙ ለእሉ ሌዋውያን በብሔረ ግብጽ ፡ ወወለደት ሎቱ ለእንበረም አሮንሃ ወሙሴሃ ወማርያምሃ እኅቶሙ ።

በግብጽ አገር እነዚህ ሌዋውያንን የወለደቻቸው የሌዊ ልጅ የእንበረም ሚስት ስሟ ዮካብድ ይባላል ፡ ለእንበረምም ሙሴንና አሮንን እኅታቸው ማርያምንም ወለደችለት ። ዘፀ ፪ ፩ ፡ ፮ ፳ ።

፶፮ ወተወልዱ ለአሮን ናዳብ ፡ ወአብዩድ ፡ ወአልአዛር ወይታምር ።

ለአሮንም አብዩድና ናዳብ ፡ ይታምርና አልአዛር ተወለዱለት ። ዘኍ ፫ ፪ ፡ ፩ ዜና ፳፬ ፩ ።

፶፯ ወሞቱ ናዳብ ወአብዩድ አመ አብኡ እሳተ ዘእምባዕድ ቅድመ እግዚአብሔር በገዳም ዘሲና ።

አብዩድና ናዳብ በሲና ምድረ በዳ ከሌላ እሳት አምጥተው ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን በገቡ ጊዜ ተቀሠፉ ። ዘሌዋ፡ ፲ ፩ ።

፶፰ ወኮነ ኍላቌሆሙ ክልኤቱ እልፍ ፡ ወሠላሳ ምእት ፡ ኵሉ ተባዕት ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ፡ እስመ ኢተኈለቁ ምስለ ደቂቀ እስራኤል እስመ ኢተውህበ ሎሙ መክፈልት ማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

በእስራኤል ልጆች መካከል ፈንታ ስለ አልተሰጣቸው ከእስራኤል ልጆች ጋር አልተቈጠሩም ነበርና ፡ ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ ቍጥራቸው ሃያ ሦስት ሺሕ ሆነ ። ዘኍ ፫ ፴፱ ፡ ፩ ፵፱ ።

፶፱ ወከመዝ ውእቱ አስተፋቅዶቶሙ ለሙሴ ወለአልአዛር ካህን እለ ኈለቍዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በአራቦት ዘሞአብ በኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ።

በዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ አጠገብ ባለችው በሞዓብ አውራጃ በአራቦት የእስራኤልን ልጆች ካህኑ አልአዛርና ሙሴ ያስቈጠሩዋቸው ማስቈጠር እንዲህ ነው ።

፷ ወእም እለ ኈለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በገዳም ዘሲና ፡ ወኢተርፈ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል ዘእንበለ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ፡ ወሆሴዕ ወልደ ነዌ ፡ እስመ ይቤሎሙ እግዚአብሔር ከመ ሞተ ይመውቱ በገዳም ።

አሮንና ሙሴ በሲና ምድረ በዳ ከቈጠሩዋቸው ሰዎች በምድረ በዳ እንዲሞቱ እግዚአብሔር ነግሯቸዋልና ከነዌ ልጅ ከሆሴዕና ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር ከእስራኤል ልጆች አንድ ስንኳ የቀረ የለም ። ዘኍ ፲፬ ፳፰ ።

## ምዕራፍ ፳፯ ።

፩ ወመጽአ አዋልደ ሰለጰአድ ወልዶ ኦፌር ወልደ ገለአድ ወልደ ማኪር ዘእምነገደ ምናሴ ወልደ ዮሴፍ ፡ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆን መሐላ ፡ ወኑኃ ፡ ወሔግላ ፡ ወሚልካ ፡ ወቴርሳ ።

ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ወገን የሚሆን የማኪር ልጅ የገለአድ ልጅ የኦፌር ልጅ የሰለጰአድ ልጆችም መጡ ፡ ስማቸውም መሐላ ፡ ኑኃ ፡ ሔግላ ፡ ሚልካ ፡ ቴርሳ ነው ። ዘኍ ፩ ፴፬ ፴፭ ፡ ፳፮ - ፴፫ ፡ ፩ ዜና መ፡ ፯ ፲፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወቆሙ ቅድመ ሙሴ ወቅድመ አልአዛር ካህን ፡ ወቅድመ መላእክት ወቅድመ ኵሉ ተዓይን ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ። | ፪ | አንድ ጋይ በሚሆን በአልአዛርና በሙሴ እንዲሁም በሠራዊቱና በአለቆቹ ፊት ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ ቆሙ ። |
| ወይቤላ አቡነ ሞተ በገዳም ፡ ወኢሀለወ ማእከሎሙ ለትዕይንት ዘተቃወሙ ቅድመ እግዚአብሔር ምስለ ትዕይንተ ቆሬ ፡ እስመ በኀጢአተ ዚአሁ ሞተ ወአልቦቱ ደቂቅ ወኢይደምሰስ ስሙ ለአቡነ ማእከለ ነገዱ እስመ አልቦቱ ውሉድ ፡ ሀቡነ መክፈልተነ በማእከለ አኀዊሁ ለአቡነ ። | ፫ | አባታችን በምድረ በዳ ሞተ ፡ ከቆሬ ሠራዊት ጋር እግዚአብሔርን በተቃወሙት ሠራዊት መካከል አልነበረም በኃጢአቱም ሙቷልና ፡ ወንድ ልጅም ስላልኖረው የአባታችን ስም ከነገዱ መካከል እንዳይጠፋ ። በአባታችን ወንድሞች መካከል የአባታችንን ዕጣ ስጡን አሉ ። |
| ወአብአ ሙሴ ቃሎን ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፬ | ሙሴም ነገራቸውን (አቤቱታቸውን) ወደ እግዚአብሔር አቀረበ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ርቱዐ ይቤላ አዋልደ ሰለጰአድ ሀቦን መክፈልተ ርስቶን በማእከለ አኀዊሁ ለአቡሆን ፡ ወታገብእ ሎን መክፈልተ አቡሆን ። | ፭ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ የሰለጰአድ ልጆች የሚገባ ነገር ተናግረዋልና በአባታቸው ወንድሞች መካከል ፈንታቸው የሚሆን ርስታቸውን ስጣቸው የአባታቸውንም ዕጣ መልስላቸው ። |
| ወንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ፡ ለእመ ሞተ ብእሲ ወአልቦቱ ደቂቅ ትሁቡ ርስቶ ለአዋልዲሁ ። | ፮ | ሰው ሲሞት ወንድ ልጅ ባይኖረው ርስቱን ለሴቶች ልጆቹ ስጡ ፡ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ። |
| ወለእመ አልቦቱወለት ፡ ሀቡ ርስቶ ለአኀዊሁ ። | ፯ | ሴት ልጅም ባትኖረው ርስቱን ለወንድሞቹ ስጡ ። |
| ወለእመ አልቦ አኀው ፡ ሀቡ ርስቶ ለእኁወ አቡሁ ። | ፰ | ወንድሞችም ባይኖሩት ፡ ርስቱን ለአባቱ ወንድሞች ስጡ ። |
| ወለእመ አልቦ እኁወ አቡሁ ፡ ሀቡ ርስቶ ለቤት ዘቅሩቡ ዘእምነገዱ ይወርስ ። | ፱ | ያባቱም ወንድም ባይኖረው ርስቱን ለቅርብ ዘመዱ ስጡ ፡ ከነገዱም የተወለደ ይውረሰው ። |
| ወይኩን ዝንቱ ፍትሐ ወሥነኔ ለደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፲ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ይህ ለእስራኤል ልጆች ፍርድና ቅጣት ይሁን ። ዘሌ፡ ፲፰ ፮ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ፡ ዕርግ ውስተ ደብረ ናባው ወረአይ ለምድረ ከነአን ዘአነ እሁቦሙ ለደቂቀ እስራኤል ይኩንንዋ ። | ፲፩ | እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ ናባው ተራራ ወጥተህ ይህቺ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች የምሰጣቸው የከነዓን ምድር እያት አለው ። ዘኍ፡ ፴፩ ፲፩ ፡ ዘዳ፡ ፫ ፳፯ ። |
| ወተወሰክ ኀበ ሕዝብከ አንተሂ በከመ ተወሰከ አሮን እኁከ በደብረ ሆር ። | ፲፪ | ወንድምህ አሮን በሖር ተራራ በሞት እንደተጨመረ አንተም በሞት ወደ ወንድሞችህ ተጨመር ። |
| እስመ ተዐወርክሙ ቃልየ በገዳም ዘጺን ፡ አመ ተዋቀሥክምዎሙ ለትዕይንት ። | ፲፫ | ሠራዊቱን በተከራከራችኋቸው ጊዜ በጺን ምድረ በዳ ቃሌን ቸል ብላችኋልና ። |
| ወቀድሶሂ ኢቀደስክሙኒ በበይነ ማይ በቅድሜሆሙ ዘውእቱ ማየ ቅስት ዘበቃዴስ በገዳም ዘጺን ። | ፲፬ | በፊታቸውም ስላለው ውኃ ማመስገንን አላመሰገናችሁኝም ፡ ይኸውም በጺን ምድረ በዳ በቃዴስ ጠብ የተደረገበት ውኃ ነው ። ዘኍ፡ ፳ ፲፪ ፡ ዘዳ፡ ፴፪ ፶፩ ። |
| ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ፡ ለይርአይ እግዚአብሔር አምላከ ለኵሉ ዘሥጋ ወለኵሉ ዘነፍስ ብእሴ ለዛቲ ትዕይንት ፡ ዘይወፅእ ወዘይበውእ ወዘያወፅኦሙ ወዘያበውኦሙ በቅድመ ገጾሙ ። | ፲፭ | ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፤ የሥጋዊና የደማዊ ሰውነት ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ይህችን ሠራዊት የሚያወጣና የሚያገባውን በፊታቸውም የሚያወጣቸውንና የሚያገባቸውን ሰው እግዚአብሔር (ይምረጥ) ። |
| ወኢትኩን ትዕይንቱ ለእግዚአብሔር ከመ አባግዕ ዘአልቦ ኖላዊ ። | ፲፮ | ይህችም የእግዚአብሔር ሠራዊት ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች አትሁን አለው ። ዘዳ፡ ፴፩ ፬ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንሥአ ኀቤከ ለዮሴዕ ወልደ ነዌ ብእሴ ዘሀለወ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ ወደይ እዴከ ላዕሌሁ ። | ፲፯ | እግዚአብሔርን ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፤ መንፈስ ቅዱስ ያደረበትን ሰው የነዌን ልጅ ሆሴዕን ወደ አንተ ውሰደው እጅህንም በላዩ ላይ አኑር ። |
| ወአቅሞ ቅድመ አልአዛር ካህን ወአገዝዞ ቅድመ ኵሉ ተዓይን ፡ ወአዝዝ በእንቲአሁ ቅድሜሆሙ ። | ፲፰ | በካህኑ በአልአዛር ፊት አቁመው በሠራዊቱም ሁሉ ፊት እዘዘው ፡ ስለ ርሱም በፊታቸው እዘዝ ። |
| ወታገብእ ክብረከ ላዕሌሁ ከመ ይትአዘዙ ሎቱ ደቂቀ እስራኤል ። | ፲፱ | የእስራኤል ልጆች ይታዘዙለት ዘንድ ክብርህን (ሹመትህን) ስጠው ። ኢያ፡ ፬ ፲፩ ፡ መሳ፡ ፩ ፩ ፡ ፳ ፲፰ ። |
| ወይቁሙ ቅድመ አልአዛር ካህን ወይስአልዎ ፍትሐ ዘይትናገር ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳ | በካህኑ በአልአዛር ፊት ቁመው በእግዚአብሔር ፊት የሚናገረው ፍርድ ይጠይቁት ። |

፳፩ ወበቃለ ዚአሁ ይበኡ፣ ወበቃለ ዚአሁ ይፃኡ፤ ውእቱ ወደቂቀ እስራኤል ኅቡረ ወኵሉ ተዓይን ።

የእስራኤል ልጆችና እርሱ ሠራዊቱም ሁሉ በርሱ ቃል ይግቡ፤ በርሱ ቃል ይውጡ አለው ።

፳፪ ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ወነሥኦ ለኢያሱ ወአቀሞ ቅድመ አልአዛር ካህን ወቅድመ ኵሉ ተዓይን፤ ወወደየ እዴሁ ላዕሌሁ ወሤሞ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ።

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፣ ኢያሱን ወስዶ በካህኑ በአልአዛር ፊትና በሠራዊቱ ሁሉ ፊት አቆመው እግዚአብሔር እንዳዘዘውም እጁን በላዩ ላይ አድርጎ ሾመው ።

## ምዕራፍ ፳፰ ።

## ምዕራፍ ፳፰ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ቍርባንየ ወሀብትየ ወመሥዋዕትየ ዘመዓዛ ሠናይ ዕቀቡ ከመ ታብኡ ሊተ በበዓላትየ ።

የምትሠዉልኝንና የምታቀርቡልኝን ወድጄም ልቀበለው የምትሰጡኝን መሥዋዕቴን በበዓላቶቼ ታገቡልኝ ዘንድ ጠብቁ በላቸው ብለህ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ።

፪ ወበሎሙ ዝንቱ ውእቱ መሥዋዕትየ ኵሉ ዘታበውኡ ለእግዚአብሔር አባግዐ ዘዘዓመት ንጹሓነ ክልኤተ ለለዕለቱ መሥዋዕት ዘዘልፍ ።

ለእግዚአብሔር የምታቀርቡትም መሥዋዕት ሁሉ ይህ ነው፣ ዕለት ዕለት የዘወትር መሥዋዕት ንጹሐን የሆኑ ዓመት ዓመት የሆናቸው ሁለት በጎችን አግቡ በላቸው ።

፫ አሐደ በግዐ ትገብሩ በጽባሕ ወአሐደ በግዐ ትገብሩ በሠርክ ።

አንዱን በግ ጧት፤ አንዱን በግ ማታ አድርጉ (ሠዉ.)።

፬ ወትገብሩ ሥንዳሌ ዓሥራተ እዴሃ ለኢፍ ለመሥዋዕት ዘዘልፍ ዘግቡር በቅብዕ ።

ለዘወትር መሥዋዕት በገንቦ አራተኛ ዘይት የታሸ የኢፍ አሥረኛ አንድ ላዳን ሥንዴ አድርጉ (ሠዉ.)።

፭ ወመሥዋዕት ዘዘልፍ በከመ ተገብረ በደብረ ሲና ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር በራብዕተ እዴሃ ለኢን ።

ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ሊሆን በደብረ ሲና እንደ ተደረገው ለዘወትር መሥዋዕት፣ በገንቦ አራተኛ ዘይት አድርጉ ። ዘፀ፡ ፳፱ ፴፪ ።

፮ ወሞጻሕቱ ራብዕተ እዴሃ ለኢን ወይን ለአሐዱ በግዕ ታወጽሕ ሞጻሕተ ቅዱሰ ለእግዚአብሔር ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትን የገንቦ አራተኛ ወይን ላንዱ በግ ለእግዚአብሔር የተለየውን ወይን ፍልቅ አድርገህ አፍስበት ።

፯ ወይገብሩ ካልአ በግዐ ፍና ሠርክ በከመ መሥዋዕቱ ወበከመ ሞጻሕቱ ትገብሩ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

ሁለተኛውን በግ ማታ ጊዜ ሠዉት፤ ጧት እንደ ሠዋችሁትና ፍልቅ አድርጋችሁ እንደ ጠጣችሁት በሠርክም እግዚአብሔር ወዶ እንዲቀበለው አድርጉ ።

፰ ወበዕለተ ሰንበት ትገብሩ ክልኤተ አባግዐ ዘዘዓመት ንጹሓነ፤ ወክልኤተ ዓሥራተ ዘሥንዳሌ ለመሥዋዕት ዘግቡር በቅብዕ ።

በቅዳሜም ዕለት አንዳንድ ዓመት የሆናቸው ሁለት ንጹሐን በጎችን ሠዉ፣ በዘይት የታሸ ሁለት ላዳን ሥንዴም ለመሥዋዕት አድርጉ ።

፱ ወሞጻሕቱ ወቍርባኑ ለሰንበት ዘእምሰናብት ላዕለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ሎቱኒ ሞጻሕቱ ።

ዘወትር በሚሠዋው መሥዋዕት ላይ በየሰምንቱ ከሚመጣው ቅዳሜ በአንዱ ቅዳሜ ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱትና የሚያቀርቡት እንደዚህ ነው ። ሕዝ፡ ፵፮ ፬ ።

፲ ወአመ ሠርቀ ወርኅ ታበውኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር አሥዋረ ክልኤተ እምአልሕምት፤ ወበግዐ አሐደ፤ ወማሕስአ በግዕ ሰብዓተ ዘዘዓመት ።

በወሩ መባቻም አንድ በግና ከላሞች ሁለት ጎቾችን አንዳንድ ዓመት የሆናቸው ከበጎች ሰባት ጠቦቶችን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቡ ። ዘኍ፡ ፲ ፲ ።

፲፩ ወሠለስተ ዓሥራተ ሥንዳሌ ዘመሥዋዕት በቅብዕ ለአሐዱ ላሕም ወክልኤተ ዓሥራተ ሥንዳሌ መሥዋዕት ዘግቡር በቅብዕ ለአሐዱ በግዕ ።

ያንድ ላም መሥዋዕት በዘይት የታሸ ሦስት ላዳን ሥንዴ ነው፣ ያንዱም በግ መሥዋዕት በዘይት የታሸ ሁለት ላዳን ሥንዴ ነው ። ዘኍ፡ ፲፭ ፬ ፲፪ ።

፲፪ ወዓሥራተ ዓሥራት ሥንዳሌ መሥዋዕት ዘግቡር በቅብዕ ለአሐዱ ማሕስእ መሥዋዕተ መዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው የአንዱ ጠቦት በግ መሥዋዕት በዘይት የታሸ ልጠ ጉርዶ የወጣለት አንድ አንድ ላዳን ሥንዴ ነው ።

፲፫ ወሞጻሕቶሙ መንፈቃ ለኢን ወይን ይኩን ለአሐዱ ላሕም፤ ወሣልስተ እዴሃ ለኢን ይኩን ለአሐዱ በግዕ፤ ወራብዕተ እዴሃ ለኢን ይኩን ለለአሐዱ ማሕስእ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይን ለአንዱ ጎች የገንቦ እኩሌታ ይሁን ላንዱም በግ የገንቦ ሢሶ ይሁን ለያንዳንዱም ጠቦት የገንቦ እርቦኛ ይሁን ።

፲፬ ዝንቱ ውእቱ መሥዋዕተ ወርኅ በበወርኁ እምአውራኀ ዓመት ።

በየዓመቱ ከሚመጡ ወራቶች በየወሩ የሚሠዋው መሥዋዕት ይህ ነው ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፲፭ ወሐርጌ አሐዱ እምአጣሊ ለእግዚአብሔር በእንተ ኀጢአት ባዕለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ትገብሩ ወሞጻሕቶሂ ።

፲፮ ወበቀዳሚ ወርኅ አመ ዐሡር ወረቡዑ ለሠርቅ ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር ።

፲፯ ወአመ ዐሡር ወሐሙሱ ለሠርቅ ውእቱ ወርኅ በዓል ሰቡዐ ዕለተ ናእተ ትበልዑ ።

፲፰ ወቀዳሚት ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ በቲ ።

፲፱ ወታበውኡ ቍርባነ ለእግዚአብሔር አሥዋረ ክልኤተ እምአልሕምት ፡ ወበግዐ አሐደ ወመሐስአ አባግዕ ሰብዐተ ንጹሓነ ዘዘዓመት ይኩኑክሙ ።

፳ ወመሥዋዕቶሙ ሥንዳሴ ዘግቡር በቅብዕ ሠለስቱ ዓሥራት ለአሐዱ ላሕም ፡ ወክልኤቱ ዓሥራት ለአሐዱ በግዕ ።

፳፩ ወዓሥራተ ዓሥራተ ትገብር ለአሐዱ ማሕስአ በግዕ ፡ ወከማሁ ለሰብዓቲሆሙ መሐስአ አባግዕ ።

፳፪ ወሐርጌ አሐዱ እምአጣሊ በእንተ ኀጢአት በዘበቱ ያስተሠርዩ ለክሙ ዘእንበለ መሥዋዕት ዘኵሉ ጊዜ በበነግሁ ዘመሥዋዕት ዘልፍ ።

፳፫ ወከመዝ ትገብሩ ለለዕለቱ ለሰቡዐ መዋዕል ቍርባነ ወመሥዋዕተ ለመዓዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር በዲበ መሥዋዕት ዘዘልፍ ፡ ወትገብር ሞጻሕተኒ ።

፳፬ ወዕለት ሳብዕት ቅድስተ ትኩንክሙ ፡ ወኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢ፡ ግበሩ በቲ ።

፳፭ ወእመ ዕለተ ሰዊት አመ ታበውኡ መሥዋዕተ ሰዊት ለእግዚአብሔር ሰንበተ ቅድስተ ትኩንክሙ ወኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ በቲ ።

፳፮ ወታበውኡ መሥዋዕተ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር አሥዋረ እምአልሕምት ክልኤተ ፡ ወአሐደ በግዐ ወመሐስአ በግዕ ሰብዐተ ዘዘዓመት ንጹሓነ ።

፳፯ ወመሥዋዕቶሙኒ ሥንዳሴ ዘግቡር በቅብዕ ሠለስቱ ዓሥራት ለአሐዱ ላሕም ፡ ወክልኤቱ ዓሥራት ለአሐዱ በግዕ ።

፳፰ ወዓሥራተ ዓሥራት ለአሐዱ ማሕስአ በግዕ ፡ ወከማሁ ለሰብዓቲሆሙ መሐስአ አባግዕ ።

፳፱ ወሐርጌ አሐዱ እምአጣሊ በእንተ ኀጢአት በዘበቱ ያስተሠርዩ ለክሙ ዘእንበለ መሥዋዕት ዘልፍ ።

፴ ወመሥዋዕቶሙኒ ትገብሩ ሊተ ወንጹሓነ ለይኩኑ ለክሙ ወሞጻሕቶሙኒ ።

## ምዕራፍ ፳፱ ።

፩ ወበሳብዕ ወርኅ አመ ሠርቀ ወርኅ ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ይእቲ ዕለት ፡ ኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ በቲ ፡ ወዕለተ ትእምርት ትኩንክሙ ።

፪ ወትገብሩ መሥዋዕተ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር

፲፭ ዘወትር በሚሠዋው መሥዋዕት ላይ ከፍየሎች አንድ ሙክት ስለ ኃጢአት ለእግዚአብሔር ሠዉ ፡ ፍልቅ አድርጋችሁ አፍስሳችሁ የምትጠጡትም እንደዚሁ ነው ።

፲፮ በመጀመሪያው ወር ሚያዝያ በበተ በአሥራ አራተኛው ቀን የእግዚአብሔር ፋሲካ (በዓል) ነው ።

፲፯ ያም ወር (ሚያዝያ) በበተ በዓሥራ አምስተኛው ቀን በዓል ነው ፡ ሰባት ቀን ቂጣ ብሉ ። ዘሌ፡ ፳፫ ፯ ።

፲፰ መጀመሪያይቱ ቀን ለናንተ የከበረች በዓል ናት ፡ አትረሱባት አትቈፍሩባት ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፮ ።

፲፱ ከላሞች ሁለት ጊቾችን አንድ በግን ሰባት ጠቦቶችን ለእግዚአብሔር አምጡ ፡ እነዚህም ዓመት ዓመት የሆናቸው ንጹሐን ይሁኗችሁ ። ዘሌዋ፡ ፳፪ ፳ ።

፳ መሥዋዕታቸውም ለአንዱ ወይፈን በዘይት የታሸ ሦስት ላዳን ሥንዴ ለአንዱም በግ ሁለት ላዳን ሥንዴ ነው ።

፳፩ ላንዱ የበግ ጠቦት አንድ ላዳን አድርጉ ፡ ለሰባቱም የበጎች ጠቦቶች እንደዚሁ አድርጉ ።

፳፪ በየጊዜው በነግህና በሠርክ ከምትሠዉት መሥዋዕት በቀር ኃጢአታችሁን በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ከፍየሎች አንድ ሙክት አምጡ ። ዘኍ፡ ፳፰ ፲፱ ።

፳፫ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ዘወትር በምትሠዉት መሥዋዕት ላይ በሰባቱ ቀን ዕለት ዕለት የምታቀርቡትንና የምትሠዉትን እንደዚህ አድርጉ ፡ ፍልቅ አድርጋችሁ አፍስሳችሁ የምትጠጡትንም ወይን እንደዚሁ አድርጉ ።

፳፬ ሰባተኛይቱ ቀን ግን የከበረች በዓል ትሁናችሁ ፡ አትረሱባት አትቈፍሩባት ። ዘኍ፡ ፳፰ ፫ ።

፳፭ እሸት በገባችሁ ጊዜ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሰዊትን የምትሰጡባት ቀን የከበረች ትሁናችሁ አትረሱባት አትቈፍሩባት ። ዘፀ፡ ፲፪ ፲፯ ፡ ፲፫ ፯ ።

፳፮ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ከላሞች ሁለት ጊቾችን ፡ አንድ በግን ፡ ንጹሐን የሆኑ ዓመት ዓመት የሆናቸው ሰባት የበግ ጠቦቶችን መሥዋዕት አምጡ ።

፳፯ መሥዋዕታቸውም ላንድ ወይፈን በዘይት የታሸ ሕዕበ ጕርዶ የወጣ ሦስት ላዳን ሥንዴ ፡ ላንዱም በግ ሁለት ላዳን ሥንዴ አቅርቡ ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፲፰ ።

፳፰ ላንዱም የበግ ጠቦት የዓሥራት ዓሥረኛ ላዳን ሥንዴ ነው ፡ ለሰባቱም የበግ ጠቦቶች እንደዚሁ ነው ።

፳፱ ኃጢአታችሁን በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ከዘወትሩ መሥዋዕት በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት አቅርቡ ።

፴ መሥዋዕታቸውንም እንዲህ አድርጉልኝ ፡ ለናንተ ንጹሐን ይሁኗችሁ ፍልቅ አድርጋችሁ አፍስሳችሁ የምትጠጡት ወይኑንም እንዲሁ አድርጉ ።

## ምዕራፍ ፳፱ ።

፩ በሰባተኛይቱ ወር የጥቅምት መባቻ ያች ቀን ለናንተ የተከበረች ትሁናችሁ ፡ አትረሱባት አትቈፍሩባትም ምልክት ያላት ቀን ትሁናችሁ ። ዘሌ፡ ፳፫ ፳፬ ።

፪ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው ከላሞች አንድ ጊቾ

ሦረ አሐደ እምአልሕምት ወበግዐ አሐደ፡ ወመሐስአ አባግዕ ሰብዐተ ንጹሓነ ዘዘዓመት ።

አንድ በግ ዓመት ዓመት የሆናቸው ንጹሐን የሆኑ ሰባት የበግ ጠቦቶችን መሥዋዕት አድርጉ።

፫ ወመሥዋዕቶሙኒ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ሠለስቱ ዓሥራት ለአሐዱ ላሕም፡ ወክልኤቱ ዓሥራት ለአሐዱ በግዕ ።

መሥዋዕታቸውም ላንዱ ላም በዘይት የታሸ ንጹሕ ሦስት ላዳን ሥንዴ ነው፡ ላንዱም በግ ሁለት ላዳን ሥንዴ ነው።

፬ ወዓሥራተ ዓሥራት ለአሐዱ ማሕስእ በግዕ ወከማሁ ለሰብዓቲሆሙ መሐስአ አባግዕ ።

ላንዱም የበግ ጠቦት አንድ ላዳን ሥንዴ ነው፡ ለሰባቱም የበግ ጠቦቶች እንደዚሁ ነው ።

፭ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኀጢአት በዘበቱ ያስተሠርዩ ለክሙ፡ ዘእንበለ መሥዋዕት ዘበበሠርቀ ወርኅ ወመሥዋዕት ዘዘልፍ ።

በየወሩ መባቻ ከሚሠዉት መሥዋዕት በቀር ኃጢአትን በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ ።

፮ ወመሥዋዕቶሙኒ ወሞጻሕቶሙኒ ዘከመ ሕጎሙ ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

መሥዋዕታቸውና ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትም እግዚአብሔር ወዶ እንዲቀበለው እንደ ሥርዓታቸው ነው።

፯ ወአመ ዐሡሩ ለሠርቀ ውእቱ ወርኅ ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ፡ ወአሕምምዋ ለነፍስክሙ ወኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ ባቲ ።

(ጥቅምት) በባተ ባሥረኛው ቀን ለናንተ የተከበረች በዓል ትሁናችሁ፡ ሰውነታችሁን አሳዝኑባት አትረሱባት አትቈፍሩባት ። ዘሌ፡ ፲፯ ፳፱፡ ኢሳ፡ ፶፰ ፭ ።

፰ ወታበውኡ መሥዋዕተ ለመዐዛ ሠናይ ሦረ አሐደ እምአልሕምት፡ ወበግዐ አሐደ፡ ወመሐስአ አባግዕ ሰብዐተ ንጹሓነ ዘዘዓመት ይኩኑ ለክሙ ።

ከላሞች አንድ ጊደር፡ አንድ በግ፡ ሰባት የበግ ጠቦቶችን በጎ መዓዛ ያለው አድርጋችሁ አቅርቡ፡ እነዚህም አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው ንጹሐን ይሁኗችሁ ።

፱ ወመሥዋዕቶሙኒ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ሠለስቱ ዓሥራት ለአሐዱ ላሕም፡ ወክልኤቱ ዓሥራት ለአሐዱ በግዕ፡ ወዓሥራተ ዓሥራት ለአሐዱ ማሕስአ በግዕ፡ ወከማሁ ለሰብዐቲሆሙ መሐስአ አባግዕ ።

መሥዋዕታቸውም ላንዱ ላም በዘይት የታሸ ሦስት ላዳን ንጹሕ ሥንዴ የዓሥራት ዓሥረኛ ላንዱም በግ አራት ላዳን ሥንዴ ነው፡ ለሰባቱም ጠቦቶች እንደዚሁ ነው ።

፲ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኀጢአት በዘበቱ ያስተሠርዩ ለክሙ ዘእንበለ ዘበእንተ ኀጢአት ለአስተሥርዮ፡ ወመሥዋዕት ዘዘልፍ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕትና ኃጢአትን ለማስተሥረይ ከሚሠዋው መሥዋዕት በቀር ኃጢአታችሁን በሚያስተሠርዩላችሁ ገንዘብ ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት አቅርቡ ።

፲፩ ወመሥዋዕቶሙኒ ወሞጻሕቶሙ በከመ ሕጎሙ ለመዐዛ ሠናይ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይንና መሥዋዕታቸውም በጎ መዓዛ ሊሆን እንደ ሕጋቸው እንደ ሥርዓታቸው ነው ። ዘሌዋ፡ ፲፯ ፭፡ ዘኍ፡ ፳፰ ፲፭ ።

፲፪ ወአመ ዐሡር ወኀሙሱ ለሠርቀ ውእቱ ወርኅ ሳብዕ ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ፡ ወኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ ባቲ ወግበሩ በዓለ ለእግዚአብሔር ሰቡዐ መዋዕለ ።

(ጥቅምት) በባተ በዓሥራ አምስተኛው ቀን የተከበረች በዓል ትሁናችሁ፡ አትረሱባት አትቈፍሩባት፡ ሰባት ቀን ለእግዚአብሔር በዓል አድርጉ ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፴፬ ።

፲፫ ወአብኡ መሥዋዕተ ቍርባን ለመዐዛ ሠናይ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው በጎ መዓዛ ያለው አድርጋችሁ የቍርባኑን መሥዋዕት አቅርቡ ።

፲፬ <u>አመ ዕለተ ቀዳሚት</u> ዐሠርተ ወሠለስተ አሥዋረ፡ ወክልኤተ አርባግዐ፡ ወዐሠርተ ወአርባዕተ መሐስአ አባግዕ ዘዘዓመት ንጹሓነ ይኩኑ ።

<u>በመጀመሪያይቱ ቀን</u> አሥራ ሦስት ጊደሮችን ሁለት በጎችንና፡ አሥራ አራት የበግ ጠቦቶችን አምጡ፡ እነዚያም ዓመት ዓመት የሆናቸው ንጹሐን ይሁኑ ።

፲፭ ወመሥዋዕቶሙ ሠለስቱ ዓሥራት ለአሐዱ ላሕም ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብእ፡ ወከማሁ ለዐሠርቲሆሙ ወሠለስቲሆሙ አልሕምት፡ ወክልኤቱ ዓሥራት ለአሐዱ በግዕ፡ ከማሁ ለክልኤሆሙ አባግዕ ።

መሥዋዕታቸውም ላንዱ ላም በዘይት የታሸ ሦስት ላዳን ንጹሕ ሥንዴ ነው፡ ላሥራ ሦስቱም ላሞች እንደዚሁ ነው፡ ላንዱም በግ ሁለት ላዳን ሥንዴ ነው፡ ለሁለቱም በጎች እንደዚሁ ነው ።

፲፮ ወአሐዱ ዐሥራት ለአሐዱ ማሕስአ በግዕ፡ ወከማሁ ለዐሠርቲሆሙ ወአርባዕቲሆሙ መሐስአ አባግዕ ።

ላንዱም የበግ ጠቦት አንድ ላዳን ሥንዴ ነው፡ ላሥራ አራቱም የበጎች ጠቦቶች እንደዚሁ ነው ።

፲፯ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኀጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘልፍ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕት በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፡ መሥዋዕታቸውና ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትም (ወይን) እንደዚሁ ነው ።

፲፰ <u>ወበሳኒታ ዕለት</u> ዐሠርተ ወክልኤተ አሥዋረ ታበውኡ ወክልኤተ አበግዐ ወዐሠርተ ወአርባዕተ መሐስአ አባግዕ ንጹሓነ ዘዘዓመት ።

<u>በማግሥቱም ሁለት</u>፡ በጎችንና አሥራ ሁለቱን ጊደሮች አንዳንድ ዓመት የሆናቸው ዓሥራ አራት የበጎች ጠቦቶችን አምጡ ።

፲፱ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለአልሕምትኒ ወለአባግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቊሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም ለላሞችም ለበጎች ጠቦቶችም በየቍጥራቸው እንደ ሕጋቸው ነው ። ዘኁ፡ ፳፱ ፳፡ ፲፰ ፲፱ ።

፳ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕት በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፤ መሥዋዕታቸውም ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይኑም እንደዚሁ ነው ።

፳፩ ወበሣልስት ዕለት ዓሠርተ ወአሐደ አሥዋረ ወክልኤተ አባግዐ፤ ወመሐስአ አባግዕ ዓሠርተ ወአርባዕተ ንጹሓነ ዘዘዓመት ።

በሦስተኛይቱም ቀን ሁለት በጎችንና ዓሥር ጊደሮችን ንጹሐን የሆኑ አንድ አንድ ዓመት የሆናቸው ዓሥራ አራት የበጎች ጠቦቶችን ሠዉ ።

፳፪ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለአልሕምትኒ ወለአባግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቊሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

መሥዋዕታቸውና ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይኑም ለላሞችም ለበጎችም ለበጎች ጠቦቶችም እንደ ሥርዓታቸው በየቍጥራቸው ነው ።

፳፫ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ወመሥዕዋቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕትም በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፤ ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም እንደዚሁ ነው ።

፳፬ ወበራብዕት ዕለት ዐሠርተ አሥዋረ ወክልኤተ አባግዐ ወዓሠርተ ወአርባዕተ መሐስአ አባግዕ ንጹሐነ ዘዘዓመት ።

በአራተኛይቱም ቀን ሁለት በጎችንና አሥር ጊደሮችን ያንዳንድ ዓመት ንጹሐን የሆኑ ዓሥራ አራት የበጎች ጠቦቶችን ሠዉ ።

፳፭ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለአልሕምትኒ ወለአባግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቊሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም ለላሞችም ለበጎችም ለበጎች ጠቦቶችም በየቍጥራቸው እንደ ሥርዓታቸው ነው ።

፳፮ ወሐርጌ አሐዱ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ፤ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕት በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፤ ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም እንደዚሁ ነው ።

፳፯ ወበሐምስ ዕለት ተስዓተ አሥዋረ ወክልኤተ አባግዐ ወዓሠርተ ወአርባዕተ መሐስአ አባግዕ ንጹሐነ ዘዘዓመት ።

በአምስተኛይቱም ቀን ሁለት በጎችንና ዘጠኝ ጊደሮችን ንጹሐን የሆኑ ዓመት ዓመት የሆናቸው ዓሥራ አራት የበጎች ጠቦቶችን ሠዉ ።

፳፰ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለአልሕምትኒ ወለአባግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቊሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም ለላሞችም ለበጎችም፤ ለበግ ጠቦቶችም እንደ ሥርዓታቸው በየቍጥራቸው ነው ።

፳፱ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ፤ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕትም በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፤ ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይኑና መሥዋዕታቸውም እንደዚሁ ነው ።

፴ ወበሳድስት ዕለት ሰመንተ አሥዋረ ወክልኤተ አባግዐ ወዐሠርተ ወአርባዕተ መሐስአ አባግዕ ንጹሐነ ዘዘዓመት ።

በስድስተኛይቱም ቀን ሁለት በጎችንና ስምንት ጊደሮችን ንጹሐን የሆኑ የአንድ አንድ ዓመት ዓሥራ አራት የበጎች ጠቦቶችን ሠዉ ።

፴፩ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለአልሕምትኒ ወለአባግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቊሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም ለላሞችም ለበጎችም ለበግ ጠቦቶችም እንደ ሥርዓታቸው በየቍጥራቸው እንደዚሁ ነው ።

፴፪ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

ከዘወትሩ መሥዋዕትም በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፤ ፍልቅ አድርገው አፍሰው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም እንደዚሁ ነው ።

፴፫ ወበሳብዕት ዕለት ሰብዓተ አሥዋረ ወክልኤተ አባግዐ ወዓሠርተ ወአርባዕተ መሐስአ አባግዕ ንጹሐነ ዘዘዓመት ።

በሰባተኛይቱም ቀን ሁለት በጎችንና ሰባት ጊደሮችን ንጹሐን የሆኑ ያንዳንድ ዓመት ዓሥራ አራት የበጎች ጠቦቶችን ሠዉ ።

፴፬ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለአልሕምትኒ ወለአባግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቊሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይኑና መሥዋዕታቸውም ለላሞችም ለበጎችም ለበግ ጠቦቶችም እንደ ሥርዓታቸው በየቍጥራቸው እንደዚሁ ነው ።

፴፬ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

፴፭ ወበሳምንት ዕለት ዕለተ ተሐውሶ ይእቲ ለክሙ ፣ ኵሎ ግብረ ማሕረስ ኢትግበሩ ባቲ ።

፴፮ ወአብኡ መሥዋዕተ ወቍርባነ ለሠናየ መዓዛ ለእግዚአብሔር ላሕመ አሐደ ወበግዐ አሐደ ለመሥዋዕት ፣ ወሰብዓተ መሐስአ አባግዕ ንጹሓነ ዘዘዓመት ።

፴፯ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ለላሕምኒ ወለበግዕኒ ወለመሐስአ አባግዕኒ በበኍላቌሆሙ በከመ ሕጎሙ ።

፴፰ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ዘእንበለ መሥዋዕት ዘዘልፍ ወመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ ።

፴፱ ወከመዝ ግበሩ ዘንተ በበዓላቲክሙ ለእግዚአብሔር ።

፵ ዘእንበለ ዘበፈቃድክሙ ፣ ወቍርባንክሙኒ ወመሥዋዕቲክሙኒ ወሞጻሕቲክሙኒ ወዘመድኃኒትክሙኒ ።

፵፩ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ።

ምዕራፍ ፴ ።

፩ ወነገሮሙ ሙሴ ለመላእክተ ሕዝብ ዘደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ ፣ ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘአዘዘ እግዚአብሔር ።

፪ ብእሲ ብእሲ ለእመ በፅዐ ብፅዐተ ለእግዚአብሔር ወለእመኒ መሐለ መሐላ ፡ አው ፈለጠ ፍሉጠ በእንተ ነፍሱ ፣ ኢያገምን ኵሎ ቃሎ ዘወፅአ እምአፉሁ ይግበር ።

፫ ወለእመኒ ብእሲት በፅዐት ብፅዐተ ለእግዚአብሔር አው ፈለጠት ፍሉጠ በቤተ አቡሃ በንእሳ ወሰምዐ አቡሃ ጸሎታ ወኵሎ ብፅዐታ ዘበፅዐት በእንተ ነፍሳ ወተጸመማ አቡሃ ይቀውም ላዕሌሃ ኵሉ ጸሎታ ወኵሉ ብፅዓቲሃ ዘበፅዓት በእንተ ነፍሳ ።

፬ ወለእመሰ ገብረ ላቲ አቡሃ ወፈጸመ በዕለተ ሰምዐ ኵሎ ጸሎታ ወብፅዐቲሃ ዘበፅዓት በእንተ ነፍሳ ኢይነብር ላዕሌሃ ፣ ወያነጽሓ እግዚአብሔር በዕለተ ገብረ ላቲ አቡሃ ።

፭ ወለእመሰ አውሰበት ብእሴ ወሀለወ ላዕሌሃ ጸሎታ በከመ ነበበት በከናፍሪሃ ኵሉ ዘበፅዐት በእንተ ነፍሳ ።

፮ ወሰምዐ ምታ ወተጸመማ በዕለተ ሰምዐ ከማሁ ይቀውም ላዕሌሃ ኵሉ ጸሎታ ወብፅዓቲሃ ዘበፅዐት በእንተ ነፍሳ ።

፯ ወለእመሰ ገብረ ላቲ ምታ ወፈጸመ በዕለተ ሰምዐ ኵሎ ጸሎታ ወብፅዓቲሃ ዘበፅዐት በእንተ ነፍሳ ኢይነብር ላዕሌሃ እስመ ገብረ ላቲ ምታ ወያነጽሓ እግዚአብሔር ።

፰ ወጸሎታሂ ለመበለት ወለእንተ አውጽአ ምታ ኵሉ ዘበፅዐት በእንተ ነፍሳ ይሄሉ ላዕሌሃ ።

፴፬ ከዘወትሩም መሥዋዕት በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፣ ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም እንደዚሁ ነው ።

፴፭ በስምንተኛይቱም ቀን ለናንተ በዓለ ተሐውሶ ናት፣ አትረሱበት አትቈፍሩበት ።

፴፮ እግዚአብሔር ወዶ ሊቀበለው የምትሠዉትንና የምታቀርቡትን አንድ በግንና አንድ ላምን አንዳንድ ዓመት የሆናቸው ንጹሐን የሆኑ ሰባት የበጎች ጠቦቶችን ሠዉ ።

፴፯ ፍልቅ አድርገው የሚጠጡትና መሥዋዕታቸውም ለላሞችም ለበጎችም ለበግ ጠቦቶችም እንደየ ሥርዓታቸው በየቍጥራቸው ነው ።

፴፰ ከዘወትሩ መሥዋዕት በቀር ስለ ኃጢአት ከፍየሎች አንድ ሙክት ሠዉ፣ ፍልቅ አድርገው የሚጠጡት ወይንና መሥዋዕታቸውም እንደዚሁ ነው ።

፴፱ በፈቃዳችሁ ከምታገቡት ሌላ በበዓላቶቻችሁ ለእግዚአብሔር ብላችሁ እንደዚህ አድርጉ ።

፵ ቍርባናችሁም መሥዋዕታችሁም ፍልቅ አድርጋችሁ የምትጠጡት ወይናችሁና ድኅነትን የሚያስጣችሁ መሥዋዕትም እንደዚሁ ነው አላቸው ። ዘሌ፡ ፳፫ ፬ ።

፵፩ ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ለእስራኤል ልጆች ሁሉን ነገራቸው ። ፩ ዜና መ፡ ፳፫ ፴፩ ፣ ዘዳ፡ ፴፫ ፳፮ ።

ምዕራፍ ፴ ።

፩ ሙሴ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ይህ ነው ብሎ ለእስራኤል ልጆች ወገኖች አለቆች ነገራቸው ።

፪ አንዱም አንዱም ሰው ለእግዚአብሔር ስለት ቢሳል እሰጣለሁ ብሎም መሐላን ቢምል ወይም ስለ ሰውነቱ ይህን እሰጣለሁ ብሎ የለየው መለየት ቢኖር ከአንደበቱ የወጣውን ቃል ሁሉ አያስቀር (ያድርግ) ።

፫ ሴትም ለእግዚአብሔር ስለትን ብትሳል ፣ ወይም በበቷ ቤት በሕፃንነቷ ይህን እሰጣለሁ ብላ ለይታ ብትሳል ፣ አባቷም ስለቷን ሰምቶ ቸል ቢላት፣ ስለቷ ሁሉ በእሷ ይጸናል፡ ስለ ሰውነቷ የተሳለችው ስለቷ ሁሉ በእሷ ጸንቶ ይኖራል ። ዘኍ፡ ፴ ፫፣ መክ፡ ፶፮ ፲፪ ።

፬ አባቷ ቢያደርግላት ግን ስለ ሰውነቷ የተሳለችው ስለቷን ሁሉ በሰማበት ቀን ቢፈጽምላት በእሷ ጸንቶ አይኖርም አባቷ ባደረገላትም ቀን እግዚአብሔር ያነጻታል ።

፭ ባል ብታገባ ግን ስለ ሰውነቷ የተሳለችው ስለቷን ሁሉ በአንደበቷ እንደ ተናገረች ስለቷ በላይዋ ላይ ነው።

፮ ባሏም ሰምቶ በሰማበት ቀን ቸል ቢላት ስለ ሰውነቷ የተሳለችው ስለቷ ሁሉ እንደዚሁ በርሷ ጸንቶ ይኖራል ።

፯ ባሏ ቢያደርግላት ግን ስለ ሰውነቷ የተሳለችው ስለቷን ሁሉ በሰማበት ቀን ቢፈጽምላት ባሏ ፈጽሞላታልና በሷ ጸንቶ አይኖርም ፣ እግዚአብሔር ያነጻታል ።

፰ የጋለሞታዋም ስለት፣ ባሏ የፈታትም፣ ስለ ሰውነቷ የተሳለችው ስለት ሁሉ በርሷ ጸንቶ ይኖራል ።

| | | |
|---|---|---|
| ወለእመኒ እንዘ ሀለወት በቤተ ምታ ጸለየት ወበፅአት በእንተ ነፍሳ ወሰምዐ ምታ ወተጸመማ ወኢገብረ ላቲ ኵሉ ጸሎታ ወኵሉ ብፅዓቲሃ ዘበፅዓት በእንተ ነፍሳ ይቀውም ዲቤሃ ። | ፱ | በባሏም ቤት ሳለች ስለ ሰውነቷ ብትሳል ፡ ባሏም ሰምቶ ቸል ቢላት ስለ ሰውነቷ የተሳለችውም ስለት ባያደርግላት በርሷ ጸንቶ ይኖራል ። |
| ወለእመሰ ገብረ ላቲ ምታ ወፈጸመ በዕለተ ሰምዐ ኵሎ ዘወፅአ እምከናፍሪሃ ዘከመ ጸለየት ወዘከመ በፅዐት በእንተ ነፍሳ ኢይነብር ላዕሌሃ እስመ ገብረ ላቲ ምታ ወያነጽሓ እግዚአብሔር ። | ፲ | ባሏ ቢያደርግላት ግን ስለ ሰውነቷ እንደ ተሳለች ከአንደበቷ የወጣውን ስእለቷን ሁሉ በሰማበት ቀን ቢፈጽምላት ባሏ አድርጎላታልና በርሷ ጸንቶ አይኖርም ፡ እግዚአብሔርም ያነጻታል ። |
| ወኵሎ ብፅዓተ ወኵሎ ማእሰረ መሐላ ዘይከውን እኩየ ላዕለ ነፍሳ ያቀውም ምታ ወይገብር ላቲ ። | ፲፩ | በሰውነቷ ክፉ የሚሆን በፍዳ የሚያስይዝ መሐላውንና ስለቱን ሁሉ ባሏ ያጸናበታል ዕዳም ያደርግበታል ። |
| ወለእመሰ ተጸመማ ዕለተ እምዕለት ኵሎ ጸሎታ ወብፅዓቲሃ ይቀውም ዲቤሃ እስመ ተጸመማ በዕለተ ሰምዐ ። | ፲፪ | ከቀን ቀን እያለ ቸል ቢላት ግን በሰማበት ቀን ቸል ብሏታልና ስለቷ ሁሉ በርሷ ጸንቶ ይኖራል ። |
| ወለእመሰ ገብረ ላቲ እምድኅረ ዕለት እንተ በቲ ሰምዐ ኢይከውና ኀጢአተ ። | ፲፫ | ከሰማበት ቀን በኋላ ቢያደርግላት ግን ኃጢአት አይሆንበትም ። ዘሌዋ፡ ፳ ፩ ። |
| ዝንቱ ውእቱ ኵነኔ ኵሉ ዘአዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ማእከለ ብእሲ ወብእሲቱ ወማእከለ አብ ወወለቱ በንእሳ እንዘ ሀለወት ቤተ አቡሃ ። | ፲፬ | በሚስቱና በባሏ መካከል በአባቷ ቤት ሳለች በሕፃንነቷ የሚደረግ በልጅና በአባት መካከል የሚደረግ እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘው ሥርዓት ይህ ነው ። |
| ምዕራፍ ፴፩ ። | | ምዕራፍ ፴፩ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ተበቀል በቀሎሙ ለደቂቀ እስራኤል እመድናውያን ወድኅረ ትትዌሰክ ኀበ ሕዝብከ ። | ፩ | እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው ፡ ከምድያም ሰዎች የእስራኤልን ልጆች በቀል መልስ ከዚያም በኋላ በሞት ወደ ወገኖችህ ትጨመራለህ ። |
| ወነገሮሙ ሙሴ ለሕዝብ ወይቤሎሙ አስተጋብኡ እምኔክሙ አደወ ወትቃተሉ ቅድመ እግዚአብሔር ምስለ ምድያም ከመ ያግብኡ በቀለ እምኀበ እግዚአብሔር ለምድያም ። | ፪ | ሙሴም ለሕዝቡ ከናንተ ሰዎችን ሁሉ ሰብስቡቸሁ ስለ እግዚአብሔር በቀል የምድያምን ሰዎች ይበቀሉ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ከምድያም ሰዎች ጋራ ተዋጉ ብሎ ነገራቸው ። ዘኍ፡ ፳፭ ፲፯ ፡ ፯ ፳፱ ። |
| ወዐሠርተ ምእተ እምነገድ ፡ ወዓሠርተ ምእተ እምነገድ እምኵሉ ነገደ እስራኤል ፈንዉ ዘይትቃተል ። | ፫ | ከእስራኤል ነገድ ሁሉ የሚዋጋ ከንዱ ነገድ ሺሕ ከንዱም ነገድ ሺሕ ሰው ላኩ ። ዘኍ፡ ፴፩ ፳፯ ። |
| ወኍልቁ እምአእላፍ ዘእስራኤል እምነገድ ነገድ ዐሠርተ ምእት ፡ ወኮኑ እልፈ ወዕሥራ ምእት እለ ተረሰዩ ለቀትል ። | ፬ | ከእስራኤል ሠራዊት ከየወገን ከየወገኑ ሺሕ ሺሕ ሰው ቍጠሩ ለሰልፍ የተዘጋጁት እልፍ ከሁለት ሺሕ ኾኑ። ኢያ፡ ፬ ፲፫ ። |
| ወፈነዎሙ ሙሴ በበዐሠርቱ ምእት ዘዘነገድ ነገድ ፡ ምስለ ኀይሎሙ ። | ፭ | ሙሴም ከየነገዱ ነገድ ከሠራዊቶቻቸው ጋር ሺሕ ሺሕ እያደረገ ላካቸው ። |
| ወፊንሐስ ወልደ አልአዛር ወልደ አሮን ካህን ወንዋየ ቅድሳት ወመጣቅዕት ዘተአምር ምስሌሆሙ ። | ፮ | የካህን የአሮን ልጅና የአልአዛር ልጅ ፊንሐስም ነበሩ ፡ ምልክት የሚደረግባቸው ነጋሪቶችና ንዋየ ቅድሳቱም ከነሱ ጋር ነበሩ ። ዘኍ፡ ፲፯ ፱ ፡ ዘሌ፡ ፳፫ ፳፬ ። |
| ወተቃተልዎሙ ለምድያም በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ወቀተሉ ኵሎ ተባዕቶሙ ። | ፯ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የምድያምን ሰዎች ወጉዋቸው ወንድ ወንዱን ሁሉም አጠፉ ። ዘዳ፡ ፳ ፲፫ ። |
| ወለነገሥተ ምድያምሂ ቀተልዎሙ ኅቡረ በውእቱ ቀትሎሙ ለኤዎን ወለሮቆሙሂ ወለሱርሂ ወለሑርሂ ወለሩባቅሂ ኅምስቱ ነገሥተ ምድያም ወለበለዓምሂ ወልደ ቤዖር ቀተልዎ በሐፂን በውእቱ ቀትሎሙ ። | ፰ | የምድያምንም ነገሥታት ሮቆምንና ኤዎንን ሱርንና ሩባቅን አምስቱን የምድያም ነገሥታት በዚያው ሰልፍ አንድነት ገደሉዋቸው ፡ የቤዖር ልጅ በለዓምንም በዚያ ሰልፋቸው በጦር ገደሉት ። |
| ወፄወዉ አንስትያሆሙ ለምድያም ወሕፃናቲሆሙኒ ወእንስሳሆሙኒ ወኵሎ ጥሪቶሙ ወኀይሎሙ በርበሩ ። | ፱ | የምድያምን ሴቶች ልጆቻቸውንም ከብቶቻቸውንም ገንዘባቸውንም ሁሉ ማረኩ ፡ ሠራዊቶቻቸውንም ሁሉ ዘረፉ ። ዘፍ፡ ፴፬ ፳፱ ። |
| ወኵሎ አህጉሪሆሙ ዘይነብሩ ውስቴቶን ፡ ወአዕፃዳቲሆሙኒ አውዐዩ በእሳት ። | ፲ | የሚኖሩባቸው አገሮቻቸውን ሁሉ ፡ በታዎቻቸውንም ሁሉ በእሳት አቃጠሉ ። |
| ወነሥኡ ኵሎ ፄዋሆሙ ወምህርካሆሙ እምሰብእ እስከ እንስሳ ። | ፲፩ | የከብት ምርኮና የሰውን ምርኮ ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ ወሰዱ ። ዘዳ፡ ፳ ፲፬ ። |

፲፪ ወወሰዱ ኀበ ሙሴ ወኀበ አልአዛር ካህን ወኀበ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ፄዋ ወምህርካ ወዘበርበሩ ውስተ ትዕይንት በአራበት ዘሞዓብ እንተ ኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ።

ወደ ካህኑ ወደ አልአዛርና ወደ ሙሴ ወደ እስራኤል ልጆች ሁሉ ዘንድ የማረኩትን ምርኮ ወሰዱ ፤ በዮርዳኖስ ማዶ የኢያሪኮ አንጻር በምትሆን በሞዓብ በአራበት ከተማ የዘረፉትንም ወሰዱ ። ዘኍ፡ ፳፪ ፩ ።

፲፫ ወወፅኡ ሙሴ ወአልአዛር ካህን ወኵሉ መላእክተ ተዓይን ወተቀበልዎሙ አፍአ እምትዕይንት ።

ካህኑ አልአዛርና ሙሴ የሠራዊቱም አለቆች ሁሉ ወጥተው ከከተማው ውጪ ተቀበሉዋቸው ።

፲፬ ወተምዐ ሙሴ መበተ ላዕለ ሠራዊት ወላዕለ መሳፍንቲሆሙ ወላዕለ መላእክቲሆሙ እለ አተዉ እምጸብእ እምኀበ ይትቃተሉ ።

ሙሴም በሺማምንቱና በሠራዊቱ ከሚዋጉበት ሰልፍ በተመለሱ በአለቆችም ላይ ቍጣን ተቈጣ ።

፲፭ ወይቤሎሙ ሙሴ ለምንት አሕየውክሙ ኵሎ አንስተ እስመ እማንቱ ውእቶን እለ ይከውናሆሙ ዕቅፍተ ለደቂቀ እስራኤል ።

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች መሰናክል የሚሆኑዋቸው እነዚህ ናቸውና ሴቶቹን ሁሉ ለምን አዳናችሁ ፤ ። ዘኍ፡ ፴፩ ፲፬ ፤ ዘሌዋ፡ ፬ ፲፪ ።

፲፮ በከመ ይቤ በለዓም እለ ያስሕታሆሙ ወያኀድጋሆሙ ቃለ እግዚአብሔር በበይነ ፌጎር ወመጽአ መቅሠፍተ እግዚአብሔር ላዕለ ትዕይንት ።

በለዓም በጣኦቱ ምክንያት የሚያስቷቸውና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተውዋቸው እሊህ ናቸው ብሎ እንደ ተናገረ በነሱም ምክንያት ከእግዚአብሔር ታዝዞ መቅሠፍት መጥቷልና ለምን አዳናችሁ ፤ ብሎ ተቈጣ ።

፲፯ ወይእዜኒ ቅትሉ ኵሎ ተባዕተ በኀበ ሀሰዉ ወኵሎ ብእሲተ እንተ አእመረት ብእሴ ቅትሉ ።

አሁንም ወንድ ወንዱን ሁሉ በየአሉበት በታ ግደሉ ለወንድ የደረሰችንም ሴት ግደሉ ። መሳ፡ ፳፩ ፲፪ ።

፲፰ ወኵሎ አዋልደ እለ ኢያእመራ ብእሴ አሕይዉ ወአንትሙኒ ተዓየኑ አፍአ እምትዕይንት ሰቡዐ መዋዕለ ።

ከወንድ ያልደረሱ ሴቶችን ግን አድኑ ፤ (አትግደሉ) እናንተም ሰባት ቀን ከከተማው ውጭ ስፈሩ ።

፲፱ ኵሉ ዘቀተለ ወዘገሠሠ ምዉተ ያንጽሕ ርእሶ አመ ሣልስት ዕለት ወአመ ሳብዕት አንትሙ ወፄዋክሙ ።

ነፍስ የገደለ ፤ ሬሳን የዳሰሰ ሰው ሁሉ በሦስተኛው ቀን ራሱን ንጹሕ ያድርግ ፤ በሰባተኛይቱ ቀን ደግሞ እናንተም ምርኮቻችሁም ራሳችሁን ንጹሕ አድርጉ አላቸው ።

፳ ወኵሎ ልብሰ ወኵሎ ንዋየ ማእስ ወኵሎ ንዋየ ዘማእሰ ጠሊ ወኵሎ ንዋየ ዕፅ አንጽሑ ።

ልብስንም ሁሉ ከቁርበቱም ወገን ሁሉ (ዳውላን) ከፍየል ወገን የሚሆን ሌጦውን ሁሉ ሰደቃውን ገበታውን ሁሉ ንጹሕ አድርጉ ። ዘሌዋ፡ ፲፫ ፵፱ ፤ ፲፭ ፲፬ ።

፳፩ ወይቤሎሙ አልአዛር ለእደወ ኀይል እለ አተዉ እምጸብእ እምኀበ ይትቃተሉ ዝንቱ ውእቱ ኵነኔሁ ለሕግ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

አልአዛርም ከሚዋጉበት ሰልፍ የተመለሱ አርበኞችን እግዚአብሔር ሙሴን ያዘዘው የሕጉ ቅጣት ይህ ነው አላቸው ።

፳፪ ኵሎ ወርቅ ወብሩር ወብርት ወሐፂን ወዓረር ወናእክ ወኵሉ ንዋይ ዘይትገበር በእሳት ይነጽሕ ወያንጽሕዎ ።

ወርቁ ፤ ብሩና ብረቱ ፤ ናሱና ቀልቀሉ ሁሉ ፤ የሚሠራበት ዕቃ ሁሉ በእሳት ይጸራል ፤ (ይነጻል) ።

፳፫ በማየ አንጽሖ ወለኵሉ ዘኢይበውእ ውስተ እሳት ለይጥምዕዎ ውስተ ማይ ።

በሚያነጹበትም ጊዜ በውኃ ያንጹት ወደ እሳት የማይገባውን ዕቃ ሁሉ ግን በውኃ ይንከሩት ። ዘኍ፡ ፲፱ ፱ ።

፳፬ ወሕፅቡ አልባሲክሙ በሳብዕት ዕለት ወትነጽሑ ፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ትበውኡ ውስተ ትዕይንት ።

በሰባተኛይቱም ዕለት ልብሳችሁን እጠቡ ከነጢአትም ትነጻላችሁ ፤ ከዚያም በኋላ ወደ ከተማው ግቡ አላቸው ።

፳፭ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ ንሣእ መሠንዮ ለፄዋ ወለምህርካ እምሰብእ እስከ እንስሳ አንተ ወአልአዛር ወመላእክተ አበዊሆሙ ለተዓይን ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ፤ ከከብቱ ምርኮና ከሰው ምርኮ ያማረ የማረውን ፤ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብቱ ድረስ አንተና አልአዛር የሠራዊቱን አባቶች አለቆችን ይዘህ ። ፩ ሳሙ፡ ፴ ፳፬ ።

፳፮ ወትከፍሎ ምህርካ ማእከሎሙ ለእለ ፀብኡ ወለእለ ሖሩ ይትቃተሉ ወማእከለ ኵሉ ተዓይን ።

ሊዋጉ በሄዱት መካከልና በሰልፍ በዋሉት በሠራዊቱም መካከል ምርኮውን ክፈሉ ። ኢያሱ ፳፪ ፰ ።

፳፯ ወታወጽኡ ጸብሖ ለእግዚአብሔር እምኀቤሆሙ ለእለ ፀብኡ ወለእለ ሖሩ ይትቃተሉ አሐተ ነፍሰ እምሐምስቱ ምእት ሰብእ ወእምእንስሳ ወእምአልሕምት ወእምአባግዕ ወእምአእዱግ ።

ይዋጉ ዘንድ ወደ ሰልፍ ከሄዱት ፤ ከአምስት መቶ ሰዎች ግብሩን ለእግዚአብሔር አንድ ሰው አውጡ ፤ ከላሙና ከፈረሱ ከበቅሎው ከአህዮች ከበጎችም ከአምስት መቶ አንድ አውጡ አላቸው ። ዘኍ፡ ፲፰ ፳፮ ።

፳፰ ወትነሥእ እመንፈቆሙ ወትሁቦ ለአልአዛር ካህን ቀዳምያቲሁ ለእግዚአብሔር ።

ከእኩሌታቸው ተቀብለህ ለካህኑ ለአልአዛር የእግዚአብሔር ግብሩን ስጠው ። ፩ ሳሙ፡ ፴ ፳፬ ።

፳፱ ወእመንፈቆሙ ለደቂቀ እስራኤል ትነሥእ አሐደ እምኀምሳ እምሰብእ ወእምአልሕምት ወእምአባግዕ ወእምአ

ከእስራኤል ልጆች እኩሌታም ከበጎችና ከላሞች ከፈረሶችና ከበቅሎች ከአህዮችም ከአምሳ አንድ ተቀብለህ

እዱግ ወእምእንስሳ ወሀበሙ ለሌዋውያን እለ የዐቅቡ ሕገ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር ።

፴ ወገብሩ ሙሴ ወአልአዛር ካህን በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

፴፩ ወኮነ ኍልቈ አባግዕ ዘማህረኩ እደው እለ ፀብኡ ስሳ ወሰብዓቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ።

፴፪ ወአልሕምት ሰብዓቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ።

፴፫ ወአእዱግ ሰብዓቱ እልፍ ወዓሠርቱ ምእት ።

፴፬ ወሰብእ ዘመንፈሰ አንስት እለ ኢያእመራ ብእሴ ፡ ሠለስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ።

፴፭ ወኮነ መንፈቀ ክፍሎሙ ለእለ ሖሩ ፀብአ እምኍልቈ አባግዕ ሠላሳ ወሠለስቱ እልፍ ፡ ሰብዓ ምእት ፡ ወሐምስቱ ምእት ።

፴፮ ወኮነ ጸባሕቱ ለእግዚአብሔር እምአባግዕ ሰብዓቱ ምእት ሰብዓ ወሐምስቱ ።

፴፯ ወአልሕምት ፡ ሠለስቱ እልፍ ወስሳ ምእት ።

፴፰ ወኮነ ጸባሕቱ ለእግዚአብሔር ፡ ሰብዓ ወክልኤቱ ።

፴፱ ወአእዱግ ሠለስቱ እልፍ ፡ ወሐምስቱ ምእት ።

፵ ወኮነ ጸባሕቱ ለእግዚአብሔር ፡ ስሳ ወአሐዱ ።

፵፩ ወሰብእ ዘመንፈስ ፡ እልፍ ወስሳ ምእት ።

፵፪ ወኮነ ጸባሕቱ ለእግዚአብሔር ፡ ሠላሳ ወክልኤቱ ።

፵፫ ወወሀበ ሙሴ ጸባሕተ ዘፈለጡ ለእግዚአብሔር ለአልአዛር ካህን ፡ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

፵፬ ወእመንፈቆሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘአውጽአ ሙሴ እምእደው እለ ሖሩ ፀብአ ።

፵፭ ወኮነ መንፈቁ ለዝ እምትዕይንት ፡ እምአባግዕ ፡ ሠላሳ ወሠለስቱ እልፍ ፡ ወሰብዓ ምእት ፡ ወሐምስቱ ምእት ።

፵፮ ወአልሕምት ፡ ሠለስቱ እልፍ ፡ ወስሳ ምእት ።

፵፯ ወአእዱግ ሠለስቱ እልፍ ፡ ወሐምስቱ ምእት ።

፵፰ ወሰብእ ዘመንፈስ እልፍ ወስሳ ምእት ።

፵፱ ወነሥአ ሙሴ መንፈቆሙ ለደቂቀ እስራኤል አሐደ እምሐምሳ እምሰብእ ወእምእንስሳ ፡ ወወሀቦሙ ለሌዋውያን እለ የዐቅቡ ሕገ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።

፶ ወመጽኡ ኀበ ሙሴ ኵሎሙ መላእክተ ዐሠርቱ ምእት ሠራዊት ወመላእክተ ምእት ፡ ወይቤልዎ ለሙሴ ።

፶፩ አግብርቲከ ነሥኡ ሠርጐሆሙ ለእደው እለ ቀተሉ ምስሌነ ወኢያይድዑነ ወኢአሐዱ እምኔሆሙ ።

፶፪ ወናሁ አምጻእነ ቍርባኖ ለእግዚአብሔር ብእሲ ብእሲ ዘረከበ ሠርጐ ወርቅ በዝግና ፡ ወአውቃፈ ፡ ወኀልቀተ ፡ ወሐብላተ ዘዕፍሮ ከመ ታስተሥርዩ በእንቲአነ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፶፫ ወነሥኡ ሙሴ ወአልአዛር ካህን ውእተ ወርቀ እምኔሆሙ ወኵሎ ሠርጐ ዘግቡር ።

፶፬ ወኮነ ኵሉ ወርቅ ዘመባእ ዘፈለጡ ለእግዚአብሔር እልፍ ወስሳ ምእት ፡ ወሰብዓቱ ምእት ወሐምሳ ፡ በሰቅል እምኀበ መላእክተ ዐሠርቱ ምእት ወመላእክተ ምእት ።

የእግዚአብሔርን የድንኳኑን ሥርዓት ለሚጠብቁ ለሌዋውያን ሰጣቸው አለው ። ዘፀ፡ ፲፱ ፳፩ ።

ሙሴና ካህኑ አልአዛርም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ ።

ወደ ሰልፍ የሄዱ ሰዎች የማረኳቸው የበጎቹ ቍጥር ስሳ ሰባት እልፍ ከአምስት ሺሕ ሆነ ።

ላሞችም ሰባት እልፍ ከሁለት ሺሕ ሆኑ ።

አህዮችም ሰባት እልፍ ከአሥር ሺሕ ሆኑ ።

ከወንድ ያልደረሱ የሴት አካል ያላቸው ሰዎችም ሦስት እልፍ ከሁለት ሺሕ ሆኑ ።

ከበጎችም ቍጥር ወደ ሰልፍ የሄዱ የአርበኞቹ ክፍል እኩሌታ ሠላሳ ሦስት እልፍ ሰባት ሺሕ ከአምስት መቶ ሆነ።

ከበጎች ለእግዚአብሔር የወጣው ዓሥራት ሰባት መቶ ከሰባ አምስት ሆነ ።

ላሞችም ፡ ሦስት እልፍ ከስድስት ሺሕ ሆኑ ።

የእግዚአብሔርም ግብሩ (ዓሥራቱ) ሰባ ሁለት ሆነ ።

አህዮችም ፡ ሦስት እልፍ ከአምስት መቶ ሆኑ ።

የእግዚአብሔርም ግብሩ ስሳ አንድ ሆነ ።

አእምሮ ያላቸው የተማረኩት ሰዎች (ከሴት ያልደረሱ) እልፍ ከስድስት ሺሕ ሆኑ ። ዘኍ፡ ፲፰ ፳ ።

የእግዚአብሔርም ዐሥራት ሠላሳ ሁለት ሆነ ።

ሙሴም ለእግዚአብሔር ብለው የለዩትን ዓሥራት እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ለአልአዛር ካህን ሰጠው ።

ከእስራኤል ልጆች እኩሌቶች ወደ ሰልፍ ከሄዱት ሰዎች ሙሴ ያወጣው ይህ ነው ። ዘኍ፡ ፵፩ ፴ ።

ከሠራዊቱ ከበጎች የተገኘው የዚህ እኩሌታ ፡ ሠላሳ ሦስት እልፍ ሰባት ሺሕ ከአምስት መቶ ሆነ ።

ላሞችም ፡ ሦስት እልፍ ስድስት ሺሕ ናቸው ።

አህዮችም ፡ ሦስት እልፍ አምስት መቶ ናቸው ።

ከሴት ያልደረሱ (የወንድ አካል ያላቸው) ሰዎች እልፍ ፡ ከስድስት ሺሕ ናቸው ።

ሙሴም ከእስራኤል ልጆች እኩሌታ ከሰዎችም ከከብቶችም ከአምሳ አንዱን ተቀብሎ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነች የደብተራ ኦሪትን ሥርዓት ለሚጠብቁ ሌዋውያን ሰጣቸው ።

የሺ አለቆች ፡ የመቶ አለቆችም ሁሉ ወደ ሙሴ መጥተው እንዲህ አሉት ። ዘፍ፡ ፳፱ ፳፪ ፡ ሕዝ፡ ፲፮ ፲፪ ።

ባሮችህ ከኛ ጋር የወጉዋቸውን ሰዎች ጌዋ ሽልማት ወሰዱ ፡ ከነሱም አንዱ ስንኳ አልነገሩንም ።

አንዱም አንዱም ሰው ያገኘውን እነሆ የወርቁን ጌጣ ጌጥ አምባሩንና ዝርግፉን እንጥልጥሉንና ቀለበቱን ስለኛ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአታችንን ታስተሠርዩልን ዘንድ ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርገን አምጥተናል አሉት ።

ሙሴና ካህኑ አልአዛርም ከነዚያ ያንን የወርቁን ጌጣ ጌጥ ሁሉ ተቀበሉ ። ዘፀ፡ ፴ ፲፮ ፡ ፳ ፲፬ ።

ከመቶ አለቆችና ከሺ አለቆች የተቀበሉት ለእግዚአብሔር ለይተው ያገቡት ወርቁ ሁሉ በሚዛን እልፍ ስድስት ሺሕ ከሰባት መቶ አምሳ ሆነ ።

፶፫ ወእልክቱሰ እደው እለ ፀብኡ አእተዉ ለለርእሶሙ ዘሰለቡ ።

፶፬ ወነሥኡ ሙሴ ወአልአዛር ካህን ውእተ ወርቀ እምኀበ መላእክተ ዐሠርቱ ምእት ወእምኀበ መላእክተ ምእት ወአብኡ ውስተ ደብተራ መርጡል ተዝካሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

ምዕራፍ ፴፪ ።

፩ ወበሙ ለደቂቀ ሮቤል ወለደቂቀ ጋድ ብዙኀ እንስሳ ጥቀ ወርእዩዎ ለብሔረ ያዜር ወለብሔረ ገለአድ ከመ ብሔረ እንስሳ ብሔሩ ።

፪ ወመጽኡ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወይቤልዎሙ ለሙሴ ወለአልአዛር ካህን ወለመላእክተ ተዓይን እንዘ ይብሉ ።

፫ አጣሮት ወዴቦን ወያዜር ወናምራ ፣ ወሐሴቦን ፣ ወእልያሌ ፣ ወሴባማ ፣ ወናበው ፣ ወቤያን ፣ ምድር ዘወሀበ እግዚአብሔር ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ምድረ እንስሳ እማንቱ ፣ ወብነ ለአግብርቲከ ብዙኀ እንስሳ ።

፬ ወይቤልዎ ለእመ ረከብነ ሞገሰ በቅድሜከ ሀበነ ኣላንተ በሐውርተ ለአግብርቲከ መክፈልተ ይኩናነ ወኢታዕድወነ ዮርዳኖስ ።

፭ ወይቤሎሙ ሙሴ ለደቂቀ ሮቤል ወለደቂቀ ጋድ አኀዊክሙ የሐውሩ ይትቃተሉ ወአንትሙሰ ትነብሩ ዝየ ።

፮ ለምንት ትገፈትዑ ልበሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ኢይሑሩ ውስተ ምድር ዘይሁበሙ እግዚአብሔር ።

፯ እኩኑ ከመዝ ገብሩ አበዊክሙ አመ ፈነውክዎሙ እም ቃዴስ በርኔ ከመ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር ።

፰ ወዐርጉ ኀበ ቈላተ ዐጽቅ ከመ ይነጽርዋ ለይእቲ ምድር ወሜጥዎ ለልበሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ኢይበኡ ውስተ ይእቲ ምድር ዘይሁበሙ እግዚአብሔር ።

፱ ወተምዐ መዐተ እግዚአብሔር በይእቲ ዕለት ወመሐለ እንዘ ይብል ፣ ከመ ኢይበውእዋ ለይእቲ ምድር እደው እለ ወፅኡ እምግብጽ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ።

፲ ለምድር ዘመሐልኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እስመ ኢተለዉ ድኅሬሁ ዘእንበለ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ዘተፈልጠ ወሆሴዕ ወልደ ነዌ እስመ ተለዉ ድኅሬሁ ለእግዚአብሔር ።

፲፩ ወተምዐ መዐተ እግዚአብሔር ላዕለ እስራኤል ወአዔሎሙ ውስተ ገዳም አርባዓ ዓመተ እስከ ጠፍኡ ኵሉ ትውልድ እለ ገብሩ እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፲፪ ወናሁ ተንሣእክሙ ህየንተ አበዊክሙ በማዕሌተ ሰብእ ኃጥአን ከመ ትወስኩ ዓዲ መዐተ በዲበ መዐቱ ለእግዚአብሔር ላዕለ እስራኤል ።

፲፫ እስመ ኀደግሞዎ ዓዲ ትደግሙ ኀዲጎቶ በገዳም ወትኤብሱ ላዕለ ኵሉ ዝንቱ ትዕይንት ።

፲፬ ወቀርቡ ኀቤሁ ወይቤልዎ ንንድቅ ዝየ አዕጻዳተ ለእንስሳነ ወአህጉረ ለደቂቅነ ።

፲፭ ወንሕነሰ ምስለ ንዋየ ሐቅልነ ፍጹመ ንሐውር ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እስከ ናበጽሖሙ ውስተ መካኖሙ ።

እነዚያ የተዋጉ ሰዎች ግን የዘረፉትን እየራሳቸው አገቡ ።

ካህኑ አልአዛርና ሙሴም ያንን ወርቅ ከሺ አለቆችና ከመቶ አለቆች ተቀብለው ለእስራኤል ልጆች መታሰቢያ ሊሆን ወደ ደብተራ ኦሪት አገቡ ።

ምዕራፍ ፴፪ ።

ለጋድ ልጆችና ለሮቤል ልጆች እጅግ ብዙ ከብት ነበራቸው ፣ የገለአድ አገርና የያዜር አገርም አገርነቱ የከብት አገር እንደሆነ አዩተው ።

የጋድ ልጆችና የሮቤል ልጆች መጥተው ለካህኑ ለአልአዛርና ለሙሴ ለሠራዊቱም አለቆች እንዲህ አሉዋቸው ።

አጣሮታና ዲቦን ፣ ናምራና ሐሴቦን ፣ አልያሌና ሴባማ ፣ ናባውና ቤያን እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች ፊት የሰጠን የከብት አገሮች ናቸው ፣ ለኛ ለባሮችህም ብዙ ከብት አለን አሉዋቸው ።

በፊትህ ባለሟልነትን አግኝተን እንደሆነ ፈንታችን ይሆኑን ዘንድ እነዚያን አገሮች ለኛ ለባሮችህ ስጠን ፣ ዮርዳኖስንም አታሻግረን አሉት ።

ሙሴም የጋድ ልጆችንና የሮቤልን ልጆች ወንድሞቻችሁ ሊዋጉ ይሄዳሉ እናንተ ግን ከዚህ ልትኖሩ ነውን ፧ ።

እግዚአብሔር ወደ ሚሰጣቸው አገር እንዳይሄዱ የእስራኤልን ልጆች ልቡና ለምን ታጠፋታላችሁ ፧ ።

ያችን አገር ያዩዋት ዘንድ ወደ ቃዴስ በርኔ በላክኋቸው ጊዜ አባቶቻችሁ እንዲህ ያደረጉ አይደለምን ፧ ።

ያችን አገር ያዩዋት ዘንድ የወይን ዘለላ ወዳለበት ቈላ ወጥተው እግዚአብሔር ወደሚሰጣቸው ወደዚያች አገር እንዳይገቡ የእስራኤልን ልጆች ልቡና ለወጡ ።

እግዚአብሔር በዚያች ቀን ቍጣን ተቈጣ ፣ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያሉ ከግብጽ የወጡ ሰዎች ያችን ምድር አያዩዋትም ብሎ ማለ ። ዘኍ ፲፫ ፴፫ ።

ግብራቸው ከተለየ ከየፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከሆሴዕ በቀር እግዚአብሔርን (በሃይማኖት) አልተከተሉትምና ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማልሁላቸውን ያችን ምድር እንዳይገቡባት ብሎ ማለ ፣ ካሌብና ሆሴዕ ግን እግዚአብሔርን ተከትለዉታልና ከነዚህ በቀር ።

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ የሠሩት ትውልድ ሁሉ እስኪጠፉ ድረስ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ተቈጥቶ በምድረ በዳ አርባ ዘመን አዞራቸው ።

በእግዚአብሔር መዓት ላይ ዳግመኛ በእስራኤል ላይ መዓትን ትጨምሩ ዘንድ ኃጥአን በሚሆኑ ሰዎች በደል እነሆ ስለ አባቶቻችሁ ፈንታ ተነሣችሁ ፧ ።

እግዚአብሔርን ትታችሁታልና ዳግመኛም በምድረ በዳ ተዋችሁት ፣ በዚህች ወገን ላይም ትበድላላችሁ ።

ወደርሱም ቀርበው ከዚህ ለበጎቻችን ማደሪያ እንሥራ ለልጆቻችንም አገር እናቅና አሉት ።

እኛ ግን ወደ በታቸው እስከናደርሳቸው ድረስ በእስራኤል ልጆች ፊት ጦራችንን ይዘን በፊት እንሄዳለን ።

፲፯ ወይነብሩ ደቂቅነ ውስተ አህጉር እለ ቦቶን ቅጽር በእንተ ሰብአ ብሔር ።

በአገር ስላሉም ሰዎች ቅጽር ባላቸው አገሮች ልጆቻችን ይቀመጡ ። ዘኍ፡ ፴፩ ፫፡ ኢያ፡ ፬ ፲፪ ።

፲፰ ወኢንገብእ ውስተ አብያቲነ እስከ ይትከፈሉ እስራኤል ርስቶሙ ዘዘዚአሆሙ ።

እስራኤል የየራሳቸውን ርስት እስኪካፈሉ ድረስ ወደ ቤቶቻችን አንመለስም ። ኢያ፡ ፳፪ ፬ ።

፲፱ ወኢንትከፈሎሙ እንከ እማዕዶተ ዮርዳኖስ ፡ ወከሐከ እምኔሆሙ እስመ ነሣእነ ክፍለነ እማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ጽባሕ ።

በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ ከዚያም ወዲያ እንግዲህ አንከፈላቸውም አሉት ። ኢያ፡ ፩ ፲፬ ።

፳ ወይቤሎሙ ሙሴ ለእመ ገበርክሙ በከመ ትቤሉ ወሖርክሙ ምስለ ንዋየ ሐቅልክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ ፀብእ ።

ሙሴም እንዳላችሁት ከደረጋችሁ ጋሻ ጦራችሁን ይዛችሁ በእግዚአብሔር ፊት ወደ ጦርነት ትሄዳላችሁ ። ዘዳ፡ ፫ ፲፰ ።

፳፩ ወዐደውክሙ ኵልክሙ ምስለ ንዋየ ሐቅልክሙ ዮርዳኖስ ቅድመ እግዚአብሔር ።

ጋሻ ጦራችሁን ይዛችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዮርዳኖስን ከተሻገራችሁ ። ዘፀ፡ ፲፩ ፱፡ ኢያ፡ ፩ ፲፬ ።

፳፪ ወእምድኅረ ዝንቱ ትገብኡ ወንጹሓነ ትከውኑ ቅድመ እግዚአብሔር ወእምእስራኤልኒ ወትከውን ለክሙ ዛቲ ምድር መክፈልተክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ።

ከዚያም በኋላ ተመልሳችሁ እግዚአብሔርን ከመበደል እስራኤልንም ከማሳዘን ንጹሐን ትሆናላችሁ ፡ ያችም አገር በእግዚአብሔር ፊት ዕድል ፈንታችሁ ትሆናለች ።

፳፫ ወለእመሰ ኢገበርክሙ ከመዝ ትጌግዩ ቅድመ እግዚአብሔር ፡ ወአመ ረከበተክሙ እኪት ተአምርዋ ለአበሳክሙ ።

እንደዚህ ካላደረጋችሁ ግን በእግዚአብሔር ፊት ትበድላላችሁ ፡ ያችም መከራ ባገኘቻችሁ ጊዜ ኃጢአታችሁን ታውቋታላችሁ ። ዘፍ፡ ፵፬ ፲፮ ፡ ኢሳ፡ ፶፱ ፲፪ ።

፳፬ ወንድቁ ለክሙ አህጉረ ለደቂቅክሙ ፡ ወአፀዳተ ለእንስሳክሙ ፡ ወግበሩ በከመ ወፅአ እምአፉክሙ ።

ለልጆቻችሁ አምባ ለከብቶቻችሁም ዘለሳ ሥሩ ፡ ከአፋችሁም እንደወጣ አድርጉ ።

፳፭ ወይቤልዎ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ለሙሴ ንሕነ አግብርቲከ ንገብር በከመ አዘዝከነ እግዚእነ ።

ሙሴን የጋድ ልጆችና የሮቤል ልጆች እና ባሮችህ አንተ ጌታችን እንዳዘዝከን እናደርጋለን አሉት ።

፳፮ ደቂቅነ ወአንስትያነ ይነብሩ ውስተ አህጉረ ገለአድ ወኵሉ እንስሳነ ።

ሚስቶቻችንና ልጆቻችንም በገለአድ አምባዎች ሁሉ ይቀመጡ ።

፳፯ ወንሕነሰ ነሐውር ኵልነ ምስለ ንዋየ ሐቅልነ ተረሲየነ ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ ፀብእ በከመ ትቤለነ እግዚእነ ።

እኛ ግን ሁላችን ጋሻ ጦራችንን ይዘን አንተ ጌታችን እንዳልከን በእግዚአብሔር ፊት ተጸርረን ወደ ጦርነት እንሄዳለን አሉት ። ዘኍ፡ ፴፩ ፳ ።

፳፰ ወአዘዞሙ ሙሴ ለአልአዛር ካህን ወለኢያሱ ወልደ ነዌ ፡ ወለመላእክተ አበዊሆሙ ለነገደ እስራኤል ።

ሙሴም የነዌ ልጅ ኢያሱንና ካህኑ አልአዛርን የእስራኤል ነገድ የሚሆኑ የአባቶቻቸውን አለቆች አዘዛቸው ።

፳፱ ወይቤሎሙ ለእመ ዐደዉ ምስሌክሙ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ዮርዳኖስ ኵሎሙ ምስለ ተዋየ ሐቅሎሙ ውስተ ፀብእ ቅድመ እግዚአብሔር ዛተ ምድረ ገለአድ እንተ ቅድሜክሙ ትሁብዎሙ መክፈልቶሙ ።

የጋድ ልጆችና የሮቤል ልጆች ከናንተ ጋራ ሁላቸው ጋሻ ጦራቸውን ይዘው በእግዚአብሔር ፊት ዮርዳኖስን ቢሻገሩ በፊታችሁ የምታዩዋት ይህችን የገለአድ አገር ፈንታቸውን ስጡዋቸው ። ዘኍ፡ ፳፯ ፲፰ ።

፴ ወለእመሰ ኢዐደዉ ምስሌክሙ ውስተ ፀብእ በንዋየ ሐቅሎሙ ቅድመ እግዚአብሔር አግዕዙ ደቂቆሙ ወአንስትያሆሙ ወእንስሳሆሙ ቅድሜክሙ ውስተ ምድረ ከነዓን ።

ከናንተ ጋር ጋሻ ጦራቸውን ይዘው በእግዚአብሔር ፊት ወደ ጦርነት ባይሄዱ ግን ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ከብቶቻቸውንም ሁሉ ወደ ፊታችሁ ወደ ከነዓን ምድር ንዱዋቸው ።

፴፩ ወአውሥኡ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወይቤሉ ኵሎ ዘይቤለነ እግዚእነ ከማሁ ንገብር ንሕነ ።

የጋድ ልጆችና የሮቤል ልጆች ጌታችን ያለንን ሁሉ እኛ እናደርጋለን አሉ ።

፴፪ ወነዐዱ በንዋየ ሐቅልነ ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ ምድረ ከነዓን ወሀቡነ መክፈልተነ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

ጋሻ ጦራችንን ይዘን በእግዚአብሔር ፊት ወደ ከነዓን እንሻገራለን ፡ በዮርዳኖስ ማዶ ፈንታችንን ስጡን ብለው መለሱ ።

፴፫ ወወሀቦሙ ሙሴ ለደቂቀ ጋድ ወለደቂቀ ሮቤል ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወልደ ዮሴፍ መንግሥተ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ፡ ወመንግሥተ አግ ንጉሠ ባሳን ምድሮሙ ወአህጉሪሆሙ ምስለ አድባሪሆሙ ወአህጉረ ዘውስተ ምድር ዘዓውዶሙ ።

ለጋድ ልጆችና ለሮቤል ልጆች ለዮሴፍም ልጅ ለምናሴ ነገድ እኩሌታም የባሳን ንጉሥ የአግን ግዛትና የአሞሬዎንን ንጉሥ የሴዎንን ግዛት ፡ አምባቸውንና አገራቸውን ከአውራጃዎቻቸው ጋር በዙርያቸው ምድር ያሉ መንደሮቻቸውንም ሰጧቸው ። ዘዳ፡ ፫ ፲፪ - ፲፯ ።

፴፬ ወነደቁ ደቂቀ ጋድ ዴቦንሃ ፡ ወአጣሮት ወአሮኤር ፡ ወሶፋን ወያዜር ።

የጋድም ልጆች አጣሮትንና ዴቦንን ሳፋንና አሮኤርን ያዜርንም ። ዘኍ፡ ፴፪ ፫፡ ፳፩ ፬ ።

፴፬ ወናምራ ወቤታራን ሰብዓተ አህጉረ ጽኑዐተ ወአንጎ
ዎን ወአዕፃዳተ አባግዕ ።
፴፭ ወደቂቀ ሮቤል ነደቁ ሐሴቦንሃ ወእልያሌ ወቀርያቴም
ወቤኤልሜዎን ወቀጽሮን ወሴባማ ።
፴፮ ወሰመይዎን በበአስማቲሆን ለአህጉር ዘነደቁ ።
፴፯ ወሖረ ገለአድ ወልደ ማኪር ወልደ ምናሴ ወነሥአ
ለገለዓድ ወአጥፍአሙ ለአሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስቴታ ።
፴፰ ወወሀበ ሙሴ ለማኪር ወልደ ምናሴ ገለዓድሃ ፡ ወነበረ
ውስቴታ ።
፴፱ ወኢያዕር ወልደ ምናሴ ሖረ ወነሥአ አዕፃዳቲሆሙ
ወሰመይዎን አዕፃዳተ ኢያዕር ።
፵ ወሖረ ናባው ወነሥአ ለቃናት ወለአዕፃዳቲሃ ወሰመያ
ናባት በስመ ዚአሁ ።

ምዕራፍ ፴፫ ።

፩ ወዝንቱ ውእቱ ማኅደሪሆሙ ለደቂቀ እስራኤል
እምዘወፅኡ እምግብጽ ምስለ ኀይሎሙ በእደ ሙሴ
ወአሮን ።
፪ ወጸሐፈ ሙሴ ማኅደሪሆሙ እምጣነግዕዞ በቃለ እግ
ዚአብሔር ፡ ወዝንቱ ውእቱ ማኅደሪሆሙ ዘግዕዞ ።
፫ ወግዕዙ እምራምሴ በቀዳሚ ወርኅ አመ ዐሡሩ ወኀ
ሙሱ ለቀዳሚ ወርኅ በሳኒታ ፋሲክ ወፅኡ ደቂቀ እስራ
ኤል በእድ ልዕልት ፡ በቅድመ ኵሉ ግብጽ ።
፬ ወግብጽሰ ይቀብሩ ምውቶሙ ኵሎ ዘቀተለ እግዚአብ
ሔር ፡ ኵሎ በኵራ ለምድረ ግብጽ ወላዕለ አማልክቲሆ
ሙኒ ገብረ እግዚአብሔር በቀለ ።
፭ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምራምሴ ወኀደሩ ውስተ
ሰቆት ።
፮ ወግዕዙ እምነ ሰቆት ወኀደሩ ውስተ ኁታን ወአሐዱ
ኅብረ በድው ውእቱ ።
፯ ወግዕዙ እምኁታን ወኀደሩ ኀበ አፉሁ ለኤሮት ዘቅ
ድመ ብዔልሴፎር ወቅድመ መግደሎ ።
፰ ወግዕዙ እምቅድመ መግደሎ ዘኤሮት ወዐደዉ እንተ
ማእከለ ባሕር ውስተ ገዳም ወሖሩ ሠለስ ዕለተ ውስተ
መገዳ ኤታም ወኀደሩ ውስተ ምረት ።
፱ ወግዕዙ እምረት ወበጽሑ ውስተ ኤሌም ወሀለዉ
ውስተ ኤሌም ዐሡርቱ ወክልኤቱ አንቀዕተ ማይ ፡ ወሰብዓ
በቀልተ ተመርት ወኀደሩ ህየ ኀበ ማይ ።
፲ ወግዕዙ እምኤሌም ወኀደሩ ውስተ ባሕረ ኤርትራ ።
፲፩ ወግዕዙ እምባሕረ ኤርትራ ወኀደሩ ውስተ ገዳም ዘሲን
፲፪ ወግዕዙ እምገዳም ዘሲን ወኀደሩ ውስተ ራፉቃ ።
፲፫ ወግዕዙ እምራፉቃ ወኀደሩ ውስተ ኤሉስ ።
፲፬ ወግዕዙ እምኤሉስ ወኀደሩ ውስተ ራፊድን ፡ ወአልቦ
ህየ ማይ ዘይሰትዩ ሕዝብ ።
፲፭ ወግዕዙ እምራፊድን ወኀደሩ ውስተ ገዳም ዘሲና ።

ናምራንና ቤታራንን ጽኑዓን የሆኑ እነዚህን ሰባቱ
አገሮች አስፋፍተው የበጎችን ማደሪያዎች ቀጸሩ ።
የሮቤልም ልጆች እልያሌንና ሐሴቦንን ቤኤልሜዎ
ንንና ቀርያቴምን ፡ ቀጽሮንንና ሴባማን ቀጸሩ ።
የቀጸሩዋቸውንም አገሮች በየስማቸው ጠሩዋቸው ።
የምናሴ ልጅ የማኪር ልጅ ገለአድም ሄዶ ገለዓድን
እጅ አደረጋት ፡ በውስጧ የሚኖሩ አሞሬዎንንም አጠ
ፉቸው ። ዘፍ፡ ፶ ፳፫ ።
ሙሴም ለምናሴ ልጅ ለማኪር ልጅ ገለዓድን ሰጠው
በርሷም ኖረ ። ዘዳ፡ ፫ ፲፫ - ፲፭ ፣ ኢያ፡ ፲፫ ፴፩ ።
የምናሴ ልጅ ኢያዕርም ሂዶ አውራጃዎቻቸውን ሁሉ
እጅ አደረገ ፡ አውራጃዎቹንም የኢያዕር አውራጃዎች
አሏቸው ። ዘዳ፡ ፫ ፲፬ ፣ ፩ ዜና ፪ ፳፩ ።
ናባውም ሂዶ ቃናትን ከአውራጃዎቿ ጋር እጅ አደረ
ጋት ፡ በሚንም በስሙ ናባት አላት ። ዘኍ፡ ፳፩ ፳፭ ።

ምዕራፍ ፴፫ ።

በሙሴና በአሮን መሪነት ከሠራዊቶቻቸው ጋር ከግ
ብጽ ከወጡ በኋላ የእስራኤል ልጆች ሰፍረው ያደሩበት
ማደሪያቸው ይህ ነው ።
ሙሴም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ተጓዙና በተጓ
ዙት ልክ ሰፍረው ያደሩበት ማደሪያቸውን ጻፈ ፡ ተጕ
ዘው ያደሩበት ሰፈራቸው ይህ ነው ።
በመጀመሪያው ወር ከራምሴ ተጓዙ ፡ ሚያዝያ በባተ
በዓሥራ አምስት ቀን በፋሲካ ማግስት የእስራኤል ልጆ
ች በጽኑ ሥልጣን የግብጽ ሰዎች እያዩዋቸው ወጡ ።
የግብጽ ሰዎች ግን እግዚአብሔር በግብጽ አገር የገደ
ለውን በኵር በኵሩን ሁሉ ሬሳቸውን ይቀብሩ ነበር ፡ እግ
ዚአብሔር በጣኦቶቻቸው በቀልን አደረገ ።
የእስራኤልም ልጆች ከራምሴ ተጕዘው በሰቆት
አደሩ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፴፯ ።
ከሰቆትም ተጕዘው በኁታን አደሩ ፡ ይኸውም አንድ
ወገኑ ምድረ በዳ ነው ። ዘፀ፡ ፲፫ ፳ ።
ከኁታንም ተጕዘው በመግደሎና በብኤል ሴፎር አን
ጻር ባለ በኤሮት አፋፍ አደሩ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፪ ።
ከኤሮት ክፍል ከምትሆን ከመግደሎን ተጕዘውም በባ
ሕር መካከል ወደ ምድረ በዳ ተሻገሩ ፡ ወደ ኤታም ምድ
ረ በዳ ሦስት ቀን ተጕዘው በምረት አደሩ ።
ከምረትም ተጕዘው ወደ ኤሌም ደረሱ ፡ በኤሌምም
ዓሥራ ሁለት የውኃ ምንጮች ሰባ የተምር ዘንባባ ነበሩ ፡
በዚያም በውኃው ዘንድ አደሩ ። ዘፀ፡ ፲፭ ፳፯ ።
ከኤሌምም ተጕዘው በኤርትራ ባሕር ዳር አደሩ ።
ከኤርትራ ባሕርም ተጕዘው በሲና ምድረ በዳ አደሩ ።
ከሲና ምድረ በዳም ተጕዘው በራፉቃ አደሩ ።
ከራፉቃም ተጕዘው በኤሉስ አደሩ ።
ከኤሉስም ተጕዘው በራፊድን አደሩ ፡ በዚያም ሕዝ
ቡ የሚጠጡት ውኃ አልነበረም ። ዘፀ፡ ፲፯ ፩ ።
ከራፊድንም ተጕዘው በሲና ምድረ በዳ አደሩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወግዕዙ እምገዳም ዘሲና ፣ ወኅደሩ ውስተ መቃብረ ፍትወት ። | ፲፮ | ከሲና ምድረ በዳም ተጕዘው በምኞት መቃብር (እስ ራኤል ሥጋ ተመኝተው ወደ ተቀበሩበት) መቃብር ሰፈሩ። |
| ወግዕዙ እመቃብረ ፍትወት ወኅደሩ ውስተ አሴሮት ። | ፲፯ | ከምኞት መቃብርም ተጕዘው በአሴሮት ሰፈሩ ። |
| ወግዕዙ እምአሴሮት ወኅደሩ ውስተ ራታማ ። | ፲፰ | ከአሴሮትም ተጕዘው በራታማ አደሩ ። ዘኍ፣ ፲፪ ፲፮። |
| ወግዕዙ እምራታማ ወኅደሩ ውስተ ሬሞት ዘፋሬስ ። | ፲፱ | ከራታማም ተጕዘው የፋሬስ ዕጣ በምትሆን በሬሞት አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ሬሞት ዘፋሬስ ወኅደሩ ውስተ ሌበና ። | ፳ | የፋሬስ ዕጣ ከምትሆን ከሬሞትም ተጕዘው በሌበና አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ሌበና ወኅደሩ ውስተ ሊስ ። | ፳፩ | ከሊበናም ተጕዘው በሊስ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ሊስ ወኅደሩ ውስተ መቄዶት ። | ፳፪ | ከሌስም ተጕዘው በመቄዶት አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ መቄዶት ወኅደሩ ውስተ አርሳፍር ። | ፳፫ | ከመቄዶትም ተጕዘው በአርሳፍር አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ አርሳፍር ወኅደሩ ውስተ ከሬዳ። | ፳፬ | ከአርሳፍር ተጕዘው ወደ ከሬዳ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ከሬዳ ወኅደሩ ውስተ መቄዶት ። | ፳፭ | ከከሬዳም ተጕዘው በመቄዶት ሰፈሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ መቄዶት ወኅደሩ ውስተ ቀጣዓት ። | ፳፮ | ከመቄታም ተጕዘው በቀጠዓት (በቀጥዖት) አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ቀጣዓት ወኅደሩ ውስተ ተሬት ። | ፳፯ | ከቀጥዖትም ተጕዘው በተሬት ሰፈሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ተሬት ወኅደሩ ውስተ መቴቃ ። | ፳፰ | ከተሬትም ተጕዘው በመቴቃ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ መቴቃ ወኅደሩ ውስተ ኤሴምና ። | ፳፱ | ከመቴቃም ተጕዘው በኤሴምና ሰፈሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ኤሴምና ወኅደሩ ውስተ መሱሩት ። | ፴ | ከኤሴምና ተጕዘው በመሱሩት አደሩ ። ዘዳ፣ ፲ ፮ ። |
| ወግዕዙ እምነ መሱሩት ወኅደሩ ውስተ በንያቅን ። | ፴፩ | ከመሱሩትም ተጕዘው በበንያቅን አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ በንያቅን ወኅደሩ ውስተ ገድገድ ። | ፴፪ | ከበንያቅንም ተጕዘው በገድገድ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምገድገድ ወኅደሩ ውስተ ኤጤቤት ። | ፴፫ | ከገድገድም ተጕዘው በኤጤቤት አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ኤጤቤት ወኅደሩ ውስተ ኤብሮና ። | ፴፬ | ከኤጤቤትም ተጕዘው በኤብሮና አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ኤብሮና ወኅደሩ ውስተ ጋስዮን ጋቤር ። | ፴፭ | ከኤብሮናም ተጕዘው በጋስዮን ጋቤር አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምጋስዮን ጋቤር ወኅደሩ ወስተ ገዳም ዘጺን ። | ፴፮ | ከጋስዮን ጋቤር ተጕዘው በሲና ምድረ በዳ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምገዳም ዘጺን ወኅደሩ ውስተ ገዳም ዘፋራን ዘውእቱ ቃዴስ ። | ፴፯ | ከሲና ምድረ በዳም ተጕዘው በፋራን ምድረ በዳ አደሩ ፣ ይኸውም ቃዴስ ነው ። ዘኍ፣ ፳ ፳፪ ፣ ፳፩ ፬ ። |
| ወግዕዙ እምቃዴስ ወኅደሩ ውስተ ደብረ ሆር ዘገቦሁ ለምድረ ኤዶም ። | ፴፰ | ከቃዴስም ተጕዘው በኤዶም ምድር ጐን ባለ በሆር ተራራ አደሩ ። ዘኍ፣ ፳ ፳፩ ፣ ዘዳ፣ ፴፪ ፶ ። |
| ወዐርገ አሮን ካህን በትእዛዘ እግዚአብሔር ወሞተ በ ሀየ አመ አርበዓ ዓም እምዘወፅኡ ደቂቀ እስራኤል እምግብጽ በኃምስ ወርኅ አመ ሠርቀ ወርኅ ። | ፴፱ | ካህኑ አሮን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥቶ የእስራ ኤል ልጆች ከግብጽ በወጡ በአርበ ዓመት በአምስተኛው ወር የነሐሴ መባቻ በዚያ በደብረ ሆር ሞተ ። |
| ወዓመቲሁ ለአሮን አመ ሞተ በደብረ ሆር ምእት ወዕ ሥራ ወሠለስቱ ዓመት ። | ፵ | በደብረ ሆር በሞተ ጊዜ የአሮን ዘመኑ ፣ መቶ ሃያ ሦስት ነበረ። ዘኍ፣ ፳፩ ፩ ። |
| ወሰምዐ ከነአን ንጉሠ አራድ እንዘ ይነብር ውስተ ምድረ ከነአን አመ ይበውኡ ደቂቀ እስራኤል ። | ፵፩ | የአራድ ንጉሥ ከነዓንም በከነዓን ተቀምጦ ሳለ የእስ ራኤልን ልጆች መምጣት ሰማ ። ዘኍ፣ ፳፩ ፬ ። |
| ወግዕዙ እምደብረ ሆር ወኅደሩ ውስተ ሴልሞና ። | ፵፪ | ከደብረ ሆርም ተጕዘው በሴልሞና አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ሴልሞና ወኅደሩ ውስተ ፊኖ ። | ፵፫ | ከሴልሞናም ተጕዘው በፊኖ አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምነ ፊኖ ወኅደሩ ውስተ አቦት ። | ፵፬ | ከፊኖም ተጕዘው በአቦት ሰፈሩ ። ዘኍ፣ ፴፫ ፵፮ ። |
| ወግዕዙ እምአቦት ወኅደሩ ውስተ ጋይ እንተ ማዕዶተ ደወሎሙ ለሞዓብ ። | ፵፭ | ከአቦትም ተጕዘው በሞዓብ ዳርቻ ማዶ ባለች በጋይ አደሩ ። ዘኍ፣ ፳፩ ፴ ። |
| ወግዕዙ እምነ ጋይ ወኅደሩ ውስተ ዴቦን ዘጋድ ። | ፵፮ | ከጋይም ተጕዘው የጋድ ዕጣ በምትሆን በዴቦን አደሩ። |
| ወግዕዙ እምዴቦን ዘጋድ ወኅደሩ ውስተ ጌልሞን ዘዴ ብላቴን ። | ፵፯ | ከዴቦን ተጕዘው የዴብላቴን ክፍል በምትሆን በጌል ሞን አደሩ ። ዘዳ፣ ፴፪ ፵፱ ። |
| ወግዕዙ እምነ ጌልሞን ዘዴብላቴን ወኅደሩ ውስተ አድዋለ አባርም ዘአንጻረ ናባው ። | ፵፰ | ከዴብላቴን ክፍል ከምትሆን ከጌልሞንም ተጕዘው በናባው አንጻር ባለች በአባርም ተራሮች አደሩ ። |
| ወግዕዙ እምአድባረ አባርም ዘአንጻረ ናባው ወኅደሩ ውስተ ዐረቢሃ ለሞዓብ ኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ፣ ወኅደሩ ውስተ ዮርዳኖስ ማእከለ አሲሞት እስከ አቤል ሳጢም ። | ፵፱ | ከናባው አንጻር ባለች ከአባርም ተራሮች ተጕዘው በዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ አንጻር በሞዓብ ግራ በኩል አደሩ ፣ በአሲሞትም መካከል እስከ አቤልሳጢም ድረስ አደሩ ። ዘኍ፣ ፳፭ ፩ ። |

፶ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ በዐረቢሃ ለሞዓብ በኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ፡ ናሁ ተዐድዉ አንትሙ ዮርዳኖስ ውስተ ምድረ ከነዓን ።

፶፩ ወአጥፍእዎሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር እምቅድመ ገጽክሙ ወደምስሱ ግብሮሙ ወሡሉ አማልክቲሆሙ አጥፍኡ ወኵሎ አምሳሊሆሙ አሰስሉ ።

፶፪ ወደምስስዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር ወንበሩ ውስቴታ ፡ እስመ ለክሙ ወሀብኩክሙ ምድሮሙ ርስተ ።

፶፫ ወተዋረስዋ ለይእቲ ምድር ወተከፈልዋ በበነገድክሙ ለእለ ይበዝኁ አብዝኁ ሎሙ መክፈልቶሙ ፡ ወለእለ ይውኅዱ አውኅዱ ሎሙ መክፈልቶሙ ፡ ወለለዘበጽሖ በስሙ ይኩኖ ሎቱ ህየ በበነገድክሙ ወበበአብያተ አበዊክሙ ተከፈልዋ ።

፶፬ ወለእመሰ ኢያጥፋእክምዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ምድር እምቅድመ ገጽክሙ ይከውኑክሙ እለ አትረፍክሙ አሥዋከ ለአዕይንቲክሙ ፡ ወአሜከላ ለገበዋቲክሙ ወይፃረሩክሙ ፡ በውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ትነብሩ አንትሙ ።

፶፭ ወዝከተ ዘሐለይኩ ከመ እግበር ላዕሌሆሙ እገብር ላዕሌክሙ ።

ምዕራፍ ፴፬ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ናሁ ትበውኡ ውስተ ምድረ ከንአን እንትሙ ወርስትክሙ ይእቲ ለክሙ ምስለ አድዋሊሃ ።

፪ ወይኩንክሙ ገበሃ ዘመንገለ ገበሃ ለአዜብ እምገዳም ዘሢን እንተ መአኀዘ ኤዶም እምነ ገበሃ ለባሕረ ሌሊቁ ዘመንገለ ጽባሕ ።

፫ ወየዐውድ ደወላ ለአዜብ እምዓቀበ አቅራቢን ወይበጽሕ እስከ ኤናቅ ወይከውን ሞፃእቱ ለዘመንገለ አዜብ ቃዴስ ዘበርኔ ወይበውእ ውስተ አህጉረ አራድ ወይወፅእ እንተ አሴሞና ።

፬ ወየዐውድ ደወሉ እምአሴሞና ፈለገ ግብጽ ወይከውን ወሰኑ ባሕር ።

፭ ወደወልክሙኒ ዘመንገለ ባሕር ትኩንክሙ ባሕር ዐባይ ወሰንክሙ ወዝንቱ ውእቱ ወሰንክሙ ዘመንገለ ባሕር ።

፮ ወደወልክሙኒ ዘመንገለ መስዕ እምባሕር ዐቢይ እንተ መንገለ ደብር ይከውን ለክሙ ።

፯ ወእምደብር እስከ ደብር ይከውን ለክሙ ፡ ወይበጽሕ እስከ ኤማት ወይከውን ሞፃእቱ አርሴናይን ዘሴፋማ ፡ ወበዝንቱ ይኩንክሙ ወሰንክሙ ዘመንገለ መስዕ ።

፰ ወደወልክሙኒ ዘመንገለ ጽባሕ እምአርሴናይን ዘሴፋማ ወይወርድ ደወልክሙ እምሴፋማ እስከ አርሬላ ።

፱ ወይትራከብ በዘበነ ባሕረ ኬኔሬት እምጽባሕ ።

፶ እነሆ ወደ ከነዓን ለመሄድ ዮርዳኖስን ትሻገራላችሁ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ብሎ በዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ አንጻር ባለች በሞዓብ ግራ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ። ዘዳ፥ ፱ ፩ ፡ ኢያ፥ ፫ ፲፯ ።

፶፩ በዚያች አገር የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ከፊታችሁ አጥፋቸው ፡ ሥራቸውንም አጥፉ ፡ ጣኦቶቻቸውንም ሁሉ አጥፉ ፡ ምስሎቻቸውንም ሁሉ አርቁ ። ዘኍ፥ ፴፪ ፳፩ ።

፶፪ ምድራቸውን ርስት አድርጌ ለናንተ ሰጥቻችኋለሁና በዚያች አገር የሚኖሩትን ሰዎች አጥፍታችሁ በዚ ኑሩ ። ዘፀ፥ ፲፭ ፱ ፡ ፳፫ - ፳፬ ፡ ዘኍ፥ ፴፫ ፶፪ ።

፶፫ ያችን ምድር ወርሳችሁ በየነገዳችሁ ተካፈሏት ፡ ለብዙዎቹ ፈንታቸውን አብዙላቸው ፡ ለሚያንሱትም ፈንታቸውን አሳንሱላቸው ፡ ለየደረሰው በስሙ ይጠራበት ፡ በየነገዳችሁ በየአባቶቻችሁ ወገኖች ተካፈሏት ።

፶፬ በዚያች አገር የሚኖሩትን ሰዎች ከፊታችሁ ባታጠፉቸው ግን ያስቀራችኋቸው ሰዎች ለዓይናችሁ እሾኽ ለጎኖቻችሁ አሜከላ ይሆኑባችኋል ፡ እናንተ በምትኖሩበትም አገር ይጣሏችኋል ። ኢያ፥ ፳፫ ፲፫ ፡ መሳ፥ ፪ ፫ ።

፶፭ (ያልኳችሁን ባታደርጉ ግን) በነሱቸው አደርግ ዘንድ ያሰብኩትን ይህን ጥፋት በናንተ አደርግባችኋለሁ ።

ምዕራፍ ፴፬ ።

፩ እነሆ እናንተ ወደ ከነዓን ትገባላችሁ ፡ ከአውራጃዋ ጋር ለናንተ ርስታችሁ ናት ብለህ ለእስራኤል ልጆች እዘዛቸው ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው ። ዘፍ፥ ፲፯ ፰ ።

፪ በምሥራቅ አንጻር ካለች ከሌሌቂም ባሕር ጐን ባለች በኤዶም መገናኛ ጺን የሚባል ዕንጨት ካለበት ምድር ጀምራችሁ በግራ በኩል ያለ ርስት ይሁናችሁ ።

፫ የአዜብም አውራጃዋ ከአቅራቢን ዓቀበት ጀምሮ እስከ ኤናቅ ይደርሳል ፡ በአዜብ በኩል ያለው ፍጻሜውም ቃዴስ በርኔ ነው ፡ ወደ አራድ አገሮችም ይደርሳል ወደ አሴሞናም ይደርሳል (ይወጣል) ። ኢያ፥ ፲፭ ፫ ።

፬ ዳርቻውም በግብጽ ወንዝ (ፈሳሽ) አሴሞና ይዞራል ፡ ወሰኑም ባሕር ነው ። ዘፍ፥ ፲፭ ፲፰ ፡ ኢያ፥ ፬ ፲፭ ።

፭ በምዕራብ በኩል ያለች ድንበራችሁ ታላቋ ባሕር ትሁናችሁ ፡ በምዕራብም በኩል ወሰናችሁ ይህ ነው ።

፮ በመስዕ በኩል ያለም ድንበራችሁ በተራራው አንጻር ካለ ከታላቁ ባሕር ወንዝ ጀምሮ ለናንተ ርስት ይሁናችሁ ።

፯ ከተራራው ጀምሮ እስከ ተራራው ድረስ ለናንተ ርስት ይሁናችሁ ፡ እስከ ኤማትም ይደርሳል ፡ መውጫው ፍጻሜውም የሴፋማ ዕጣ የሚሆን አርሴናይን ነው ፡ በመስዕ በኩል ያለ ወሰናችሁም በዚህ ይሁን ።

፰ በምሥራቅ በኩል ያለ ዳርቻችሁም የሴፋማ ዕጣ ከምትሆን ከአርሴናይን ጀምር ፡ እስከ አርሬላ ድረስ ይወርዳል ።

፱ በምሥራቅም በኩል በኬኔሬት ባሕር ጀርባ (አጠገብ) ይገናኛል ። ፪ ነገ፥ ፳፪ ፴ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይወርድ ደወሉ ኀበ ዮርዳኖስ ወይከውን ሞፃእቱ ባሕረ ኤሌቄ፤ ወዝንቱ ውእቱ ምድርክሙ ምስለ አድዋሊሃ ዘዐውዳ ። | ፲ | ዳርቻውም ወደ ዮርዳኖስ ይወርዳል፤ ፍጻሜውም የኤሌቄ ባሕር ይሆናል፤ በዙርያዋ ካለው ከአውራጃዎቿ ጋር አገራችሁ ይህ ነው፤ አላቸው ። ዘኍ፡ ፴፬ ፫ ። |
| ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ፤ ዛቲ ይእቲ ምድርክሙ እንተ ትወርስዋ ወትትከፈልዋ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ከመ የሀብዎሙ ለተስዐቱ ነገድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ። | ፲፩ | ሙሴም የምትወርሷትና የምትከፈሏት አገራችሁ ይህች ናት ብሎ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው፤ ለምናሴ ነገድ እኩሌታና ለዘጠኙ ነገድ ይሰጧቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ነገራቸው ። |
| እስመ ነሥኡ ነገደ ደቂቀ ሮቤል ወነገደ ደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ በበአብያተ አበዊሆሙ ። | ፲፪ | የጋድ ልጆች ነገድና የሮቤል ልጆች ነገድ የምናሴም ነገድ እኩሌታ በየአባቶቻቸው ወገኖች ፈንታቸውን ይዘዋልና ። ዘኍ፡ ፴፪ ፪፤ ኢያ፡ ፲፬ ፪ ። |
| ክልኤቱ ነገድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ ነሥኡ መክፈልቶሙ ወሠለጡ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘኀበ ኢያሪኮ እምዘባኑ ዘመንገለ ጽባሕ ። | ፲፫ | የምናሴ ነገድ እኩሌታና ሁለቱ ነገድ በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ አንጻር በሞዓብ ግራ ፈንታቸውን ጨርሰው ተቀበሉ ። |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤ ዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለእደው እለ ያስተከፍልዎሙ ይእተ ምድረ አልአዛር ካህን ወያኢሱ ወልደ ነዌ ። | ፲፬ | እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው ይህችን አገር የሚያካፍሏቸው ሰዎች ስማቸው ይህ ነው፤ የነዌ ልጅ ኢያሱና ካህኑ አልአዛር ናቸው ። ኢያ፡ ፲፬ ፩ ። |
| ወይነሥኡ አሐደ አሐደ መልአከ እምአሐዱ አሐዱ ነገድ ከመ ያስተከፍልዎሙ ይእተ ምድረ ። | ፲፭ | ምድሪቱንም ርስት አድርገው ያካፍሉዋቸው ዘንድ ከየነገዱ አንዳንድ አለቃ ይውሰዱ ። |
| ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለውእቶሙ እደው ዘእምነገደ ይሁዳ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ። | ፲፮ | የነዚያም ሰዎች ስማቸው ይህ ነው፤ ከይሁዳ ነገድ የተመረጠው የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ነው ። |
| ወዘእምነገደ ስምዖን ሰላምያል ወልደ አምዩድ ። | ፲፯ | ከስምዖንም ነገድ የተመረጠው የአምዩድ ልጅ ሰላምያል ነው ። |
| ወዘእምነገደ ብንያም ኤልዳን ወልደ አስሎን ። | ፲፰ | ከነገደ ብንያም የተመረጠው የአስሎን ልጅ ኤልዳን ነው ። |
| ወዘእምነገደ ዳን በቂ ወልደ ዮቅሊ ። | ፲፱ | ከነገደ ዳን የተመረጠው የዮቅሊ ልጅ በቂ ነው ። |
| ወዘእምነገደ ዮሴፍ ዘእምነገደ ደቂቀ ምናሴ አንሔል ወልደ ሱፋድ ። | ፳ | ከዮሴፍ ልጆች ነገድ ከሚሆን ከምናሴ ልጆች ከነገደ ምናሴም የተመረጠው የሱፋድ ልጅ አንሔል ነው ። |
| ወዘእምነገደ ደቂቀ ኤፍሬም ቃሙሔ ወልደ ሰፍጣን ። | ፳፩ | ከኤፍሬም ልጆች ነገድ የተመረጠው የሰፍጣን ልጅ ቃሙሔ ነው ። |
| ወዘእምነገደ ደቂቀ ዛብሎን ኤልሳፍን ወልደ በርናበክ ። | ፳፪ | ከዛብሎን ልጆች ነገድ የተመረጠው የበርናበክ ልጅ ኤልሳፍን ነው ። |
| ወዘእምነገደ ደቂቀ ይሳኮር ፈሊጢሔል ወልደ ሐዛ ። | ፳፫ | ከይሳኮር ልጆች ነገድ የተመረጠው የሐዛ ልጅ ፈሊጢሔል ነው ። |
| ወዘእምነገደ ደቂቀ አሴር አኪሖር ወልደ ሴሌሚ ። | ፳፬ | ከአሴር ልጆች ነገድ የተመረጠው የሴሌሚ ልጅ አኪሖር ነው ። |
| ወዘእምነገደ ደቂቀ ንፍታሌም ፋዳሔል ወልደ ዩምዩድ ። | ፳፭ | ከንፍታሌም ልጆች ነገድ የተመረጠው የዩምዩድ ልጅ ፋዳሔል ነው ። |
| እሉ እሙንቱ ዘአዘዞሙ እግዚአብሔር ከመ ይስፍሩ ሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ምድረ ከነዓን ። | ፳፮ | ለእስራኤል ልጆች የከነዓንን ምድር ሰፍረው ያከፍሉዋቸው ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛቸው እሊህ ናቸው ። |
| **ምዕራፍ ፴፭ ።** | | **ምዕራፍ ፴፭ ።** |
| ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ በዐረቢሃ ለሞዓብ ዘኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ። | ፩ | በዮርዳኖስ አጠገብ በኢያሪኮ አውራጃ በሞዓብ ግራ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ። |
| ወይቤሎ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ የሀብዎሙ ለሌዋውያን እምዘይትከፈሉ ርስቶሙ አህጉረ ዘውስቴቶን ይነብሩ ወአድያሚሆን ዘዐውዶን፤ ለውእቶን አህጉር የሀብዎሙ ለሌዋውያን ። | ፪ | ከሚከፈሉት ርስታቸው የሚኖሩባቸውን አገሮች ለሌዋውያን ይሰጡዋቸው ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው የነዚህም አገሮች ዙርያ አውራጃዎች ለሌዋውያን ይስጧቸው ። ኢያ፡ ፲፬ ፬፤ ፳፪ ፪፤ ሕዝ፡ ፵፭ ፩ ። |

፫ ወይኩናሆሙ አህጉረ ዘውስቴቶን ይነብሩ ወአዕፃዳቲ
ሆን ይኩናሆሙ ለላሕሞሙ ወለእንስሳሆሙ ።

፬ ወደወሎን ለአህጉር ዘትሁብዎሙ ለሌዋውያን እምሀ
ገሩ ዐሠርተ ምእተ በእመት ትሚጥኑ ለአፍአ እምዓውዱ ።

፭ ዕሥራ ምእት በእመት እምአረፍተ ጽባሐዊ ለሀገር፡
ወዕሥራ ምእት በእመት እምገቦሁ መንገለ አዜብ ።

፮ ወዕሥራ ምእት በእመት እምገቦሁ ዘመንገለ ባሕር፡
ወዕሥራ ምእት በእመት እምገቦሁ ዘመንገለ መስዕ፡
ወሀገሩ ማእከለ ዝንቱ ትኩንክሙ ።

፯ ወሀገር ዘትሁብዎሙ ለሌዋውያን ስሱ አህጉር ለምስ
ካይ ዘትፈልጡ ከመ ይኩናሆሙ ምስካየ ለቀታሊ ወዘእን
በለ እላንቱ ዘትሁብዎሙ በዕዳት አህጉር አርብዓ ወክል
ኤቱ ።

፰ ወይከውና ኵሎን አህጉር ዘትሁብዎሙ ለሌዋውያን
አርብዐ ወሰማኒተ ወእላንቱሂ አህጉር ምስለ አድያሚሆን ።

፱ ወአህጉር ዘትሁብዎሙ እመክፈልቶሙ ለደቂቀ እስ
ራኤል እምዘብዙኅ ብዙኅ፡ ወእምዘውኁድ ውኁድ እም
ርስቶሙ ዘይትከፈሉ ለለአሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ የሀብ
ዎሙ ለሌዋውያን አህጉረ ።

፲ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡ ንግሮሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ናሁ ተዐድው አንትሙ ዮርዳ
ኖስ ውስተ ምድረ ከናዓን ።

፲፩ ወፍልጡ ለክሙ አህጉረ ምስካይ ከመ ይኩናክሙ
ኀበ ይሰኪ ህየ ቀታሊ ኵሉ ዘቀተለ ነፍሰ በኢያእምሮ ።

፲፪ ወይኩናክሙ ውእቶን አህጉር ምስካየ እምአበ ደም፡
ከመ ኢይሙት ቀታሊ እስከ ይቀውም ቅድመ ትዕይንት
ወይትሐተት ።

፲፫ ወውእቶን አህጉር እለ ትሁቡ ስሱ አህጉረ ምስካይ
ይኩናክሙ ።

፲፬ ሠላሰ አህጉረ ትፈልጡ በማዕዶተ ዮርዳኖስ፡ ወሠላሰ
አህጉረ ትፈልጡ በምድረ ከናዓን ።

፲፭ ወምስካየ ይኩናሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፡ ለግዩራኒ
ወለፈላሲኒ ዘሀለዉ ኀቤክሙ ይኩናሆሙ ምስካየ እላንቱ
አህጉር ከመ ይስኪ ህየ ኵሉ ዘቀተለ ነፍሰ በኢያእምሮ ።

፲፮ ወእመሰ በንዋየ ሐፂን ዘበጦ፡ ወሞተ ቀታሊ ውእቱ
ሞተ ለይሙት ዘቀተለ ።

፲፯ ወለእመኒ በእብን ወገሮ እው አውደቀ ላዕሌሁ እምእ
ዴሁ ወሞተ፡ ቀታሊ ውእቱ ሞተ ለይሙት ዘቀተለ ።

፲፰ ወለእመኒ በንዋየ ዕፅ ዘበጦ እው አውደቀ ላዕሌሁ
እምእዴሁ ወሞተ፡ ቀታሊ ውእቱ ሞተ ለይሙት ዘቀተለ
ወአበ ደም ለሊሁ ይቅትሎ ።

፲፱ ወለእመኒ ጽልእ ይጸልእ ወአውደቀ ላዕሌሁ ዘከነ
ንዋየ እንዘ ይጸንሕ ወሞተ፡ ቀታሊ ውእቱ ሞተ ለይ
ሙት ዘቀተለ፡ ወአበ ደም ለይቅትሎ በኀበ ረከበ ።

የሚኖሩባቸው አገሮች ይሁኗቸው፡ የከብቶቻቸውና
የላሞቻቸው መሠማሪያ ይሁኗቸው ። ዘሌ፡ ፳፭ ፴፬ ።
ከአገሩም ለሌዋውያን የምትሰጡዋቸው አገሮች ውስ
ጣቸውን በዙርያ ወደ ውጪ አንድ ሺሕ ክንድ ስፈሩ ።
በምሥራቅ በኩል ከአገሩ ቅጽር ጀምራችሁ ሁለት
ሺሕ ክንድ በአዜብ በኩል ካለው ከጐኑ ጀምራችሁ ሁለት
ሺሕ ክንድ ።
በምዕራብ በኩል ካለው ከጐኑ ጀምራችሁ ሁለት ሺሕ
ክንድ በሰሜን በኩል ካለው ከጐኑ ጀምራችሁ ሁለት
ሺሕ ክንድ ስፈሩ ከተማውም በመከከል ይሁናችሁ ።
ለነፍሰ ገዳይ መማፀኛ ይሆኑ ዘንድ ለሌዋውያን ለይ
ታችሁ የምትሰጡዋቸው መማፀኛዎች አገሮች ስድስት
ናቸው፡ ከምትሰጡዋቸውም ከነዚህ በቀር አርባ ሁለት
አህጉር ስጡዋቸው ። ዘዳ፡ ፬ ፵፩፡ ኢያ፡ ፳፱ ፰ ።
ለሌዋውያን የምትሰጡዋቸው አገሮች ሁሉ አርባ
ስምንት ይሁኑ፡ እነዚህም አገሮች ከእውራጃዎቻቸው
ጋር ናቸው ። ኢያ፡ ፳፩ ፵፩ ።
ከእስራኤል ልጆች ዕጣ ለሌዋውያን የምትሰጡዋቸው
አገሮች ከብዙው ብዙ፡ ከጥቂቱም ጥቂት ነው፡ ከነሱም
ከሚከፈሉት ርስታቸው አንዱም አንዱ ለሌዋውያን አገሮ
ችን ይስጧቸው አለው ። ዘኍ፡ ፳፮ ፶፬፡ ፴፫ ፶፬ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ እነሆ
እናንተ ወደ ከነዓን ለመሄድ ዮርዳኖስን ትሻገራላችሁ
ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ።
በለማወቅ ነፍስን የገደለ ነፍሰ ገዳይ ሁሉ በዚያ ይማ
ጠን ዘንድ መማጠኛ አገሮች ሊሆኑዋችሁ መማጠኛ አገ
ሮችን ለዩ ። ዘፀ፡ ፳፩ ፲፫፡ ዘኍ፡ ፴፭ ፲፭ ።
እነዚህም አህጉረ ምስካይ ነፍሰ ገዳይ በአደባባይ ቁሞ
ነገሩ እስኪመረመር ድረስ ነፍስ የገደለ ሰው እንዳይሞት
ከባለ ደሙ ይጠበቅበት ዘንድ ሀገረ ምስካይ ይሁኗችሁ ።
እነዚያም የምትሰጡዋቸው ስድስት አገሮች አህጉረ
ምስካይ (መማጠኛ) ይሁኗችሁ ። ዘኍ፡ ፴፭ ፮ ።
ለእስራኤል ልጆች መማጠኛ ይሆኗቸው ዘንድ በዮር
ዳኖስ ማዶ ሦስት አገሮችን በከነዓንም ሦስት አገሮችን ለዩ ።
እነዚያም አገሮች ሳያውቅ ነፍስ የገደለ ሁሉ በነዚያ
ይማጠን ዘንድ በናንተ ዘንድ ለሚኖሩ ስደተኛና መጻተኛ
መማጠኛ ይሁኗቸው ። ዘኍ፡ ፴፭ ፲፮ ።
በጦር ወግቶት ቢሞት ግን ያ ሰው ነፍሰ ገዳይ ነውና
ያ የገደለ ሰው ይሙት ። ዘፀ፡ ፳፩ ፲፪ - ፲፬ ።
በደንጊያ መትቶ ቢገድለው ወይም በእጁ ወርውሮ
ቢገድለው ያ ሰው ነፍሰ ገዳይ ነውና፡ ያ የገደለ ሰው
ይሙት ። ዘኍ፡ ፴፭ ፳፮፡ ዘዳ፡ ፲፱ ፲፮ ።
በዕንጨትም (በመንዶ) መትቶ ቢገድለው ወይም ት
ልቅ ግንድ ገፍቶ ጥሎበት ቢሞት ነፍሰ ገዳይ ነውና ያ የገ
ደለው ሰው ይሙት፡ ባለ ደምም (አስፈርዶ) ይግደለው ።
ጠብንም ቢጣላው ሸምቆም ቢሆን በማናቸውም መሣ
ሪያ መቶት ቢሞት ነፍሰ ገዳይ ነውና፡ ያ የገደለው ሰው
ይሙት፡ ባለ ደሙም በገኘበት ቦታ ይግደለው፡ (ካስፈ
ረደ በኋላ ነው) ። ኢያ፡ ፳፫ ፭ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወእመሰ ግብት ውእቱ እንዘ ኢይጸልእ ወአውደቀ ላዕሌሁ ዘከነ ንዋየ እንዘ ኢይጸንሖ፤ አው በዘከነ እብን ወሞተ ቦቱ ወቀተሎ እንዘ ኢየአምር ወኢኮነ ጸላኢሁ ወኢይፈቅድ ያሕስም ላዕሌሁ፤ ይሕትቱ ትዕይንት ማእከለ ቀታሊ ወማእከለ አበ ደም በከመ ዝንቱ ፍትሕ ። | ፳ | ሳይጣላው ድንገት መትቶት ቢሞት ሳይሸምቅም ለሞት የሚያበቃ መሣሪያ ቢጥልበት ወይም በተገኘው ደንጊያ መትቶት ቢሞትበት ሳያውቅና ጠላቱም ሳይሆን ቢገድለው በርሱም ክፉ ነገር ለማድረግ ሳይወድ ቢገድለው፤ ሠራዊቱ እንደዚህ ፍርድ በባለ ደሙና በገዳዩ መካከል ይመርምሩ ። ዘኍ፡ ፴፭ ፲፪ ። |
| ወያድኅንዎ ትዕይንት ለዘቀተለ እምአበ ደም ወይመይጥዎ ትዕይንት ውስተ ሀገረ ምስካይ ኀበ ይስኪ ወይነብር ህየ እስከ ይመውት ካህን ዐቢይ ዘቀብዕዎ ቅብዐ ቅድሳት ። | ፳፭ | ሠራዊቱም ነፍሰ ገዳዩን ከባለ ደሙ ያድኑት፤ ሠራዊቱ ወደሚማጠንበት ወደ ሀገረ ምስካይ ይውሰዱት፤ ቅብዓ ክህነት የቀቡት ታላቁ ካህን እስኪሞትም ድረስ በዚያ ይኑር ። ዘሌ፡ ፳፩ ፲፡ ኢያ፡ ፳ ፯ ። |
| ወለእመሰ ወፅአ አፍአ ቀታሊ ውስተ አድዋለ ሀገር እንተ ውስቴታ ሰከየ ህየ ወረከቦ አበ ደም ለቀታሊ በአፍአ ውስተ አድዋለ ሀገር ዘምስካይ፤ ወቀተሎ አበ ደም ለቀታሊ አልቦ ጌጋይ ። | ፳፮ | ነፍሰ ገዳዩ ከዚያ ከተማጠነበት አገር ዳርቻ ወጥቶ ቢሄድ ግን ባለ ደሙም ከተማጠነበት አገር አውራጃ ወጥቶ በአፍአ አግኝቶ ያነን ነፍሰ ገዳይ ባለ ደሙ ቢገድለው ዕዳ የለበትም ። |
| እስመ ውስተ ሀገረ ምስካይ ይነብር እስከ ይመውት ካህን ዐቢይ፤ ወእምድኅረ ሞተ ካህን ዐቢይ ይገብእ ውስተ ምድረ ብሔሩ ። | ፳፰ | ታላቁ ካህን (ሊቀ ካህናቱ) እስኪሞት ድረስ በአገረ ምስካዩ ይኖራልና ሊቀ ካህናቱ ከሞተ በኋላ ግን ወደ አገሩ ይመለሳል ። ዘዐ፡ ፳፱ ፱ ። |
| ወከመዝ ይኩንክሙ ፍትሐ ኵነኔ በመዋዕሊክሙ በኵሉ በሐውርቲክሙ ። | ፳፱ | በዘመናችሁ በአገራችሁ ሁሉ ይህ የቀጣት ፍርድ እንደዚህ ይሁናችሁ ። ዘኍ፡ ፳፯ ፲፩ ። |
| ኵሉ ዘቀተለ ነፍሰ ወዘለፎ ማሕተት ትቀትልዎ ለቀታሊ ፤ ወስምዕ አሐዱ ኢይከውን ማሕተት ለኢቀትሎ ነፍስ ። | ፴ | ነፍስ የገደለ ሰው ሁሉ ምስክር ቢመሰክርበት ገዳዩን ግደሉት፤ አንድ ምስክር ግን ነፍስን ለማስገደል ምስክር አይሁን ። ዘዳ፡ ፲፯ ፯፣ ፲፱ ፲፮፣ ማቴ፡ ፲፰ ፲፮ ። |
| ወኢትንሥኡ ቤዛ በእንተ ነፍስ እምቀታሊ ዘጌጋዩ ለመዊት ሞተ ለይሙት ። | ፴፩ | ፍርዱ በደሉ ለሞት ከሚያበቃው ከነፍሰ ገዳዩ ማማለጃን አትቀበሉ፤ ለሞት የሚያበቃው ቢሆን ይሙት ። |
| ወኢትንሥኡ ቤዛ ከመ ታኅድይዎ ውስተ ሀገረ ምስካይ ከመ ይነበር ከዐበ ውስተ ምድር እስከ ይመውት ካህን ዐቢይ ። | ፴፪ | ሊቀ ካህናቱ እስኪሞት ድረስ በሌላ ሀገረ ምስካይ ለመኖር ወደ ሌላ ሀገረ ምስካይ ታሸሹት ዘንድ ማማለጃን አትቀበሉ ። |
| ወኢትግበርዋ ቀታሊተ ለምድር እንተ ውስቴታ ትነብሩ፤ እስመ ውእቱ ደም ዘይፈስስ ቀታሊተ ለምድር ወኢትሠረ ሎቱ ምድር ለዘከዐወ ደመ ላዕሌሃ ። | ፴፫ | ምድርን ነፍሰ ገዳይ የሚያደርጋት ያ ደም ነውና በላይዋ ላይ ደም ያፈሰሰውንም ሰው ይቅር አትለውምና የምትኖሩበት አገራችሁን ነፍሰ ገዳይ አታድርጓት ። |
| ወኢታገምኑዋ ለምድር እንተ ውስቴታ ትነብሩ እንትሙ፤ ወእንተ ውስቴታ አነ አኀድር ምስሌክሙ፤ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአኀድር ማእከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፴፬ | በእስራኤል ልጆች መካከል በረድኤት የምኖር እኔ እግዚአብሔር ነኝና እናንተ የምትኖሩበት እኔም ከናንተ ጋራ የምኖርበትን ምድር አታሳድፉዋት ። |
| ምዕራፍ ፴፮ ። | | ምዕራፍ ፴፮ ። |
| ወመጽኡ መላእክተ ነገደ ቤተ አበዊሁ ለገለዓድ ወልደ ማኪር ወልደ ምናሴ ዘእምነገደ ደቂቀ ዮሴፍ ወቆሙ ቅድመ ሙሴ ወቅድመ አልአዛር ካህን ወቅድመ መላእክተ አብያተ አበዊሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ። | ፩ | ከዮሴፍ ልጆች ነገድ የተወለደ የምናሴ ልጅ የማኪር ልጅ የገለዓድ የአባቶቹ ወገን ነገድ አለቆች መጥተው በካህኑ በአልአዛርና በሙሴ ፊት በእስራኤል ልጆች አባቶች ወገኖች አለቆችም ፊት ቆሙ ። ዘኍ፡ ፳፯ ፳፱ ። |
| ወይቤሉ አዘዘ እግዚአብሔር ለእግዚእነ ከመ የሀበሙ ምድረ ርስቶሙ በበመክፈልቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአዘዘ እግዚአብሔር ለእግዚእነ ከመ የሀበን መክፈልተ ሰለጰአድ እኁነ ለአዋልዲሁ ። | ፪ | ለእስራኤል ልጆች በየፈንታቸው ርስታቸው የሚሆን አገርን ትሰጣቸው ዘንድ አንተን ጌታችንን እግዚአብሔር አዘዘህ፤ የወንድማችን የሰለጰአድንም ፈንታ ለሴቶች ልጆቹ ትሰጣቸው ዘንድ አንተን ጌታችንን እግዚአብሔር አዘዘህ ። ዘኍ፡ ፳፯ ፶፭፣ ኢያ፡ ፲፯ ፬ ። |
| ወይከውና አንስትያሆሙ ለአሐዱ እምነገዶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይወጽእ መክፈልቶን እመክፈልተ አቡሆን ወይትዌሰክ ውስተ ካልእ መክፈልተ ነገድ ኀበ አውሰበ፤ ወይወፅእ እመክፈልተ ርስትነ ። | ፫ | ከእስራኤል ነገድ ላንዱም ላንዱም ሚስቶች ይሆናሉ ፈንታቸውም ከአባታቸው ፈንታ ወጥቶ ወደ ገቡበት ወደ ሌላ ነገድ ፈንታ ይጨመራል ከርስታችንም ፈንታ ይወጣል ። ዘኍ፡ ፳፯ ፬ ። |

| | | |
|---|---|---|
| ወለእመ ይከውን ይወፅእ እምደቂቀ እስራኤል ወይገብእ ርስቶሙ ውስተ ርስተ ካልእ ነገድ ኀበ አውሰብ እስመ ናሁ ይወፅእ እምውስተ ርስቶሙ ወመክፈልቶሙ ለነገደ አበዊነ ። | ፬ | ከእስራኤል ልጆች ወጥቶ ርስታቸው ወደ ገቡበት ወደ ሌላ ነገድ ርስት የሚገባ ከሆነ፤ እነሆ ከአባቶቻችን ነገድ ፈንታና ርስት ይወጣልና ስጡን አሉ ። |
| ወአዘዞሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል በትእዛዘ እግዚአብሔር ወይቤሎሙ ከመዝ ለነገደ ደቂቀ ዮሴፍ ። | ፭ | ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ የእስራኤልን ልጆች አዘዛቸው፤ የዮሴፍን ልጆች ነገድንም እንዲህ አላቸው ። |
| ዝንቱ ውእቱ ቃል ዘአዘዘን እግዚአብሔር ለአዋልደ ሰለጰአድ ወይቤ ዘአደሞን በቅድሜሆን ለያውስባ ወዳእሙ እምደቂቀ አበዊሆን ለያውስባ ። | ፮ | እግዚአብሔር የሰለጰአድን ልጆች ያዘዛቸው ቃል ይህ ነው፤ በፈቃዳቸው የወደዱትን ያግቡ፤ ነገር ግን ከአባቶቻቸው ልጆች ያግቡ ። ዘኍ፡ ፴፮ ፫ ፲ ። |
| ወኢይግባእ ርስቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እምነገድ ለነገድ እስመ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ ውስተ ርስተ አበዊሆሙ ይትልዉ ደቂቀ እስራኤል ። | ፯ | የእስራኤል ልጆች እያንዳንዳቸው ፈንታቸውን ይከተሉ እንጂ ርስት ከነገዱ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ አይግባ አለ። |
| ወኵላ ወለት እንተ ተኀሥሥ ርስተ እምደቂቀ እስራኤል አሐደ እምነገዳ ለታውስብ፤ ከመ ይኅሥሡ ደቂቀ እስራኤል አሐዱ አሐዱ ርስተ ለርእሱ ወርስተ አቡሁ ። | ፰ | የእስራኤል ልጆች ከነሳቸው አንዱም አንዱም ርስቱን ያበቱንም ርስት ይፈልጉ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች ርስት የምትፈልግ ሴት ልጅ ሁሉ ከነገዷ አንድ ሰው ታግባ። |
| ወኢይግባእ ርስት እምነገድ ውስተ ካልእ ነገድ፤ አላ አሐዱ አሐዱ ውስተ መክፈልቶሙ ይትልዉ ደቂቀ እስራኤል ። | ፱ | የእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም ፈንታቸውን ይከተሉ እንጂ ርስት ከነገድ ወደ ሌላ ነገድ አይግባ ። |
| ወገብራ አዋልደ ሰለጰአድ መሐላ፤ ወቴርሳ፤ ወሔግላ፤ ወሚልካ፤ ወኑሓ፤ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ። | ፲ | የሰለጰአድ ልጆች ቴርሳና መሐላ፤ ሚልካና ሔግላ፤ ኑሐም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ ። |
| ወአውሰባ ዘእምደቂቀ ቅሩቦን ዘእምነገደ ደቂቀ ምናሴ ወልደ ዮሴፍ ወገብአ መክፈልቶን ውስተ ነገደ ሕዝበ አበዊሆን ። | ፲፩ | እቅራቢያቸው ከሚሆኑ ልጆች ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ልጆች አገቡ፤ ፈንታቸውንም ወደ አባቶቻቸው ወገኖች ነገድ ተመለሰ። ዘኍ፡ ፳፯ ፩ ። |
| ዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ዘአዘዘ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ፤ በዐረቢሃ ለሞኣብ ዘኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ። | ፲፪ | በዮርዳኖስ ማዶ በኢያሪኮ አንጻር ባለች በሞኣብ ግራ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል ያዘዘው ትእዛዝ (ዘጠኝ ሕግጋት) ፍርድ ፍትሕ አምስት መቶ ሰባ "ወነበበ„ ይህ ነው። |

ኦሪት ዘኍልቍ ተፈጸመ፤
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ዘፈጠረ ኵሎ ዓለመ
አሜን ።

የእስራኤልን ቍጥር የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ፤
ለእግዚአብሔር የዘለዓለም ክብርና ምስጋና ይግባው፤
አሜን።